አማርኛ

الأمهرية

የሸይኽ ዶክተር ሀይሳም ሰርሐን ሰይንሳዊ መጸሕፍት ቤተ-መጸሕፍት

المكتبة العلمية للشيخ د. هيثم سرحان



በሸይኽ ዶክተር ሀይሳም ቢን መሐመደ ሰርሐን የተዘጋጁ ሦስት አስፈላጊ የእስልምና መጸሕፍትን የያዘ የአውቀት ስብስብ ነው፡

Artinya: Koleksi ilmu yang memuat tiga kitab Islam penting yang disusun oleh Syekh Dr. Haytham bin Muhammad Sarhan.

1

ሽርሐ ሲራ ነቢ እና ሳሀራያችው

አጭርና ጠቃሚ የነቢዎ ﷺ የሲይውት ታረክ እና የተላያዩ በሀሬያትው።

Ikhtisar sirah Nabi ﷺ dan sifat-sifat beliau yang istimewa.

2

ይህ ነው እስልምና

የእስልምናን መሠረተዊ ትምህርትች በቀላልና ግልፅ መንገድ የሚያብራራ መጸሕፍ።

Pengenalan Islam dan ajaran dasarnya secara mudah dan jelas.

3

የእስራላጊ ትምህርትች ለስራው ሕዝብ ማሰራሪያ

የተውፊሕድንና የእስልምናን እስራላጊ መሠረትች የሚያብራራ መጸሕፍ።

Penjelasan pelajaran penting bagi masyarakat, termasuk dasar-dasar tauhid.

ስለ ማጸሕፍት

ይህ የመጻሕፍት ስብሰበ መፅኀሌምች የእስልምናን ዕዮመረታዊ ትምህርትችኖ፡ ትክክለኛ ዕቂደን, ተውሕድን; የእምልክ ሥርዓትችን, የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የሕይውት ታክንና አስረላጊ የሸረዋ አውቀችን በቀላል፡ በግልፅና በተደረጀ መንገድ አንዲማሩ ይረዳል።

ስለ ሸይኻ

ሸይኽ ዶክተር ሀይሰም ቢን መሐመድ ሰርሐን ቀይም ሲል በወደና በሚገኘው መሰጂድ አን-ነቢዊ እና በቀበ መሰጂድ ውሰጥ አሰተማሪ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ የመልሃድ አሰ-ሱና (معهد السنة) የሳይንሰዊ ትምህርት ለረ ናቸው።

መፅሃድ አሰ-ሱና
معهد السنة
የሳይንሰዊ እውቀችና የእስልምና ትምህርት

የሸይኽ ድረ ገጅ
https://sarhaan.com/


መፅሃድ አሰ-ሱና
https://mahadsunnah.com/

የአማርኛ መጸሕፍትን በነደ ያውርዱ
https://sarhaan.com/a/amharic-አማርኛ/

እጥር ምጥን ያለ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ እና ለየት ያሉ እበይት መገለጫ ባህሪዎቻቸው

المختصر المفيد في سيرة النبي ﷺ وشمائله

አማርኛ | الأمهرية



ደራሲ: ሸይኽ ዶክተር ሀይሰም ቢን ሙሐመድ ሰርሐን

تأليف الشيخ الدكتور هيثم بن محمد سرحان

MAHAD SUNNAH

sarhaan.com | mahadsunnah.com



እጥር ምጥን ያለ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ

እና

ለየት ያሉ አበይት መገለጫ ባህሪዎቻቸው



هيثم بن محمد سرحان

ዝግጅት፡-

ሸይኽ ሀይሠም ኢብን ሙሐመድ ሰርሓን

በመስጂድ አን-ነበዊ ውስጥ የቀድሞ አስተማሪ

እና የዚህ ድረ ገፅ ዳይሬክተር:-

www.alsarhaan.com

غفر الله له ولوالديه ولمن أعانه على إخراج هذا الكتاب

አላህ ለርሳቸው፣ ለወላጆቻቸውና ይህን መጽሐፍ በማሳተም ረገድ ላገዟቸው አካላት ምሕረቱን ይለግሳቸው!

ትርጉም፡-

አቡ የሕያ (አሊ አማኖ)



الطَّبعة الأولى

جميع الحقوق محفوظةٌ

لا يُسمح بنسخ هذا الكتاب أو تخزينه في أيِّ مجالٍ أو نقله بأيِّ شكلٍ من الأشكال إلَّا في حالات الاقتباس القصيرة مع الإشارة إلى المصدر.

للتَّواصل مع الرَّجاء:

islamtorrent@gmail.com

تصميم وإخراج وزارة العالم الإسلامي

መግቢያ

بسم الله الرحمن الرحيم

ምስጋና ሁሉ ለኃያሉ አላህ የተገባ ይሁን፡፡ እርሱን እናመሰግነዋለን፤ በርሱም እንታገዛለን፤ ምሕረቱንም እንለምነዋለን፤ ከነፍሶቻችን ክፋቶችና ከመጥፎ ሥራዎቻችን ውጤትም በርሱ እንጠበቃለን፡፡ አላህ የመራውን ሰው ማንም አያጠመውም፡፡ እርሱም በጥመት ላይ የተወውን ሰው ለርሱ አቅኚ የለውም፡፡ ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም እመሰክራለሁ፡፡ እርሱም ብቸኛና ኢጋር የለሽ ነው፡፡ ሙሐመድም የአላህ ባሪያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት፡፡ እናንተም ሙስሊሞች ኾናችሁ እንጅ አትሙቱ፡፡» (ኣሉ ዒምራን 3፡102)

«እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርሷም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን፣ ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡» (አን-ኒሳእ 4፡1)

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፡፡ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡ ሥራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና፡፡ ኀጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል፡፡ አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝም ሰው በእርግጥ ታላቅን ዕድል አገኘ፡፡» (አል-አሕዛብ 33፡70-71)

ከዚህም በመቀጠል ለዚያ የራሱን ነብይ ከታሪካቸውና ከምሪታቸው አነስተኛውን ነገር ማወቅ እርሱ ዘንድ ዝቅተኛው ሐሳብ ለሆነበት ሰው ሁሉ እነርሱን ከማወቅ የማይብቃቃባቸው እነዚህ ቀላል ቃላት ቀርበውለታል፡፡ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክና ምሪታቸውን የማወቅን አንገብጋቢነት አስመልክቶ ታላቁ ሊቅ ኢማም ኢብኑል ቀይም (አላህ ይዘንላቸውና) እንዲህ ብለዋል፡- «በሁለቱም ሀገራት ውስጥ የአንድ የአላህ ባሪያ ደስታው ከነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ምሪት ጋር የተቆራኘ እስከሆነ ድረስ፣ በዚያ ለነፍሱ መልካምን ነገር ለሚሻ፣ ድነቷንና ደስታዋንም ለሚወድ ሰው ሁሉ ከርሳቸው ምሪት፣ ከታሪካቸውና ከጉዳያቸው (የሚገባውን ያህል) ማወቅ በርሱ ላይ ግዴታ ይሆንበታል፡፡

በዚህም (ዕውቀቱ) ሳቢያ ከዚህ ጉዳይ አላዋቂዎች ከሆኑት ሰዎች መካከል ይወጣበታል፤ በዚህም አማካኝነት ከተከታዮቻቸው፣ ከደጋፊዎቻቸውና ከፓርቲያቸው ተርታ ይገባበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሰዎች አነስተኛ ዕውቀትን ብቻ የተሰጡ፣ ብዙ ዕውቀትን የተሰጡና (ከዚህ ዕውቀት ምንም ድርሻ) የሌላቸው በሚል መካከል ይካፈላሉ፤ ምክንያቱም ትርፋቱ በአላህ እጅ ሲሆን፣ እርሱም ትሩፋቱን ለሚሻው ሰው ይሰጣል፤ አላህም የታላቅ ትሩፋት ባለቤት ነውና፡፡

ልዕለ ኃይሉ አላህ እኔንና እናንተንም የነብዩን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ውዴታ፣ ያዘዙትን ነገር መታዘዝንና ከከለከሉት ነገር መራቅንና መገሰጽን እንዲለግሰን እማፀነዋለሁ፡፡ አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ እዝነትህን አስፍን፤ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ እንዳሰፈንክ ሁሉ፡፡ አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን አስፍን፤ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ፤ አንተ ምስጉኑና ልዑሉ ነህና፡፡ ምስጋና ሁሉ የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ይሁን፡፡



ክፍል ፡ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መገለጫ ባህሪያት እና ምሪታቸው



መገለጫ ባህሪዎቻቸው

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዘር ሐረግ

ስማቸው ሙሐመድ ኢብን ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል ሙጧሊብ ኢብን ሃሺም ኢብን ዐብዱ መናፍ ኢብን ቁሰይ-ዩ ኢብን ኪላብ ኢብን ሙር-ረህ ኢብን ከዕብ ኢብን ሉአይ-ዩ ኢብን ጋሊብ ኢብን ፊህር ኢብን ማሊክ ኢብን አን-ነድር ኢብን ኪናነህ ኢብን ኹዘይመህ ኢብን ሙድሪከህ ኢብን ኤሊያስ ኢብን ሙደር ኢብን ነዛር ኢብን መዐድ-ዲ ኢብን አድናን ሲሆኑ፣ አድናንም የኢስማዒል አዝ-ዘቢሕ ልጅ ናቸው። ኢስማዒልም የኢብራሂም አል-ኸሊል (ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በጥቅሉ በዘር ሐረጋቸው ረገድ ከመላው የምድር ነዋሪዎች መካከል እጅግ ምርጡ ናቸው። በሐዲሥም እንደተዘገበው የሮማው ንጉሥ ሂረቅል ለአቢ ሱፍያን እንዲህ ብሏቸዋል፡- «ስለዘር ሐረጉ ጠየቅኩ። አንተም እርሱ በዘር ሐረጉ ረገድ ከናንተ መካከል ምርጡ እንደሆነ አወሳህልኝ። ልክ እንደዚሁ መልዕክተኞች ከሕዝቦቻቸው መካከል ከምርጡ የዘር ሐረግ ይላኩ ነበር።»

አላህ መረጣቸው

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእውነቱ አላህ ከኢስማዒል ልጆች መካከል ኪናናን መርጧል፤ ከኪናና ልጆች መካከልም ቁረይሽን መርጧል፤ ከቁረይሽም መካከል የሃሺም ልጆችን መርጧል፤ እኔንም ከሃሺም ልጆች መካከል መርጦኛል።» (ሙስሊም)

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች

ሁሉም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች መገለጫዎች እንጂ ለትውውቅ ብቻ የሚያገለግሉ ስሞች አይደሉም። ይልቁንስ እነርሱ ውዳሴና ምሉዕነት ከሚገባቸው ከተረጋገጡ መለያ ባህሪዎቻቸው የተገኙ ስሞች ናቸው።

ሙሐመድ

ይህ ከርሳቸው ስሞች መካከል እጅግ ታዋቂው ነው። ይህ ስም በተውራት (ኦሪት) ውስጥም በግልጽ የተጠሩበት ነው። ትርጓሜውም የተመሰገነ፣ እርሱ ያ ለብዙ መልካም ባህሪያቱ የተወደሰ ማለት ነው።

አሕመድ

ይህም ከፍጥረታት መካከል አላህን እጅግ ሲበዛ የሚያመሰግነው ወይም አመሰጋኙ ማለት ነው። በመለያ ባህሪዎቻቸው ብዛት የተነሳ የሰማያትና የምድር ነዋሪዎች፣ የዱንያና የኣኺራ ነዋሪዎችም ያመሰግኑታል (ያወድሱታልም)። ይህ አል-መሲሕ ዒሳ (ዐ.ሰ) እርሳቸውን የጠሩበት ስማቸውም ነው።

አል-መኣዊ-ኪል

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ስም የተጠሩበት ምክንያት ዲኑን በማቋቋም ረገድ ማንም የማይጋራቸውን ትክክለኛ ተወክ-ኩልን (በአላህ ላይ መመካትን) በአላህ ላይ በመመካታቸው ነው።

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች		
	አል-ማሒ (አስወጋጁ)	አል-ማሒ ማለት ያ በእርሱ አማካኝነት ኃያሉ አላህ ክህደትን የሚያስወግድበት ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ኃያሉ አላህ በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት ክህደትን ባስወገደበት ልክ በሌላ በማንም አማካኝነት አላስወገደም፡፡
	አል-ሓሽር (ሰብሳቢው)	አል-ሓሽር ማለት እርሱ ያ መላው የሰው ዘር በርሳቸው እግር ሥር የሚሰባሰብለት ማለት ነው፡፡ ይህም ልክ እርሳቸው የሰውን ልጆች ለማሰባሰብ እንደተላኩት ዓይነት ነው፡፡
	አል-ዓቂብ (የመጀመሪያው)	አል-ዓቂብ (የመደምደሚያው) ማለት እርሱ ያ ከኋላው ሌላ ነብይ የማይመጣበት ማለት ነው፡፡ ስለሆነም እርሳቸው የነብያት ሁሉ መቋጫ ናቸው፡፡
	አል-ሙቀፍ-ፊ (ዱካን ተከታዩ)	አል-ሙቀፍ-ፊ ማለት እርሱ ያ የቀደሙትን (ነብያት) ዱካን ተከትሎ የተላከ ማለት ነው፡፡ ኃያሉ አላህም ከመልዕክተኞች እርሳቸውን በቀደሙት ዱካ ላይ ተከታይ አድርጎ ላካቸው፡፡
	ነብዩት-ተውባ	የተውበቱ ነብይ ማለት ያ በርሱ አማካኝነት አላህ ለምድር ነዋሪዎች የተውበትን በር የከፈተበት ሲሆኑ (ተከታዮቻቸውም) ከርሳቸው በፊት ማንም ያላገኘውን ተውበትን (በማግኘት አላህም ፀፀታቸውን ተቀብሎ በምሕረቱ) ተመለሰላቸው፡፡ እናም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው ተውበት ማድረግንና ምሕረት መለመንን ከሚያበዙ ሰዎች ሁሉ በላጩ ናቸው፡፡
	ነብዩል መልሐማ	ነቢይ-ዩል መልሐማ (ጀግናው ነብይ) ማለት ያ የአላህን ጠላቶች እንዲታገል የተላከ ጀግና ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው በአላህ መንገድ ላይ በታገሉት ልክ የታገለ ሌላ ነብይና ተከታዮቹ የሉም፡፡ እነዚያ የተሰው ታላላቅ ጀግኖችም ከርሳቸው በፊት ፈፅሞ እንደሚነሱ ቃል አልተገቡም ነበር፡፡
	ነብዩር-ረሕማ	ነቢይ-ዩል መልሐማ (ጀግናው ነብይ) ማለት ያ የአላህን ጠላቶች እንዲታገል የተላከ ጀግና ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው በአላህ መንገድ ላይ በታገሉት ልክ የታገለ ሌላ ነብይና ተከታዮቹ የሉም፡፡ እነዚያ የተሰው ታላላቅ ጀግኖችም ከርሳቸው በፊት ፈፅሞ እንደሚነሱ ቃል አልተገቡም ነበር፡፡
	አል-ፋቲሕ (ከፋቹ)	አል-ፋቲሑ ማለት ያ አላህ ምሪትን (የቅናቻ መንገድን)፣ እርሱ ከተወዛወዘ በኋላ የከፈተበት ነው፡፡ የዕውሮችን ዓይኖች፣ የደንቆሮዎችን ጆሮዎችና የተሸፈኑ ልቦችን የከፈተበት ነው፡፡ እንደዚሁም በርሳቸው አማካኝነት ኃያሉ አላህ የከሀዲዎችን ግዛቶች ከፈተበት፡፡ በርሳቸው አማካኝነትም የጀነትን በሮች ከፈተበት፡፡ እንደዚሁም ወደጠቃሚ ዕውቀትና ወደ መልካም ሥራ (የሚያደርስ) መንገድን ከፈተበት፡፡

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሞች	አል-አሚን (ታማኙ)	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዓለማት እንደዚህ ዓይነት ስም ይኖራቸው ዘንድ እጅግ ተገቢው ሰው ናቸው፡፡ በወሕዩ እና በዲኑ ረገድ በአላህ ዘንድ ታማኙ ሰው ናቸው፡፡ እርሳቸው በሰማይ ነዋሪዎች ዘንድም ታማኙ ናቸው፡፡ በምድር ነዋሪዎች ዘንድም ታማኙ ናቸው፡፡ እንዲያውም መልዕክተኛ ሆነው ከመላካቸው በፊት የቁረይሽ ከሀዲያን እርሳቸውን ‹አል-አሚን› በማለት መሰየማቸው የሚታወስ ነው፡፡
	አል-በሺር (አብሳሪው)	አል-በሺር ማለት እርሱ ያ እርሳቸውን የሚታዘዙ ሰዎች ታላቅ ምንዳን በማግኘት የሚያበስሩና እርሳቸውን የሚያምፁትን ደግሞ በቅጣት የሚያስጠነቅቁ ናቸው፡፡
	የአደም ልጆች ሁሉ አለቃ	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ በትንሳኤው ዕለት የአደም ልጆች ሁሉ አለቃ ነኝ፤ ይህም ጉራ አይደለም .... »
	አስ-ሲራጅ አል-ሙኒር (አንፀባራቂ ደማቅ ብርሃን)	አስ-ሲራጅ አል-ሙኒር ማለት ያ ሳያቃጥል ደማቅ ብርሃንን የሚያስገኝ ነው፡፡ ይህም ከወህ-ሃጅ ተቃራኒ መሆኑ ነው፤ ምክንያቱም በወህ-ሃጅ ውስጥ አቃጣይ የሆነ የብርሃን ዓይነት አለበትና፡፡
		ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዐብዱሏህ ናቸው፡፡ ትርጉሙም የአላህ ባሪያ ሲሆን ዒባዳ ሁሉ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው፡፡ ዐብዱሏህ የተባሉበት ሁሉንም የዒባዳ ደረጃዎችን ስላሟሉ ነው፡፡
ውብ መገለጫዎቻቸው		የነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እጅግ የተሟላ መግለጫዎቻው እርሳቸው ራሳቸውን የገለጹበት መንገድ ነው፡፡ እንዲህም ብለዋል፡- *«እኔ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው ሙሐመድ ነኝ፡፡ (ስለሆነም ልዕለ ኃያሉ) አላህ እኔን ካሰቀመጠበት ደረጃ በላይ እናንተ ከፍ እንድታደርጉኝ አልወድም፡፡»*
		ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአፈጣጠርና በምግባር ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ ናቸው፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡»* (68፡4) እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ምግባራቸው ቁርአን ነበር፡፡» ስለሆነም በቁርአኑ ይሠሩበት፤ ሕግጋቱም ጋር ይቆሙ፤ የሚወደውንም ይወዱና በሚያስከፋውም ይከፉ ነበር፡፡
	የአላህ ወዳጅ	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእውነቱ አላህ ልክ ኢብራሂምን ወዳጁ አድርጎ እንደያዛቸው ሁሉ እኔንም ወዳጁ አድርጎ ይዞኛል፡፡»
የአፈጣጠራቸው መገለጫዎች	ክቡር ገላቸው	አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ደማቅ የሆነ (የፊት) ቀለም ያላቸው ነው፤ (ማለትም ነጭና ክብ) መልክ አላቸው፡፡ የላቦታቸው (ጠቢታዎች) ልክ እንደ ሉል (የሚያንፀባርቁ) ናቸው፡፡ በሚራመዱበትም ጊዜ ወደፊት አዘምመው ነው፡፡ እኔ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መዳፍ ይበልጥ ለስላሳ የሆነ ዲባጅንም (ከሐር የበለጠ ውድ ልብስ) ሆነ ሐርንም አልነካሁም፡፡ እንደዚሁም እኔ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጠረን የበለጠ ምርጥ መዓዛ ያለው ሚስክም ሆነ ዐንበር አሽትቼ አላውቅም፡፡»

የአረጠራቸው መገለጫዎች

ተክለ ቁመናቸው

አል-በራእ ኢብን ዓዚብ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሀከለኛ ቁመት አላቸው (ረጅምም አጭርም አይደሉም)። በሁለቱ ትከሻዎቻቸው መካከል ያለው ቦታም ሰፊ ነው። እስከ ጆሮአቸው የሚደርስ ፀጉርም አላቸው። ቀይ ሙሉ ልብስ ለብሰው አይቻቸዋለሁ። ከርሳቸው ይበልጥ ያማረ አንዳችም ነገር ፈፅሞ አይቼ አላውቅም።»

ፊታቸው

ከዕብ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(አንድ ቀን) ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታን ሳቀርብ ከደስታ የተነሳ ፊታቸው ያብረቀርቅ ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ደስተኛ በሆኑ ጊዜ ፊታቸው ልክ እንደ ጨረቃ ቁራሽ ያበራ ነበር። ስለሆነም እኛም ይህንኑ ከፊታቸው ላይ እናውቅ ነበር።»

እንደዚሁም አል-በራእ «የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊት ሰይፍን ይመስል ነበር ወይ?» ተብለው ተጠይቀው ነበር። እርሳቸውም «የለም! ይልቁንስ ፊታቸው ጨረቃን ነው የሚመስለው» በማለት መለሱ።

ፀጉራቸው

አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ትላልቅ እጆች አላቸው። እኔም ከርሳቸው በኋላ የርሳቸውን እጆች የሚመስል (እጅ) ፈጽሞ አይቼ አላውቅም። የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፀጉር ያልተረጋጋ ሲሆን የተጠቀለለ ፀጉርም አይደለም፤ ቀጥ ብሎ የቆመም አይደለም።»

ዓይኖቻቸው

ጃቢር ኢብን ሰሙረህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሰፊ አፍና ቀያይ (ሰፋፊ) ዓይኖች (በነጫጭ ዓይኖች ውስጥ ቅላት ያለበት) እና ቀጫጭን ተረከዞች አላቸው።

ላባቸው

አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደቤታችን ገቡና እኛም ዘንድ ቀይሉላን (በቀኑ ከ/ጊዜ የሚተኛውን እንቅልፍ) ተኙ። ላብም አላባቸው። እናቴም ብልቃጥ ይዛ መጣችና (ላባቸውን ወደዚያ) አንቆረቆረች (ወይም በዕቃው ውስጥ) ላቡቱን ሰበሰበች። (የኋላ ኋላም) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንቅልፋቸው ነቁና ‹ኡም-ሙ ሰለይም ሆይ! ምን እያደረግሽ ነው?› አሏት። እርሷም ‹ይህ የርስዎ ላብ ነው፤ በሽቶአችንም ውስጥ እናደርገዋለን፤ እርሱም ከሽቶዎች ሁሉ በላጩ ሽቶ ይሆናል› አለች።»

የነብይት ማሕተማቸው

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በትከሻዎቻቸው መካከል የነብይነት ማሕተም አለባቸው። ይህም ልክ እንደ ልደት ምልክት በሰውነታቸው ላይ የሚገኝ አንዳች ለየት ያለ ነገር ነው።

ጃቢር ኢብን ሰሙረህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «ትከሻቸው ላይ የፔንጊዮን እንቁላልን የሚመስል ማሕተም አየሁ። ከሰውነታቸው (የቆዳ ቀለም) ጋርም ይመሳሰላል።»

የመወቢያዎች መገለጫዎች

ባልደሮቻቸው ለርሳቸው የነበራቸው አክብሮት

ዐምር ኢብን አል-ዓስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በላይ እኔ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ሰው የለም፤ ከርሳቸውም በላይ በዓይኖቼ ዘንድ የላቀ ሰው የለም፤ ለርሳቸው ካለኝ አክብሮት የተነሳ በሙሉ ዓይኖቼ ልመለከታቸው ዘንድ ድፍረቱ አልነበረኝም፡፡ ስለሆነም እርሳቸውን እንድገልጻቸው ብጠየቅ፣ ያንኑ ማድረግ አልችልም፤ ምክንያቱም በሙሉ ዓይኖቼ እርሳቸውን አይቻቸው አላውቅምና፡፡»

ዑርዋ ኢብን መስዑድ አሽ-ሸቀፊይ-ይ (ረ.ዐ) በሑደይቢያው (ስምምነት) ዕለት እርሳቸውን ለቁረይሾች በሚገልጽበት ጊዜ እንዲህ ብለዋል፡- «በአላህ እምላለሁ! የሙሐመድ ባልደረቦች ሙሐመድን እንደሚያከብሩት ባልደረቦቹ (የክብር ባለሟሎቹ) ዘንድ እንደዚያ የሚከበር ንጉሥ አላየሁም፡፡ በአላህ እምላለሁ! እርሳቸው አንዲት ምራቅን የተፉ እንደሆነ፣ ምራቁ ከነርሱ (ከነብዩ ባልደረቦች) መካከል በአንዳቸው መዳፍ ላይ የሚያርፍ ቢሆን እንጂ አይተፉም ነበር፡፡ እርሱም በዚያ (ምራቅ) ፊቱንና (የሰውነቱን) ቆዳ ያብስበታል፡፡ አንዳች ነገርን ባዘዛቸው ጊዜም ትዕዛዛቸውን ለመፈጸም ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡ እርሳቸው ዉዱእ ያደረጉ እንደሆነ፣ የተቀረውን ውሃ ለመውሰድ ሲሉ እርስ በርሳቸው ለመታገል ይቀርቡ ነበር፡፡ እርሳቸው በሚናገሩበት ጊዜ፣ ከርሳቸው ዘንድ ድምፃቸውን ዝቅ ያደርጉ ነበር፡፡ ለርሳቸው ካላቸው አክብሮት የተነሳም ወደርሳቸው ፊት በቀጣይነት አይመለከቱም ነበር፡፡»

ከአላህ ጋር የነበራቸው አዳብ

ዐብዱል-ሏህ ኢብን አሽ-ሺኽ-ኺር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን እኛ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)) ‹እርስዎ አለቃችን (ሰይ-ዱዳችን) ነዎት› አልናቸው፡፡ እርሳቸውም «አለቃው የተባረከውና የተላቀው አላህ ነው» አሉ፡፡ እኛም «እርስዎ በላጫችንና በልግስናም ረገድ ታላቃችን ነዎት» አልናቸው፡፡ እርሳቸውም «ማለት የሚገባችሁን ነገር ብቻ በሉ፤ ወይም ማለት ከሚገባችሁ ነገር ከፊሉን በሉ፤ ሸይጣንም (ከመንገዳችሁ ላይ) እንዳያሮጣችሁ አደራችሁን (ተጠንቀቁ)› አሉን፡፡»

ጀግንነታቸው

ዐሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «ጦርነቱ በሚፋፏምበትና ሁለቱም ጎራዎች ለውጊያ ግንባር ለግንባር በሚገናኙበት ጊዜ እኛ ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንፈራላቸው ነበር፤ (ምክንያቱም) ከኛ መካከል የርሳቸውን ያህል ወደሰዎቹ (ወደጠላት) የሚቀርብ አንድም ሰው የለምና ነው፡፡»

ለአላህ የነበራቸው ፍራቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «... በአላህ እምላለሁ! እኔ ከናንተ መካከል ይበልጥ አላህን ፈሪውና ከናንተም በላይ ይበልጥ ከርሱ ተጠንቃቂው ነኝ፡፡ ....»

ለቤተሰቦቹ ያላቸው ደግነት

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «ከናንተ መካከል ምርጡ ለቤተሰቡ (ለሚስቱ) ይበልጥ ምርጡ የሆነው ሰው ነው፡፡ እኔም ከናንተ መካከል ለቤተሰቦቼ ይበልጥ ምርጡ ነኝ፡፡»

ዓይናፋርነታቸው

አቡ ሰዒድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በዓይናፋርነት ረገድ በጓኖቻው ውስጥ ካሉ ልጃ ገረዶች ይበልጥ ብርቱ ናቸው፡፡ አንዳች የሚጠሉትንም ነገር በተመለከቱ ጊዜ፣ ያንኑ ከፊታቸው ላይ እናውቅ ነበር፡፡»

ማማራታቸው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሁለት ጉዳዮች መካከል ምርጫን አያደርጉም ነበር፤ ይበልጥ ገር የሆነውን ነገር የመረጡ ቢሆን እንጂ፤ ያ ነገር ኃጢአትን የማያስከትል እስከሆነ ድረስ፡፡ ጉዳዩ (ኃጢአት ከሆነ) ግን፣ ከማንም በላይ ከሁለቱም (አማራጮች) ይበልጥ የሚርቁ ነበሩ፡፡»

የሰሃባዎቻቸው መገለጫዎች

ለራሳቸው ብለው አልተበቀሉም

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «በአላህ እምላለሁ! የአላህ ክልከላዎች እስካልተጣሱ ድረስ (ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/) ወደርሳቸው ለመጣው በማንኛውም ነገር ለራሳቸው ብለው የበቀል እርምጃ ወስደው አያውቁም። (ነገር ግን) ለአላህ ብለው የበቀል እርምጃን ይወስዱ ነበር።»

ምግብን አናውረው አያውቁም

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ምግብን አነውረው (ለምግብ አቃቂር አውጥተው) አያውቁም። (ይልቁንስ) የወደዱት እንደሆነ ይመገቡት፣ የጠሉት እንደሆነ ደግሞ ይተውት ነበር።»

ስጦታን ይቀበሉ ነበር

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ስጦታን ይቀበሉና በአጸፋውም አንዳች ነገርን ይሰጡ ነበር።»

ምጽዋትን ተቀብለው አያውቁም

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «የሙሐመድ ቤተሰቦች ከሰደቃ (ከምጽዋት) አይመገቡም።»

ትሕትናቸው

ዐቅባ ኢብን ዓሚር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «(ከዕለታት አንድ ቀን) አንድ ሰውዬ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና አናገራቸው። በሚያወራበት ጊዜም (ከአክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ) በደረቱና በትከሻዎቹ መካከል ያለው የሰውነት ክፍሉ በኃይለኛው ይንቀጠቀጥ (ይመታ) ነበር። (በዚህን ጊዜ) ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ‹ተረጋጋ፤ ምክንያቱም እኔ ንጉሥ አይደለሁምና። በእውነቱ እኔ የዚያች ድርቆሽ (ተምር) የምትበላ ሴት ልጅ ብቻ ነኝ› አሉት።»

ቤተሰቦቻቸውን ማገልገላቸው

ከአል-አስወድ ኢብን የዚድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንደተወራው እኔ ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በቤታቸው ውስጥ ምን እንደሚሠሩ ዓኢሻን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጠየቅኳቸው። እርሷም «በቤተሰቦቻቸው አባላት ሙያ ላይ ይሆኑ ነበር - የቤተሰቦቻቸውን አባላት በመስተንግዶ ያግዙ ነበር። ሶላትም በደረሰች ጊዜ ወደ ሶላት ይወጡ ነበር» አለች።

አለቁጭኝነታቸው ችላ ማለታቸው

የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «ኃያሉ አላህ የቁረይሾችን ስድብና እርግማናቸውን ከኔ ላይ እንዴት እንደመለሰ (ብታውቁ) አያስደንቅቻሁምን? እነርሱ ሲሰድቡ የነበረው ሙዘም-መምን ነው። ሲረግሙትም የነበረውም ሙዘም-መምን ነው፤ ይሁንና እኔ ሙሐመድ ነኝ (እንጂ ሙዘም-መም አይደለሁም)።»

እውነተኛ-ነታቸው

ዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የእውነተኞች ሁሉ እውነተኛ የሆኑት የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) (እንደዚያና እንደዚህ) ብለው ነግረውናል።»

ከአገልጋዮቻቸው ጋር የነበራቸው ምግባር

አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኔ የአላህን መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ለአስር ዓመታት ያክል አገልግያቸዋለሁ፤ እርሳቸውም ለኔ (አንድም ቀን ፊጽሞ) ‹ኡፍ-ፍ› (ውድቅ የማድረጊያ ቃል) ብለውኝ አያውቁም። እንደዚሁም ለአንዳች እኔ ለሠራሁት ነገር ‹እንዲህ ለምን አደረግክ?› ብለውኝ አያውቁም። እንደዚሁም አንዳች እኔ ያልሠራሁትን ነገር አስመልክቶም ‹እንደዚህ አላደረግኽምን?› ብለውኝ አያውቁም።»

የሰሃባዎቹ መገለጫዎች

ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ለየት ብለው ኢያውቁም

አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «እኛ በመስጊድ ውስጥ ተቀምጠን ሳለ በግመል ላይ የተቀመጠ ሰው ገባና ግመሉም በመስጊዱ ውስጥ እንዲንበረከክ አደረገ፡፡ ከዚያም ግመሉን አሰረውና ለነርሱም ‹ከናንተ መካከል ሙሐመድ የትኛችሁ ነው?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው በስተ ጀርባ ጋደም ብለው ተቀምጠው ነበር፡፡ እኛም ለሰውዬው ‹ይህ ጋደም ብሎ የተቀመጠ ነጩ ሰውዬ ነው› አልነው፡፡ ሰውየውም ለርሳቸው ‹አንቱ የዐብዱል ሙጠሊብ ልጅ ሆይ!› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹አቤት ብያለሁ› አሉት፡፡ ሰውዬውም ‹ሙሐመድ ሆይ! እኔ ጥያቄዎችን ልጠይቅህ ነው፤ በአጠያየቄ ውስጥም ኃይለኛ እሆንብሀለሁ፤ ስለሆነም እንዳትከፋብኝ› አላቸው፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹የተገለጠልህን ነገር ጠይቅ› አሉት፡፡ ሰውዬውም «እኔ ባንተና በነዚያ ካንተ በፊት በነበሩ ሰዎች ጌታ ስም እማጸንህለሁ፤ ለመሆኑ አንተን ወደመላው የሰው ልጆች የላከህ አላህ ነውን?» አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን› አሉት፡፡ እርሱም ‹እኔ በአላህ ስም እማፀንህለሁ፤ በእያንዳንዱ ቀንና ሌሊት አምስት ወቅት ሶላቶችን እንድንሰግድ ያዘዘን አላህ ነውን?› አላቸው፡፡

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡ እርሱም ‹እኔ በአላህ ስም እማፀንህለሁ፤ ከዓመቱ ውስጥ ይህንን ወር እንድንፆም ዘንዳ ያዘዘን አላህ ነውን?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡ እርሱም ‹በአላህ ስም እማፀንህለሁ! ይህንን ዘካት ከሀብታሞቻችን እንድትወስድና በድሆቻችንም መካከል እንድታከፋፍል ያዘዘህ አላህ ነውን?› አላቸው፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹በአላህ እምላለሁ! አዎን!› አሉት፡፡

ሰውዬውም ‹እኔ አንተ ይዘህ በመጣኸው ነገር አምናለሁ፤ እኔም ከኔ ኋላ ላሉ ሕዝቦቼ መልዕክተኛቸው ነኝ፤ እኔ ዲማም ኢብን ሠዕለባ፣ የበኑ ሰዐድ ኢብን በክር ወንድም ነኝ› አለ፡፡»

ሞግበሽው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)» ቤተሰቦች ለሁለት ተከታታይ ቀናት ከገብስ የተሠራ ዳቦን ጠግበው በልተው ኢያውቁም፡፡

በዱንያ ውስጥ የነበራቸው ዘህድ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከዚህ ከኡሑድ (ተራራ) ጋር የሚስተካከል ወርቅ ቢኖረኝ አያስደስተኝም፤ ከርሱ የሆነ ምንም ነገር - ከርሱ የሆነ አንዲት ዲናር እንኳ ሳይቀር - ዕዳን ለመክፈል ከማስቀረው ነገር በስተቀር እኔ ዘንድ ከሦስት ቀናት በላይ መቆየቱ አያስደስተኝም፤ (ይልቁንስ) እርሱን በአላህ ባሮች መካከል ልከ እንደዚህ፣ ልከ እንደዚህ እና ልከ እንደዚህ እያልኩ (የማከፋፍለው) ብሆን እንጂ፡፡»

ፀያፍ ቃላትን አልተናገሩም

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባለጌም አይደሉም፡፡ የብልግና ቃላትንም የሚናገሩ አይደሉም፡፡ በገበያ ቦታዎች ውስጥም ጮኸ ብለው የሚያወሩ አይደሉም፡፡ ለመጥፎ ሥራ በመጥፎ ሥራ አማካኝነት አጸፋ ሰጥተው አያውቁም፡፡ ይልቁንስ ይቅርታን ያደርጉና ባላየ ያልፉ ነበር፡፡»

የባዳ ሴትን እጅ ከጉው አያውቁም

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- « ... የአላህ መልዕክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እጆች የባዳ ሴትን መዳፍ ፈፅሞ ነክተው አያውቁም፡፡»

ትምህርትና ውትወታ	የአኗኗሯቸው ሁኔታ	
		ዑመር (ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከቁጠማ የተሠራ ሰሌን ላይ ሳሉ በርሳቸው ላይ ገባሁና ተቀመጥኩ::ሽርጣቸውም ተጣብቆባቸዋል:: ከዚህ ውጭም ሌላ ነገር በርሳቸው ላይ የለም ::ስለሆነም የቁጠማው ምንጣፍ በጎናቸው ላይ ምልክቶችን አሳርፏል:: በዓይኔም ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዕቃ ቤት ተመለከትኩ:: በዚህን ጊዜ አንድ እፍኝ፣ ከሞላ ጎደል አንድ ሷዕ የሚሆን ገብስ ተመለከትኩ:: በተመሳሳይ መልኩ የተወሰኑ የግራር ቅጠሎችን በክፍሉ ጥግ ላይ ተመለከትኩ:: እንደዚሁም የተንጠለጠለ ሌጦም (ተመለከትኩ):: ዓይኖቼ በእንባ ተጥለቀለቁ:: እርሳቸውም ‹የአል-ኸጧብ ልጅ ሆይ! ምንድነው የሚያስለቅስህ?› አሉኝ:: እኔም ‹የአላህ ነብይ ሆይ! ለምንድነው የማላለቅሰው? ይህ ሰሌን እኮ በርስዎ ጀርባ ላይ ሰንበርን አሳርፏል፤ እርስዎ ያከማቹት ነገር ሁሉ ይህ ብቻ ነው:: በዚህች (የዕቃህ) ክፍልህ ውስጥ ከማየሁ ነገር ውጭ ሌላ አንዳችም ነገር ማየት አልቻልኩም:: ከወደዚያ ቄሰርና ኪስራ (ንጉሦቻቸው) በፍራፍሬዎችና በወንዞች ውስጥ (የሚንደላቀቁ ናቸው):: ይሁንና እርስዎ የአላህ መልዕክተኛና የርሱ ተመራጩ ሰው ነዎት፤ እናም እርስዎ ያከማቹት ነገር ይኼው ነው?› አልኳቸው:: እርሳቸውም ‹የአል-ኸጧብ ልጅ ሆይ! ለመሆኑ ኣኺራ ለኛ ብትሆንና ዱንያም ለነርሱ ብትሆን አትደሰትምን? (ማለትም እነዚህ ነገሮች በቀጣዩ ዓለም ለኛ መሆናቸውና በዚህች ዓለም ውስጥ ደግሞ ለነርሱ መሆናቸውን (ማወቅህ) አያስደስትህም ወይ?› አሉኝ:: እኔም ‹እንዴታ! (ያስደስቱኛል እንጂ)› አልኳቸው::

የመጀመሪያው ፈተና

ውሸት	እውነት	ጥያቄዎች
£	□	የአንድ የአላህ ባሪያ ደስታው በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ውስጥ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምሪት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡
£	£	መልዕክኞች የተላኩት ከሕዝቦቻቸው ምርጥ የዘር ሐረግ ነው፡
£		የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምርጡ መገለጫ ቢኖር እርሳቸው «እኔ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው ሙሐመድ ነኝ» በማለት ራሳቸውን የገለጹበት መንገድ ነው፡፡
£	£	አላህ በመልዕክተኛው ዘንድ ሁሉንም የተሟሉ ምግባራትንና የተዋቡ መገለጫ ባህሪያትን አሰብስቧል፡፡ ለርሳቸውም ከዕውቀትና ከትሩፋትም ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም ውስጥ በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ድል፣ ስኬትና ደስታ አለበት፡፡ ይህ (ሁሉ ለቅናም) ከዓለማት ውስጥ ለለ ለአንዮም ሰው አልተሰጠም፡፡
£	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያልተማሩ፣ ማንበብም ሆነ መጻፍ የማይችሉ፣ እንደዚሁም አንድም ሰብአዊ አስተማሪ ያልነበራቸው ሰው ናቸው፡፡

1. በደፈናው በዘር ሐረግ ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ፡
   ሀ/ ዩኑስ ኢብኑ መት-ታ ለ/ ሙሐመድ ኢብን ዐብደላህ (ሰ.ዐ.ወ)
2. ስሞቻቸው፡- ሀ/ ሁሉም መገለጫዎች ናቸው ለ/ ለትውውቅ ብቻ የሚጠቅሙ ምልክቶች ናቸው ሐ/ ምስጋናንና ውዳሴን ከሚያስከትሉ የተረጋገጡ ባህሪያት የተገኙ ናቸው መ/ ሁሉም ሠ/ ሀ እና ሐ
3. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «ምግባራቸው ሁሉ ቁርኣን ነው» ማለት፡- ሀ/ ቁርኣኑን በሚያስደስት ነገር ይደሰቱ ነበር ለ/ ቁርኣኑን በሚያስቆጣ ነገር ይቆጡ ነበር ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
4. ኸሊሉሏህ (የአላህ ወዳጅ) ማነው? ሀ/ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ለ/ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሐ/ ሁለቱም
5. «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቆዳ ቀለማቸው በጣም ደመቅ ያለ ነው» ማለት፡- ሀ/ ስንዴያማ (ፈዘዝ ያለ ቢጫ) ለ/ ነጭ ሐ/ እጅግ የነጣ
6. ከሸቶዎች ሁሉ ምርጡ ሽቶ፡- ሀ/ ሚስክ ለ/ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላብ
7. «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቁመታቸው መሀከለኛ ነው» ማለት፡-
   ሀ/ ረጅምም አጭርም አይደሉም ለ/ ቁመታቸው ረጅም ነው
8. የነብይነት ማሕተማቸው፡- ሀ/ በትከሻዎቻቸው መካከል ይገኛል ለ/ ከሰውነታቸው ጋር ይመሳሰላል ሐ/ የፔንጊዮንን እንቁላል ይመስላል መ/ ሁሉም ልክ ነው

ከቁረይሽ መካከል	ኢስማዒል	ከሃሺም ልጆች መካከል	ከኪናና	አላህ መረጠ፡-
£	£	£	£	ኪናናን ከ ..... ልጆች መካከል
£	£	£	£	ቁረይሽን ከ .....
£	£	£	£	ከሃሺም ልጆች .....
£	£	£	£	ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከ.....

የቅመ ቅምቅመ አያታቸው ስም	የቅምቅመ አያታቸው ስም	የቅመ አያታቸው ስም	የአያታቸው ስም	የአባታቸው ስም	ስማ-ቸው	የዘር ሐረጋቸው፡-
£	£	£	£	£	£	ሃሺም
£	£	£	£	£	£	ዐብዱል ሙጠሊብ
£	£	£	£	£	£	ዐብደሏህ
£	£	£	£	£	£	ሙሐመድ
£	£	£	£	£	£	ኢስማዒል
£	£	£	£	£	£	ኢብራሂም

አስ-ሲራጅ	አል-ዓቂብ	አሕመድ	ሙሐመድ	ቀጥሎ ያሉትን አዛምዱ፡-
£	£	£	£	ያ ጌታውን እጅግ አብዝቶ የሚያመሰግነው
£	£	£	£	ያ ያለ ማቃጠል ደማቅ ብርሃንን የሚሰጥ
£	£	£	£	ያ በርካታ ምስጉን ባህሪያት ያለው
£	£	£	£	ያ ከኋላው ነብይ የማይመጣበትና የነብያት ሁሉ መቋጫ የሆነው

አላህን በመፍራት	በአፈጣጠርና ምግባር	በአናኗር	ጠረናቸው	መዳፎቻቸው	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-
□	£	£	£	£	ከሰዎች ሁሉ ምርጡ
□	£	£	£	£	እጅግ ለስላሳ ናቸው
□	£	£	£	£	እጅግ የሚያውድ ነው
□	£	£	£	£	እጅግ ደግ ናቸው
□	£	£	£	£	እጅግ የበረቱ ናቸው

ስጦታ	ምጽዋት	ለረሳቸው	ምግብ	ለአላህ	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-
£	£	£	£	£	ብለው አይበቀሉም
£	£	£	£	£	ብለው ይበቀሉ ነበር
£	£	£	£	£	አያነውሩም ነበር
£	£	£	£	£	ይቀበሉና አብዝተውም ይሰጡ ነበር
£	£	£	£	£	አይቀበሉም ነበር

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ

አለባበስን፣ አመጋገብንና አጠጣጥን የሚመለከቱ መመሪያዎቻቸው

እርሳቸው ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑ ከለሮች

ከከለሮች ሁሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የሆነው ነጭ ከለር ነው፡፡ ይህንኑ በማስመልከትም እንዲህ ብለዋል፡- «እርሷ (ነጭ ከለር) ከልብሶቻችሁ (ከለሮች) መካከል በላጩ ናት፤ ስለሆነም ሙታኖቻችሁን በርሷ (በነጭ ልብስ) ከፍኑ፡፡»

አለባበሳቸው

አለባበሳቸውን በተመለከተ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመልበስ ቀላል የሆኑትን ልብሶች ይለብሱ ነበር፡፡ ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ ከሱፍ የተሠሩ ልብሶችን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከጥጥና ከላይነን የተሠሩ ልብሶችን ይለብሱ ነበር፡፡ እንደዚሁም ልብሳቸውን በሚለብሱበት ጊዜ ከቀኞቸው ይጀምሩ ነበር፡፡

በአለበስ መህከለኛ መሆናቸው

ከቀደምቶቻችን መካከል አንዳንዶቻቸው እንዲህ ብለዋል፡- «እነርሱ (ሰለፎች) ሁለት ዓይነት ልብሶችን - ውድ የሆኑ የይዩልኝ ባይነት (የጉራ) ልብሶችንና ያረጁ ያፈጁ የሆኑ (የዛሂድነት ማሳያ የሚመስሉ ልብሶችን) - ይጠሉ ነበር፡፡» ከዐብዱሏህ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) በተወራው ሐዲሥ ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የይዩልኝ ባይነትን (የጉራን) ልብስን የለበሰ ሰው፣ አላህ በትንሳኤው ዕለት እርሱን የውርደት ልብስ ያለብሰዋል፡፡ ከዚያም በውስጡ እሳት ይቀጣጠልበታል፡፡» ይህም የሆነበት ምክንያት እርሱ (በልብሱ) በኩራትና እብሪት ለማጉረር አቅዶ ስለተነሳ ነው፡፡ ስለሆነም አላህ ለዚህ (ወንጀሉ) ቀጣው፡፡ እንደዚሁም ከኢብን ዑመር (ረ.ዐ) በተወራው መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ያ ከኩራት ተነሳ ልብሱን (ከቁርጭምጭሚቶቹ በታች አውርዶ) የሚጎትት ሰው፣ በትንሳኤው ዕለት አላህ ወደርሱ አይመለከትም፤ (ከወንጀሉም አያፀዳውም)፡፡»

ምግባቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያገኙትን ነገር መመገብን እምቢ አይሉም ነበር፡፡ የሌለ ነገር እንዲሠራ በማድረግም ጫና አይፈጥሩም ነበር፡፡ ከንጹሕ ነገሮች አንዳችም ነገር አይቀርብላቸውም፤ የተመገቡት ቢሆን እንጂ፡፡ አንዳች በግላቸው የማይወዱት ነገር ሲሆን ግን፣ ያንኑ ነገር ሐራም ሳያደርጉት ይተውት ነበር፡፡እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፊፅሞ ለምግብ አቃቂር አውጥተው አያውቁም፡፡የወደዱት እንደሆነ ይመገቡት፣ አልያም ይተውት ነበር፡፡» ይህም ልክ የአርጃኖን ሥጋ መመገብን ክልክል ሳያደርጉት እንደተውት ነው፡፡

የአመጋገብ ሁኔታቸው

- አብዛኛው ምግባቸው በሱፍራ ተደርጎ መሬት ላይ ይደረግ ነበር፡፡
- በሦስት ጣቶቻቸው አማካኝነት ይመገቡ ነበር፡፡
- ተጋድመው በመቀመጥ አይመገቡም ነበር፡፡
- በምግባቸው ጅማሮ ላይ የአላህን ስም ይጠሩ ‹ቢስሚሏህ› (በአላህ ስም) ይሉና በስተ መጨረሻም እርሱን ያመሰግኑት ‹አል-ሐምዱ ሊሏህ› (ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባ) ይሉ ነበር፡፡
- ምግባቸውን ከጨረሱ በኋላ ጣቶቻቸውን ይልሱ ነበር፡፡

መጠጣቸው

- አብዛኛውን ጊዜ ተቀምጠው ይጠጡ ነበር፡፡ እንደዚሁም ቁመው ከመጠጣት ገስጸዋል (አስጠንቅቀዋል)፡፡ ይሁንና መቀመጥን የሚከለክል በቂ ምክንያት ሲኖር ቁመው መጠጣትን በይቅርታ አልፈውታል፡፡
- ከጠጡ በኋላ በቀኞቸው በኩል ለሚገኙ ባልደረቦቻቸው መጠጣቸውን ያጋሩ ነበር፤ የቱንም ያህል በዕድሜ የገፉት ከግራቸው በኩል ቢቀመጡም፡፡

ጋብቻና የትዳር ሕይወታቸው

- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከዚህች ዓለማችሁ ውስጥ ሴቶችና ሽቶ እኔ ዘንድ ተወዳጅ ተደርገዋል፡፡ የዓይን ማረፊያዬም በሶላት ውስጥ ተደርጎልኛል፡፡»
- አዳራቸውን (ሌሊቶቻቸውን)፣ ቀረቤታቸውን (ጉድኝታቸውን) እና ቀለብን በሚስቶቻቸው መካከል (በፍትሐዊነት) ያከፋፍሉ ነበር፡፡
- እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጉዞ ለማድረግ ሲያቅዱ በሚስቶቻቸው መካከል ዕጣን ይጥሉ ነበር፡፡ ከዚያም በዕጣ የተመረጠችዋን ከራሳቸው ጋር ይዟት ይሄዱ ነበር፤ እንደዚሁም ለተቀሩት ሚስቶቻቸው (በጉዞ ወቅት ከአንዷ ጋር ብቻ በመሆናቸው ሲመለሱ የተቀሩትን ሴቶች የሌሊቶቻቸውን) ቀድ አያወጡም ነበር፡፡»
- ከሚስቶቻቸው ጋር የነበራቸው የሕይወት ታሪክ ባማረ አብሮነት (አብሮ መኗኗር) እና ባማረ ምግባር ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡
- ከአንሷር የሆኑ ልጃ ገረዶችን ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጋር አብረው ይጫወቱ ዘንድ ወደርሷ ይልኩ ነበር፡፡ እርሷም በትርፍ ጊዜዋ አንዳችም ክልከላ የሌለበትን ነገር መሥራት በምትፈልግበት ጊዜ በዚያ (ሥራዋ) ላይ ይከተሏት (አብሯት ይሠሩ) ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) በዓኢሻ ታፋ ላይ ተጋድመው በመቀመጥ ቁርአንን ይቀሩ ነበር፡፡ እርሷ በወር አበባዋ ዑደት ላይ ብትሆን እንኳን (ይህንኑ ያደርጉ ነበር)፡፡
- እርሷ በወር አበባዋ ዑደት ላይ በምትሆንበት ጊዜ አጭር ልብስን እንድትለብስ ያዟትና ከዚያም አንዳቸውም በአንዳቸው ይደሰቱ ነበር፡፡
- ፆም ላይ እያሉም ይስሟት ነበር፡፡
- ይህም ከሚስቶቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ከእዝነተ ረቂቅነታቸውና ከምግባራቸው ማማር ነው፡፡ ያም ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ጨዋታን እንድትጫወት ሁኔታዎችን ያመቻቹላት ነበር፡፡ በጉዞ ላይ እያሉ ሁለት ጊዜ በሩጫ ተሽቀዳድመዋል፡፡ አንድ ጊዜም ሁለቱም ከቤታቸው (ለጉዞ) ሲወጡ ሰላማዊ ትግል ገጥመዋል፡፡
- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለጉዞ ሲወጡም ሆነ ከጉዞ ሲመለሱ በሌሊቱ ክ/ጊዜ ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው አያውቁም፡፡ ከዚህ ዓይነቱ (ልማድም) ይከለከሉ ነበር፡፡

እንቅልፍንና ትኩረትን የሚመለከት መመሪያቸው

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለእንቅልፍ ወደ መኝታቸው በተጠጉ ጊዜ «ቢስሚከ አል-ሏሁም-መ አሕያ ወአሙት» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «አላህ ሆይ! እኔ የምኖረውና የምሞተውም ባንተ ስም ነው» ማለት ነው፡፡
- በሐዲሥ እንደተዘገበው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በየሌሊቱ ወደመኝታቸው በተጠጉ ቁጥር ሁለቱን መዳፎቻቸውን ያገናኙና (ከዚያም ውስጣቸውን ያጎደጎዱ)፣ ከዚያም በውስጣቸው እትፍ እትፍ ይሉና በውስጣቸውም ሱረቱል ኢኽላስን፣ ሱረቱል ፈለቅንና ሱረቱን ናስን ይቀሩበት ነበር፡፡ (ከዚያም) በሁለቱ መዳፎቻቸው አማካኝነት ከራሳቸው፣ ከፊታቸውና ከፊት ለፊት የሰውነት ክፍሎቻቸው በመጀመር ከሰውነታቸው ክፍል የቻሉትን ሁሉ ያብሱበት ነበር፡፡ ይህንኑ (ተግባርም) ሦስት ጊዜ ይደጋግሙት ነበር፡፡
- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለእንቅልፋቸው ብለው መኝታቸው ላይ መጋደም በሚፈልጉበት ጊዜ ቀኝ እጃቸውን በጉንጫቸው ሥር ያደርጉና ከዚያም ሦስት ጊዜ «አል-ሏሁም-መ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተብዐሡ ዒባደከ» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «አላህ ሆይ! ባሮችህን ከሞት በምትቀሰቅስበት ዕለት ከቅጣትህ ጠብቀኝ» ማለት ነው፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜ «አል-ሐምዱ ሊሏሂል-ለዚ አሕያና በዕደ ማ አማተና ወኢለይሂን-ኑሹር» ይሉ ነበር፡፡ ትርጉሙም «ለዚያ ከሞትን በኋላ ሕይወትን ለለገሰን አላህ ምስጋና ሁሉ ይገባው፤ መሰብሰቢያችንም ወደርሱ ነው» ማለት ነው፡፡ ከዚያም ሚስማክ በመጠቀም ጥርሳቸውን ይፍቁ/ይቦርሹ ነበር፡፡
- የሌሊቱን የመጀመሪያ ክፍል ይተኙና በመጨረሻው ክፍል ደግሞ በሶላት ይቆሙ ነበር፡፡ (ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ) የሙስሊሞችን ጉዳዮች ለማሰማመር ሲሉ የሌሊታቸው የመጀመሪያው ክፍል ወደመገባደድ ይቃረብ ነበር፡፡ (በሌላ አነጋገር ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ የተከታዮቻቸውን ጉዳዮች ለመከታተል ያመሹ ነበር)
- ዓይኖቻቸው ይተኙ ነበር፤ ይሁንና ልባቸው ንቁ እንደሆነ ያነጋ ነበር፡፡

መዓመላን የሚመለከት መመሪያቸው

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች ጋር ይቃለዱና በቀልዳቸውም ውስጥ እውነትን ብቻ ይናገሩ ነበር።
- የቃላት ጨዋታንም ይጫወቱ ነበር፤ ነገር ግን በቃላት ጨዋታቸው ውስጥ ከእውነት ውጭ ሌላ አይናገሩም ነበር።
- (ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ መንገድንም ሆነ መፍትሔን) ራሳቸው ያመላክቱና አመላካችንም ይጠይቁ ነበር (ምክርንም ይሰጡ፤ ምክርንም ይጠይቁ ነበር)
- የታመመን ሰው ይጠይቁ፣ ጀናዛን ለመቅበር ይገኙ፣ ግብዣን ይቀበሉ፣ ጉዳዮቻቸውን ለመፈጸም ሲሉ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ሴቶች፣ ከምስኪኖችና ከአቅመ ደካሞች ጋር ይራመዱ ነበር።
- እርሳቸውን የሚያወድስ ግጥምን ሰምተዋል። ለገጣሚውም ምንዳን ከፍለዋል (ሽልማትን ሰጥተውታል፤ ምንም እንኳን ከርሳቸው የላቁ መልካም ምግባራት ጋር ሲነፃፀር ግጥሙ አጭር የነበረ ቢሆንም)። ማንኛውም እርሳቸው የሚወደሱበት (ትክክለኛ ነገር) ከርሳቸው ተወዳሽነት አኳያ ሲታይ አነስተኛ የሆነ ክፍሉ ነው። ከርሳቸው ውጭ ላሉ ሰዎች የሚደረግ ውዳሴ ግን አብዛኛው ክፍሉ ውሸት ነው።
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጫማቸውን በእጃቸው ጠግነዋል። ልብሳቸውንም በእጃቸው ሰፍተዋል። እንደዚሁም ባልዲያቸውን በእጃቸው ሰፍተዋል። ፍየላቸውን በእጃቸው አልበዋል። ልብሳቸውን አጣጥፈው አስቀምጠዋል። ቤተሰቦቻቸውንና ራሳቸውን አስተናግደዋል። በመስጊድ ግንባታ ላይ ከባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው የጭቃ ብሎኬቶችንም ተሸክመዋል።
- አንዳንድ ጊዜ ከረሃብ የተነሳ ድንጋይን ሆዳቸው ላይ አስረዋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጠግበው በልተዋል።
- እንግዶቻቸውን አስተናግደዋል፤ በእንግድነትም ተስተናግደዋል።
- በጭንቅላታቸው መሃል ላይ፣ ከእግራቸው ኋላ ላይ፣ አል-አኽደዐይን (በሁለቱም በኩል ከአንገት ኋላ ላይ የሚገኙ ሁለቱ የደም መልስ ቧንቧዎች) እና አል-ካሂል (በሁለቱ ትከሻዎች መካከል የሚገኝ ቦታና ወደ ጀርባም መግቢያ ነው) ላይ ታግመዋል (ሒጃማ ተደርገዋል)።
- በመድኃኒት ታክመዋል። ሰዎችን ቢጋለ ብረት ተኩሰዋል። ግና እርሳቸው አልተተኮሱም። ሩቅያም አድርገዋል። ነገር ግን ለራሳቸው እንዲደረግላቸው ከሌሎች ጠይቀው አያውቁም። የታመመን ሰው (በአጠገቡ) የሚያስቸግር ነገር ከመፈጸም ከልክለዋል።
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሙዓመላ ረገድ ከሰዎች ሁሉ ምርጡ ናቸው። አንዳች ነገርን በተዋሱ ወይም በተበደሩ ጊዜም፣ ከተበደሩት ነገር በላይ አብዝተው ይመልሱ ነበር።

የአረማመዳቸው ሁኔታ

- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) የእግር መንገድ ሲሄዱ አረማመዳቸው ከሁሉም ሰው የፈጠነ ሲሆን ነገር ግን እርምጃቸው ከሁሉ ያማረና የተረጋጋ ነበር።
- በአረማመዳቸው ከባልደረቦቻቸው የበለጠ ፈጣን ነበሩ። ስለሆነም እርሳቸው ላይ መድረስ በኃይለኛው ያታግላቸው ነበር።
- አንዳንድ ጊዜ ባዶ እግራቸውን አልያም በሸበጥ (ነጠላ) ጫማ አድርገው ይሄዱ ነበር።
- ባልደረቦቻቸው ብዙውን ጊዜ ከርሳቸው ፊት ለፊት ይሄዱ ነበር። እርሳቸውም ከነርሱ ኋላ ይሆኑ ነበር።
- በተናጠል ወይም በቡድን ሆነው ከባልደረቦቻቸው ጋር ይሄዱ ነበር።

አላህን የማውሳት ሁኔታቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኃያሉ አላህን በማውሳት (እና በማስታወስ) ረገድ ከሰዎች ሁሉ እጅግ የተሟሉት ናቸው። ይልቁንስ ንግግራቸው ሁሉ በአላህ ትውስታ ውስጥ (የተገደበ) እና ለርሱም የተደረገ ነው። ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜ አላህን ያውሱ ነበር። ሶላታቸውን በሚከፍቱበት ጊዜ፣ ከቤታቸው በሚወጡበት ጊዜም፣ መስጊድ በሚገቡበት ጊዜም፣ በጠዋትና በማታ ክ/ጊዜም፣ ልብሶቻቸውን በሚለብሱበት ጊዜም፣ ወደማረፊያ በሚገበቡት ወይም በሚወጡበት ጊዜም፣ መፀዳጃ ቤት በሚገቡበት ጊዜም፣ ዉዱእ ከማድረጋቸው በፊትና ካደረጉ በኋላም፣ የሶላት ጥሪን (አዛንን) በሚሰሙበት ጊዜም፣ አዲስ ጨረቃን በሚመለከቱበት ጊዜም፣ ከመመገባቸው በፊትና ከተመገቡ በኋላም፣ በሚያስነጥሳቸው ጊዜም፣ ... ወዘተ አላህን ያወሱ ነበር።

የተፈጥሮ ሁነኖችንና እነርሱንም ወከተልን የሚመለከት መመሪያቸው	የአካል ገጽታ
	ከቁመጃጀመር መጀመር
	ፀጉር
	ሲዋክ
	ሽቶ
	ቁመና ቁመቀመ ቁመጠ
	የጊዜ ገደብ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «አስር (ተግባራት) ከፊጥራ ተርታ የሚመደቡ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስን) ማሳጠር፣ ፂምን ማሳደግ፣ ሲዋክን (የጥርስ መፋቂያን) መጠቀም፣ አፍንጫን በውሃ ማፅዳት (አል-ኢስቲንሻቅ)፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ የጣት መገጣጠሚያዎችን መታጠብ፣ የብብት አካባቢ ፀጉርን መንጨት፣ የብልት አካባቢ ፀጉርን መላጨት፣ (ከሰገራ ወይም ከሽንት በኋላ) የግል አካላትን በውሃ ማፅዳት ናቸው፡፡ የሐዲሡ አስተላላፊ አስረኛውን ረስቶታል፡፡ (ለፈጣን መረጃ ሲባል 10ኛው ነጥብ ግርዛት ነው፡፡)»

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቀኝ የመጀመር ልማዳቸው የሚያስደንቅ ነው፡፡ ጫማቸውን በሚያደርጉበት፣ በሚራመዱበት፣ ንጽሕናቸውን በሚያሟሉበት፣ አንዳች ነገርን በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር፡፡ ቀኝ እጃቸውን ለመመገብ፣ ለመጠጣትና ለጠሃራ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ግራ እጃቸውን ደግሞ ለመፀዳዳትና ሌሎችንም ተመሳሳይ የሆኑ ቆሻሻ ነገሮችን ለማስወገጃነት ይጠቀሙበት ነበር፡፡

የራስ ፀጉርን በተመለከተ የነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) መመሪያቸው ወይ እንዳለ መተው አልያም እንዳለ መላጨት ነበር፡፡

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሲዋክ መጠቀምን ይወዱ ነበር፡፡ በሚፆሙበትና በማይፆሙበት ጊዜም ሲዋክን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ከእንቅልፋቸው በሚነሱበት ጊዜም፣ ዉዱእን በሚያደርጉበት ጊዜም፣ ከሶላት በፊትም (ወደ ሶላት ሊገቡ በቆሙበት ጊዜ) እና ወደ ቤት በሚገቡበት ጊዜም ሲዋክን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ጥርሳቸውን ሲፍቁ የነበረው ዑዲል አራክ ከሚባል የዛፍ ዓይነት በሚገኘው መፋቂያ ነበር፡፡

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) ሽቶ መጠቀምን ያበዙ ነበር፡፡ እንደዚሁም ሽቶን ይወዱ ነበር፡፡

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፡- «ኢጋሪያን (ከሚያደርጉት) ተቃራኒ ሁኑ፡፡ ስለሆነም ፂምንም አሳድጉ፤ የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስንም) በአጭሩ ቁረጡ፡፡»

አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «የከንፈር ፂምን (ቀድሞ ቀመስን) ማሳጠር፣ ጥፍርን መቁረጥና (የብልት አካባቢ ፀጉርን መላጨትን) በተመለከተ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጊዜ ገደብ አስቀምጦልናል፡፡ ይህም ከአርባ ቀናትና ሌሊቶች በላይ (ባሉበት) እንዳንተዋቸው ነው፡፡»

ጉባኤያቸው

- እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «ልክ እናንተ አሁን እንደምታደርጉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፍጥነት በተሞላበት አኳኋን አይናገሩም ነበር፤ ይልቁንስ እነዚያ በዙሪያቸው የተቀመጡ ሰዎች በቃላቸው መሸምደድ በሚያችሉላቸው መልኩ በተብራራና አለያይ በሆነ ንግግር ይናገሩ ነበር፡፡»
- ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) አብዛኛውን ጊዜ ንግግራቸውን ሦስቴ የሚደጋግሙበት ምክንያት ሰዎች በቀላሉ እንዲረዱላቸው ነበር፡፡ ሰላምታን በሚያቀርቡበት ጊዜም ሦስት ጊዜ ደጋግመው ያቀርቡ ነበር፡፡
- አስፈላጊ ባልሆነበት ጊዜ አይናገሩም ነበር፡፡ ሆኖም ግን በተናገሩ ጊዜ እጥር ምጥን አድርገው በጠቅላይ ቃላት ይናገሩ ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለማይመለከታቸው ጉዳይ ፊፅሞ ተናግረው አያውቁም፡፡ እንደዚሁም ምንዳ ማግኘትን በሚከጅሉበት ጉዳይ ዙሪያ ቢሆን እንጂ አይናገሩም ነበር፡፡
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለጌም ሆነው አያውቁም፡፡ የብልግና ቃላትንም ተናግረው አያውቁም፡፡ ጮኽ ብለውም ተናግረው አያውቁም፡፡

የንግራቸው፣ የሳቃቸው፣ የለቀሷቸውና የኹጥባቸው ሁኔታ	ሳቃቸው	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሳቃቸው ሁሉ የፈገግታ ነበር። እርሳቸው ሲበዛ የሳቁበት ሁኔታ ቢኖር የመንጋጋ ጥርሶቻቸው መታየት የቻሉበት (ኢጋጣሚ) ላይ ነበር።
	ለቅሷቸው	▪ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁከትን በሚፈጥር ሁኔታ ከፍ ባለ ድምጽ አልቅሰው አያውቁም። ነገር ግን በኃይለኛው ያነቡና ከደረታቸውም የመነሰቅሰቅ ድምጽ ይሰማ ነበር። ▪ አንዳንድ ጊዜ የለቅሷቸው ምክንያት ለሟች ካላቸው እዝነት የተነሳ ነበር። አንዳንድ ጊዜም የለቅሷቸው ምክንያት ለተከታዮቻቸው ካላቸው ፍርሃት ወይም የሌላውን ስሜት ከመጋራት ነበር። አንዳንድ ጊዜ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ የለቅሱ ነበር። አንዳንድ ጊዜም ቁርአንን ሰ ሰሙ የለቅሱ ነበር።
	ኹጥባቸው	▪ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሬት ላይ ቁመውም፣ ሚንበር ላይ ወጥተውም፣ በወንድ ግመል ላይ ሆነው እየተጓዝዙም፣ በሴት ግመል ላይ ሆነው እየተጓዝዙም ኹጥባ አድርገዋል (ምክርን ለግሰዋል)። ▪ ጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፦ «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባ በሚያደርጉበት (ሕዝቡን በሚመክሩበት ጊዜ) ዓይኖቻቸው ይቀሉ፣ ድምፃቸው ይጎላ፣ ቁጣቸውም ይበረታ ነበር፤ (ይህም) ልክ እንደዚያ የጦር ሠራዊት አስጠንቃቂ እስከሚመስሉ ድረስ ነበር።» ▪ ኃያሉ አላህን በማመስገን (በማወደስ) የከፈቱት ቢሆን እንጂ አንድም ኹጥባ አድርገው አያውቁም። ▪ የተመካሪዎችን ጉዳይ በሚፈጽምና ለእምርታቸው (አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጉዳይ ዙሪያ) በማንኛውም ወቅት ኹጥባን ያደርጉ ነበር።

ሁለተኛው ፈተና

ውሸት	እውነት	ጥያቄዎች
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልብሳቸውን ሲለብሱ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር፡፡
□	£	አብዛኛውን ምግባቸው የሚመገቡት መሬት ላይ በሱፍራ ተደርጎ ነበር፡፡
□	£	ነብዩ (ሰ.ወ) ለጉዞ ሲወጡም ሆነ ሲገቡ በሌሊት ወደ ቤተሰቦቻቸው አይገቡም ነበር፤ ይህንኑ ማድረግንም ይከለክሉ ነበር፡፡
□	£	ከረሃብ መጥናት የተነሳ ሆዳቸው ላይ ድንጋይን አስረዋል፡፡
□	£	ለሌሎች ሩቃ አድርገዋል፡፡ እንዲደረግላቸው ግን አልጠየቁም፡፡
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወስዋስ ሰዎች የተፈተኑባቸውን ተግባራት ፈፅሞ አልተገበሩም፡፡ ከወስዋስ ሰዎች ቢድዓም (ከየት-መጤ ተግባራትም) ከልክለዋል፡፡
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በትክክለኛው የሐነፊያ እምነት የተላኩ ሲሆን፣ እርሱም የሺርክ እና ሐላልንም ሐራም የማድረግ ልማዶች ተቃራኒ ነው፡፡
□	£	ልጆቻቸው ሰባት ሲሆኑ፣ ከነርሱም አራቱ ወንዶችና ሦስቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡
□	£	ሁሉም ልጆቻቸው ከኸዲጃ (ረ.ዐ) የተወለዱ ሲሆኑ ሌሎች ግን ምንም አልወለዱም፡፡
□	£	ሁሉም ልጆቻቸው የሞቱት ከርሳቸው በፊት ነበር፡፡
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘጠኝ ሚስቶቻቸውን ትተው እንደሞቱ በዑለሞች መካከል ምንም አለመግባባት የለም፡፡ እነርሱም፡- ዓኢሻ፣ ሐፍሳ፣ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ፣ ኡም-ሙ ሰለማ፣ ሰፊይ-ያ፣ ኡም-ሙ ሐቢባ፣ መይሙና፣ ሰውዳና ጁወይሪያ (ረ.ዐ) ናቸው፡፡
□	£	ኃያሉ አላህ በጂብሪል በኩል ለኸዲጃ (ረ.ዐ) ሰላምታን ልኮላታል፡፡ ይህም ለርሷ ለየት ባለ ሁኔታ የተሰጠ ትሩፋት ሲሆን ለሌላ ሴት ግን አይታወቅም፡፡

1. የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተወዳጁ ቀለም፡- ሀ/ ነጭ ለ/ ጥቁር ሐ/ ከቀለማት የገራላቸውን ሁሉ
2. ልብሳቸው፡- ሀ/ የሱፍ ልብስን አይለብሱም ነበር ለ/ የጥጥና የላይነን ልብሶችን ይለብሱ ነበር ሐ/ ያላቸውን የትኛውንም ዓይነት ልብስ ይለብሱ ነበር መ/ ሀ እና ለ
3. ልብሳቸው፡- ሀ/ ከልብሶች ሁሉ እጅግ ውዱ ነበር ለ/ ከዛሂድነት መገለጫ ልብሶች በላይ ያረጀ ያፈጀ ነበር ሐ/ በሁለቱ መሀከል መካከለኛ የሆነ ነበር

1. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቢስሚሏህ እና አል-ሐምዱ ሊሏህ ሲሉ የነበረው፡- ሀ/ በምግባቸው መጀመሪያ ላይ ለ/ በመጨረሻው ላይ ሐ/ በመጀመሪያም በመጨረሻም ላይ
2. አብዛኛውን ጊዜ ሲሰጡ የነበረው፡- ሀ/ ተቀምጠው ለ/ ቁመው ሐ/ ሁለቱም
3. «ከዚህች ዓለማችሁ እኔ ዘንድ ..... ተወዳጅ ተደርገዋል» ብለዋል፡- ሀ/ ሴቶች ለ/ ሽቶ ሐ/ ሁለቱም
4. «የዓይኖቼ ማረፊያ ..... ውስጥ ተደርጎልኛል» ብለዋል፡- ሀ/ በጀነት ለ/ በሶላት ሐ/ ሁለቱም
5. ከሚስቶቻቸው ጋር የነበራቸው ታሪክ ጥሩ የነበረው፡- ሀ/ በአኗኗር ለ/ በምግባር ሐ/ ሁለቱም
6. አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዳወሩት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቀድሞ ቀመስ በማሳጠር፣ ጥፍርን በመቁረጥ (የብልት አካባቢ ፀጉርን በመላጨት) ረገድ ከ ..... በላይ እንዳንተዋቸው የጊዜ ገደብን አስቀምጦልናል፡፡ ሀ/ 30 ቀናት ለ/ 40 ቀናት ሐ/ 50 ቀናት
7. የራስ ፀጉርን በተመለከተ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ፡- ሀ/ ከፊሉን ይላጩና ከፊሉንም ይተውት ነበር ለ/ እንዳለ ይተውት አልያም እንዳለ ይላጩት ነበር
8. ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲዋክን ይወዱና በ ..... ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ሀ/ በሚያሙበት ጊዜ ለ/ በማይያሙበት ጊዜ ሐ/ ሁለቱም
9. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሳቃቸው፡- ሀ/ ሁሉም ፈገግታ ነበር ለ/ አብዛኛው ፈገግታ ነበር
10. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላኩት፡- ሀ/ ወደ መላው የሰው ዘር ለ/ ወደ ጋኔኖችና የሰው ልጆች
11. የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምርጧ ሴት ልጅ፡- ሀ/ ሁላቸውም ለ/ ፋጢማ ሐ/ ዘይነብ
12. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በ ..... ታፋ ላይ ተጋድመው ተቀምጠው እንጂ በሌላዋ ላይ (በዚህ ሁኔታ) መለኮታዊ ራዕይ ወርዶባቸው አያውቅም ነበር፡፡ ሀ/ በዓኢሻ ለ/ ሐፍሳ ሐ/ ኡም-ሙ ሰለማ

የታመመን	ከጋላሞታዎች፣ ድሆችና ደካሞች	ግብዣን	ቀብር ላይ	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)፡-
£	£	£	☐	ይጠይቁ ነበር
£	£	£	☐	ይገኙ ነበር
£	£	£	☐	ይቀበሉ ነበር
£	£	£	☐	ጋር አብረው ይራመዱ ነበር

ቤተሰባቸውን ራሳቸውን	ጫማቸውን በእጆቻቸው	ልብሳቸውን በእጆቻቸው	መስጊድ ለመስራት ብሎኬቶችን	ፍየላቸውን	ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባራት መካከል፡-
£	£	£	£	☐	ይጠግኑ ነበር
£	£	£	£	☐	ይሰፉ ነበር
£	£	£	£	☐	ያልቡ ነበር
£	£	£	£	☐	ያስተናግዱ ነበር
£	£	£	£	☐	ይሸከሙ ነበር

ቀድሞ ቀመስ	ፒም	የብልት ፀጉር	የብብት	ጥፍር	ከሱነን ተግባራት መካከል፡-
£	£	£	£	£	መከርከም
£	£	£	£	£	ማስረዘም
£	£	£	£	£	መቁረጥ
£	£	£	£	£	መንጨት
£	£	£	£	£	መላጨት

ያለውን ምግብ	ሐራም ሳያደርጉ ይተውት ነበር	የተመገቡት ቢሆን እንጂ	በሌለ ምግብ	የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአመጋገብ ሁኔታ፡-
£	£	£	□	እምቢኝ ብለው አይመልሱም ነበር
£	£	£	□	ጫና አይፈጥሩም ነበር
£	£	£	□	ከንጹሕ ነገሮች የቀረበላቸውን
£	£	£	□	ውስጣቸው ያልፈለገው ሲሆን

ሦስት	በአምስት ጣቶች	በአንድ ጣቱ	ምግብ	በጨረሱ ጊዜ	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)
£	£	£	£	£	የሚመገቡበት ጣቶች ብዛት
£	£	£	£	£	ጣቶቻቸውን ይልሷቸው ነበር
£	£	£	£	£	በላይ ይበልጥ የተከበሩ ናቸው
£	£	£	£	£	ኩራተኛ ሰው የሚመገበው
£	£	£	£	£	ሆዳም ሰው የሚመገበው

ልዩ መገለጫዎቻቸው

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልዩ መገለጫዎች መካከል

በቁጥርና ንጹሕ ሃይማኖት ተልከዋል

ኢማም ኢብኑል ቀይም (ረሂመሁሏህ) እንዲህ ብለዋል፦ «የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተልዕኮ ቀጥተኛና ንጹሕ (ሃይማኖትን) አንድ ላይ ያሰባሰበ ሲሆን፣ እርሱም በተውሒድ ረገድ ቀጥተኛ ነው። በአኽላቅ ረገድ ደግሞ ንጹሕ ነው። የሁለቱ ጉዳዮች ተቃራኒያቸው ደግሞ ሺርክ (በአላህ ማጋራት) እና ሐላል የሆነን ነገር ሐራም ማድረግ ናቸው።»

ወደጋኔንና የሰው ዘር ሁሉ ተልከዋል

ነብዩ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰል-ለም) እንዲህ ብለዋል፦ «(ከኔ በፊት ያለፈ) ነብይ ሁሉ ወደራሱ ሕዝቦች (ወገኖች) ብቻ ይላክ ነበር። ነገር ግን እኔ የተላኩት ወደ መላው የሰው ዘር ነው።»

የተሰጠቸው መጽሐፍና ጥሪያቸው

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«ሐ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርአን) በጊታቸው ፈቃድ ሰዎችን ከጨለማዎች ወደ ብርሃን፣ አሸናፊ ምስጉን ወደሆነው ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው።» (ሱረቱ ኢብራሂም 14፡1)*

የተሰጧቸው ተአምራት

ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተሰጧቸው ተአምራት መካከል እጅግ የላቀው ክቡር ቁርኣኑ ነው። እንደዚሁም ለርሳቸው ከዚያ ላይ ድርሻ ቢኖራቸው እንጂ ከርሳቸው በፊት ያለፈ ነብይም ሆነ መልዕክተኛ ከተአምር አንድንም አልተሰጠም።

ጠይአቸውን የሚመለከት ድንጋጌ

ታላቅ የክህደት ወንጀልን የፈጸመ ከሀዲ ይሆናል። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«ጠይሀ (የሚጠላህ) እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው።» (ሱረቱ አል-ከውሠር 108፡3)*

አርሳቸውን መውደድ የኢማን አካል መሆኑ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «እኔ እርሱ ዘንድ ከልጁ፣ ከአባቱና ከመላው የሰው ዘር ሁሉ ይበልጥ ተወዳጅ እስከምሆን ድረስ ከናንተ መካከል አንዳችሁም አላመነም።»

የአላህ ወዳጅ መሆናቸው

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «በእውነቱ አላህ እኔን ወዳጁ አድርጎ ይዞኛል፤ ልክ እርሱ ኢብራሂምን ወዳጁ አድርጎ እንደያዘው ሁሉ።»

የቅርጥት ከሆኑ ነብያት መካከል አንዱ መሆናቸው

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም፣ ከኑሕም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም፣ ከመርየም ልጅ ዒሳም በያዝን ጊዜ (አስታውስ)። ከነርሱም የከበደን ቃል ኪዳን ያዝን።» (አል-አሕዛብ 33፡7)*

ዕውቅታቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «እኔ ከናንተ መካከል አላህን ይበልጥ አዋቂው ነኝ» ብለዋል። አላህ እንዲህ ብለዋል፦ *«ለእናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም። ሩቅንም አላውቅም። ለናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም። ወደእኔ የሚወርድልኝን እንጂ ሌላን አልከተልም ...» በላቸው።» (አል-አንዓም 6፡50)*

ከሌዩ መገለጫዎቻቸው

ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) የታዘዙና ያመጹ ሰዎችን የሚመለከት ድንጋጌ

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«በላቸው፦ ‹አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና፡፡ ኀጢኣቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፡፡› … »* *(ኣሉ ዒምራን 3፡31)*

«እናንተም የበላዮች ስትኾኑ ምእመናን እንደኾናችሁ ኣትሰነፉ፤ ኣትዘኑም፡፡» *(ኣሉ ዒምራን 3፡139)*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «እምቢ ያለኝ ሰው ሲቀር ሁላችሁም ጀነት ትገባላችሁ» አሉ፡፡ እነርሱም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እምቢ ባዩ (የሚያምፀው) ማነው?» አሉ፡፡ እርሳቸውም «እርሱ ያ እኔን ታዘዘ ሰው ጀነት ገባ፡፡እኔን የሚያምጽ ሁሉ ግን እርሱ ያ (ጀነት ለመግባት) እምቢ ያለ ነው» አሉ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዚህም ብለዋል፦ «የኔን ትዕዛዝ በሚቃረን ሰው ላይ ውርደትና አናሳነት ተደርጎበታል፡፡»

ተከታዮቻቸው

ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ፤ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ፤ በአላህም (ኣንድነት) ታምናላችሁ፡፡ … »* *(ኣሉ ዒምራን 3፡110)*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «በዚያ ነፍሴ በእጁ በሆነችው (ጌታዬ) እምላለሁ! እናንተ የጀነት ነዋሪዎችን ግማሹን እንደምትሆኑ ተስፋ አድርጋለሁ፡፡»

ከተማቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የትውልድ ሀገራቸው መካ ነው፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«ለሰዎች (መጸለያ) መጀመሪያ የተኖረው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመሪያ ሲኾን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ነው፡፡ በውስጡ ግልጽ የኾኑ ተዓምራት የኢብራሂምም መቆሚያ ኣልለ፡፡ ወደ ውስጡ የገባ ሰው ጸጥተኛ ይኾናል፡፡ ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ ኣለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡»* *(ኣሉ ዒምራን 3፡96-97)*

ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት መካ ቅድስት ቦታ ናት፡፡ እንዲህም ብለዋል፦ «በእውነቱ አላህ ሰማያትንና ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ይህቺን ከተማ የተቀደሰች አድርጓታል፡፡ ስለሆነም እርሷ በአላህ ውሳኔ መሠረት (እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ) ቅድስት ናት፡፡» ከዚህም በተጨማሪ ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት እስከ ዕለተ ትንሳኤው ድረስ መካ የሙስሊሞች ናት፡፡ እንዲህም ብለዋል፦ «ከመካ መከፈት በኋላ ስደት የለም፡፡»

ቂብላቸው

የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የሶላት አቅጣጫቸው (ቂብላቸው) ከዕባ ነው፡፡ ይሁንና መጀመሪያ ላይ ወደቢይተል መቅዲስ ነበር፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፦ *«የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን፡፡ ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን፡፡ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር፡፡ የትም ሰፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ፡፡ … »* *(ኣል-በቀራ 2፡144)*

እንደዚሁም መካ ውስጥ የሚገኘው መስጂድ አል-ሐራም በምድር ላይ የተኖረው የመጀመሪያው መስጂድ ነው፡፡ አቡ ዘር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፦ «እኔ የአላህ መልዕክተኛን በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተኖረው መስጂድ ጠየቅኳቸው፡፡ እርሳቸውም ‹መስጂድ አል-ሐራም ነው› አሉኝ፡፡»

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «እርሱ ያ (የሐጅ ሥነ-ሥርዓትን በመፈጸም ሐሳብ) ወደዚህ ቤት (መስጂድ) የመጣ ሰው፣ ፀያፍ ነገርን ያልተናገረና የአመፅ ተግባርንም ያልፈጸመ ሰው፣ ልክ እናቱ እንደወለደችው ዕለት (ከኃጢአቱ ነፃ ሆኖ) ይመለሳል፡፡»

ከልዩ መገለጫዎቻቸው	ቁብላችው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህም ብለዋል፡- «በመስጂድ አል-ሐራም ውስጥ የሚሰገድ (አንድ) ሶላት ከአንድ መቶ ሺ ሶላቶች ጋር እኩል ሲሆን በኔ መስጂድ ውስጥ የሚሰገድ አንድ ሶላት ደግሞ ከአንድ ሺ ሶላቶች ጋር እኩል ነው፤ በበይተል መቅዲስ የሚሰገደው አንድ ሶላት ደግሞ ከአምስት መቶ ሶላቶች ጋር እኩል ነው።»

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህም ብለዋል፡- «ወደሦስት መስጂዶች ካልሆነ በስተቀር ወደማንኛውም ቦታ (ሃይማኖታዊ) ጉዞ አይደረግም። እነዚህም መስጂዲል ሐራም (መካ)፣ የኔ መስጂድ (መስጂድ አን-ነበዊ - መዲና) እና መስጂድ አል-አቅሷ (ኢየሩሳሌም) ናቸው።»

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዚህም ብለዋል፡- «ለመፀዳዳት በምትሄዱበት ጊዜ፣ በፊታችሁ ወደቂብላ አትዙሩ፤ ጀርባችሁንም ወደርሱ አታዙሩ። ይልቁንስ ወይ ወደ ምሥራቅ አልያም ወደ ምዕራብ ዙሩ።»

ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው

ሰባቱ ልጆቻቸው - 3 ወንዶች እና 4 ሴቶች

[1] አል-ቃሲም - ይህ የርሳቸው ቅፅል ስም ጭምር ነው።።

[2] ዘይነብ (ረ.ዐ)

[3] ሩቀይ-ያ (ረ.ዐ)

[4] ኡም-ሙ ኩልሡም (ረ.ዐ)

[5] ፋጡማ (ረ.ዐ)

[6] ዐብዱሏህ - ሌላ ስሙ አጥ-ጠይ-ዩብ እና አጥ-ጣሂር ነው

[7] ኢብራሂም፣ እርሱ የማሪያቱ አል-ቂብጢይ-ያ ልጅ ሲሆን እርሷ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድብቅ ሚስት ነበረች።። ከኢብራሂም በስተቀር የተቀሩት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች ሁሉ ከኹዲጃ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) የተወለዱ ናቸው።። ከርሷ ውጭ ሌሎች ሚስቶቻቸው ለርሳቸው ምንም ልጅ አልወለዱላቸውም።።

ልጃቸው ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ስትቀር ሁሉም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች ከርሳቸው በፊት የሞቱ ናቸው።። እርሷም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕልፈት በኋላ ስድስት ወራት ቆየች።። በትዕግስቷና ከአላህ ዘንድ (ምንዳን አገኛለሁ) ብላ በመተሳሰቧ ሳቢያ ኃያሉ አላህ በዓለማት ሴቶች ላይ ብልጫን በምታገኝባቸው ደረጃዎች ከፍ አደረጋት።። በደፈናው ሲታይ ከሴት ልጆቻቸው ሁሉ በላጭዋ ፋጢማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ናት።። ሁሉም ሴት ልጆቻቸውም የእስልምና ፀጋ ላይ ደርሰዋል።። እስልምናንም ተቀብለዋል።። ከርሳቸውም ጋር ወደ መዲና ተሰደዋል።።

በአባታቸው በኩል ያሉ ዘጠኙ አጎቶቻቸው

1. ሀምዛ (ረ.ዐ) - የሰማዕታት አለቃ

2. አል-ዐብ-ባስ (ረ.ዐ)

3. ዐቡ ጧሊብ፣ ዐብዱ መናፍ

4. አቡ ለሀብ፣ ዐብዱል ዑዝ-ዛ

5. ዙበይር

6. ዐብዱል ከዕባ

7. አል-ሙቀዊም

8. ዲራር

9. ቁሠም

10. አል-ሙጊራ - ሌላ ስማቸው ሐጀል

11. አል-ገይዳቅ፣ ስማቸው ሙስዐብ ነው

በአባታቸው በኩል ከሚዛመዷቸው አጎቶቻቸው መካከል ሀምዛ እና አል-ዐብ-ባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) ሲቀሩ የተቀሩት አንዳቸውም እስልምናን አልተቀበሉም።።

በአቡታቹው በኩል ያሉ 6ቱ አከሰቆቻቹው				
2. ኡሙ ሐኪሚን አል-በይዳእ	1. ሰፍ-ፊያ - የአዝ-ዙበይር ኡብን ዐው-ዋም (ረ.ዐ) እናት			
6. ኡመይማ	5. ኡርዋ	4.በር-ራ	3. ዓቲካ	

ዐ ቃፍ ፀ የሚስቶቻቹው ስሞች- የመጀመሪያ ፊደል በማናኘት		
ج ز	አል-ሓኡ፡- ሐፍሳ ቢንት ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አል-ጀም፡- ጁወይሪይ-ያ ቢንት አል-ሓሪሥ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አዝ-ዛይ፡- ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ እና ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ)	
ص ظ	አስ-ሷድ፡- ሰፊይ-ያ ቢንት ሑየይ-ዱ ኢብን አኽጠብ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አል-ካኡ፡- ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አር-ራኡ፡- ኡም-ሙ ሐቢባ ረምላ ቢንት አቢ ሱፍያን (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
ع ء ه	አስ-ሲን፡- ሰውዳ ቢንት ዘምዓ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አል-ሚም፡- መይሙና ቢንት አል-ሓሪሥ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አል-ዐይን፡- ዓኢሻ ቢንት አቢ በክር (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	
	አል-ሃ፡- ኡም-ሙ ሰለማ ሂንድ ቢንት አቢ ኡመይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)	

ኸዲጃ (ረ.ዐ)	ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል የመጀመሪያዋ ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ አል-ቁረሺይ-ያ አል-አሰዲይ-ያ (ረ.ዐ) ስትሆን እርሷንም ያገቧት በነብይነት ከመላካቸው በፊት ነበር። ሲጋቡም ዕድሜዋ 40 ዓመት ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷ በሕይወት እስካለች ድረስም ሌላ ሚስትን አላገቡም ነበር። ኢብራሂም ሲቀር ሁሉም ልጆቻቸውም ከኸዲጃ የተወለዱ ናቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የነብይነት ማዕረጋቸውን እንደተቀበሉ ኸዲጃ ከነናቸው ሆና ታበረታታቸውና ከርሳቸውም ጋር ትታገል ነበር። በሕይወቷና በገንዘቧ አማካኝነት ኃይል ትሆናቸው ነበር። ስለሆነም አላህ በመላኢካው ጂብሪል በኩል ለኸዲጃ ሰላምታን ላከላት። ይህም ለርሷ ብቻ የተለየና ከርሷ ውጭ ላሉ ሴቶች ሁሉ ተሰጥቶ የማይታወቅ ትሩፋት ነው። እርሷም ከኢስላማዊ ስደት በፊት በሦስት ዓመታት አስቀድማ ሞተች።
ሰውዳ (ረ.ዐ)	የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከኸዲጃ ሕልፈት አጭር ቆይታ በኋላ ሰውዳ ቢንት ዘምዓ አል-ቁረሺይ-ያን አገቡ። እርሷም (የኋላ ኋላ) ሌሊቶቿን በስጦታ መልክ ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ያበረከተች ናት።

ዓኢሻ (ረ.ዐ)

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዓኢሻ አስ-ሲድ-ዲቃ ቢንት አስ-ሲድ-ዲቅን አገቧት። ዓኢሻ (ረ.ዐ) የቅፅል ስሟ ኡም-ሙ ዐብዱሏህ ነው። ዓኢሻ ያቺ ጎያሉ አላህ ከሰባት ሰማያት በላይ ሆኖ ከተወራባት ቅጥፈት ነፃ ያደረጋት ሚስታቸው ናት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድም ከሁሉም በላይ ይበልጥ ተወዳጅ ናት። ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ከመጋባቷ በፊት ለርሳቸው ከሐር በሆነ ቁራጭ ልብስ ውስጥ ሆና የቀረበችላቸው በመላኢካ አማካኝነት በሕልማቸው ውስጥ ነበር። መላኢካውም «ይህቺ ሚስትህ ናት» አላቸው። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዓኢሻን በሸው-ዋል ወር ውስጥ፣ እርሷ የስድስት ዓመት ልጅ ሆና ሳለች ኒካሕ አሰሩላት። ከዚያም ዕድሜዋ 9 ዓመት በሞላ ጊዜ በአንደኛው የሂጅሪያ ዓመት በጋብቻ ጠቅልለው ወሰዷት። መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከርሷ ውጭ ልጃ ገረድ አግብተው አያውቁም። እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በታፋዋ ላይ ተጋድመው ተቀምጠው ሳሉ እንጂ በሌላዋ ላይ ሳሉ መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) አልወረደባቸውም።

ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከፍጡራን መካከል መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅዋ ናት። የርሷ ንጹሕነትም ከሰማያት በላይ የወረደ ሲሆን በርሷ ላይ የውሸት ወሬን የቀጠፈ ግለሰብም ከሀዲ መሆኑን ኡም-ማው በአንድ ድምጽ ተስማምተውበታል። ዓኢሻ (ረ.ዐ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ሁሉ ዲኑን ይበልጥ የተገነዘበችና ከሁላቸውም በላይ ዐዋቂ ናት። በደፊናው ከኡምማው ሴቶች ሁሉ ይበልጥ ፈቂሃ እና ዓሊማ ናት። ታላላቆቹ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሳይቀሩ አስተያየቷን ይሹና ሂይማኖታዊ ብያኔዋንም ይጠይቁ ነበር።

ሐፍሳ (ረ.ዐ)

በማስከተልም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሐፍሳ ቢንት ዑመር ኢብን አል-ኸጧብን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) አገቧት። እርሷ አስቀድማ ከመጀመሪያ ባሏ ከኹነይስ ኢብን ሑዛፋ አስ-ሰህሚይ-ይ ጋር እስልምናን ተቀብላ ነበር። ከርሱም ጋር ወደ መዲና ተሰድዳ ነበር። እርሱም ከኡሑድ ዘመቻ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞተ። ስለሆነም ከዚያ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አገቧት።

ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ (ረ.ዐ)

በማስከተልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ኹዘይማ ኢብን አል-ሓሪሥ አል-ቀይሲይ-ያን፣ ከበኑ ሂላል ኢብን ዓሚር ጎሳ አገቧት። ይሁንና እርሷ መልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ካገባች ከሁለት ወራት በኋላ ሞተች። እርሷ የምስኪኖች እናት የሚል ሌላ ስምም ተሰጥቷት የነበረች ናት።

ኡም-ሙ ሰለማ (ረ.ዐ)

በማስከተልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡም-ሙ ሰለማ ሂንድ ቢንት አቢ ኡመይ-ያ አል-ቁረሺይ-ያ አል-መኽዙሚይ-ያን አገቧት። የአቡ ኡመይ-ያ ስማቸው ሑዘይፋ ኢብን ሙጊራ ነው። ኡም-ሙ ሰለማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል መጨረሻ ላይ የሞተች ናት። የሞተችውም ከሂጅሪያ በኋላ በ62 ዓመት ነበር።

ጁወይሪያ (ረ.ዐ)

በተመሳሳይ መልኩ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጁወይሪይ-ያ ኢብን አል-ሓሪሥ ኢብን አቢ ዲራር አል-ሙስጠሊቂይ-ያን አግብተዋል። እርሷ ከበኒ አል-ሙስጠሊቅ ምርኮኞች መካከል ነበረች። ነፃነቷን ለማግኘት ስትልም የመልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) እገዛ ፍለጋ ወደርሳቸው መጣች። ስለሆነም እርሳቸውም ይህንኑ መለሱላትና አገቧት።

ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ (ረ.ወ)

በማስከተልም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ጀሕሽን ከበኑ አሰድ ኢብን ኹዘይማ ነሳ አገቧት። እርሷም በአባታቸው በኩል የምትዛመዳቸው የአክስታቸው ኡመይማ ልጅ ናት። ቀጣዩ የአላህ ቃልም የወረደው እርሷን አስመልክቶ ነው፡- *«... ዘይድም ከእርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ ኣጋባንህ። ... »* *(አል-አሕዛብ 33፡37)*

በዚህም ሳቢያ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ በተቀሩት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ላይ እንዲህ እያለች ትፎክር ነበር፡- «እናንተን (ለአላህ መልዕክተኛ) የዳሩዋችሁ ቤተሰቦቻችሁ ናቸው። ይሁንና (እኔን ለአላህ መልዕክተኛ) የዳረኝ ከሰባቱ ሰማያት በላይ የሆነው አላህ ነው።»

ከዘይነብ (ረ.ዐ) ልዩ መገለጫዎች መካከል ለርሷ ወሊይ (የጋብቻዋ ተያዥ ወይም ወኪልዋ) ሆኖ ለመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የዳራቸው ከሰማያቱ በላይ የሆነው ልዕለ ኃያሉ አላህ መሆኑ ነው። እርሷም የሞተችው በዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ) የኸሊፋነት ዘመን ጅማሮው ላይ ነበር።

ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ (ረ.ዐ) መጀመሪያ ላይ የተዳረችው ለዘይድ ኢብን ሓሪሣ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ነበር። እርሱንም ያሳደጉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ። ዘይድም (ረ.ዐ) እርሷን በፈታት ጊዜ ኃያሉ አላህ እርሷን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዳራት። (ይህም የሆነበት ምክንያት) የጉዲፈቻ ልጆችን የቀድሞ ሚስቶቻቸውን ማግባት ፍቁድ መሆኑን ለኡምማው ለማሳየት ሲባል ነው።

ኡም-ሙ ሐቢባ (ረ.ወ)

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡም-ሙ ሐቢባን አገቧት። (ሙሉ) ስሟም ረምላ ቢንት አቢ ሱፍያን ሰኽር ኢብን ሐርብ አል-ቁረሺይ-ያ አል-አመዊይ-ያ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ያገቧት እርሷ አቢሲኒያ ውስጥ ስደተኛ ሆና ሳለች ነበር። ንጉሡ ነጃሺም ለርሷ መሕር (ይሆን ዘንድ) አራት መቶ ዲናርን ሰጡ። ከዚያም እርሷ ከዚያ ወደ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ታጅባ ተላከች። የሞተችውም በወንድሟ በሙዓዊያ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) የአገዛዝ ዘመን ነበር።

ሰፊይ-ያ (ረ.ዐ)

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰፊይ-ያ ቢንት የይ-ዩ ኢብን አኽጠብን አገቧት። አኽጠብ የበኑ አን-ነዲር ነሳ አለቃ ሲሆን፣ በኒ አን-ነዲርም የነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ወንድም የሆኑት የሃሩም ኢብን ዒምራን ተወላጆች ናቸው። ስለሆነም ሰፊይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) በአንድ በኩል የነብይ ልጅ ስትሆን በሌላ በኩል ደግሞ የነብይ ሚስትም ናት። ሰፊይ-ያ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ከዓለማት ሴቶች ሁሉ እጅግ ቆንጆዋ ነበረች። ይሁንና ምርኮኛ ሆና ነበር። ከሴት ምርኮኞች መካከል ሆና ወደርሳቸው መጣች። ከባርነትም ነፃ አወጧት። ነፃነቷንም መሕሯ አደረጉላት። ይህም የሱንና ተግባር ሆኖ ተወሰደ።

መይሙና (ረ.ወ)

ከዚያም በማስከተል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መይሙና ቢንት አል-ሓሪሥ አል-ሂላሊይ-ያን አገቧት። እርሷ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች መካከል የመጨረሻዋ ስትሆን እርሳቸውም እርሷን ያገቧት ዑምራን ለማድረህ ወደ መካ ከተመለሱ በኋላ ነበር።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሞቱ ጊዜ ከሚስቶቻቸው መካከል ዘጠኙ በሕይወት እንደነበሩ በዑለሞች መካከል ምንም አለመግባባት የለውም። ከርሳቸው ሕልፈት በኋላም እርሳቸውን ለመከተል የመጀመሪያዋ ሚስታቸው በሂጅሪያ 20 የሞተችው ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ ነበረች። ከሚስቶቻቸው መካከል መጨረሻ ላይ የሞተችው ደግሞ ኡም-ሙ ሰለማ ስትሆን የሞተችውም በ62 ዓመተ ሂጅሪያ በየዚድ ኢብን ሙዓዊያ የኸሊፋነት ዘመን ነበር።



ክፍል 2 - የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ



ከነብይነታቸው በፊት

ውልደታቸው

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተወለዱት በዝሆን ዓመት (ዓሙል ፊል - አብረሃ በዝሆን ሠራዊት አማካኝነት መካን ለማጥቃት በተንቀሳቀሰበት ዓመት)፣ በዕለተ ሰኞ፣ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል፣ ከሂጅራ 55 ዓመታት በፊት ሲሆን በግሪጎሪያን አቆጣጠር መሠረት በ571 ነበር። የዝሆን ሠራዊት ክስተትና አላህ እነርሱን መግታታቸው ኃያሉ አላህ ለራሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለተቀደሰው ቤቱ (ለከዕባ) ያስቀደመው ድል ነበር።

አባታቸው

አባታቸው ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል ሙጧሊብ ናቸው። እርሳቸውም የሞቱት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተፀንሰው ሳሉ ነበር። ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወለዱት የቲም ሆነው ነበር።

እናታቸው

እናታቸው ኣሚና ቢንት ወህብ ስትሆን ከበኑ ዙህራ ጎሳ ናት። እርሷም የሞተችው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰባት ዓመት ሳይሞላቸው በፊት ነበር።

አሳዳጊዎቻቸው

እናታቸው ከሞቱ በኋላ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በኃላፊነት የተቀበሏቸው አያታቸው ዐብዱል ሙጠሊብ ነበሩ። ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 8 ዓመት ሲሞላ አያታቸውም ሞቱ። ከዚያም በአባታቸው በኩል የሚዛመዷቸው አጎታቸው አቡ ጧሊብ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በኃላፊነት ተቀበሏቸው። የአቡ ጧሊብ ስምም ዐብዱ መናፍ ነበር።

የጥቢ እናቶቻቸው

ሡወይባ

አሳዳሪዋ አቡ ለሀብ ሲሆን በልጇ በመስሩሕ ወተትም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር አቡ ሰለማ ዐብዱሏህ ኢብን ዐብዱል አሰድ አል-መኽዙሚይንም አጥብታለች። እንደዚሁም ከሁለቱ ጋር የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጉት የሆኑትን ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብንም አጥብታለች።

ሐሊማ አስ-ሰዕዲይ-ያ

ሐሊማ የኡኒሳና የጁዛማ ወንድም በሆነው በልጇ ዐብዱሏህ ወተት ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አጥብታለች። ኡኒሳ አሽ-ሸይማእ በመባልም ትታወቃለች። እነርሱም የአል-ሓሪሥ ኢብን ዐብዱል ዑዝ-ዛ ኢብን ረፋዓ አስ-ሰዕዲይ ልጆች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ሐሊማ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የአጎታቸው ልጅ የሆነውን አቡ ሱፍያንም አጥብታለች።

አሳዳጊዎቻቸው

ሐሊማ ቢንት አቢ ዙኣይብ አስ-ሰዕዲይ-ያ	የአቡ ለሀብ ባሪያ ሡወይብ	እናታቸው ኣሚና

ሸይማእ

የሐሊማ ሴት ልጅና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የጡት እህታቸው ናት። እርሷም ከሀዋዚን (ከመካ መከፈት በኋላ ከነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ውጊያን ካደረጉ ጎሳዎች መካከል አንዱ ከሆነው) ልዑካን ጋር ወደርሳቸው የመጣች ናት። እርሳቸውም ልብሳቸውን ዘረጉላት። ከርሳቸው ላይ ያላትን ሐቅ-ቋን ለመጠበቅ ሲሉም እዚያ ላይ አስቀመጧት።

አሳዳጊዎቻቸው

ኡም-ሙ አይመን

ኡም-ሙ አይመን ሌላ ስሟ በረካ አል-ሐበሺይ-ያ ናት፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ከአባታቸው ወርሷታል፡፡ እርሷም አሳዳጊ እናታቸው ነበረች፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እርሷን ለወዳጃቸው ለዘይድ ኢብን ሓሪሣ ዳሯት፡፡ ከዚያም ኡሳማ ኢብን ዘይድን ወለደችለት፡፡

ኡም-ሙ አይመን (ረ.ዐ) ያቺ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕልፈት በኋላ (ከዕለታት አንድ ቀን) አቡ በክር እና ዑመር (ረ.ዐ) የነበሟት ናት፡፡ እርሷም አለቀሰች፡፡ እነርሱም «ምንድነው የሚያስለቅስሽ? ለመሆኑ አላህ ዘንድ ያለው ነገር ለመልዕክተኛው በላጭ አይደለምን?» አሏት፡፡ እርሷም «በእውነቱ አላህ ዘንድ ያለው ነገር ለመልዕክተኛው በላጭ መሆኑን በደንብ አውቃለሁ፡፡ በእውነቱ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከነበሩበት መልካም ይልቅ በላጭ ወደሆነው (መልካምነት) ተመልሰዋል፡፡ ይሁንና እኔ የማለቅሰው ከሰማይ የሆነው መለኮታዊ ራዕዩ ወደኛ (ከመውረድ) በመቋረጡ ምክንያት ነው» አለች፡፡ እነርሱም በለቅሶው ተቀላቀሏት፡፡ (ይህም ንግግሯ) እነርሱም ከርሷ ጋር እንዲያለቅሱ አደረጋቸው፡፡

ሥራቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እረኛ ሆነው ፍየሎችን አግደዋል፡፡ ይህም ለትዕግስታቸው፣ ለአቅመ ደካሞች ለሳዩት እዝነትና ስለነርሱም ኃላፊነትን በመሸከም ለከፈሉት (መስዋዕትነት) አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «የፍየል እረኛ የሆነን እንጂ አላህ ሌላ ነብይን አልላከም፡፡ ባልደረቦቻቸውም (ረ.ዐ) «እርስዎም ቢሆኑ?» ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ «አዎን! እኔም በጥቂት ካራቶች ከፍያ ለመካ ሰዎች (ፍየሎችን) አግጃለሁ» አሉ፡፡»

ሥራቸውና ትዳራቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 25 ዓመት በደረሰ ጊዜ፣ ለንግድ ሥራ ብለው ወደሶሪያ መንገድ ወጡ (አመሩ)፡፡ ከቡስራ ጋርም ተገናኙ፡፡ ከዚያም ተመለሱ፡፡ በምልሰታቸው መጨረሻ ላይም የመጀመሪያ ሚስታቸው የሆነችዋን ኹዲጃ ቢንት ኹወይሊድን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) አገቧት፡፡

ከዕቦን የመገንባቱ ሂደት

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 35 ዓመት በደረሰ ጊዜ ከዕባ ፈርሶ ነበር፡፡ ስለሆነም ቁረይሾች መልሰው ለመገንባት ተነሱ፡፡ የተለያዩ የቁረይሽ ጎሳዎችም ከዕባን ተከፋፍለው ለመሥራት ተስማሙ፡፡ እያንዳንዳቸውም በየፊናቸው የተለያዩ ኮርነሮችን ወሰዱ፡፡ ግንባታውም የጥቁሩ ድንጋይ ኮርነር ላይ በደረሰ ጊዜ ወደቦታው ማን ይመልስ በሚለው ጉዳይ ዙሪያ አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ አራት ወይም አምስት ቀናትን ቆዩ፡፡

.... ከዚያም በመስጊዱ በር በኩል በቅድሚያ የሚገባ ሰው በመካከላቸው ዳኝነትን እንዲሰጥ ተስማሙ፡፡ በቅድሚያ የገባ ሰውም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነበሩ፡፡ በመካከላቸውም ፍርድን እንዲሰጥ አደረጉ፡፡ እርሳቸውም ልብስ እንዲመጣ አዘዙ፡፡ ድንጋዩንም በርሱ ላይ አደረጉት፡፡ ከዚያም (ድንጋዩ) እቦታው እስከሚደርስ ድረስ ሁሉም ጎሳዎች (የልብሱን) ጠርዝ ይዘው እንዲሸከሙ አደረጉ፡፡ ከዚያም ራሳቸው በእጃቸው (ጥቁሩን ድንጋይ) ቦታው ላይ አስቀመጡት፡፡

መገለላቸው

እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) እንዲህ ብላለች፡- «መገለል (አል-ኽላእ ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/) ዘንድ ተወዳጅ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ወደ ሒራእ ዋሻ ይገለሉና እዚያም ይቆዩ ነበር፡፡ (እዚያም) ቁጥራቸው ለሚታወቅ ሌሊቶች ያህል (አላህን በብቸኝነት) ያመልኩ ነበር፡፡» እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ታቦታትና የሕዝቦቻቸው ዲንም የተጠላ ተደርገዋል፡፡ እርሳቸው ዘንድም ከነዚህ የበለጠ እጅግ የተጠላ ሌላ ነገር የለም፡፡

የራዕዩ መውረድ ጅማሮ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 40 ዓመት በሞላ ጊዜ የነብይነት ብርሃኑ ከርሳቸው ላይ ደምቆ ነበር። ጋያሉ አላህም በዕለተ ሰኞ መልዕክቱን (በርሳቸው ላይ በማውረድ) አላቃቸው።

ነብይነትን መቀበላቸው

እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) (የነብይነት ማዕረጋቸውን) በቀዳምነት እንዲጀምሩበት የተደረገው ነገር ቢኖር በእንቅልፍ ውስጥ (በሚገለጽ) መለኮታዊ ራዕይ በሆነው ጥሩ ሕልም (አማካኝነት) ነበር። (ስለሆነም) እንደ ንጋት ጎህ መቅደድ አምሳያ (እውነት) ሆኖ ቢመጣ እንጂ ሕልምን አያዩም ነበር። ከዚያም መገለል እርሳቸው ዘንድ ተወዳጅ ተደረገ። እናም ወደ ሒራእ ዋሻ ይገለሉና በርሱም ውስጥ ይቆዩ ነበር። ከዚያም ወደቤተሰባቸው ከመግባታቸውና ለዚህም (ዓላማ ዳግም) ስንቅን ይዘው ከመጓዛቸው በፊት ቁጥራቸው በውል ለሚታወቅ ሌሊቶች ያህል (እዚያው ሒራእ ዋሻ ውስጥ በመሰንበት አላህን በብቸኝነት) ያመልኩ ነበር። ከዚያም በሒራእ ዋሻ ውስጥ እያሉ እውነቱ (ሐቁ) እስኪመጣቸው ድረስ ወደ ኸዲጃ ይመለሱና ለተመሳሳዩ (ዓላማም) ይሰነቁ ነበር። (እውነቱ በመጣ ጊዜም) መላኢካው ወደርሳቸው መጣና ‹ኢቅራእ ወይም አንብብ› አላቸው። እርሳቸውም ‹እኔ ማንበብ አልችልም› አሉት። ከዚያም እንዲህ አሉ፡- ‹(መላኢካው) ያዘኝ፤ ከዚያም ጭንቀቴ ጥግ እስከሚደርስ ድረስ ጨመቀኝና ከዚያም ለቀቀኝ፤ ከዚያም (ዳግም) አንብብ› አለኝ። እኔም ‹(ዳግም) ማንበብ አልችልም› አልኩት። ከዚያም ያዘኝና ጥንቀቴ ጥግ እስከሚደርስ ድረስ ለሁለተኛ ጊዜ ጨመቀኝ። ከዚያም ለቀቀኝ። ከዚያም ‹(ለሦስተኛ ጊዜ) አንብብ› አለኝ። እኔም ‹ማንበብ አልችልም› አልኩት። ከዚያም ያዘኝ፤ ለሦስተኛ ጊዜም ጨመቀኝ። ከዚያም ለቀቀኝ። ከዚያም እንዲህ አለ፡-

«አንብብ! በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። አንብብ! ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ። ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን።» (አል-ዐለቅ 96፡1-5)

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ልባቸው እየተርገፈገፈ እነዚህን የቁርአን አናቅጽ ይዘው ተመለሱ። ወደ ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ ገቡና ‹ሸፍኑኝ! ሸፍኑኝ!› አሉ። ፍርሃቱ እስከሚወገድላቸው ድረስም በልብስ ሸፈኑዋቸው። ለኸዲጃም የተከሰተውን ሁሉ ከነገሯት በኋላ ‹በእውነቱ ለሕይወቴ ፍርቻለሁ› አሏት። ኸዲጃም ‹አይሆንም! በአላህ እምላለሁ! አላህ እርስዎን ፈጽሞ አያዋርድዎትም። በእውነቱ ዝምድናን ትቀጥላህ፤ ረዳት የለሽን ትሸከማለህ፤ ድሃን ትመነዳለህ፤ እንግዳን ታሳርፋለህ፤ ከባድ አደጋ የደረሰባቸውንም ሰዎች በትክክል ታግዛለህ› አለቻቸው። ከዚያም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ወረቃ ኢብን ነውፈል ኢብን አሰድ ኢብን ዐብዱል ዑዝ-ዛ - የኸዲጃ የአጎቷ ልጅ ወደሆነው - ዘንድ ወሰደቻቸው። እርሱም በጃሂሊያው ዘመን ክርስትናን የተቀበለ ሰው ሲሆን፣የእብራይስጥ መጽሐፍንም ይጽፍ ነበር። አላህ እንዲጽፍ የፈቀደለትን ያህልም ኢንጂልን በእብራይስጥ ይጽፍ ነበር። ዕድሜው የገፋ አዛውንት ሲሆን ዓይኑም ታውሯል። ኸዲጃም (ረ.ዐ) ‹የአጎቴ ልጅ ሆይ! እስኪ የወንድምህ ልጅ የሚያወራውን አዳምጥለት› አለችው። ወረቃም ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ‹የወንድሜ ልጅ ሆይ! ምንድነው ያየኸው?› አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) የተመለከቱትን ነገር ነገሩት። ወረቃም ‹ይህ አላህ በሙሳ ላይ ያወረደው መላኢካ ነው፤ ዋ ምኞቴ! ምነው በዚህ ጊዜ ወጣት በሆንኩ? ዋ ምኞቴ! ሕዝቦችህ አንተን ከሀገርህ ሲያስወጡህ ሕያው በሆንኩ?› አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹አነርሱ ከሀገሬ ያስወጡኛል እንዴ?› አሉት። እርሱም ‹አዎን! አንድም ሰው አንተ ይዘህ የመጣኸውን ይዞ አልመጣም፤ ሕዝቦቹ ጠላታቸው አድርገው ቢይዙት እንጂ። ያንተ ጊዜ እኔ ላይ የሚደርስ ቢሆን፣ ከፍተኛ የሆነን እርዳታ እረዳህ ነበር።ከዚያም ወረቃ ብዙም ሳይቆይ ሞተ።ራዕዩም ለተወሰነ ጊዜ ተቋረጠ።

በነብይነት መመረጣቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «እኔ እየሄድኩ ሳለሁ በድንገት ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ። እኔም ወደላይ ቀና ብዬ ተመለከትኩ። በዚህን ጊዜ ያንን በሒራእ የመጣብኝን መላኢካ በሰማይና ምድር መካከል (በሚሰፋ) ወንበር ላይ ተቀምጦ ተመለከትኩ። ከርሱም ፈራሁ። (ወደቤትም) ተመለስኩና ‹ሸፍኑኝ! ሸፍኑኝ!› አልኩ። ኃያሉ አላህም ቀጣዮቹን የቁርኣን አናቅጽ አወረደ፦

‹አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ተነሳ አስጠንቅቅም። ጌታህንም አክብር። ልብስህንም አጥራ። ጣዖትንም ራቅ።› (አል-ሙድ-ደሥ-ሢር 74፡1-5)

ከዚህ በኋላ መለኮታዊ ራዕዩ (ወሕዩ) እያየለና እየተከታተለ መምጣቱን ተያያዘው።»

የመለኮታዊ ራዕዩ ደረጃዎች

1/ እውነተኛ ሕልም

ይህም መለኮታዊ ራዕዩ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መውረድ የጀመረበት ሁኔታ ነው። እመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብላለች፦ ‹እንደ ንጋት ጎህ (ደማቅ ሆኖ በገቢር) የሚመጣን እንጂ ሌላን ሕልም አይመለከቱም ነበር።›

2/ ልባቸው ላይ በቀጥታ መግለጹ

አንዳንድ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መላኢካውን ሳያዩት እርሱ ግን እርሳቸውን በመንፈሳቸውና በቀልባቸው በኩል ያገኛቸው ነበር። እንዲህም ብለዋል፦ «ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) በመንፈሴ ውስጥ ነፋብኝ፤ እንዲህ እንዲህ ብሎም ነገረኝ ....»

3/ መልአኩ በሰው አምሳል መምጣቱ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንዳንድ ጊዜ መላኢካው በሰው ቅርጽ ተመስሎ ወደኔ ይመጣና እኔንም ያናግረኝ ነበር። እኔም እርሱ የሚናገረውን ነገር እረዳ (እና አስታውስም) ነበር።» መላኢካው በዚህ ሁኔታ ላይ ሲገለጽም ባልደረቦቻቸው አንዳንድ ጊዜ ይመለከቱት ነበር።

4/ በሚያቃጭል ደውል

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንዳንድ ጊዜ (መላኢካው) በሚያቃጭል ደውል መልክ ሆኖ ወደኔ ይመጣ ነበር። ይህም በኔ ላይ ከሁሉም እጅግ ከባዱ ነው። ከዚያም የነገረኝን ነገር (የተገለጸልኝን ነገር) ከጨበጥኩ በኋላ ይህም ሁኔታ ይለቀኝ ነበር።» እመት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ በማለት አከላለች፦ «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ቀዝቃዛ በሆነ ቀን ላይ መለኮታዊ ራዕዩ ሲገለጽላቸው አይቻለሁ፤ (እንዳለቀም) ያ ሁሉ (መጨናነቅ) ሲለቃቸውና ከግንባራቸውም ላይ ላብ ሲንጠባጠብ አስተውያለሁ።» እንደዚሁም ራዕዩ በሚገለጽላቸው ጊዜ እርሳቸው መጓጓቸው ላይ ከሆኑ እንስሳዋ ትንበረከክ ነበር።

5/ በተፈጥሮ ቅርጹ መገለጹ

አንዳንድ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራዕዩን ሲቀበሉ መላኢካውን በተፈጥሯዊ መልኩ ይመለከቱት ነበር። ከዚያም አላህ የፈቀደለትን ያህል ከራዕዩ ይገልጽላቸው ነበር። ይህም ልክ አላህ በሱረቱን ነጅም ውስጥ እንደገለጸው ሁለት ጊዜ በርሳቸው ላይ ተከስቷል።

6/ ከአላህ የሆነ ቀጥተኛ ራዕይ

ይህም ኃያሉ አላህ በርሳቸው ላይ መልዕክቱን በቀጥታ ያወረደበት ሁኔታ ሲሆን እርሱም የሆነው ከሰባቱ ሰማያት በላይ በእርገት ሌሊት (ለይለቱል ሚዕራጅ) ነበር። እንደ ሶላትና መሰል ጉዳዮችም ግዴታ ሆነው የተደነገጉት በዚህ ዓይነት ራዕይ አማካኝነት ነበር።

7/ የአላህን ንግግር በመስማት

ይህም ልክ ኃያሉ አላህ ሙሳን (ዐለይሂስ-ሰላም) በቀጥታ እንዳናገራቸው ሁሉ እርሳቸውንም ያለ አገናኝ መላኢካ ኃያሉ አላህ በቀጥታ ባናገራቸው ወቅት የተከሰተ ነበር።

የመጀመሪያው ራዕይ

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረደው የመጀመሪያው መለኮታዊ ራዕይ ቢኖር የሱረቱል ዐለቅ የመጀመሪያዎቹ አምስት አንቀጾች ናቸው፡-

«አንብብ! በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡ አንብብ! ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብርዕ ያስተማረ፡፡ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን፡፡» (አል-ዐለቅ 96፡1-5)

የደዕዋቹ ደረጃዎች

1. ነብይነት
2. የቅርብ ዘመዶችን ማስጠንቀቅ
3. ሕዝባቸውን ማስጠንቀቅ
4. እነዚያን ከዚህ በፊት ምንም አስጠንቃቂ ያልመጣላቸውን ሰዎች በሙሉ ማስጠንቀቅ - እነዚህ ሁሉም ዐረቦች ናቸው፡፡
5. እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ከጋኔንና ከሰው ዘር ሆነው ጥሪያቸው (ደዕዋቸው) የደረሳቸውን በሙሉ ማስጠንቀቅ ነው፡፡

የደዕዋቹ እርከኖች

1. **ምስጢራዊ ደዕዋ፡-** ይህም እንደተላኩ ለመጀመሪያዎቹ 3 ዓመታት የቀጠለው ነበር
2. **ይፋዊ ደዕዋ፡-** ይህም በልዕለ ኃያሉ አላህ እንዲህ እንዲያደርጉ በታዘዙ ጊዜ ነበር፡- *«የታዘዝክበትንም ነገር በይፋ ግለጽ፡፡ ኣጋሪዎችንም ተዋቸው፡፡» (አል-ሒጅር 15፡94)*

የመጀመሪያዎቹ አማኞች

- ከወንዶች አቡ በክር አስ-ሲድ-ዲቅ (ረ.ዐ)
- ከሴቶች ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)
- ከታዳጊዎች ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ
- ከባርነት ነፃ ከተደረጉ ከአገልጋዮች ዘይድ ኢብን ሓሪሣ (ረ.ዐ)
- ከባሮች ቢላል ኢብን ረባሕ አል-ሐበሺ (ረ.ዐ) ናቸው፡፡

በኢስላም ቀዳሚ ከሆኑት ከፊሎቻቸው

ከነዚያ ከላይ ከገለጽናቸው ቀዳሚ አማኞች በኋላ በርሳቸው በማመን ረገድ የርሳቸው ቤተሰብ አባላት የመጀመሪያዎቹ ናቸው፡፡ ከዚያም ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፋን፣ ጦልሃ ኢብን ዑበይዲሏህ፣ አዝ-ዙበይር ኢብን አል-ዐው-ዋም፣ ሰዕድ ኢብን አቢ ወቅ-ቃስ፣ ዐብዱር ረሕማን ኢብን ዐውፍ፣ ኸብ-ባብ ኢብን አል-አረት፣ ሱሀይብ አር-ሩሚይ፣ ዐም-ማር ኢብን ያሲር እና እናቱ ሱመይ-ያ፣ አቡ ዑበይዳ ዓሚር ኢብን አል-ጀር-ራሕ፣ ዑሥማን ኢብን መዝዑን፣ አቡ ሰለማ ኢብን ዐብዱል አሰድ እና ዑትባ ኢብን ገዝዋን (ረዲየሏሁ ዐንሁም አጅመዒን) ናቸው፡፡

የመካው ምዕራፍ

ጣዖታዉያኑ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸውን (ረ.ዐ) ማሰቃየታቸው

ጣዖታዉያኑ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ደዕዋን እውነተኝነትና የሰዎችን በርሳቸው ዙሪያ መሰብሰብን በተመለከቱ ጊዜ በአማኞች ላይ ከስቃዮች ሁሉ የከፋትን ስቃይ አድርሰዋል። አማኞችን ሲያሰቃዩ ከነበሩባቸው መንገዶች መካከልም ከፊሎቹ፡-

- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አስማተኛ እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ በማሰራጨት ሰዎች ከዙሪያቸው እንዲሸሹና እንዲፈሯቸው ማድረግ
- እርሳቸው እብድ እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ ማሰራጨትና በዚህም ሰዎች እርሳቸው ሞኝ እንደሆኑ አምነው እንዲቀበሉ ማድረግ
- እርሳቸው ውሸታም እንደሆኑ (የውሸት) ወሬ ማሰራጨት፣ ይሁንና ይህ ውድቅ ሆነባቸው፤ ምክንያቱም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱ ዘንድ አስቀድሞ በእውነተኝነታቸውና በአማና ጠባቂነታቸው ሳቢያ በአል-አሚንነት (ታማኙ በመሆን) ይታወቁ ነበርና
- በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና እርሳቸው ይዘው በመጡት መልዕክት ላይ መሳለቅ፣ ማፌዝ
- ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰዎች ደዕዋ ለማድረግ በመጡ ቁጥር በማወክና በመረበሽ ሰዎችን መለኮታዊ ራዕዩንና ከሐቅ በኩል እርሳቸው የመጡበትን መልዕክት ከመስማት ማገድ
- በመካ መውጪያ በሮች ላይ ሆነው ለዑምራ ወይም ለሐጅ አልያም ከሁለቱ ውጭ ላሉ (ጉዳዮች ወደ መካ) የሚመጣን ሰው ተቀብለው ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማስጠንቀቅ
- በርሳቸው ላይ አካላዊ ጥቃትን ማድረስ፤ ዑቅባ ኢብን አቢ ሙዒጥ አንድ ጊዜ አቡ በክር (ረ.ዐ) ደርሰው እስከሚመልሱላቸው ድረስ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በልብሳቸው ይዟቸው እየጎተታቸው ሊያንቃቸው ቀረበ። (ሌላ ጊዜ ደግሞ) የግመል ፈርስን በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ወረወረባቸው። ከዚያም ልጃቸው ፋጢማ ከርሳቸው ላይ አንስታ አስወገደች።
- ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል ማሴራቸው፣ ይህም የተከሰተው ወደአጎታቸው አቡ ጧሊብ ቀርበው እርሳቸውን በዐማራ ኢብን አል-ወሊድ እንዲለውጧቸውና ከዚያም እርሳቸውን ደግሞ (ለመግደል ዶልተው በጠየቁ ጊዜ) ነበር። ልክ እንደዚሁ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስደት ለመውጣት ባሰቡ ጊዜም እርሳቸውን ለመግደል ሞክረው ነበር።
- ከአማኞች መካከል ደካሞች የሆኑትን በቅጣት ማሰቃየትና ከፉኛ ማስቸገር፣ ይህም ልክ በቢላል ሆድ ላይ የድንጋይ ቋጥኝን እንዳስቀመጡት፣ እንደዚሁም ልክ የዐመ-ማር ቤተሰቦች ላይ እንዳደረጉትና በሌሎችም ላይ እንዳደረጉት ነበር።

ወደ ሐበሻ የተደረገው ስደት

የአማኞች ቁጥር በጨመረና አጋሪያንም እነርሱን መፍራት በጀመሩ ጊዜ በሙስሊሞች ላይ የሚደርሰው ስቃይና መከራ በኃይለኛው ጨመረ። ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊሞች ወደ ሐበሻ ይሰደዱ ዘንድ ፈቀዱላቸው።እንዲህም አሉ፡-

«በእውነቱ (በሐበሻ) ውስጥ ሰዎች እርሱ ዘንድ የማይበደሉበት ንጉሥ አለ።»

ወደ ሐበሻ የተደረገው ስደት

የመጀመሪያው ስደት

በመጀመሪያው ስደት 12 ወንዶችና 4 ሴቶች ወደ ሐበሻ ተሰደዱ። ከነርሱም መካከል አንዱ ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፋን (ረ.ዐ) ነበሩ። እርሳቸውም መጀመሪያ ላይ የወጡ ነበሩ። ከርሳቸው ጋር ሚስታቸው ሩቀይ-ያ፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ የሆነችው ነበረች። እነርሱም ምርጥ በሆነ ጎርብትና ሐበሻ ውስጥ መኖር ጀመሩ። ከዚያም ቁረይሾች እስልምናን ተቀብለዋል የሚል (ዜና) ደረሳቸው። ይሁንና ይህ የውሸት ዜና ነበር። ከዚያም ወደመካ ተመለሱ። በተመለሱ ጊዜም ሁኔታው በፊት ከነበሩበት በላይ የከፋ ሆነ። ከነርሱም መካከል (ወደ መካ) ተመልሰው ከመጡት (ዳግም ወደ ሐበሻ) ተመለሱ። የተወሰነው ስብስብ ደግሞ ወደ መካ ገባና ከቁረይሾች በኩልም እጅግ የከፋውን ስቃይ ተቀበለ። (ከሐበሻ ተመልሰው ወደ መካ) ከገቡት መካከልም ዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) አንዱ ነበሩ።

ሁለተኛው ስደት

በዚህን ጊዜ 83 ወንዶችና 18 ሴቶች ስደት የወጡ ሲሆን እነርሱም ከንጉሥ አን-ነጃሺ ዘንድ በምርጥ ሁኔታ ሰፈሩ። ይህም (ዜና) ቁረይሾች ዘንድ ደረሰ። ከዚያም ዐምር ኢብን ዓስ እና ዐብዱሏህ ኢብን አቢ ረቢዓን ከተሟላ ስብስብ ጋር አድርገው (ሙስሊሞችን) ከአን-ነጃሺ ጋር ለማጣላት ሴራ ያሴሩ ዘንድ ላኳቸው። ሆኖም ግን ኃያሉ አላህ የነርሱን ሴራ በፊታቸው ላይ መለሰባቸው (ያሴሩት ሴራ ከሸፈባቸው)።

የዑመርና ሐምዛ መስለም

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነብይነት ከተላኩ በ6ኛው ዓመት አጎታቸው ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ እስልምናን ተቀበሉ። ሀምዛ የቁረይሽ ኃያላን (ጀግኖች) ሁሉ አለቃ ተብለው ይጠሩ ነበር። አላህም በሀምዛ አማካኝነት መልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ኃያል አደረጋቸው። ከዚያም በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዱዓ በረከት ዑመር ኢብኑል ኸጣብም እስልምናን ተቀበሉ።በዚህን ጊዜ አማኞች ኃይልን አገኙ።ከቁረይሾች ጥቃትም ዳኑ።

የአቡ ጣሊብ ሽለቆ

ከቁረይሾች በኩል በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የሚደርሰው ስቃይ ይባሱኑ ከፋ። ለሦስት ዓመታት ያክልም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ቤተሰቦቻቸውን በአቢ ጣሊብ ተራራማ መንገድ መሀከልም አግልለው አገቷቸው። ዐብዱሏህ ኢብን ዐብ-ባስም የተወለዱት በዚህ ተራራማ መንገድ ላይ ነበር። በዚህን ጊዜ ኢጋሪያኑ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከፍተኛ ስቃይን አደረሱ። በአርባ ዘጠኝ ዓመታቸውም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታግተው ከኖሩበት ስፍራ ሰብረው ወጡ።

የአቡ ጣሊብና የኹዲጃ ሞት

ታግተው ሲኖሩ ከነበረው ስፍራ ከወጡ ከጥቂት ወራት በኋላ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑት አቡ ጣሊብ በሰማንያ ሰባት ዓመታቸው ከዚህች ዓለም በሞት ተለዩ። ከዚያም ከአጭር ጊዜ በኋላ ከዲጃም በሞት ተለየቻቸው። በዚህን ጊዜ ከኢጋሪያኑ በኩል በርሳቸው ላይ ሲደርስ የነበረው ስቃይ ይባሱኑ ተፋፋመ።

ወደ ጧኢፍ *መጓዛቸው*

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዘይድ ኢብን ሓሪሣ ጋር ሆነው ወደኃያሉ አላህ ለመጣራት ወደ አጥ-ጧኢፍ አመሩ። እዚያም የተወሰኑ ቀናትን ቆዩ። ሆኖም ግን ሰዎቹ መልዕክቱን ውድቅ አደረጉት። ይልቁንስ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አጠቁት። ከሀገራቸውም አስወጡት። ቁርጭምጭሚታቸው እስከሚደማ ድረስም በድንጋይ ወገሯቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መካ ለመመለስ ከነርሱ ዞረው ተመለሱ። ከዚያም በአል-ሙጥዒም ኢብን ዐዲይ-ይ ከለላ ሥር ሆነው ወደ መካ ገቡ።

የወድ-ዳስ መስለም

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በደርሶ መልስ ጉዞአቸው መንገድ ላይ ከወድ-ዳስ ጋር ተገናኙ። እርሱም ክርስቲያን የነበረ ሲሆን በርሳቸውም አመነ፤ እውነተኛ መሆናቸውንም አረጋገጠላቸው።

የጋኔኖች ሞመን

እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመንገዳቸው ላይ ነቅላ በሚባል ቦታ ላይ ከጋኔኖች ጭፍራ የሆኑት ወደርሳቸው ዞሩ። ከነርሱ መካከልም ሰባቱ ከነሲቢን ወገኖች ነበሩ። እነርሱም ቁርኣኑን ሰሙ፤ እስልምናንም ተቀበሉ።

የሌሊት ጉዞውና እርገቱ

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመንፈሳቸውና በሥጋቸው በሌሊት ጉዞ አማካኝነት ወደ መስጂድ አል-አቅሷ ተወሰዱ። ከዚያም በመንፈሳቸውና በሥጋቸው ወደአላህ ከሰባቱ ሰማያት በላይ አረጉ። ኃያሉ አላህም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አናገራቸው፤ አምስቱን ዕለታዊ ሶላቶችንም ግዴታ አድርጎ ደነገገባቸው።

እስልምናን ለተለያዩ ጎሳዎች ማቅረባቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካ ውስጥ መኖራቸውን ገፉበት። እዚያም እስካሉ ድረስ የተለያዩ ጎሳዎችን ወደኃያሉ አላህ ይጠሩ ነበር። በየወቅቱ ወደነርሱ በመቅረብ የጌታቸውን መልዕክት እስኪያደርሱ ድረስ እንዲያስጠጓቸውና በአጸፋውም ጀነትን እንደሚመነዱ ይነግሯቸው ነበር። ይሁንና አንድም (የመካ አካባቢ) ጎሳ አልተቀበላቸውም። ኃያሉ አላህም ይህንን ከራማ (ክብር) (የእስልምና ፀጋን) ለአንሷር ጠብቆ አቆየ። (በዚሁ መሠረት በመካ ውስጥ ሳሉ) መልዕክቱ ከነርሱ መካከል ለስድስቱ ደረሳቸው። እነርሱም ለአላህና ለመልዕክተኛው ጥሪ ምላሽን ሰጡ። ወደ አል-መዲናም ተመለሱ። እስልምና በነርሱ ውስጥ እስከሚሰራጭና ከአንሷር ቤቶች መካከል የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሚወሳበት እንጂ ሌላ ቤት እስከማይኖር ድረስም ሕዝቦቻቸውን ወደ እስልምና ተጣሩ።

አንሷሮችና የዐቀባው ቃል ኪዳን

የመጀመሪያው የታማኝነት ቃል ኪዳን

ከዚያም በቀጣዩ ዓመት ከአንሷር የሆኑ 12 ሰዎች፣ ከነርሱ መካከል አምስቱ ከመጀመሪያዎቹ ስድስት ሰዎች መካከል የነበሩ ሲሆኑ፣ ወደ መካ መጡና ዐቀባ ላይ (በሚና) ሱረቱል ሙምተሒና (በነርሱ ሳቢያ) በወረደችባቸው ሴቶች ቃል ኪዳን ላይ ሆነው ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የታማኝነት ቃል ኪዳንን ፈጸሙ። ከዚያም እነርሱ ወደ አል-መዲና ተመለሱ።

ሁለተኛው የታማኝነት ቃል ኪዳን

በቀጣዩ ዓመት 73 ወንዶችና 2 ሴቶች ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡና እነርሱም የመጨረሻው የቃል ኪዳን ሰዎች ሲሆኑ፣ ልክ የገዛ ሴቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና ነፍሶቻቸውን ከጥቃት እንደሚከላከሉ ሁሉ ለአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ሊከላከሉላቸው ዘንድ የታማኝነት ቃል ኪዳንን ፈጸሙ። ከዚህ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው ወደነርሱ (አል-መዲና) ተጓዙ። ከነርሱም መካከል 12 አለቆችን መረጡ።

የመዲናው ምዕራፍ

የስደት ፍቄድነት

ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለባልደረቦቻቸውንም (ረ.ዐ) ወደ አል-መዲና እንዲሰደዱ ተፈቀደላቸው። ስለሆነም እነርሱ ትኩረት እንዳይደረግባቸው ዘንድ በምስጢር እየተከለሉ ወጡ። ከነርሱ መካከልም የመጀመሪያው አቡ ሰለማ ዐብዱል አሰዲ አል-መኽዙሚ ነበር ተብሏል። ሙስዐብ ኢብን ዑመይርም ነበር ተብሏል። (የሆኖ ሆኖ) እየተከፋፈሉ (ከፊል ከፊል እየሆኑ) ወደ አንሷሮች አመሩ። አንሷሮችም እነርሱን አስጠጓቸው። ረዲቸውም። እስልምናንም በአል-መዲና ውስጥ ተስፋፋ (ተሰራጨ)።

የኋላ ኋላም ለአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ስደት ተፈቀደላቸው። እርሳቸውም በዕለተ ሰኞ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል ውስጥ ለስደት ከመካ ወጡ። በዚህን ጊዜ ዕድሜያቸው 53 ዓመት ነበር። ከርሳቸውም ጋር አቡ በክር (ረዲየሏሁ ዐንሁ)፣ የአቡ በክር አገልጋይ የሆነው ዐሚር ኢብን ፉሀይራ እና መንገድ መሪያቸው የሆነው ዐብዱሏህ ኢብን ኡረይቂጥ አል-ለይሲ ነበሩ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና አቡ በክርም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ሠውር ዋሻ ገቡ። እዚያም ውስጥ ሦስት ቀናትን ቆዩ። ከዚያም በጠረፍ በኩል ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና መግቢያቸው

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከርሳቸው ጋር የነበሩ ሰዎች መዲና በደረሱ ጊዜ - ዕለቱ ሰኞ ሲሆን ረቢዑል አው-ወል ወር አስራ ሁለት ቀናት አልፈው የነበረ ሲሆን - በኒ ዐምር ኢብን ዐውፍ ዘንድ የመዲና ከፍታ በሆነው ቁባእ ላይ አረፉ። እነርሱም ዘንድ ለ14 ቀናት ቆዩ።

የመጀመሪያው መስጂድ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና እንደገቡ የቁባእ መስጂድን ገነቡ። ኢብን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በየእያንዳንዱ ቅዳሜ በእግራቸው እየተራመዱ አልያም በመጓጓዣቸው እየጋለቡ ወደ ሙስጂድ ቁባእ ይመጡ ነበር።» ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ማለታቸውም ተዘግቧል፡- «ቁባእ መስጂድ ውስጥ የሚሰገድ ሶላት ልክ ዑምራ እንደማድረግ ነው።»

መስጂድ አን-ነበዊን መገንቢያቸው

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሴት ግመላቸውን ተሳፍረው (በመዲና መንገዶች) ላይ መጓዝ ጀመሩ። (የመዲና) ሰዎችም እርሳቸው መጥተው እነርሱ ዘንድ እንዲያርፉ በመጠየቅ ያናግሯቸው ነበር። የግመላቸውን ልጓምም ይይዙ ነበር። እርሳቸውም «እርሷ (የት ማረፍ እንዳለባት) ታዛለችና መንገዷን ልቀቁላት» ይሉ ነበር። ግመሏም ዛሬ መስጂዳቸው ያለበት ቦታ ላይ (ስትደርስ) ተንበረከከች። ቦታውም (የግመሎችና ሌሎችም እንስሳት መቆሚያ ሲሆን) ከበኑ አን-ነጅ-ጃር መካከል የሆኑት፣ ሰህልና ሱሀይል የሚባሉ ሁለት ታዳጊ ልጆች ይዞታ ነበር። ከዚያም አቡ አይ-ዩብ አል-አንሷሪ (ደጅ ሲደርሱ) ከግመላቸው ላይ ወረዱ። ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸው (ረዲየሏሁ ዐንሁም) እዚያው (የግመሎች መቆሚያ ቦታ ላይ) ከጭቃ በሆነ ብሎኬትና በዘምባባ ቅጠል አማካኝነት መስጂዳቸውን (መስጂድ አን-ነበዊን) ገነቡ። ከዚያም በመቀጠል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን ቤትና የሚስቶቻቸውንም ቤቶች ከመስጂዱ ጀርባ ሠሩ። ከቤቶች ሁሉ ለመስጂዳቸው ይበልጥ ቅርብ የሆነውም የእመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ቤት ነበር። ከዚያም ከሰባት ወራት በኋላ ከአቡ አይ-ዩብ ቤት ወጥተው ወደርሷ ቤት አመሩ።

ወንድማማችነት

መስጂድን ከገነቡ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሙሃጂሩን፣ እነዚያ በቁጥር 90 በነበሩትና በአንሷሮች (እነዚያ ከሙሃጂሩን በብዙ እጥፍ በሚበልጡት) መካከል ኢስላማዊ ወንድማማችነትን መሠረቱ። እነርሱም እስከ በድር ዘመቻ ድረስ እርስ በርሳቸው ይወራረሱ ነበር።

አይሁዶች

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ አል-መዲና በመጡ ጊዜ አይሁዶች እርሳቸውን አይተዋል። እርሳቸውም እውነተኛው የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን አውቀዋል። እርሳቸውም ያ እነርሱ ዘንድ በተውራት ተጽፎ የሚያገኙት መሆናቸውን ደርሰውበታል። ይሁንና ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነርሱ መካከል ጥቂት ጭፍሮች እንጂ ሌሎች እስልምናን አልተቀበሉም። ከነዚህም አንዱ ይበልጥ ዐዋቂያቸውና ሊቃቸው የነበረው ዐብዱሏህ ኢብን ሰላም ነበር። ይሁንና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለአይሁድ ጉሳዎች ራሱን የቻለ የቃል ኪዳን ስምምነት አረቀቁላቸው። እነዚህም ጎሳዎች በኑ ቀይኑቃዕ፣ በኑ አን-ነዲር እና በኑ ቁረይዛ ነበሩ።

የቁብላ መቀየር

በሌሊት ጉዞ ወቅት ሶላት ግዴታ ከተደረገች በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ በይቱል መቅዲስ ዙረው ይሰግዱ ነበር። ይሁንና ቂብላቸው ወደከዕባ እንዲቀየርላቸው ይፈልጉ ነበር። ይህንኑ በመከጀልም ፊታቸውን ወደሰማይ ያዞሩ ነበር። ስለሆነም አላህ ቀጣዩን አንቀጽ አወረደባቸው፡- *«የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን። ወደምትወዳትም ቂብላ እናዞርሃለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር። የትም ሰፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ።»* *(አል-በቀራ 2፡144)* ይህም በመሆኑ ከሂጅሪያ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቂብላቸውን (የሶላት አቅጣጫው) ወደከዕባ አዞሩ።

የተጋድሎ መፈቀድ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አል-መዲና አን-ነበዊይ-ያ ውስጥ ከሰፈሩና አንሷሮችም ለርሳቸው ሰብአዊ ጥበቃን ካደረጉላቸው በኋላ አላህ ቀጥሎ ያሉትን የቁርአን አንቀጾች አወረደ፡- *«ለእነዚያ ለሚገደሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው። አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት። ...»* *(አል-ሐጅ 22፡39-40)*

በዚህም መሠረት ኃያሉ አላህ ለአማኞች እነርሱን ከሚዋጉ ጣዖታዉያን ጋር እንዲዋጉ (ተጋድሎ እንዲያደርጉ) ፈቀደላቸው። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎች መካከልም የመጀመሪያዎቹ የአል-አብዋእ፣ የቡዋጥ፣ የዑሺራና በከፊል ወደ አስ-ሰራያ የተደረጉ ዘመቻዎች ተጠቃሾች ናቸው።

የበድር ዘመቻ

ከሂጅራ በኋላ በሁለተኛው ዓመት በወርሃ ረመዷን ውስጥ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአማኞች የሆኑና ሦስት መቶ አስራ ምናምን የሆኑ ሰዎችን ይዘው ከመዲና ወጡ። (የዚህም ምክንያቱ) ከሶሪያ የሚመለሱ የቁረይሾችን የንግድ ቅፍለት ፍለጋ ነበር። ይሁንና አቡ ሱፍያን በሌላ መንገድ ዞሮ በመሄድ ቅፍለቱን አስመለጠ። ዳሩ ግን ሸይጣን ቁረይሾችን አታለላቸውና እነርሱም አማኞችን ለመውጋት (የጦር ኃይላቸውን ይዘው) ወጡ። ሁለቱም (አማኞችና ከሀዲዎች) በበድር ላይ ተገናኙ። ይህም ታላቁ የበድር ጦርነት ሆነ። (የበድር ጦርነትም) ያ በሌላ ስሙ ‹የውመል ፉርቃን› (የመለያያ ቀን) ተብሎ የተሰየመው ነበር።

ሁለቱ ሠራዊቶች ለመፋለም በአውደ ውጊያ ግንባር በተገናኙ ጊዜ፣ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወደርሱ በመተናነስ ጌታቸውን (በኃይለኛው) ለመኑ። ስለሆነም ኃያሉ አላህ ከነርሱ ጋር ይዋጉ ዘንድ አማኞችን በመላእክት አማካኝነት አበረታቸው። ኃያሉ አላህ በከሀዲያን ሕዝቦች ላይም ድልን አጎናጸፋቸው። ቃሉንም የበላይ አደረጋት። በበድር ጦርነት ላይም ከኢጋሪያን መካከል ሰባ ሰዎች ተገደሉ። ከአማኞች መካከል ደግሞ አስራ አራት ሰዎች የሰማዕትነት ደረጃን አገኙ።

የቀይኑቃዕ ዘመቻ

በ3ኛው ዓመተ ሂጅሪያ የበኑ ቀይኑቃዕ ሰዎች የእርቀ ሰላም ቃል ኪዳናቸውን አፈረሱ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ለ15 ሌሊቶች ያክል እነርሱን በጦር ኃይል ከበባ ውስጥ አስገቧቸው፡፡ ከዚያም በርሳቸው ብያኔ መሠረት እጃቸውን ሰጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱን ከሀገራቸው አስወጧቸው፡፡ እነርሱም በቁጥር ሰባት መቶ ነበሩ፡፡

የኡሑድ ጦርነት

የኡሑድ ዘመቻ የተካሄደው በሸው-ዋል ወር ውስጥ ሲሆን ቁረይሾቹ በበድር ጦርነት የደረሰባቸውን ሽንፈት ለመበቀል ሲሉ ወደ ሦስት ሺ የሚጠጋ ሰው ይዘው ወደ መዲና ወጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ወደ ሰባት መቶ የሚጠጋ ሰው ይዘው ወደ ኡሑድ ወጡ፡፡ ሙናፊቆቹ ግን ከጦራቸው መካከል የተወሰነውን ገንጥለው ተመለሱ፡፡

በቀኑ መጀመሪያ አካባቢ ኳሷ (ስለቱ) ለሙስሊሞች ሆና ነበረ፡፡ ከዚያም ኃያሉ አላህ ሙስሊሞችን ሞከራቸውና የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ነጥለው የጥቃታቸው ዒላማ እስከሚያደርጉ ድረስም ኳሷን (ስለቱን) ወደሙሽሪኮች እጅ መለሰ፡፡ ስለሆነም ግንባራቸውን አቆሰሉ፡፡ የፊት ጥርሳቸውንም ሰበሩ፡፡ በዚያን ዕለት መላኢኮች ከርሳቸው ጋር ተዋጉ፡፡ ከርሳቸው ባልደረቦች መካከልም ሰባዎቹ ተሰው (የሰማዕትነት ክብርን ተጎናጸፉ)፡፡ ከነርሱም መካከል ሀምዛ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ፣ ሙስዐብ ኢብን ዑመይር፣ አነስ ኢብን አን-ነድር፣ ሐንዘላ አል-ገሲል እና ከነርሱ ውጭ ያሉትም ሰማዕት ሆኑ፡፡ በዚያን ዕለት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ እስኪሉ ድረስ አቢ ጦልሓ ኢብን ዑበይዱላህ በታላቅ ጀግንነት ተዋጋ፡- «ጀነት ለጦልሓ ተገቢው ሆነች፡፡»

ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ሙስሊሞቹ ዳግም ለተመሳሳይ ዓላማ ተሰባሰቡ፡፡ አላህም የሙሽሪኮችን እጅ ከነርሱ ላይ ከለከለ፡፡

የኡሑድ ዕለት የመሞከሪያና የመከበቢያ ዕለት ነበር፡፡ ኃያሉ አላህም በዚያች ዕለት ሙእሚኖችን ሞከራቸው፡፡ ሙናፊዎችንም ግልጽ አደረጋቸው፡፡ የሻቸውንም ሰዎች በሰማዕትነት አማካኝነት አላቃቸው፡፡

ከዘመቻው በኋላ ቁረይሾቹ ሙስሊሞችን ከናካቴው ለመጨረሽ ፈልገው ዳግም ተመልሰው እየመጡ መሆናቸውን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሙ፡፡ ስለሆነም ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ከአማኞቹና ከቁስለኞቻቸው ጋር ሆነው ወደነርሱ አቅጣጫ አመሩ፡፡ ሙስሊሞቹም ሐምራአል አሰድ በደረሱ ጊዜ ይህም (ድርጊታቸው) ቁረይሾች ዘንድ ደረሰ፡፡ ከዚያም ተገነጣጠሉ፡፡ ወደ መካም ተመለሱ፡፡

ከሂጅራ በኋላ 4ኛው ዓመት

በአራተኛው ዓመተ ሂጅራ ቢእር መዑና በተባለ ቦታ አንድ ክስተት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይኸውም ከሰሓቦች መካከል 70 የሚሆኑት፣ እነዚያ በቁርኣኑ እጅግ አዋቂዎች የሆኑት የተገደሉበት ቦታ ሆነ፡፡ እንደዚሁም የበኑ አን-ነዲር ዘመቻ ተደርጎ ነበር፡፡ እነዚህም እነዚያ ኃያሉ አላህ በልቦቻቸው ውስጥ ፍርሃትን እስከሚለቅባቸው ጊዜ ድረስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጦር ከበባ ሥር አስገብቷቸው የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) እነርሱን ከአል-መዲና አስወጧቸው፡፡ ሱረቱል ሐሽርም የወረደችው እነርሱን በማስመልከት ነበር፡፡

የሙሪሲዕ ዘመቻ

በአምስተኛው ዓመተ ሂጅራ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኒ አል-ሙስጠሊቅን ለመዋጋት ወጡ፡፡ የድል ባለቤትም ሆነው ተመለሱ፡፡ በዚህ ጉዞ ወቅትም አት-ተየም-ሙም ተደነገገ፡፡ በእመት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) ላይ የተወራው ቅጥፈትም ተከሰተ፡፡ ይህም የተገኘው ሙናፊቆቹ የሙእሚኖች እናት በሆነችው ዓኢሻ ላይ ውሸትን በቀጣጠፉበት ጊዜ ነበር፡፡ ይሁንና እርሷ የንጽሕቶች ሁሉ ንጽሕት ናት፡፡ ስለሆነም ኃያሉ አላህ ንጽሕነቷን ሱረቱን ኑርን አውርዶ እስከሚያረጋግጥላት ድረስ ይህ ጉዳይ በርሷና በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሊቋቋሙት ዘንድ ሲበዛ ጠንቶባቸው ነበር፡፡ (እውነቱ በተገለጠ ጊዜም) እነዚያ የቅጥፈት ዜናውን ያሰራጩ ሰዎችም በጅራፍ ተገረፉ፡፡

የአሕዛብ ዘመቻ

የሽንደቅ (የቦዩ) ወይም የአሕዛብ ዘመቻ የተካሄደው በወርሃ ሸው-ዋል ከሂጅራ በኋላ በስድስተኛው ዓመት ነበር። በዚህን ወቅት አይሁዶቹ ቁረይሾችንና ማንኛውንም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸውን ለመውጋት በመሐላ ከሚያረጋግጥላቸው አካል ሁሉ ጋር ተስማሙ። የቁረይሾቹ ኃይል ከበኑ ሱለይም፣ ከበኑ አሰድ፣ ከፈዛረህ፣ ከአሽጀዕ እና ከነርሱም ውጭ ካሉት ኃይሎች ጋር ተጣምሮ አስር ሺ ሰው በያዘ (ጥምር የጦር ኃይል) ወደ መዲና መጣ።

ሰልማን አል-ፋሪሲ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እነርሱን ከጥምር ኃይሎቹ መከላከል የሚያስችላቸውን ቦይ (ጉድጓድ) እንዲቆፈሩ ዘንድ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምክርን ለገሱ (አመላከቱ)። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሦስት ሺ ሰው ይዘው (ለጦርነት) ወጡ። የሰልፅ ተራራንም ከበስተ ጀርባ በኩል እንደ መከላከያ ግንብ ተጠቀሙ። ቦዩን ደግሞ ከፊት ለፊታቸው እንደ መከላከያ ተጠቀሙበት። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የሰላም ስምምነት ፈጥረው ሲኖሩ የነበሩ ቁረይዛዎችም ዳግም ከርሳቸው የደህንነት ዋስትናን ጠየቁ። ካልሆነ ግን የታማኝነት ቃል ኪዳናቸውን ሊያፈርሱና (እርሳቸውን ለመውጋት ሲሉ) ከጥምር የጦር ኃይሉ ጋር ሊቀላቀሉ ሆነ።

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኑዐይም ኢብን መስዑድን ወደ በኑ ቁረይዛዎችና ወደ ጥምር ኃይሎቹም ላኩት። እርሱም በነርሱ ደረጃ ላይ ሆኖ ከነርሱ ጋር ሴራን ጎነጎነ። የኋላ ኋላም በመካከላቸው ነገሮችን አበለሻሸ። ከዚያም ኃያሉ አላህ ከነፋስ የሆነን ሠራዊት ላከባቸው። ነፋሷም ካምፖቻቸውን አፈራረሰችባቸው። የማብሰያ ዕቃዎቻቸውንም ላዩን ወደታች ገለባበጠችባቸው። እነርሱም በነፋሱ ኃይል ተንቀጠቀጡ። በልቦቻቸው ውስጥም ፍርሃትን ጣለችባቸው። ጥምር ኃይሎቹንም በታተነቻቸው። በስተ መጨረሻም ያ ሁሉ ሴራ ምንም ሳይፈይዳቸው ተመልሰው ወደሀገራቸው ሄዱ።

ከዚያ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደበኑ ቁረይዛ ዘመቱና በነርሱም ጉዳይ ላይ ዳኝነትን ይሰጥ ዘንድ ሰዕድ ኢብን ሙዓዝን ሾሙ። ሱረቱል አሕዛብም የወረደችው ይህንኑ ዘመቻን በማስመልከት ነበር።

የሑደይቢያ ስምምነት

ከሂጅራ በኋላ በስድስተኛው ዓመት ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሺ አራት መቶ ከሚሆኑ ባልደረቦቻቸው ጋር ዑምራ ለማድረግ አስበው ወጡ። አል-ሑደይቢያ በደረሱ ጊዜም ቁረይሾች እነርሱን ወደ መካ ከመግባት ከለከሏቸው። ለአስር ዓመታት ያክልም ከነርሱ ጋር የጦርነትን መዘዝ ለመተው የሚያስችል የሰላም ስምምነትንም እንዲሰጧቸው ጠየቋቸው። ይህም ልክ ኃያሉ አላህ እንዳለው ለሙእሚኖች ታላቅ ድል ሆነ፡-

«እኛ ላንተ ግልጽ የሆነን መክፈት ከፈትንልህ።» (አል-ፈትሕ 48፡1)

ይህ የሰላም ስምምነትም ካስገኛቸው (ድሎች መካከል) ቁረይሾቹ ለሙስሊሞች በቀጣዩ ዓመት ወደ መካ ተመልሰው በመግባት ዑምራ እንዲያደርጉ መፍቀዳቸው ነበር። ይህም በዙል ቂዕዳ ውስጥ ለስድስተኛ ዓመተ ሂጅራ የማካካሻ ዑምራ ወይም ‹ዑምራ አል-ቀዳእ› ሆነ።

የኸይበር ዘመቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአል-ሑደይቢያ ከተመለሱ ከ20 ቀናት በኋላ፣ ወደ ኸይበር ለመዝመት ወጡ። ኸይበር ከአል-መዲና በስተ ሰሜን በኩል የምትገኝ ስትሆን እዚያም ሙስሊሞቹ አይሁዶችን በግምት ለሀያ ቀናት ያክል በጦር ኃይል ከበባ ሥር አስገቧቸው። በኸይበር ውስጥ ሙስሊሞችም ኃይለኛ ትግልን አካሄዱ። አይሁዶቹም በሚደርስባቸው ጥቃት ሳቢያ እንደሚጠፉ እርግጠኞች በሆኑ ጊዜ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርቀ ሰላምን ጠየቁ።

ከዚያም ደማቸውን አስጠብቀው የለበሱትን ልብሶች ብቻ ይዘው እንዲወጡ ተስማሙ። ከዚያም ከመሬታቸው ከሚወጣው ነገር ግማሹን እየሰጡ በመሬታቸው ላይ እንዲሠሩበት በመስማማት ኃላፊነቱን ሰጧቸው።

የጁዕፈር መሞጣት

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኸይበር ሳሉ አቡ ሁረይራ ሙስሊም ሆነው ወደ አል-መዲና መጡ። ጀዕፈር ኢብን አቢ ጣሊብ፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአጎታቸው ልጅ የሆኑትና እነዚያ ከርሳቸው ጋር ሐበሻ ውስጥ ቀርተው የነበሩትም መጡና ነብዩንም (ሰ.ዐ.ወ) በኸይበር ሳሉ አስደሰቷቸው። እንደዚሁም ከነርሱ ጋር አቡ ሙሳ አል-አሽዐሪ እና ባልደረቦቻቸውም መጥተው (ከሙስሊሞች ጋር ተቀላቀሉ)።

የሙእጣ ዘመቻ

የሙእጣ ዘመቻ የተካሄደው ከሂጅራ በኋላ በስምንተኛው ዓመት ነበር። የዚህ ዘመቻ መነሻ ምክንያቱም ሸረሕቢል ኢብን ዐምር አል-ገስ-ሳኒ የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛ ወደ ሮማው ንጉሥ እያመራ ሳለ ገደላቸው። ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ሦስት ሺ የሚሆኑትን ላኩ። ወዳጃቸውን ዘይድ ኢብን ሓሪሣንም መሪያቸው አድርገው ሾሙ። እንዲህም አሉ፦ «ዘይድ በጦርነቱ ላይ ከተሰዋ ከዚያም ጀዕፈር ኢብን አቢ ጣሊብ ሰዎቹን ይመራል። ይሁንና ጀዕፈርም በጦርነቱ ላይ ከተሰዋ ዐብዱሏህ ኢብን ረዋሓ ሰዎቹን ይመራል።»

የሮማው ንጉሥ ሂረቅል እና እነዚያ ከርሱ ጋር የተሰለፉ የዐረብ ረዳት ጎሳዎች 200 ሺ የጦር ሠራዊት ይዘው ዘመቱ። ሁለቱም ኃይሎች ሙእጣ ላይ ተገናኙ። ውጊያም ተካሄደ።እነዚያ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት ሹመት የተሰጣቸው ሰዎችም እንዳሉ ተሰው። ከዚያም ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድ የሙስሊሞችን ባንዲራ ያዘ። እርሱም የሙስሊሞችን ጦር በምርጥ ሁኔታ መራ። የኋላ ኋላም ሙስሊሞችን ከአላህ ጠላቶችና ከጠላቶቻቸው (የጦር ከበባ ሥር) ነፃ አውጥቶ ዳግም አንድ ላይ አሰባሰባቸው።

ታላቁ የመካ መከፈት ድል

በተመሳሳይ ዓመት በኑ በክር - እነርሱም ከቁረይሾች ጋር የሰላም ስምምነት ውል ያላቸው ሲሆኑ - በኑ ኹዛዓን - እነርሱ ደግሞ ከነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ጋር የሰላም ስምምነት ያላቸው ሲሆኑ - አጠቁ። ቁረይሾችም በዚህ ጥቃት ላይ እነርሱን በምስጢር አገዙ። ይህም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በደረሰ ጊዜ እርሳቸውም መካን ለመክፈት ቆርጠው ተነሱ። አቡ ሱፍያንም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለማናገር ወደ አል-መዲና መጡ። ሆኖም ግን እርሳቸው ከርሱ ምንም ነገር ለመስማት ፈቃደኛ አልነበሩም። ስለሆነም አቡ ሱፍያን ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ያነጋግሩለት ዘንድ አቡ በክርን፣ ዑመርንና ዐሊን አናገሩ። ግና ሁላቸውም እምቢ አሉ።

የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸው ወደነርሱ መዝመታቸውን እንዳያውቁ ዘንድ አላህ ቁረይሾችን ደንቆሮዎች እንዲያደርጋቸው ለመኑ። ኃያሉ አላህም ለዚህ ዱዓቸው ምላሽን ሰጠ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) አስር ሺ ሠራዊትን ይዘው ወደ መካ ዘመቱ። ወደ መካም ዘልቀው ገቡ። ይሁንና ከመካ መከፈት ትንሽ ቀደም ብለው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑት አል-ዐብ-ባስ ኢብን ዐብዱል ሙጠሊብ እስልምናን ተቀበሉ።

መካን በድል በከፈቱ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ ከነበሯቸው ነገሮች መካከል፦ «ወደ አቡ ሱፍያን ቤት የገባ ሰው እርሱ ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው። ወደመስጂድ የገባ ሰውም ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው። በሩንም የዘጋ ሰው ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው» የሚሉት ንግግሮቻቸው ተጠቃሾች ናቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርሳቸውን ለመውጋት ከተሸቀዳደሙ አካላት በስተቀር፣ እርሳቸውንና ሙስሊሞችን ካሰቃዩና ደማቸውንም ከንተ ካደረጉ ጥቂት አካላት በስተቀር ከማንም ጋር ተዋግተው አያውቁም።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መካ በገቡ ጊዜ ከዕባን ዞረዋል። ነገር ግን በኢሕራም ሁኔታ ውስጥ ሆነው አልነበሩም። ከዚያም ዑሥማን ኢብን ጦልሓን ጠሩትና የከዕባን ቁልፍ ተቀበሉት። ከዚያም በውስጡ ያሉትንና በዙሪያው ያሉትንም ጣዖታት በሙሉ ሰባበሩ። ከዚያም ቁልፉን ለዑሥማን መለሱለት። መካ በድል ከተከፈተች በኋላ ብዙ ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ። እንደውም ብዙ ጎሳዎች እስልምናን እየተቀበሉ በፍጥነት ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡ።

ጣዖታትን ማውደሟቸው

አላህ መካን ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በድል ከከፈተላቸው በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦቻቸውን በመካ ዙሪያ ያሉትን ጣዖታት ሁሉ ያወድሟቸው ዘንድ ላኩአቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ሱዋዕን ያፈርስ ዘንድ ዐምር ኢብን ዓስን ላኩት፡፡ መናትን ያፈርስ ዘንድ ሰዕድ ኢብን ዘይድን ላኩት፡፡ አል-ዑዝ-ዛን ያፈርስ ዘንድ ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድን ላኩት፡፡ ዚል ከፍ-ፈይንን ያፈርስ ዘንድ አጥ-ጡፈይልን ላኩት፡፡ የጠይእ ታቦትን ያፈርስ ዘንድ ዐሊን ላኩት፡፡

የሑነይን ዘመቻ

የሀዋዚን ጎሳ አባላት መካ በድል መከፈቷን በሰሙ ጊዜ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በታላቅ ሰልፍ ለመዝመት ተሰባሰቡ፡፡ ሁሉንም ንብረቶቻቸውን፣ ሴቶቻቸውንና ብዛታቸውን (ልጆቻቸውን) ከራሳቸው ጋር እየነዱ መጡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) 12 ሺ ሠራዊትን ይዘው ወደነርሱ ዘመቱ፡፡ ሙስሊሞችም የሑነይን ሸለቆ እስከሚደርሱ ድረስ በቁጥራቸው ብዛት ተደነቁ፡፡ ይሁንና ሀዋዚኖች ሙስሊሞችን ባልገመቱት ቦታ ላይ አድፍጠው ድንገት አጠቁአቸው፡፡ ከድንጋጤው ኃያልነት የተነሳም ሙስሊሞቹ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እስኪሸሹ ድረስ ሀዋዚኖች ልክ እንደ አንድ ሰው ብርታት እጅግ በረቱባቸው፡፡ ከሙሃጂሮችና ከአህሉል በይት የሆኑ ውስን ጭፍሮች ግን ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፀንተው ቆሙ፡፡

ከዚያም ኃያሉ አላህ እነዚያን ያመኑትን ሰዎች አፀናቸውና ከዚያም ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ ተመለሱ፡፡ ኃያሉ አላህም በጠላቶቻቸው ላይ ድልን እስኪያጎናጽፋቸው ድረስ ከርሳቸውም ጋር ተዋጉ፡፡ የኋላ ኋላም ሀዋዚኖቹ ወደ ጧኢፍ ሸሹ፡፡ ከዚህ በኋላ ከሀዋዚን ጎሳ የሆኑ 14 ሰዎች፣ እነዚያ እስልምናን የተቀበሉት፣ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጡ፡፡ ከምርኮኞችም መካከል ቤተሰቦቻቸውን በውለታ መልክ እንዲመለሱላቸው ጠየቁ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ አደረጉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም (ረ.ዐ) ይህንኑ ከርሳቸው ጋር አደረጉ፡፡

የጧኢፍ ዘመቻ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሀዋዚንን ጉዳይ ከጨረሱ በኋላ ወደ ጧኢፍ ለመዝመት ወሰኑ፡፡ ጧኢፍ በደረሱ ጊዜም የነርሱን ምሽግ ለ18 ቀናት ያክል በጦር ኃይል ከበባ ሥር አስገቡት፡፡ ከዚያም ምንም ውጊያ ሳይገጥሙ ተመለሱ፡፡

የተቡክ ዘመቻ

በዘጠነኛው ዓመተ ሂጅራ የተቡክ ዘመቻ (ገዝወቱል ዑስራ - አስቸጋሪው ዘመቻ) ተካሄደ፡፡ ዘመቻው የተካሄደው እጅግ ሞቃታማ በሆነ ወቅት ነበር፡፡ እንደዚሁም በፍራፍሬዎችና ጥላዎች ወቅት ነበር፡፡ በዚህም ሳቢያ ለዘመቻው መውጣት በሰዎች ላይ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻ ለማድረግ በሚፈልጉበት ጊዜ ሰሓቦችን ምጽዋት በመስጠት ያነሳሱ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ዑሥማን ኢብን ዐፍ-ፋን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ሦስት መቶ ግመሎችን ከነጭነቶቻቸውና ከነኮርቻዎቻቸው ከአንድ ሺ ዲናር ጋር ለገሱ፡፡ በዚህን ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) «ዑሥማን ከዚህ ቀን በኋላ የሚሠራው ነገር እርሱን አይጎዳውም» አሉ፡፡ የተቀሩ ባልደረቦቻቸውም በአቅማቸው ልክ በአላህ መንገድ ላይ ለገሱ፡፡

ሙናፊቆቹ እንዳሉ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ከመዝመት ወደኋላ ቀሩ፡ ከምርጥ ባልደረቦቻቸው መካከልም ሦስቱ ያለ በቂ ምክንያት (እንዲሁ ወደኋላ ቀሩ)፡፡ እነርሱም ከዕብ ኢብን ማሊክ፣ ሂላል ኢብን ኡመይ-ያ እና ሚራራ ኢብን አር-ረቢዕ ነበሩ፡፡ ይሁንና ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደመዲና በተመለሱ ጊዜ የቀሩበትን ምክንያት አስረዱ፡፡ ከሱረቱት ተውባ የሆኑ የተወሰኑ አንቀጾችም የወረዱት እነርሱን በማስመልከት ነበር፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡- *«ለነዚያ ሦስት (ከነብዩ) ወደኋላ በቀሩት ላይ ..... » (አት-ተውባ 9:118)*

ኃያሉ አላህም የሦስቱን ሰሓቦች እውነተኝነታቸውን ስለሚያውቅ ፀፀታቸውን ተቀብሎ በምሕረቱ ተመለሰላቸው፡፡ ይሁንና በዚህቹ ምዕራፍ ውስጥ ሙናፊቆችን አዋረዳቸው፡፡ ስለነርሱ በማውሳትም ምዕራፏን ቋጫት፡፡ ስለሆነም ምዕራፏ አል-ፋዲሓ (አጋላጭዋ) በሚል ተሰየመች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሙናፊቆችን ስላጋለጠች ነው፡፡

የተቡክ ዘመቻ

በተቡክ ዘመቻ ላይ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአይላ ሰዎች ጋር የሰላም ስምምነትን ፈጠሩ። ልክ እንደዚሁ ከጀርባና ከአዝረሕ ሰዎች ጋርም ፈጠሩ።ለነሱም የስምምነት ውልን ጻፉላቸው። ልክ እንደዚሁ በሙስሊሞች ቃል ኪዳን ሥር ለመኖር ግብር መክፈል እንዳለባቸው በመስማማት ከኡክይደር ሰዎች ጋርም ስምምነትን ፈጠሩ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተቡክ 18 ቀናትንም ቆዩ። ከዚያም ምንም ውጊያ ሳይገጥሙ ወደመዲና ተመለሱ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደመዲና በተመለሱ ጊዜም አላህ ያን መናፍቃን የገነቡትን መስጂድ አድ-ዲራራን ያፈርሱ ዘንድ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፡-«*እነዚያም (ምእምናንን) ለመጉዳት፣ከሀደትንም ለማበርታት፣ በምእምናንም መካከል ለመለያየት፣ ከአሁን በፊት አላህንና መልክተኛውን የተዋጋውንም ሰው ለመጠባበቅ መስጊድን የሠሩት (ከነሱ ናቸው)። ... »* (አት-ተውባ 9፡107)

በዚሁ መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂዱን አፈራረሱት። ይህም እርሳቸው ራሳቸው የተሳተፉበት የመጨረሻው ዘመቻቸው ሆነ።

የልዑካን ቡድኖች

ከተቡክ ዘመቻ በኋላ ብዙ ጎሳዎች በልዑካን ቡድኖቻቸው አማካኝነት ኢስላምን ተቀበሉ። ስለሆነም ይህ 9ኛው ዓመተ ሂጅራም የልዕካኖች ዓመት ተብሎ ተሰየመ። የተለያዩ ጎሳዎች እስልምናን መቀበላቸውን እያወጁ በፍጥነት ወደነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይመጡ ጀመር። ከነርሱም መካከል የበኑ ተሚም ልዑክና መሪያቸው ዐጣሪድ ኢብን ሓጂብ አት-ተሚሚይ፣ የጠይእ ልዑክ እና መሪያቸው ዘይድ አል-ኸይል፣ የዐብዱል ቀይስ ልዑክ እና መሪያቸው አል-ጃሩድ አል-ዐብዲይ እንዲሁም የበኑ ሐኒፋ ልዑክ ሲሆኑ፣ ከነርሱም ውስጥ ሐሰተኛው ሙሰይሊማ፣ ያ የኋላ ኋላ ነብይነት ይገባኛል በሚል የሞገተው ግለሰብ ይገኙበት ነበር።

የአቡበክር ሐጅ

ከሂጅራ በኋላ በ9ኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለነዚያ ሐጅ ለሚያደርጉ ሰዎች አቡ በክርን መሪያቸው አድርገው ላኳቸው። ለሰዎችም የሐጅ ሥርዓትን አቋቋሙ። እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰዎቹ የሱረቱ አት-ተውባ የመጀመሪያዎቹን አንቀጾች ያነቡላቸውና የሺርክ ባለቤቶችንም ስምምነቶች ወደዚያ ይወረውሩላቸው ዘንድ ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብን ላኳቸው። እንደዚሁም አንድም አጋሪ (ሙሽሪክ) ከዚህ ዓመት በኋላ ሐጅ እንዳያደርግ መከልከሉንና ልክ በጃሂሊያው ዘመን ሲያደርጉ እንደነበረውም (በከዕባ ዙሪያ) እርቃን ሆነው ጠዋፍ ማድረግ መከልከሉን በማስመልከት በሰዎች መካከል ያውጁ ዘንድ (ላኳቸው)።

የሱንበት ሐጅ

ከሂጅራ በኋላ በአስረኛው ዓመት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሱንበት ሐጃቸውን (ሐጅ-ጀቱል ወዳዕ) አደረጉ። ከተለያዩ ጎሳዎችና ከተማዎች የተውጣጡ ሙስሊሞች፣ ቁጥራቸው ከአንድ መቶ ሺ በላይ ሲሆኑ፣ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ወጡ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) የሐጅ አደራረግ ሥርዓትን አስተማሯቸው። ቀጣዩን የቁርኣን አንቀጽ በማንበብም በዐረፋ ዕለት ኹጥባ አደረጉ፡- « ...*ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ምላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።* » (አል-ማኢዳ 5፡3)

እንደዚሁም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለታዳሚዎቻቸው አሁን ዲኑ መሟላቱን አሳውቋቸው። እነርሱንም በአላህ መጽሐፍና በመልዕክተኛው ሱንና አማካኝነት የመጣውን ነገር አጥብቀው እንዲያዙ መከሯቸው። በነርሱ መካከልም ደማቸውን፣ ገንዘባቸውንና ክብራቸውን እርም አደረጉ። ይህም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የስንብት ምክር መካከል ነበር።

የኡሳማ መላክ

በወርሃ ሰፈር ውስጥ ከሂጅራ በኋላ በአስራ አንደኛው ዓመት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሩሞች ጋር ለመዋጋት የጦር ሠራዊትን አዘጋጁ። ኡሳማ ኢብን ዘይድንም የሠራዊቱ መሪ አድርገው ሾሙ። የጦር ሠራዊቱም ለጉዞ ወጣ። አል-ጁርፍ ዘንድም ካምፓቸውን ቀለሱ። ከዚያም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመታመማቸው ዜና ደረሳቸው።

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎች ማጠቃለያ

የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎችን፣ ልዑካንና ሠራዊትን የሚመለከት ማጠቃለያ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያካሄዷቸው ዘመቻዎች፣ ልዑካንን የመላክ ሥራዎችና ጦርነቶች በሙሉ የተካሄዱት ከሂጅራ በኋላ በአስር ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነበር። ያደረጉትን ጦርነትና የላኩትን ልዑካን ብዛት በተመለከተ እነርሱ በግምት ወደ ስድሳ የሚሆኑ ነበሩ። ያካሄዱትን ዘመቻዎች ብዛት በተመለከተ ሀያ ሰባት ነበሩ። ከነዚህ ዘመቻዎች መካከልም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው በዘጠኙ ውስጥ ተሳትፈዋል። እነዚህም በድር፣ ኡሑድ፣ አል-ኸንደቅ፣ አል-ቁረይዛ፣ አል-ሙስጠሊቅ፣ ኸይበር፣ የመካ መከፈት (አል-ፈትሕ)፣ ሑነይን እና ጧኢፍ ሲሆኑ፣ ከነዚህም ዘመቻዎች መካከል ከፊሎቹን የሚመለከቱ የቁርኣን አንቀጾች ወርደዋል።

በቁርኣን የተገለጹ ዘመቻዎች

የበድር ዘመቻ፡- ሱረቱል አንፋል የወረደችው በዚህ ምክንያት ነበር። ምዕራፍዋም ሱረቱ በድር በመባል ተሰይማለች።

የኡሑድ ዘመቻ፡- የሱረቱ ኣሉ ዒምራን የመጨረሻው ክፍል፣ እንዲህ ከሚለው የጎያሉ አላህ ቃል አንስቶ *«ለምእምኖቹም ለውጊያ ሥራዎችን የምታዘጋጅ ኾነህ ከቢተሰብህ በማለዳህ ጊዜ (አስታውሰ)። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።»* - (3፡ 121) - እስከ ምዕራፉ መቋጫ አቅራቢያ የወረደችው ይህንኑ ዘመቻ አስመልክታ ነበር።

የኸንደቅ፣ የቁረይዛና የኸይበር ዘመቻዎች፡- የሱረቱል አሕዛብ የመሀለኛው ክፍል የወረደው እነዚኑ ዘመቻዎች አስመልክቶ ነበር።

የበኑ አን-ነዲር ዘመቻ፡- ሱረቱል ሐሸር የወረደችው ይህንኑ ዘመቻ አስመልክታ ነበር።

የአል-ሑደይቢይ-ያ፣ የኸይበርና የአል-ፈትሕ (የመካ መከፈት) ዘመቻዎች፡- ሱረቱል ፈትሕ እን አን-ነስር እነዚኑ ዘመቻዎች አስመልክተው የወረዱ ነበሩ።

የተቡክ ዘመቻ፡- ከሱረቱ ተውባ የሆኑ የተወሰኑ አንቀጾች የተገለጹት ይህንኑ ዘመቻ በማስመልከት ነበር።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቆሰሉት በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን ያም የኡሑድ ዘመቻ ነበር። በበድር፣ በኡሑድና በሑነይን ዘመቻዎች ላይ መላኢኮች ከርሳቸው ጋር ሆነው ተዋግተዋል። በኸንደቅ (የጉድጓዱ) ዘመቻ ዕለት መላኢኮች ወርደዋል።ሙሽሪኮችም ተንቀጥቅጠዋል። በረቀቀ ሁኔታ ተወግተው ተሸንፈዋል። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) በሙሽሪኮች ላይ ጠጠርን ወርወሩ። ስለሆነም እነርሱ ሸሹ። ታላቅ ድል የተገኘው በሁለት ዘመቻዎች ላይ ሲሆን እነርሱም በድርና ሑነይን ነበሩ። ‹አል-ሚንጀኒቅ› የተባለውን የጦር መሣሪያ ማስወንጨፊያን በመጠቀም የተዋጉት በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን እርሱም የጧኢፍ ዘመቻ ነበር። በተቆፈረ ቦይ አማካኝነት ምሽግን የያዙትም በአንድ ዘመቻ ላይ ብቻ ሲሆን እርሱም የአሕዛብ ዘመቻ ላይ ነበር። ይህንኑም ያመላከታቸው ሰልማን አል-ፋሪሲ (ረ.ዐ) ነበር።

መታመማቸውና መሞታቸው

መታመማቸውና መሞታቸው

ኃያሉ አላህ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዱንያ ላይ መቆየትን አልያም ከርሱ ጋር መገናኘትንና ጀነትን ይመርጡ ዘንድ ምርጫን አቀረበላቸው። ስለሆነም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጌታቸው ጋር መገናኘትንና ጀነትን መረጡ። ከዚያም በፅኑ ታመሙ። በዓኢሻ ቤት ውስጥ ያስታምሟቸው ዘንድ ከሚስቶቻቸው ፈቃድን ጠየቁ። እነርሱም ይህንኑ ፈቀዱላቸው። መስጂድ ገብተው ሰዎችን ማሰገድ በተሳናቸው ጊዜ አቡ በክር ሰዎችን እንዲያሰግዱ አዘዙ። ይህም ከርሳቸው በኋላ አቡ በክር ተተኪያቸው እንደሚሆኑ አንዳች ማረጋገጫን የሰጠ (ክስተት ነበር)።

በዕለተ ሰኞ፣ በ12ኛው ቀን፣ በወርሃ ረቢዑል አው-ወል፣ ከሂጅራ በኋላ በ11ኛው ዓመት ሰዎች የሱብሕ ሶላትን እየሰገዱ ሳሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደነርሱ ወጡ። እነርሱም እርሳቸውን እስከሚመለከቱ ድረስ መጋረጃው ተመለሰ፤ በሩም ተከፈተ። እናም ሶላታቸውን አሟልተው እንዲሰግዱ ምልክት ሰጧቸው። ለነርሱም ፈገግ አሉላቸው። ከዚያም ረፋዱ በበረታ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሕይወታቸው አለፈች። የርሳቸው ሕልፈትም አማኞች ላይ ከደረሱ መከራዎች ሁሉ እጅግ ከባዱ ሆነ። በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሞት የተነሳ ሙስሊሞችም እጅግ የበረታ ሐዘንን አዘኑ። ከዚያም ሰዎች ወደ አቡ በክር ተሰባሰቡና በተተኪነትም (በኸሊፋነትም) የታማኝነት ቃል ኪዳናቸውን ሰጧቸው። በርሳቸው ተተኪነት ዙሪያም ከሰዎች መካከል አንድም አልተቃወመም ነበር፤ ምክንያቱም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ በእስልምና የቀደማቸውንና በተቀሩት ተከታዮች ላይ ብልጫ ያለው ሰው ማን እንደሆነ ሰዎቹ ያውቁ ነበርና።

ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጸደ ገላቸው ታጠበና በሦስት ነጫጭ ልብሶች አማካኝነት ተከፈኑ። ከዚያም በዚያው በሞቱበት ቦታ ላይ የሙእሚኖች እናት የሆነችው የዓኢሻ ቤት ውስጥ ተቀበሩ። ይህም ነብያትን በተመለከተ የአላህ ሱንና ሲሆን እነርሱም የሚቀበሩት በሞቱበት ቦታ ላይ ነው። ሁለቱም የሰው ዘርና ጋኔኖች የጌታችንን ሶላትና ሰላምን በርሳቸው ላይ ያወርዳሉ። እኛም እርሳቸው አማናቸውን እንዳደረሱ፣ ተከታዮቻቸውንም እንደመከሩና በአላህም መንገድ ላይ ተገቢውን ትግል እንዳረጉ እንመሰክራለን። ስለሆነም ነብይ በተከታዮቹ ሳቢያ ከሚመነዳው በላይ ኃያሉ አላህ በተከታዮቻቸው ሳቢያ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አብዝቶ እንዲመነዳቸው እንለምነዋለን። ምስጋና ሁሉ የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ይገባ።

ማጠቃለያ

ሐስ-ሳን ኢብን ሣቢት (ረ.ዐ)፣ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ገጣሚ የሆኑት እንዲህ ብለዋል፡-

ጌታ ሆይ! እኛን ከነብያችን ጋር አንድ ላይ ሰብስበን
በምቀኞች ዓይኖች በተወደሰች ጀነት ውስጥ ስንሆን
በጀነቱል ፊርደውስ ውስጥ፣ እርሷንም ለኛ ጻፍልን
የሞገሱ ባለቤት፣ የልዕልናና የታላቅነትም ባለቤት አንተ ነህና
አላህና በዐርሹ ዙሪያ ያሉ በርሳቸው ላይ ሰለዋትን ያወርዳሉ
መልካሞቹም ለተባረከው አሕመድ ሰላምታቸውን ያደርሳሉ።

3ኛው ፈተና

ውሸት	እውነት	ጥያቄዎቹ
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ) ፍዮሎችን ማገዳቸው ትዕግስት እንዲኖራቸውና ለደካሞችም እንዲያዙ፣ እነርሱንም የመጠበቅ ኃላፊነት እንዲወስዱ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ ነበር
□	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 40 ዓመት ሲሞላ የነብይነት ብርሃኑ ከርሳቸው ላይ ደምቆ ነበር። አላህም ከርሱ በሆነ መልዕክት በዕለተ ጁምዓ ላይ አላቃቸው።
□	£.	ከቁረይሾች በኩል በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሲደርስ የነበረው ስቃይ ይበልጡኑ በረታ። እርሳቸውንና አህሉል በይትንም በአቡ ጣሊብ ተራራማ መንገድ (ሸለቆ) ውስጥ ለ3 ዓመታት አገቷቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕድሜያቸው 49 ዓመት ሲሞላ ከእገታው ሰብረው ወጡ።

1. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካ ውስጥ የተወለዱት፡- ሀ/ በዝሆን ዓመት ለ/ ከሂጅራ በፊት በ53 ዓመታት ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
2. መለኮታዊ ራዕዩ መገለጽ ሲጀምር፡- ሀ/ እርሳቸው ዘንድ ገለልተኝነት ተወዳጅ ተግባር ተደርጎ ነበር ለ/ የመጣው እንደ መልካም ሕልም ሆኖ ነበር ሐ/ ሁሉም ልክ ነው
3. መለኮታዊ ራዕዩ ስንት ደረጃዎች አለው? ሀ/ 5 ለ/ 7 ሐ/ 3
4. የደዕዋቸው እርከኖች፡- ሀ/ 2 ነበሩ ለ/ 3 ነበሩ ሐ/ 5 ነበሩ
5. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ አል-አቅሷ በሌሊቱ ክ/ጊዜ በነፍሳቸውና በሥጋቸው ተወሰዱ። ከዚያ ከሰማያት በላይ በ ..... ወደ ኃያሉ አላህ ተወሰዱ። አላህም አናገራቸው። አምስት ወቅት ሶላቶችንም ግዴታ አድርጎ ደነገባቸው። ሀ/ በሥጋቸው ለ/ በነፍሳቸው ሐ/ በሥጋቻውና በነፍሳቸው
6. በእስልምና ውስጥ የመጀመሪያው መስጂድ፡- ሀ/ አል-ሐራም ለ/ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ሐ/ አል-አቅሷ መ/ ቁባእ
7. የቂብላው አቅጣጫ የተቀየረው፡- ሀ/ በመካ ውስጥ ከሂጅራ በፊት ለ/ ከሂጅራ በኋላ በ2ኛው ዓመት ለ/ ከሂጅራ በኋላ በ3ኛው ዓመት
8. በወርሃ ረመዷን ውስጥ የተካሄደው የበድር ጦርነት በስንተኛው ዓመት ነበር? ሀ/ ከሂጅራ በኋላ በ2ኛው ዓመት ለ/ ከሂጅራ በኋላ 3ኛው ዓመት

አቡ በክር አስ-ሲድቅ	ዘይድ ኢብን ሓሪሓ	ቢላል ኢብን ረባሕ	ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ	በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ለማመን ቀዳሚዎቹ፡-
£	£	£	□	ከወንዶች
£	£	£	□	ከታዳጊዎች
£	£	£	□	ከአገልጋዮች
£	£	£	□	ከባሮች

7 ዓመት	ዐብደሏህ ኢብን ዐብዱል መጢሊብ	ወደ 8 ዓመት	ዐብዱል መጢሊብ	አቡ ጣሊብ	የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሳዳጊዎች፡-
£	£	£	£	£	ከእናታቸው ሞት በኋላ አያታቸው .....
£	£	£	£	£	አያታቸው ሲሞቱ ዕድሜያቸው .....
£	£	£	£	£	ከዚያም አጎታቸው ..... አሳደጓቸው
£	£	£	£	£	ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተረግዘው ሳሉ አባታቸው .... ሞቱ
£	£	£	£	£	እናታቸው ስትሞት ዕድሜያቸው ..... ነበር

1 ዘመቻ	9	27	60	10 ዓመት	ዘመቻዎቸውና ልዑካኖቻቸው፡-
£	£	£	£	£	ሁሉም ዘመቻዎችና ልዑካኖች የተካሄዱት ከሂጅራ በኋላ .... ዓመት ውስጥ ነበር
£	£	£	£	£	የጦራና የልዑካናቸው ቡድን ብዛት በግምት ..... ነበር
£	£	£	£	£	በጥቅሉ ..... ዘመቻዎች ተካሄደዋል
£	£	£	£	£	የተሳተፉባቸው ዘመቻዎች ብዛት ..... ነበር
£	£	£	£	£	የቆሰሉበት ዘመቻ ..... ነበር

ደስተኛ ሕይወትን ለመምራት የሚረዱ መንገዶች

ጸሐፊው፡- ዐብዱር ረሕማን ኢብን ናሲር አስ-ሲዕዲ (1307 – 1376 ዓ.ሂ)፣ በዘመናቸው እጅግ ጉልህ ከሆኑ የሙስሊም ልህቃን መካከል አንዱ ሲሆኑ፣ (በዕውቀታቸው) የኢስላማዊ ዕውቀትን መሠረተ ሐሳብ ከያዙ ኢማሞች መካከልም ተጠቃሹ ናቸው፡፡

ይህንኑ መጣጥፍን ያዘጋጁበት ምክንያት ቢኖር ሸይኹ ለሕክምናዊ ዓላማ (በ1373 ዓ.ሂ) ወደ ሊብናን በሚጓዙበት ጊዜ «ጭንቀትን እንዴት እንደምናቆምና ትክክለኛ ሕይወትን እንዴት መኖር እንደምንጀምር» የተሰኘውንና በዴል ካርኒጌ የተዘጋጀውን መጽሐፍ አንብበው በይዘቱም ስለተማረኩ ነበር፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ጭብጥን የያዘ መጽሐፍን ለማዘጋጀት በቁ፡፡ ቀጥሎ የሚቀርቡ 22 ነጥቦችም ወደ ደስተኛ ሕይወት ይመራሉ ተብለው በርሳቸው የተዘረዘሩ ናቸው፡-

1/ በኃያሉ አላህ ማመንና መልካም ተግባራትን መሥራት፡- እምነት ኃያሉ አላህ ባዘዘው ነገር ላይ ትዕግስት፣ ደስታና እርካታ እንዲኖርህ ወደዚያ ይመራሀል፡፡

2/ በንግግርና በተግባርም ለመላው ፍጡራን ደግ መሆን፤ ምክንያቱም መልካምነት መልካምነትን ያስገኛል፤ ክፋትንም ይገፈትራልና፡፡

3/ ራስን በመልካም ተግባራትና በጠቃሚ ዕውቀት ላይ ቢዚ ማድረግ፡- ይህም ልብን ስለሚያስጨንቁህ ነገሮች የማሰብ አሉታዊ ትኩረትህን ያዞርልሀል፡፡

4/ አስተሳሰብህን በዕለታዊ ሥራዎችህ አማካኝነት ቢዚ ማድረግ፡- ስለሆነም ባለፈው ነገር አታዝንም፤ ስለሚመጣውም አትጨነቅም፤ ምክንያቱም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጭንቀትና ከሐዘን በአላህ ይጠበቁ ነበርና፡፡

5/ አላህን በማውሳት ላይ ተጨማሪ ማውሳትን ማድረግ፡- ምክንያቱም አላህን አብዝተው ማውሳት ለልብ እርካታንና ስክነትን ያስገኛልና፡፡

6/ የአላህን የሚታዩና የማይታዩ (ግልጽና ስውር) ፀጋዎችን መዘርዘር፡- ምክንያቱም ይህ ምስጋናን የሚያስገኝና ትካዜንም የሚያስወግድ ተግባር ነውና፡፡

7/ ካንተ በታች ያለውን ሰው መመልከት ላለህ ነገር አላህን እንድታመሰግን ሲያደርግህ፣ በሌለህ ነገርም ከመተከዝና ከማዘን ያድንህል፡፡

8/ ያለፈውን ነገር መርሳት፤ ምክንያቱንም ያለፈውን ነገር ዳግም መልሰህ ልታገኘው አትችልምና፡፡ ስለሆነም ራስህን በዚያ ላይ ቢዚ ማድረግ ትርጉም የለሽና ከንቱነት ነው፡፡

9/ ወደ አላህ ዱዓ ማድረግ፡- ለምሳሌ ያህል ኃያሉ አላህ እምነትህን፣ ዓለማዊ ጉዳዮችህንና የቀጣዩ ዓለም ጉዳዮችህንም እንዲያስተካክልልህ (እንዲያሳምርልህ) መለመን - ይህም ልክ በሐዲሥ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ነው፡፡

10/ በአደጋ ጊዜ እጅግ ከባድ የሆነውንም ጉዳት መጠበቅ፤ ምክንያቱም ከደረሰው በላይ የባሰ መጥፎ ነገር ሊከሰት እንደሚችል ማሰብ በአነስተኛ ጉዳት ሳቢያ የመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖን ይቀንሳል፡፡

11/ በከንቱ ስሜትና በምናባዊነት ተገፋፍተው ከአቅም በላይ አለማሰብ፤ ምክንያቱም ከንቱ ስሜት መጥፎ አስተሳሰቦችን ያመርታል፤ አንተም በአሉታዊነት እንድትሞላ ያደርግሀል፤ ይህም የጭንቀትና የሕመም መንስኤ ይሆናል፡፡

12/ በአላህ ላይ መተማመንና በርሱም ላይ መመካት፡- «በአላህ ላይ ለሚመካ ሰው አላህ ለርሱ በቂው ነው፡፡» (65፡3)

13/ የሌሎች ሰዎችን ደካማ ጎኖች መቀበልና እነርሱ በሚያደርሱብህ ጉዳይ ላይ ትዕግስት ማድረግ፡- እያንዳንዱ ሰው ደካማ ጎን (ጉድለት) አለው፤ ወይም እኛ የማንወዳቸውን ነገሮች ሊፈጽሙብን ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ከነርሱ አሉታዊ ጎን ይልቅ አዎንታዊ ጎናቸውን ተመልከት ተገቢ ነው፡፡

14/ ራስን በማይረቡ ነገሮች ቢዚ አለማድረግ፡- ልክ አንተ ከአደጋዎች ጋር መኖር እንደማትፈልግ ሁሉ ራስህን በከንቱ ጉዳዮችም ማስጨነቅ የለብህም፡፡ ራስህን ከከንቱ ጉዳዮች የማራቅ ምርጫውም በእጅህ ነው፡፡

15/ ሕይወት አጭር ናት፡፡ እናም እውነተኛው ሕይወት (ምንም እንኳን) አጭር ብትሆንም የደስታና የእርካታ ሕይወት ናት፡፡ ስለሆነም ሕይወትን በጭንቀትና በሐዘን (የበለጠ) አታሳጥራት፡፡

16/ ለአብዛኞቹ ስጋቶችህ ምንም የተጨበጠ ማስረጃ የለህም፡፡ በእውነቱ አንተ የምትጨነቅላቸው አብዛኞቹ ነገሮች ገና አልተከሰቱም፡፡ ስለሆነም ገና ያልተከሰቱ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የሚችሉትን እንዲያደበዝዙ አትፍቀድላቸው፡፡

17/ ሰዎች በሚያወሩት ነገር አትጨነቅ፤ ምክንያቱም የሰዎች ሐሜት በራሳቸው ላይ ነውና፡፡ የሆነ ሆኖ አንተ በነርሱ ራስህን ቢዚ ካደረክ፣ ከዚያም ልክ እነርሱ ራሳቸውን እየነዱ እንዳሉት ሁሉ አንተም ራስህን ትነዳለህ፡፡

18/ ሕይወትህ አስተሳሰቦችህን ትከተላለች፡፡ ስለሆነም አስተሳሰቦችህ ለሃይማኖትህ ወይም ለዓለማዊ ጉዳዮችህ ጠቃሚ ከሆኑ፣ ከዚያም አንተ ደስተኛ የሆነ ሕይወት ይኖርሀል፡፡ የረካህም ትሆናለህ፡፡ አለበለዚያ ግን ተቃራኒው ይከሰትብሀል፡፡

19/ ለነዚያ ካንተ ላይ መብት ላላቸው ሰዎች ወይም ለነዚያ ባንተ ላይ መብት ለሌላቸው ሰዎችም መልካም ነገርን ስትሠራ ከነርሱ ምስጋና አትጠብቅ፡፡ የዚያኔ ይህ ባንተና በአላህ መካከል የሚደረግ ንግድ ይሆንልሀል፡፡ ስለሆነም የሰዎች ምስጋና ካንተ መቅረት አያስጨንቅህ፡፡

20/ በዚያ አንተን ተጠቃሚ በሚያደርግህ ነገር ላይ ራስን ቢዚ አድርግ፤ ምክንያቱም ጎጂ ጉዳዮች ትካዜንና ሐዘንን ያስከትላሉና፤ ስለሆነም በጠቃሚ ተግባራት በኩል እገዛን ፈልግ፡፡

21/ ጉዳዮችህን በወቅታቸው ለመጨረስ ትጋ፤ ምክንያቱም የዘገዩ ጉዳዮች ከመጪ ጉዳዮችህ ጋር ሆነው ባንተ ላይ ይወዘፉና አንተም በነርሱ አስቀድመህ የተዋጥክ ትሆናለህ፡፡

22/ ጉዳዮችህን በቅደመ ተከተል አስቀምጣቸው፤ ከዚያም እጅግ ጠቃሚ ከሆነ ጀምር፡፡ ከዚያም ቀጥሎ በጣም አስፈላጊ የሆነውን አስከትል፡፡ ከሙያም ረገድ ያንን አንተ ይበልጥ ያዘነበልክብትን ምረጥ፡፡ በዚህም አንተ በብስጭት ወይም በስልቹነት ውስጥ አትወድቅምና፡፡ እንደዚሁም ምክርን ጠይቅም፤ ምክንያቱም ምክርን ስትጠይቅ አትፀፀትምና፡፡

ማውጫ

- መግቢያ 3
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መገለጫ ባህሪያት 5
- የመጀመሪያው ፈተና 13
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምሪት 15
- ሁለተኛው ፈተና 20
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መለያ ባህሪያት 23
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች 26
- ከነብይነታቸው በፊት 31
- የራዕዩ ጅማሮ 33
- የመካው ምዕራፍ 36
- የመዲናው ምዕራፍ 39
- የዘመቻዎቻቸው አጭር ማጠቃለያ 46
- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መታመምና መሞት 47
- ሦስተኛው ፈተና 48
- ደስተኛ ሕይወትን ለመምራት የሚረዱ መንገዶች 51
- ማውጫ 53

مترجم باللغة الأمهرية
ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ

(قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ
أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ۖ وَسُبْحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ)

[سورة يوسف 108]

ሙሐመድ ሆይ! እንዲህ በላቸው፤ "መንገዴ ይህች ናት!
በግልጽ ማስረጃ ላይ ሆኜ ወደ አላህ እጠራለሁ።
የተከተለኝም ሰው እንዲሁ በማስረጃ ይጣራል።
ጥራትም ለአላህ ይገባው፤ እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም"
(ዩሱፍ 108)

شرح الدروس المهمة لعامة الأمة

ሰሁሉም ሙስሊም አሳሳቢ የሆኑ ትምህርቶች ማብራሪያ

ሰሁሉም ሙስሊም አሳሳቢ የሆኑ ትምህርቶች ማብራሪያ

تأليف فضيلة الشيخ:
عبدالعزيز بن عبدالله بن باز
شرح فضيلة الشيخ:
هيثم بن محمد جميل سرحان

ወሀፊ:
ሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ቢን ባዝ
ትንተና:
በሸይኽ ሀያሠም ሰርሐን
ትርጉም እና ህትመት:
አብነ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

www.sarhaan.net
www.attasseel-alelmi.com

የ “አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ” ማብራሪያ

በክቡር ሸይኽ:

ኢማም ዓብደል ዓዚዝ ቢን ዓብደላህ ቢን ባዝ

አላህ ይዘንለት መኖሪያውንም ያስፋለትና

ዝግጅት በክቡር ሸይኽ:

ሀይሠም ቢን ሙሓመድ ጀሚል ሰርሓን

በክቡር መስጅድ ነበውይ -ነባር- አስተማሪና የታእሲለል ዒልምይ ድረ ገፅ ሹም

http://attasseel-alelmi.com

ለሱም ለወላጆቹም ኪታቡ እንዲወጣ እገዛ ላደረገም ሁሉ አላህ መሃርታውን ይለግስ

ይህች እትም ለአላህ ሲባል ወቅፍ የተደረገች ነች

በፋጢማህ ቢንት ጀይላልይ ቢን ፉረይሓህ ልገሳ የታተመ – አላህ መሃርታውን ይለግሳት በሰፊው ጀነቱም ያስገባትና-

የመጀመሪያ እትም

መብቱ በህግ የተጠበቀ

ምናልባት ሸይኹ ካረጋገጡለት በኋላ በነፃ ለማደል ማተም
ወይም መተርጎም ለፈለገ ካልሆነ በቀር

ያግኙን:

islamtorrent@gmail.com

በመረጃ ሚኒስቴር ፍቃድ

የሸይኹ መግቢያ ማብራሪያ

ሸይኽ ኢማም ዑበይል ዓዚዝ ቢን ዑበይላህ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ፤ ፍፃሜ ለጥንቁቆች፤ የአላህ ሶለዋትና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ፣ በተከታዮቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን።

በመቀጠል፡

ይህች ብዙሃኑ ከኢስላም ማወቁ ግዴታ የሚሆንበትን የምትገልፅ አጠር ያለች ንግግር ነች። ስሟንም "አ-ድ-ዱሩሱ-ል- ሙሂማህ ሊዓመቲ ል ኡማህ" ብየ ሰይሜያታለሁ። *(አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ)*።

በሷ ሙስሊሞችን እንዲጠቅም፤ ከኔም ሊቀበለኝ ዘንድ አላህን እለምነዋለሁ እርሱ ቸርና ሊጋስ ነውና።

ዑበዱል ዓዚዝ ቢን ዑበይላህ ቢን ባዝ

ለምንድን ነው "አሳሳቢ ትምህርቶች"ን የምንማማረው?

ምክንያቱም ሸይኹም አላህ ይዘንላቸውና እንዳሏት አሳሳቢ ስለሆነች፤ ዑለሞችም የሚመክሩባት ስለሆነች።

እዚህላይ የሆነ ሰው "አዎ በርግጥ አሳሳቢ ነች፤ ነገር ግን ለብዙሃኑ ህዝብ ነው። እኔ ደሞ የቢቃሁ ተማሪ(ጧሊቡ ዒልም) እንደመሆኔ ደረጃየ ከብዙሃኑ ህዝብ ከፍ ያለ ነው።" ቢልስ

ምላሹ፡ በውስጧ ካለው (አውጣጥተን) እንጠይቀዋለን፤ መልሱን ካላገኘ ብዙሃኑ ህዝብ ከሱ የተሻለ ነው፤ ዒልም ፈላጊ ደግሞ መተናነስ፣ በዒልም ላይም ሆነ በዓሊሞች ላይ አለመኩራራት፣ በእውቀታቸው ሰሪ በሆኑ ዑለሞችም አካሄድ ሊጓዝ ነው የሚገባው።

በሶሒሕ ቡኻሪይ፡ ሙጃሂድ "(እልፍ ያለ) ሓያእ ያለውና ኩራተኛ እውቀትን ኢያገኝም" ብለዋል።

"አሳሳቢ ትምህርቶች" በምን ዙሪያ የምታጠኑትን ነች?

1. ደጋግ ቀደምቶች ቁርአን ከመቅራት፣ ከመሐፈዝ፣ ከማስተንተኑና ከመተግበሩ በኩል የነበራቸው አካሄድ
2. ስለኢስላም፣ ስለኢማን፣ ስለኢሕሳን፣ ስለተውሒድና ስለሽርክ አይነቶች ማብራሪያ
3. ስለሶላት ማብራሪያ
4. ስለወዱእ ማብራሪያ
5. በተደነገ ስነምግባር ስለማሹብረቅና በኢስላማዊ ስነስርዓት ስርዓትን ስለመያዝ
6. ከሽርክና ከአመፅ አይነቶች ስለማስጠንቀቅ
7. ሟችን ስለመሸኘት፣ እሱ ላይ ስለመስገድና እሱን ስለመቅበር

የመጀመሪያው ትምህርት

ዑለሞች ለምንድን ነው ኪታቦቻቸውን በቢስሚላህ የሚጀምሩት?

- በታላቁ ኪታብ፣ በነብያቶችና ብመመልዕክተኞች ከመመራት አንፃር
- “ጣጣ ኖሮበት በቢስሚላህ ያልተጀመረ ሁሉ የተቆረጠ ነው” የሚለውን ሓዲሥ ትርጉም ከመስጠት አንፃር፤ ዶሂፍ ቢሆንም
- አላህ ይዘንላቸውና ቀደምት ዑለሞን ከመከተል አንፃር
- በአላህ ስም በመጀመር በሚገኘው በረካ ከመቀናት አንፃር

ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና አጫጭር ሱራዎች

ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና ከአጫጭር ሱራዎች የተቻለውን ያክል፤ ከሱረቱ-ል ዘልዘላህ እስከ ሱረቱ-ን-ናስ አቀራሩን በማስያዝና በማስተካከል፤ መረዳቱ ግድ ለሚለውም ደሞ ማብራሪያ።

ማብራሪያ

ልክ የቀደምቶች አካሄድ እንደነበረው አላህ ይዘንለትና የኢብኑ ሰዕዲን ከመሰሉ አጫጭር የተፍሲር ኪታቦች ማብራሪያቸውን ከመቅራትም ጋ አስር አንቀፆችን በየቀኑ መሓፈዝ ይገባል።

አንድ የሚልም ፈላጊ የሆነ ሰው በየትኛው የተፍሲር ኪታብ ይጀምር?

አንድ እውቀት ፈላጊ የሆነ ሰው አላህ መሃርታውን ይለግሰውና በሸይኽ ዑበዱራሕማን ሰዕዲ “ተይሲሩ-ል ከሪሙ ራሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላሚ-ል መናን” ቢጀምር ይመከራል።

ለምን?

- ዑለሞች በሱ ከሰጡት ምክርና ሃሳብ አንፃር
- አጠር ያለ እንደመሆኑ ጀማሪ ሊቀራው ተመራጭ ነው።
- አገላለፁ አጠር ያለ፣ ቀላል፣ ግልፅና ድብስብስነት ስለሌለበት
- በአላህ ፍቃድ በቁርአኑ በመስራት ላይ ስለሚያግዝ
- አላህ ይዘንለትና ሸይኹ በተውሒድ ላይ መሰረት ስለሚያስይዝ



ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ { መልክተኛውም «ጌታዬ ሆይ! ሕዝቦቼ ይህንን ቁርኣን የተተወ ነገር አድርገው ያዙት» አለ።} (አል-ፉርቃን 30) የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል "ከዚህ መሰረት" ማለትም (በሓዲሡ ከተወሳው ግለሰብ) ከዝርያውና ከቤተሰቡ "ቁርአን እየቀሩ ከጉሮሯቸው የማይወርድ፤ የኢስላም ጓዶችን እየገደሉ የጣኦት ጓዶችን የሚተው፤ ከውርወራው ብርታት አንፃር የተወረወረ ቀስት ከተወረወረበት እንደሚሾልከው እነርሱም በዛ መልኩ ከኢስላም የሾለኩ ናቸው፤ እኔ ባገኛቸው ኖሮ ልክ የዓድ ህዝቦች እንደጠፉት ነበር የማጠፋቸው።"

ከ የእውቁ ዓብዱራሕማን አስ-ሰዕዲይ አላህ ይዘንትለና "*ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ራሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን*" የተወሰኑ ቅንጫቢዎችና ጥያቄዎች

[የሱረቱል ፋቲሓ ተፍሲር፤ ሱራዋ መክይ ነች]

{መክይ፡ ሲባል ነብዩ ﷺ ከመካ ወደ መዲና ሂጅራ ከማድረጋቸው በፊት የወረዱ ሱራዎችን ማለት ሲሆን **መደንይ፡** ደግሞ ከ የነብዩ ﷺ ከመካ ወደ መዲና መሰደት በኋላ የወረዱ ሱራዎችን ማለት ነው።}

(በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (1) ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው። (2) እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ (3) የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው። (4) አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን። (5) ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። (6) የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን፤ በሉ)። (7))

---

(1) ማለትም: በመላው ከፍ ያለው አሏህ ስም ሁሉ እጀምራለሁ። ይህም "ኢስም" የሚለው ቃል በዓረብኛ ቋንቋው መደበኛ ነጠላ ቃል (ኢስሙን ሙፍረድ) በመሆኑ እያንዳንዱን የአሏህን መልካም ስም ሁሉ ያጠቃልላል። "**አሏህ**" በአምልኮ ሊነጠል የሚገባው ተመላኪው አምላክ ነው። ይህም ካለው የአምላክነት መገለጫ ባህሪ አንፃር ነው። ሁሉም ደሞ ምሉእ የሆኑ ባህሪያት ናቸው። **"እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ"** እነኝህ ህይወት ያለውንም ጭምር ሁሉ ያካለለች የሆነችዋ ባለ ሰፊና ታላቅ እዝነት ባለቤት ወደሆነው ከፍያለው አሏህ አዛኝነት የሚጠቁሙ ሁለት ስያሜዎች ናቸው።ይህችን እዝነቱን ለነዚያ ነብያቶቹንና መልዕክተኞቹን ለሚከተሉት ጥንቁቆች ፅፏታል፤ ለነኝህ ልቅ የሆነው እዝነቱ ያላቸው ሲሆን ከነሱ ውጭ ያለው ከሷው የተወሰነ ድርሻ አላቸው።

እወቅ! በቀደምቶችና ኢማሞቻቸው ዘንድ ወጥ በሆነ መልኩ ከሚስማሙባቸው መርሆዎች መካከል በአሏህ ስምና ባህሪያት እንዲሁም ተያያዥ ህጎች ማመን ነው። ለምሳሌ "ራሕማን" መሆኑንና "ረሒም" (ሁሉን አቀፍ ርኅሩህና በጣም አዛኝ) መሆኑን ሲያምኑ እሱ የሚገለፅባት የሆነችው ከሚታዘንለት ጋ በተሰሰረችው አይነት እዝነት፤ እያንዳንዷ ፀጋ ከእዝነቱ ፋናዎች አንዷ በመሆኗም ያምናሉ። በሌሎች ስያሜዎችም እንዲሁ (መልዕክቱን ተቀብለው ያምናሉ) ማለት ነው።

አል-ዓሊም (ሁሉን አዋቂ) ስለሚለው ስያሜም የሚባለው 'እንዲሁ ሁሉንም የሚያውቅ የእውቀት ባለቤት ነው' ነው። "ቀዲር" (ሁሉን ቻይ) ነው ስንልም 'እንዲሁ በሁሉም ነገር ላይ የሚችል የሆነ ቻይ ነው' ማለት ነው።

(2) "ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው..." ይህ በምሉእነት ባህሪያቱ፣ በችሮታ እና ፍትህ መካከል የሚሽከረከሩ በሆኑት ድርጊቶቹ አሏህን ማወደስ ነው፤ በየትኛውም መልኩ የተሟላ ውዳሴ ለሱው ነው።

(3) **"... የዓለማት ጌታ ለኾነው።"** ጌታ፡ መላው አለምን የሚንከባከብ ነው፤ ማለትም ከሱ ውጭ ያለውን ሁሉ ማለት ሲሆን ያም እነሱን የፈጠረ፣ አስፈላጊውን ትጥቅ ሁሉ ያሟላላቸው፣ ቢያጢት ህልውና የማይኖራቸው አይነት ታላላቅ ፀጋዎችን የዋለላቸው በመሆኑ ነው። እነሱ ዘንድ ያለች የትኛዋም ፀጋ ከታላቁ አሏህ ነች።

አሏህ ፍጡራኖቹን የሚንከባከበው በሁለት አይነት አኳኋን ነው: ጥቅል እና ልዩ በሆነ መልኩ።

ጥቅል የምንለው ፍጡራኖቹን መፍጠሩ፣ ሲሳይ መለገሱ፣ ዱኒያ ላይ ላላቸው ህልውና ለሚበጃቸው ነገር መምራቱ ነው።

ልዩ የምንለው ደግሞ ለወዳጆቹ ለይቶ በሚያደርግላቸው በእምነት ይንከባከባቸዋል፤ ለሷው ይገጥማቸዋል፤ የተሟሉ ያደርጋቸዋል፤ በእርሱ እና በእነርሱ መካከል ግርዶሽ ሊሆኑ የሚችሉ መሰናክሎችንና እንቅፋቶችን ይመክትላቸዋል። ተጨባጩም ለመልካሙ ሁሉ በመግጠምና ከመጥፎው ሁሉ በመጠበቅ ነው። ምናልባትም አብዛኞቹ የነብያት ዱዓዎች "ጌታየ!" በሚል ቃል የተቆራኘበትም ሚስጥር ለዚሁ ይሆናል። የሚፈልጉት ነገር ባጠቃላይ በሱ ልዩ ጌትነት ስር ያለ ነውና። **"... የዓለማት ጌታ ለኾነው።"** የሚለው ቃሉ በመፍጠሩ፣ በማስተናበሩ፣ ፀጋን በመዋሉና ባለው የተሟላ መብቃቃት እንዲሁም አለም ሁሉ በየትኛውም መልክና ሚዛን ወደሱ ያለውን ሙሉ በሙሉ ፈላጊነት ይጠቁማል።

(4) "የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።" ባለቤት፡ የሚባለው የባለቤትነት ማንነት ያለው ሲሆን ከፋናዎቹም ማዘዝና መከልከል፣ መመንዳትና መቅጣት መቻል፤ በባለቤትነቱም ላይ በፈለገው መልኩ መሆን መቻል ከፋናዎቹ ነው። ባለቤትነቱን ታዲያ የገለፀው ከፍርዱ ቀን ጋ በማያያዝ ነው። ያም የትንሳኤ ዕለት ነው። የሰው ልጆች በመልካምም ይሁን በክፉው ስራቸው የሚመነዱበት ቀን፤ ምክንያቱም የዛን እለት የንግስናው፣ የፍትሁና የጥበቡ ሙሉነት፤ የፍጡራን ባለቤትነት መቋረጥ በተሟላ መልኩ ግልፅ የሚሆንበት ቀን ነው። ብሎም የዛን `ለት ነገስታትና እረኞች፣ ጨዋ እና ባሪያዎች እንኪ እኩል ሆነው፤ ሁሉም ለታላቅነቱ አጎብድደው፤ ለልቅናው ተናንሰው፤ ፍርዱን በመጠባበቅ፤ ምንዳውን ተስፋ አድርገው፤ ቅጣቱን ሰግተው፤ የሚጠባበቁበት ቀን ነው። ለዚህም ነው ለየት አድርጎ ያወሳው እንጅ የትንሳኤ ቀንም ይሁን የሌላው ቀን ባለቤት እርሱው ነው።

(5) **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** የሚለው ቃሉ በአምልኮና እገዛን በመሻት እንነጥልሃለን ማለት ነው። ምክንያቱም እንደዓረብኛ ቋንቋ ስዋስዋዊ አገባቡ ድርጊት ተቀባዩ(መቅደም ያለበት)ን ማዘግየት ገደብን ነው የሚጠቁመው። ማለትም ተቆራኝቶ የመጣው ፍርድ ለተወሳው የሚሆንና ከሱ ውጭ ካለው ደግሞ የሚያወግዝ ነው። ልክ እናመክልሃለን ካንተ ውጭ ሌላን ሳናመልክ፤ እገዛ እንጠይቅሃለን ካንተ ውጭ ሌላን እገዛ ሳንጠይቅ እንደማለት ነው።

አምልኮን እገዛ ከመጠይቅ ማስቀደሙ ጥቅል የሆነውን ልዩ ከሆነው ማስቀደምና ከባሮቹ መብት በፊት በራሱ መብት ቅድሚያ ለማሳሰብ ያክል ነው።

ዒባዳ (አምልኮ)፡ የሚለው ቃል **"ከጉልሁም፣ ከድብቁም፣ ውጪዊም ይሁን ውስጣዊ፣ ከንግግርም ይሁን ከተግባር አሏህ የሚወደውንና የሚደሰትበትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ነው።"** እገዛን መጠየቅ 'ኢስቲዓና' ደግሞ **"ጥቅምን በማምጣትም ይሁን ክፋትን በመመከት በኩል እውን እንደሚያደርገው ተማምኖ አሏህ ላይ መደገፍ ነው።"**

አሏህን ማምለክና በሱም መታገዝ የዘላለማዊ ስኬትና ከአጠቃላይ ክፋት የመዳን መንገዱ ነው። ከሁለቱ ውጭ ለስኬት የሚያደርስ ምንም አይነት መንገድ የለም። አምልኮ አምልኮ የምትሆነው ከነብዩ ﷺ የተያዘች እና የአሏህ ፊት የተፈለገባት ስትሆን ብቻ ነው። አምልኮ አምልኮ ልትሆን የምትችለው በነኝህ ሁሉቱ መሰረቶች ላይ ነው። በአሏህ መታገዝ በአልምኮው ሊካተት የሚችል ከመሆኑም ጋ ከአምልኮ በኋላ መወሳቱ ባርያ በየትኛውም አምልኮው በታላቁ አሏህ መታገዝ ለሱ ካለው አስፈላጊነት አንፃር ነው። አሏህ ካላገዘው ትእዛዛትን መፈፀምና ክልክላቶችን መራቅን አይነት የሚፈልገው ነገር (እንኳ) አይከሰትለትም።

ከዚያም በማስከተል ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ አለ፡

(6) "ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።" ወደ ቀጥተኛው መንገድ ጠቁመን፤ አቅናን ግጠመን ማለት ነው። ያም ብሩህ የሆነ ወደ አሏህና ወደ ጀነት የሚያደርሰው መንገድ ነው። እሱም እውነትን አውቆ በሱው መስራት ነውና ወደ መንገዱ ምራን፤ በመንገዱም ላይ ምራን። ወደ መንገዱ መመራት በጥቅሉ ዲነል ኢስላምን አጥብቆ መያዝና ከሱም ውጭ ያለውን ሃይማኖት መተው ሲሆን በመንገዱ ላይ መመራት ደሞ ከእውቀትም ሆነ ከተግባር አንፃር በእያንዳንዱ የሃይማኖቱ ዝርዝር ጉዳይ መመራትን የሚያጠቃልል ነው። ይህ ዱዓእ እጅግ ጥቅል ከሆኑና ለባሪያ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ ዱዓዎች መካከል ነው። ስለዚህም ይህ ዱዓእ ለሰው ልጅ ካለው አስፈላጊነት አንፃር በሶላት በእያንዳንዱ ረከዓ ላይ መለመኑ ግድ የሚለው ነው።

(7) ይህ መንገድ **"የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን..."** ከነብያቶች፣ ከሲዲቆች፣ ከሸሂዶችና ከሷሊሖች የሆኑትን መንገድ ምራን። እንደአይሁዶች ያሉትን እውነትን አውቀው በመተው የጠመሙትን **"...የተቆጣህባቸውን..."** እንዲሁም እንደክርስትያን ያሉትን እነዚያ ባለማወቅና በመሃይምነት እውነቱን ስተው **"የጠመሙትን" ም "...ሳይሆን..."** ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።

ይህች ሱራ ይዘቷ አጭር ከመሆኗም ጋ (በመልዕክት ደረጃ) ሌላ ሱራ ያላካለለችውን አካልላለች።

በመሆኑም ሶስቱንም የተውሒድ አይነቶችን አካትታለች: *ተውሒደል-ሩቡቢያህ* (የጌትነት አሃዳዊነቱ) **"የአለማት ጌታ"** በሚለው ስር ይገኛል፤ *ተውሒደል-ኢላሂያህ* (የአምላክነት አሃዳዊነቱ) አሏህን በአምልኮ መነጠል ማለት ሲሆን **"ለአሏህ"** በሚለውና **"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** በሚለው ቃል ስር ይገኛል፤ እንዲሁም *ተውሒደል-አስማእ ወሲፋት* (በስምና ባህሪያቱ ያለው አሃዳዊነት) ሲባል ራሱን የገለፀባቸውን ወይም መልዕክተኛው የገለፁበትን የሙሉነት መገለጫ የሆኑ ባህሪያትን ውድቅ ባለማድረግ፣ ምሳሌ ባለመስጠትና ባለማመሳሰል ለሱው ማፅደቅ ነው። ይህም እንዳሳለፍነው **"ምስጋና ባጠቃላይ..."** በሚለው ላይ ይገኛል።

"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።" በሚለው ደግሞ ነብይነትን ማፅደቅ ይዛለች። ምክንያቱም ያ ከነብያዊ ተልዕኮ ውጭ የማይሳካ በመሆኑ ነው።

"የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው።" በሚለው ቃሉ ደግሞ በስራ መመንዳትን ማፅደቅ እና መመንዳቱም በፍትህ እንደሆነ እናገኛለን። ምክንያቱም (በአንቀፁ መሰረት) **"አድ-ዲን"** የተባለው ፍትሃዊ የሆነ ምንዳን ነውና።

በቀደር ማፅደቅንም አካትታለች፤ ቀደርያን እና ጀበርያን በተቃረነ መልኩ ባርያም (በፍቃዱ) የሚሰራ እንደሆነ ይዛለች።

ኧረ እንደውም **"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** በሚለው ቃሉ ላይ በአጠቃላይ የቢድዓ ሰዎች እና የጠመሙ ሰዎች ላይ ሁሉ ረድ(አፀፋዊ ምላሽ) በውስጧ ይዛለች። ይህንንም ያልነው የአንቀፁ ጭብጥ እውነትን አውቆ በሱው መስራት በመሆኑ ነው። የቢድዓ እና የጥመት ባለቤት ሁሉ ደግሞ ይህንኑ ነው የተቃረኑት።

"አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።" በሚለው ቃልም ስራን በአምልኮውም እገዛ በመሻቱም ኢኽላስን ለአሏህ ጥርት ማድረግን ይዛለች።

☼☼☼☼☼

የ"አየተል ኩርሲይ" ተፍሲር

"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።(255)"

(255) የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ ይህች አንቀፅ በውስጧ ካለው አሏህን ብቸኛ ማድረግ፣ ስለአስገኛችን አሏህ ከያዘችው ታላቅነትና የባህርይ ጥልቀት አንፃር ከቁርአን አናቅፆች ሁሉ የበላይ አንቀፅ መሆኗን ተናግረዋል። **"አሏህ"** አጠቃላይ የአምላክነት ማንነት ያለው፤ አምላክነትና አምልኮት ከሱ ውጭ ላለ የማይገባ መሆኑንና ከሱ ውጭ ያለ አካል አምላክነት እንዲሁም ከሱ ውጭ ያለው መመለኩ ውድቅ መሆኑን አሳወቀን። እሱ የመስማት፣ የመመልከት፣ የችሎታ፣ ፍላጎትና ሌሎችም በተሟላ መልኩ ፍፁም የህይወት ትርጉም መገለጫዎች የሆኑ ሁሉ ያለው **"ህያው"** ነው። እንዲሁም ራሱን ችሎ የቆመ አል-ቀዩም እና ከፍጡራኑ ሁሉ የተብቃቃ ነው፤ አጠቃላይ ድርጊታዊ የሆኑ ባህርያትን ሁሉ "**አል-ቀዩም**" የምትለዋ እንዳካተተችው ሁሉ ማለት ነው። እሱ አለች ለተባለች ነገር ሁሉ አለኝታዋ ነው፤ አስገኛት፣ አቆያት፣ ለህልውናዋም ለቆይታዋም የሚያስፈልጋትን ሁሉ አጣቀማት። የእርሱ ህያውና ራሱን ቻይነት ካለው ሙሉነት አንፃር **"ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።"** ምክንያቱም እንቅልፍና ማንገላጀት የሚጋረጠው ድክመት፣ መሳንና ብክለት ለሚያጋጥመው ፍጡር ነው እንጅ ለታላቅነት፣ ለኩራትና ለልቅና ባለቤት ለሆነው አሏህ የሚጋረጡበት አይደሉም። አጠቃላይ የሰማዩም የምድሩም ሁሉ ባለቤት መሆኑንም ተናገረ። ሁሉም የርሱው ተገዥ ባርያዎች ናቸው። ከዚሁ ሁኔታ ደግሞ መውጣት የሚቻለው የለም።

"በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።" (19:93) የተገዥው ሁሉ ባለቤት እርሱው ነው፤ የሙሉ ባለቤትነት፣ የማስተናበር፣ የስልጣን፣ የኩራት ባህሪያት ለሱው ነው።

ከስልጣኑ ሙሉነት አንፃር **"እርሱ ዘንድ የሚያማልድ"** አንድም የለም **"በፍቃዱ ቢሆን እንጅ"**። ጎምቱዎች (ታላላቆች) እና አማላጆች ሁሉ እስኪፈቅድላቸው ድረስ ለሽምግልናው ወደፊት የማይሉ ተገዥ ባርያዎቹ ናቸው። **"«ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው። የሰማያትና የምድር ሥልጣን የእርሱ ብቻ ነው። ከዚያም ወደእርሱ ትመለሳላችሁ» በላቸው።..."** (39:44) አሏህም ደግሞ ማንንም እንዲያማልድ አይፈቅድም ለተደሰተበት ካልሆነ በቀር፤ ደሞም አይደሰትምም የሱን ብቸኛ መደረግን እና መልዕክተኞቹን ﷺ መከተልን መሰረት በማድረግ ቢሆን እንጅ (በየትኛውም ነገር አይደሰትም)። እነኝህ መገለጫዎች የሌሉት ከሷው ድርሻ የለውም።ከዚያም ስለሰፊና አካታች ዒልሙ አሳወቀን፤ እሱ ማለቂያ በሌለው መልኩ ለወደፊቱ ፍጡራኖቹ የሚጠብቃቸውን **"በስተኋላቸውም ያለውን"**፤ እንዲሁም ገደብ በሌለው መልኩ ስላለፈውም ሁሉ እንደሚያውቅ አሳወቀን። አንዳችም ተደባቂ ነገር ከሱ የሚደበቅ አይደለም። **"(አላህ) የዓይኖችን ክዳት ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል።"** (ጋፊር 19)

አሏህ ዘንድ ስላለው መረጃና እውቀት (እንዲያውቁ) "በሻውም ነገር እንጂ" የሚያካብብ አንዳችም የለም። ከነኝህም አሏህ ያሳወቃቸው ሸሪዓዊ እና ተፈጥሯዊ እውነታዎች ይገኝበታል። ይህ ግን እጅግ ኢምንትና እዚህ ግባ የማይባል ተራ ነገር ነው፤ ከአስገኝው አሏህ እውቀትና መረጃ አንፃር። ልክ ከፍጡራኖቹ መካከል እጅግ በጣም አዋቂዎቹ መልዕክተኞቹና መላእክቶቹ በሚከተለው መልኩ እንዳሉት **"«ጥራት ይገባህ፤ ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም። አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተው ብቻ ነህና» (አሉ)።"** (2:32)

ስለታላቅነቱና ስለልቅናውም እንዲሁ አሳወቀን፤ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን መስፋቱ፣ እነርሱንም በውስጣቸው ያለውንም ህልውና ሁሉ በፍጡራኖቹ ላይ ባደረጋቸው አስባቦችና አለም አቀፍ ስርዓት ይጠብቃቸዋል። ይህ ከመሆኑም ጋ ካለው ሙሉ ታላቅነትና ችሎታ፤ በህግጋቶቹም ላይ ካለው ሰፊ ጥበብ አንፃር እነርሱን መጠበቁ የሚከብደው አይደለም። **"እርሱም የሁሉ በላይ..."** በአካሉም ከአጠቃላይ ፍጡራኑ ሁሉ፣ በባህሪው ታላቅነትም የበላይ እርሱው ነው፤ ፍጡራኑን ሁሉ ያሸነፈው የበላይ እሱው ነው፤ ህላዌው ሁሉ ያጎበደደለት፤ አስቸጋሪውም ሆነ ባርያው ሁሉ የሚዋረድለት ለሱው ነው። **"...የሁሉ ታላቅ ነው"** የታላቅነት፣ የኩራት፣ የልቅናና የግርማ ባህርያትን ሁሉ የሰበሰበ፤ ያ ልቦች የሚወዱት፤ ነፍሶች የሚያልቁት፤ ከባህሪው በኩል የቱንም ያክል ልቃ የሁሏም ነገር ታላቅነት ቢጠራቀም እንኳ ከልዕለ ሃያሉ ታላቅነት አንፃር የተከላሸች መሆኗን አዋቂዎች ያውቃሉ።

ይህን የመሰለውን ከመልዕክቶች ሁሉ እጅግ ምጡቅ የሆነን መልዕክት የሰበሰበች አንቀፅ በርግጥ የቁርአን አናቅፅ ሁሉ የበላይ መሆኗ ይገባታልም፤ መልዕክቷን በማስተነተንና በመገንዘብ መልኩ ላጠናትም ልቦናው በእርግጠኝነት(የቂን)፣ በእውቀትና በኢማን የተሟላ መሆኑ ብሎም ከሸይጧን ክፋት ሁሉ መጠበቁም የሚገባ ነው።

☼☼☼☼☼

የሱረቱ-ል-*ዘልዘላህ* ተፍሲር፤ መደንይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ምድር (በኀይል) መንቀጥቀጥዋን በተንቀጠቀጠች ጊዜ፤ 1. ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤ 2. ሰውም "ምን ኾነች?" ባለ ጊዜ፤ 3. በዚያ ቀን ወሬዎችዋን ትናገራለች። 4. ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት። 5. በዚያ ቀን ሰዎች ሥራዎቻቸውን (ምንዳዋን) እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ (እንደየሥራቸው) የተለያዩ ኾነው (ከመቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ። 6. የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 7. የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 8.)

(1-2) አሏህ በትንሳኤ እለት ስለሚሆነው እያሳወቀን ነው፤ መሬቷ አጠቃላይ እሷ ዘንድ ያለው ግንባታም ይሁን ሌላ ምልክት እስኪንኮታኮት ድረስ በመርበትበት፣ በመናጋትና በመንቀጥቀጥ ትናጣለች፤ ኮረብታዎቿ ሜዳ ይሆናሉ፤ *«ትክክል ሜዳም ትኾናለች። በርሷ ዝቅታና ከፍታ የሌለባት»* **"ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤"** ማለትም በውስጧ ያሉ ሙታንም ይሁን ድልብ ይወጣሉ።

(3) "ሰውም "ምን ኾነች?" ባለ ጊዜ፤" የተጋረጠባትን ከባድ ጉዳይ ሲመለከት፤ በጉዳዩ ከባድነት: **"ምን ሆነች?"** ማለትም፡ ምን አይነት ነገር ተጋርጦባት ነው?!

(4-5) "በዚያ ቀን...ትናገራለች። 4." መሬት ነች **"ወሬዎችዋን"** (የምትናገረው)። ማለትም፡ መሬት ባሪያዎች በሰሩት ነገር ላይ ከሚመሰክሩባቸው አንዷ በመሆኗ ሰሪዎች እሷው ላይ ሆነው መልካምም ይሁን መጥፎ የሰሩትን ትመሰክራለች። ይህም የሚሆነው **"ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት። 5."** ነው። ማለትም፡ እሷው ላይ ሆነው የተሰራውን እንድትናገር አዘዛት እሷም ትእዛዙን የምታምፅ አይደለችም።

(6) "**በዚያ ቀን ሰዎች... (ከመቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ። 6.**" በመካከላቸው ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ከመሰብሰቢያ ሜዳው "...**(እንደየሥራቸው) የተለያዩ ኾነው ...**" ማለትም፡ የሚበላለጡ ቡድን **"...ሥራዎቻቸውን (ምንዳዋን) እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ..."** ማለትም፡ የሰሩትን በጎና መጥፎ ስራ እንዲሁም ምንዳውን የተከማቸ አድርጎ ያሳያቸው ዘንድ (ሰዎቹ ከመቆሚያ ስፍራው ይመለሳሉ)።

(7-8) "የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 7. የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል። 8." ይህ በጎውንም መጥፎውንም ሁሉ አጠቃሎ የሰበሰበ (አገላለፅ) ነው። ምክንያቱም ከነገራቶች ሁሉ እጅግ በጣም አናሳ የሆነችዋን የብናኝ ክብደት ያክል እንዲያያትና እንዲመነዳባት ከተደረገ ከዛ በላይ በሆነውማ በቀዳሚነት የተገባ ይሆናል። ልክ ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ እንዳለን፡ "ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሠራችውን የቀረበ ኾኖ የምታገኝበትን ቀን (አስታውስ)። ከመጥፎም የሠራችው በርስዋና በርሱ (በጎጢአትዋ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች።" "የሰሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ኾኖ ያገኙታል።" በዚህ ላይ ትንሽም ቢሆን መልካሙን በመስራት ማነሳሳትን እና የሚናቅም ቢሆን መጥፎ ከመስራት ማስጠንቀቅን ይዟል።

☼☼☼☼☼

የሱረቱ-ል-ዓድያት ማብራሪያ፤ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (እያለከለኩ ሩዋጮች በኾኑት (ፈረሶች) እምላለሁ። 1 (በሰኮናቸው) እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በኾኑትም፤ 2. በማለዳ ወራሪዎች በኾኑትም፤ 3. በእርሱ አቧራን በቀሰቀሱትም፤ 4. በ(ጠላት) ክቢ መካከል በእርሱ (በጫት) በተጋፈጡትም እምላለሁ። 5. ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው። 6. እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው። 7. እርሱም ገንዘብን ለመውደድ በጣም ብርቱ ነው። 8. (ሰው) አያውቅምን? በመቃብሮች ያሉት (ሙታን) በተቀሰቀሱ ጊዜ፤ 9. በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለጸ ጊዜ (እንዴት እንደሚኾን)?! 10. ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ (ነገር) በእርግጥ ውስጠ አዋቂ ነው። 11.)

---

(1) ከፍ ያለው አሏህ በሷ ላይ ካለው ፍጡራን ዘንድ የታወቀ ደማቅ ምልክትና ጉልህ ፀጋ አንፃር በፈረስ ይምላል። የማለበትን ከሁኔታም አንፃር ሲታይ ሌሎች መሰል እንስሳት በማይጋሩበት ሁኔታ ነው የማለው። እንዲህም አለ **“እያለከለኩ ሩዋጮች በኾኑት (ፈረሶች) እምላለሁ።”** ከብርታቱ የተነሳ ማለክለክ የሚያደርሳቸው የሆነን ሃይለኛና ጥግ የደረሰ ሩጫን ሯጮች የሆኑት። ያም (ማለክለክ) ሩጫዋ ሲበረታ ከደረቷ የሚወጣ የስትንፋሷ ድምፅ ነው።

(2) "(በሰኮናቸው) እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በኾኑትም፤” በሚሮጡበት ጊዜ በሰኮናቸው ድንጋዩ ላይ የሚወጡበት ብርታትና ሃይላቸው እሳትን ያወጣል።

(3) በጠላት ላይ **"በማለዳ ወራሪዎች በኾኑትም”**፤ ይህም አብዛኛውን ጊዜ ወረራ የሚካሄደው በማለዳ በመሆኑ ነው።

(4-5) "በቀሰቀሱበትም” በሩጫቸውና በማጋጨታቸው **"አቧራ”** (የሚቀሰቅሱት)። **"በ(ጠላት) ክቢ መካከል በእርሱ (በጫት) በተጋፈጡትም እምላለሁ።”** ወረራው በታቀደበት የጠላት ስብስብ መሃል ይጋፈጣሉ።

(6) መሃላው የተማለበት (ጭብጥ) ቀጣዩ ቃሉ ነው፡ "**ሰው ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው።**" ለአሏህ ተገቢ የሆነውን መልካም ነገር ታቃቢ (ነው)። የሰው ልጅ በተፈጠረበት ማንነት ነፍስ ያለባትን ግዴታ በተሟላ መልኩ ለመወጣት የምትመች ሆና አይደለም። ይልቅ ተፈጥሮዋ ከሚጠበቅባት ኢኮኖሚያዊም ሆነ አካላዊ ግዴታ መወጣት መስነፍና መታቀብ ነው። አሏህ መርቶት ከዚህ ባህሪ ግዴታን ወደ መወጣት የገጠመው ካልሆነ በቀር።

(7) "እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው።" ማለትም፡ የሰው ልጅ ስለራሱም ከሚያውቀው አንፃር ያለበትን የማቀብና የከሃዲነት ማንነቱ ላይ መስካሪ የሆነ እንጅ የሚያስተባብለውና የሚያወግዘውም አይደለም። ምክንያቱም ግልፅና ጉልህ የሆነ ጉዳይ ነውና። በርግጥ በአንቀፁ ላይ መስካሪ ነው የተባለው ለአሏህ ቢባልም ያስኬዳል። ማለትም፡ የሰው ልጅ ለጌታው ብርቱ ከሃዲ ነው፤ ለዛም ደሞ አሏህ መስካሪ ነው። በአንቀፁ ላይ ለጌታው ከሃዲ ለሆነ ሰው ከባድ ዛቻ አለበት። በሱ ላይ አሏህ መስካሪው ነውና።

(8) "እርሱም: ማለትም፡ የሰው ልጅ "...**መልካምን ለመውደድ...**" ማለትም፡ ገንዘብን "...**በጣም ብርቱ ነው።**" ማለትም፡ ለገንዘብ ያለው ውዴታ እጅግ የበዛ ነው። ለዛ ያለው ውዴታ ነው እሱ ላይ ያሉበትን ግዴታዎች ከመወጣት ያቀበው። የነፍሱን ፍላጎት ከጌታው ውዴታ በፊት እንዲያስቀድም ያደረገው። ይህ ሁሉ የሆነው ታዲያ እይታውን በዝች አለም ላይ ስለገደበና ከአኼራውም ስለተዘናጋ ነው።

(9-10) ለዚህም ነው ታድያ ለቀጠሮው ቀን ፍርሃት እንዲኖረው በማነሳሳት መልኩ እንዲህ ያለው፡ "**(ሰው) አያውቅምን?!...**" ማለትም፡ ይህ ተላላ አያውቅምን? "**በመቃብሮች ያሉት (ሙታን) በተቀሰቀሱ ጊዜ፤**" ማለትም፡ ሙታኖችን ለመሰብሰብና ለመቀስቀስ ከቀብራቸው ባወጣቸው ጊዜ፤ "**በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለጸ ጊዜ (እንዴት እንደሚኾን)?!**" ማለትም፡ ልቦና ውስጥ የተደበቀው የመልካምም ይሁን የመጥፎ እምቅ ግልፅ በሆነና በጎላ ጊዜ፤ ሚስጥሩ ግልፅ የውስጡም ጉልህ በሚሆንበት ጊዜ፤ በፍጡራኖች ፊትም የስራቸው ውጤት ግልፅ በሆነበት ጊዜ ማለት ነው።

(11) "ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ (ነገር) በእርግጥ ውስጠ አዋቂ ነው።" ማለትም፡ በግልፅና ውስጣዊ፤ በድብቁም በጉልሁ ስራቸው ላይ የሚመለከትና በሷውም ላይ የሚመነዳቸው ነው። ዘላለሙን የሚያውቃቸው ከመሆኑም ጋ ስለነሱ በዛንለት ያለውን መረጃ ነጥሎ ጠቀሰ፤ ይህም ምክንያቱ አሏህ የሚመነዳበት ሁኔታ መነሻነቱ በራሱ ከሚያውቀውና ከተመለከተው የሆነን ምንዳ በመሆኑ ነው።

☼☼☼☼☼

የሱረቱ አልቃሪዓህ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤ 1. ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት! 2. ቆርቋሪይቱም ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ? 3. ሰዎች እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ) በሚኾኑበት ቀን፤ 4. ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ በሚኾኑበት (ቀን ልቦችን በድንጋጤ ትቆረቁራለች።) 5. ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ፤ 6. እርሱ በምትወደድ ኑሮ ውስጥ ይኾናል። 7. ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰውማ፤ 8. መኖሪያው ሃዊያህ ናት 9. እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 10. (እርሷ) በጣም ተኪሳ እሳት ናት።11.)

(1-3) "ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤" ከእለተ ተንሳኤ ስያሜዎቿ መካከል አንዱ ነው። በዚህም የተሰየመችበት ምክንያት ሰዎችን ብሽብሯ የምትቆረቁርና የምታስደነግጣቸው በመሆኗ ነው። ለዚህም ነው ጉዳይዋን ከፍ ከበድ አድርጎ በተከታዩ ቃሉ የገለፀው **"ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤ 1. ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት! 2. ቆርቋሪይቱም ምን እንደኾነች ምን አሳወቀህ? 3"**

(4) “ሰዎች እንደ ...በሚኾኑበት ቀን፤” ካለው የድንጋጤ ብርታትና ከባድነት አንፃር። **“...እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ) . . . ”** ከፊሉ በከፊሉ ላይ እንደሚዋልል የአንበጣ መንጋ፤ በአንቀፁ ላይ “አልፈራሽ” የተባሉት አቅጣጫዋን ሳታውቅ በለሊቱ ክፍለጊዜ የሚበርሩ እሳት ቢቀጣጠልላት እንኳ ምንነቱን ባለማወቋ ጥልቅ የምትል (የእሳት እራት) ነች። የዛንለት እነዚያ የአእምሮ ባለቤት የሆኑት የሰውልጆችም ሁኔታቸው እንዲሁ ነው።

(5) እነኝህ ብርቱ የሆኑ የማይሰሙት ተራሮች ደግሞ **“... እንደ ተነደፈ ሱፍ...”** ይሆናሉ። ማለትም፡ ተነድፎ በመበጠሩ እጅጉን ደካማ ሆኖ እንደቀረ ሱፍ የትኛውም የንፋስ ቀላል ሳይቀር ይዞት የሚበር ይሆናል። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ “ጋራዎችንም እርሷ እንደ ደመና አስተላለፍ የምታልፍ ስትኾን የቆመች ናት ብለህ የምታስባት ሆና ታያታለህ። የዚያን ነገሩን ሁሉ ያጠነከረውን የአላህን ጥበብ (ተመልከት)። እርሱ በምትሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው።” (ነምል 88) ከዚህም በኋላ የተበተነ አቧራ ትሆናለች፤ የሚታይ ነገር የሌላት ሆና ትወድማለች። የዚህኔ ሚዛኖችም ይቆማሉ ሰዎችም ለሁለት ይከፈላሉ፤ ለዘላለሙ እድለኛና እድለቢስ ሆነው።

(6-7) “ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ፤” ማለትም፡ በጎው ከክፋቱ በላይ ያመዘነችለት **“እርሱ በምትወደድ ኑሮ ውስጥ ይኾናል።”** በመደሰቻ ጀነቶች ውስጥ ይሆናል።

(8-11) “ሚዛኖቹም የቀለሉበት ሰውማ፤” ክፋቱን መቋቋም የሚችል በጎ የሌለው **“መኖሪያው ሃዊያህ ናት።”** ማለትም፡ መኖሪያና መጠለያው ከስያሜዎቿ አንዱ ሃዊያህ የሆነችው እሳት ነች። ልክ እንደዛች የማትለየው እናቱ። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ እንዳለው፡ **“... ቅጣቷ የማይለቅ ነውና”** (አል-ፉርቃን) የዚህን ትርጉም በማስመልከት እንዲህ ተብሏል፡ መሃል አናቱ የእሳቱ ውስጥ ማገዶ ነች። ማለትም፡ ወደ እሳቱ በጭንቅላቱ ይወረወራል ማለት ነው።

“እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?” ይህ የሷን ጉዳይ ከፍ ከማድረግ አንፃር ነው። ከዚያም በተከታዩ ቃሉ አብራራት፡ **“(እርሷ) በጣም ተኪሳ እሳት ናት።”** ማለትም፡ ብርቱ አቃጣይ፤ የማቃጠል ብርታቷ ከዱንያዋ እሳት የማቃጠል ብርታት በሰባ እጥፍ የምትበልጥ የሆነች ነች። ከሷ በአሏህ እንጠበቃለን።



የሱረቱ ተካሡር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በብዛት መፎካከር (ጌታችሁን ከመገዛት) አዘነጋችሁ። 1. መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ። 2. ተከልከሉ፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ። 3. ከዚያም ተከልከሉ፤ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። 4. በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ ዕውቀትን ብታውቁ ኖሮ፤ (ባልዘናጋችሁ ነበር)። 5. ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ. 6. ከዚያም እርግጠኛን ማየት ታዩዋታላችሁ። 7. ከዚያም ከድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃላችሁ። 8.)

(1) ተጋሪ ሳያደርጉ እሱን በብቸኝነት ማምለክ፤ እሱኑ ማወቁ፣ ወደሱው መመለሱ፤ የሱን ውዴታ ከሁሉም ነገር ማስቀደም የሆነውን የመፈጠራቸው አላማ ለመዘናጋታቸው ባርያዎቹን በመውቀስ መልኩ ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ **"...(ጌታችሁን ከመገዛት) አዘነጋችሁ።"** አሁን ካወሳነው። "**በብዛት መፎካከር...**" ሰዎች የሚፎካከሩበትን ሁሉ ሊያካትት ዘንድ የፉክክሩን ምንነት አላወሳም፤ የአሏህ ፊት ያልተፈለገበት ተፎካካሪዎች የሚፎካከሩበትን፤ ተመፃዳቂዎች የሚመፃደቁበትን በገንዘብም፣ በልጅም፣ በረዳትም፣ በሰራዊትም፣ በሰራተኛም፣ በክብርም፣ ሌላ ሌላም አንዱ ለሌላው "እኔ እበልጥ" ብሎ የሚፎካከረትን ሁሉ ሊያካትት ዘንድ።

(2) ይህ ዝንጉነታችሁ፣ ጫወታችሁ፣ መዘናጋታችሁ ቀጥሎ "**መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ**" ዘለቅችሁ። የዚህኔ ነው ግርዶሹ የተነሳላችሁ፤ ምን ይሁን መካሱን በማትችሉበት ጊዜ ሆነ እንጅ፤ "**መቃብሮችን እስከ ጎበኛችሁ ድረስ**" የሚለው አንቀፅ "በርዘኽ" ከሱ የሚፈለገው ወደቀጣዩ አገር መሸጋገር የሆነ አገር እንደሆነ ያመላክተናል። ምክንያቱም አሏህ "ዘያሪዎች" ብሎ ነው እንጅ የገለፃቸው "የሚቆዩ" ብሎ አይደለም፤ ይህም ከሞት መቀስቀስን እና ቀሪ በሆነችዋ ጠፊ ባልሆነችዋ አገር መመንዳትን ይጠቁማል።

(3-6) ለዚህም ነው **"ተከልከሉ፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ። 3. ከዚያም ተከልከሉ፤ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። 4. በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ ዕውቀትን ብታውቁ ኖሮ፤ (ባልዘናጋችሁ ነበር)። 5."** ማለትም፡ ልቦናችሁ ድረስ የሚዘልቅ እውቀት ቢኖራችሁ ኖሮ መፎካከር ባላዘናጋችሁ፤ ወደ መልካም ስራም በተሯሯጣችሁ ነበር። ነገር ግን ተጨባጩን አለማወቃችሁ ወደምታዩት ነገር አደረሳችሁ። "**ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ።**" ማለትም፡ ትንሳኤን እንደምትመለከቱ ነው፤ አሏህ ለካፊሮች ያዘጋጃትን ቅጣት እንደምትመለከቱ ነው።

(7) "ከዚያም እርግጠኛን ማየትን ታዩዋታላችሁ።" ማለትም፡ የአይን እይታ፤ ከፍ ያለው አሏህ እንዳለው "ከሓዲዎችም እሳትን ያያሉ። እነርሱም በውስጧ ወዳቂዎች መኾናቸውን ያረጋግጣሉ። ከእርሷም መሸሻን አያገኙም።"

(8) "ከዚያም ከድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃላችሁ።" ያ በዱንያ ላይ ለተጣቀማችሁበት ተገቢውን ሹክር አደረሳችሁን? በሱ ላይ ለአሏህ የሚገባውን መብቱን ተወጣችሁን? እሱን ለማመፅ አልተጠቀማችሁበትምን? (አግባቡን ጠብቃችሁ ከነበር) የተሻለ በላጭ ፀጋውን ይውልላችሁ ዘንድ። ወይስ ተሸንግላችሁ የሚገባውን ሹክር አላደረሳችሁም? ምናልባትም ጭራሽ እሱኑ ለማመፅ ነው የተጠቀማችሁበት? በዛውም ይቀጣችኋልና። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ "እነዚያም የካዱት በእሳት ላይ በሚጋፈጡ ቀን «ጣፋጮቻችሁን በአነስተኛይቱ ሕይወታችሁ አሳለፋችሁ። በእርሷም ተጣቀማችሁ፡ ስለዚህ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩ በነበራችሁትና ታምጹ በነበራችሁት ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትምመነዳላችሁ» (ይባላሉ)።"



የሱረቱ አል-ዓስር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በጊዜያቱ እምላለሁ። 1. ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው። 2. እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ። 3.)

(1-3) ከፍ ያለው አሏህ የለሊትና ቀን መፈራረቅ፤ የባሮቹ ስራና ድርጊቶች መድረክ በሆነው ጊዜ ይምላል። የሰው ልጅ ሁሉ ከስሯል፤ ከሳሪ ደግሞ የአትራፊ ተቃራኒ ነው። ክስረት የሚበላለጥ የሆነ የተለያየ በርከት ያለ ደረጃ አለው። ክስረቱ ልቅ የሆነበት ዱኒያውንም አኼራውንም እንደከሰረው፤ ፀጋ ሁሉ አምልጦበት ለዓዛብ እንደተዳረገው አይነቱ ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም ክስረቱ በተሰነ መልኩ ብቻ የሆነ ሊሆንም ይችላል። ለዚህም ነው ከነኝህ አራቱን ባህርያት ከተላበሰ ውጭ ኪሳራ ላይ መሆኑን በጥቅሉ የገለፀው።

- አላህ እንዲያምን ባዘዘው ነገር ሁሉ ማመን፤ እምነትም ደሞ ያለ እውቀት ሊመጣ ወይም ሊሟላ የማይችል በመሆኑ ከሱ ውጭ ሙሉ ሊሆንበት የማይችልበት ቅርንጫፉ ነው።

- እንዲሁም በጎ መስራት፤ ውጫዊ ይሁን ውስጣዊ፣ ከአላህ መብቶች ጋ የተቆራኘ ይሁን ከባሮቹ መብቶች ጋር የተቆራኙ፤ ግዴታ ይሁን የሚመከር መልካም ሥራን ሁሉ መስራት

- እንዲሁም ያ ኢማንና በጎ መስራት የሆንው እውነት ላይ አደራ መባባል፤ ማለትም፡ ከፊሉ ሌላውን በዚሁ አደራ ሊለውና ሊያነሳሳው ብሎም እንዲወደውም ሊያደርገው ማለት ነው።

- አሏህን በመታዘዝ ላይ፣ አሏህን ከማመፅና አሳማሚ በሆነው ቀደር መታገስ።

አንድ ባርያ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ነገራቶች ነፍሱን ሙሉ የሚያደርግ ሲሆን በመጨረሻዎቹ ሁለት ነገራቶች ደግሞ ሌላውን ሙሉ የሚያደርግበት ነው። እነዚህ አራት ነገሮች አሟልቶ ሲገኝ ደግሞ ከኪሳራ ተጠብቆ ታላቅ ስኬትን የተጎናፀፈ ይሆናል።



የሱረቱ አል-ሁመዛህ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ለሃሜተኛ ለዘላፊ ሁሉ ወዮለት። 1. ለዚያ ገንዘብን የሰበሰበና የቆጣጠረው (ያደለበውም) ለኽነ ፤(ወዮለት)። 2. ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል። 3. ይከልከል፤ በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ በእርግጥ ይጣላል። 4. ሰባሪይቱም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 5. የተነደደችው የአላህ እሳት ናት። 6. ያቺ በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው። 7. እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ የተዘጋጀች ናት። 8. በተዘረጋች አዕማድ ውስጥ (የተዘጋች ናት)። 9.)

(1) "... **ወዮለት**" ማለትም፡ ከባድ ዛቻ፣ ጣጣ፣ ጭንቅ ቅጣት አለበት። "**ለሃሜተኛ ለዘላፊ ሁሉ...** " ማለትም፡ ያ ሰዎችን ባካሉም በቃሉም የሚዘልፈው፤ "ሃማዝ" ማለት ያ ሰዎችን የሚያነውር፤ በአሽሙርና በአካክል ሰዎችን የሚተች ነው። "ለማዝ" ማለት ደግሞ በምላሱ የሚያነውር ነው።

(2) ከዚህ ሃሜተኛና ዘላፊ ባህርያት መካከል ገንዘብ እያከማቹ እየቆጠሩ በዛው ከመቦረቅ በስተቀር ሌላ ለምንም ግድ የሌለው ሰው ነው። በጥሩ መንገዶች ላይ በማዋል ፣ ዝምድናን በመቀጠል እና የመሳሰሉት ላይ ለማዋል ፍላጎት የለውም።

(3) ባለማወቁ "**ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል።**" በዚህ ዓለም ውስጥ (የሚያዘወትርው መሆኑን ያስባል) ለዚህም ነው የህይወት ዘመናቸው የሚጨምርለት መስሎት ጥረቱ እና ትግሉ ሁሉ ገንዘቡን ለማሳደግ የሚውለው። በእውነቱ ስስት የሰዎችን ሕይወት እንደሚያጠፋ እና ቤቶችን እንደሚያፈርስ እና በጎነት ደግሞ የህይወት ዘመን እንዲጨምር ግን አያውቅም።

(4-7) "**ይከልከል፤ በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ በእርግጥ ይጣላል።**" ማለትም፡ ይወረወራል። "**በሰባሪይቱ (እሳት) ውስጥ 4. ሰባሪይቱም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ? 5.**" እሷን በማላቅና ጉዳይዋን ከባድነት በመጠቆም ነው፤ ከዚያም በቀጣዩ ቃሉ አብራራት፡ "**የተነደደችው የአላህ እሳት ናት።**" ያች መቀጣተያዋ እሳትና ድንጋይ የሆነች። ከብርታቷም የተነሳ "**ያቺ በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው።**" ማለትም፡ (መቀጣጫዋ) ከሰውነት አካል ልቦና ድረስ የሚዘልቅ የሆነ።

(8) ከዚህ ጥግ የደረሰ ቃጠሎም ጋ እነሱ እሷው ውስጥ የታገቱ ናቸው። ከሷ መውጣቱም ተስፋ የቆረጡበት ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው "**እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ የተዘጋጀች ናት።**" ያለው። ማለትም፡ የተቆለፈች። "**በተዘረጋች አዕማድ ውስጥ**" ከኋላ በርም "**(የተዘጋች ናት።**" ከሷ እንዳይወጡ ማለት ነው። "ከጭንቀት ብርታት የተነሳ ከእርሷ ለመውጣት በፈለጉ ቁጥር ከእርሷ ውስጥ እንዲመለሱ ይደረጋሉ።" ከሷም በአሏህ እንጠበቃለን፤ መሃርታውንና ጥበቃውንም እንጠይቀዋለን።



የሱረቱ አል-ፊል ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በዝሆኑ ባለቤቶች ጌታህ እንዴት እንደሠራ አላወቅህምን? 1. ተንኮላቸውን በጥፋት ውስጥ (ከንቱ) አላደረገምን? (አድርጓል)። 2. በእነርሱም ላይ መንጎች የኾኑን ዎፎች ላከ። 3. ከተጠበሰ ጭቃ በኾነ ድንጋይ የምትወረውርባቸው የኾነችን፤ (አዕዋፍ)። 4. ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራም አደረጋቸው። 5.)

(1-5) ማለትም፡ የአሏህን ችሎታ፣ የማንነቱን ታላቅነት፣ በባሮቹ ላይ ያለውን ርህራሄ፣ የአሃዳዊነቱ ማስረጃ፣ የመልዕክተኛው ሙሓመድንﷺ እውነተኝነት፣ በእነዚያ ወደተከበረው ቤቱ ደርሰው ማውደሙን የፈለጉት፤ ለዚህም የታጠቁት፤ ለማውደሙም የዝሆን መንጋ ከነሱው ጋ ይዘው የሄዱት፤ የመመለስ ተስፋ የሌላቸውን ከአቢሲኒያም ከየመንም ይዘው የመጡትን፤ የዝሆን ባለቤቶች ላይ ባደረገው አላየህምን? -ለዓረቦችም የዜያኔ መመከት በማይችሉበት ሆነው- ወደ መካ አቅራቢያ በደረሱና የመካ ሰዎችም በራሳቸው ላይ ከነሱ ሰግተው ከመካ በወጡ ጊዜ አሏህ በእነርሱ ላይ መንጎች የኾኑን ወፎችን ላከባቸው። ማለትም፡ የተለያየ የሁነ። ከሸክላ የሆኑ ድንጋዮችን ይወረውሩባቸዋል። በሷም መታቻቸው፤ ቅርቡንም ሩቁንም ተከታተለችው፤ ሞቱም ተንኮታኮቱም፤ እነሱም ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራ ሆኑ። አሏህም ከክፋታቸው ታደገ፤ ክፋታቸውንም በራሳቸው ላይ መለሰ። ታሪካቸው የታወቀና የተሰራጨ ነው። ይህች ነብዩ ﷺ የተወለዱባት አመት ከተልዕኮው ጠቋሚዎችና ከጥሪው አመላካቾች መካከል ሆነች። ለአሏህ ምስጋናና ሹክር ይገባው።

☼☼☼☼☼

የሱረቱ ሊኢላፊ ቁረይሽ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ቁረይሽን ለማላመድ (ባለዝሆኖቹን አጠፋ)። 1. የብርድና የበጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሠራ። 2. ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ። 3. ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)። 4. ናት)።)

(1-4) በርካታ የተፍሲር ሊቃውንት የዚህ ሱራ መጀመሪያው ከሱ በፊት ያለው ሱራ እንደሆነ ይገልፃሉ።(أي: إن الجار والمجرور متعلق بالسورة التي قبلها) ማለትም፡ ለቁረይሾች ሰላም፣ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ፣ በክረምት ለየመኖች በበጋውም ደሞ ለሻም የንግድና የሲሳይ ፍለጋ ጉዟቸውን ለማስተካከል ስንል ይህን በዝሆኑ ሰዎች ላይ ያደረግነውን አደረግን። እነሱን በክፋት የፈለጉቸውን አሏህ ﷻ የሓረምና የሰዎቹን ጉዳይ በዓረቦች ዘንድ እስኪያከብሯቸውና በየትኛውም የጉዞ ፍላጎታቸው እስከማያደናቅፏቸው ድረስ ከፍ አደረገ። ለዚህም ነው አሏህ ﷻ ሹክር እንዲያደርሱ ያዘዛቸው እንዲህም አለ ፡ "**ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ።**" ማለትም፡ በብቸኝነት ሊነጥሉትና አምልኮም ለሱ ብቻ ሊያጠሩ።

"**ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)። 4. ናት)።**" የሲሳይ ፍለጋ መግራቱና ከስጋት መዳን ከፍ ላለው አሏህ ሹክር ማድረስ ግድ ከሚያስብሉ ዱኒያዊ ጉዳዮች መካከል ናቸው። ጌታየ ሆይ! ለድብቁም ለግልሁም ፀጋህ ምስጋና ባጠቃላይ ላንተ የተገባ ነው። አሏህ በዝች ሱራ ላይ ጌትነቱን ከቤቱ ጋ ነጥሎ አቆራኝቶ ያመጣው ቤቱ(ካዕባ) ካለው ክብርና ደረጃ አንፃር እንጅ እሱ የሁሉም ጌታ ነው።



የሱረቱ አል-ማዑን ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን? (ዐወቅከውን?) 1. ይህም ያ የቲምን በጎይል የሚገፈትረው፤ 2. ድኻንም በማብላት ላይ የማያግባባው ሰው ነው። 3. ወዮላቸው ለሰጋጆች። 4. ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለኾኑት፤ (ሰጋጆች)። 5. ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዮች ለኾኑት። 6. የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለኾኑት (ወዮላቸው)። 7.)

---

(1) አሏህ ﷻ የሱንና የባሮቹን ሓቅ የተውትን በመውቀስ መልኩ እንዲህ ይላል፡ "**ያንን በምርመራው የሚያስተባብለውን አየህን? (ዐወቅከውን?)**" ማለትም፡ ሞቶ በመቀስቀስና በምንዳው፤ መልዕክተኞች ይዘውት በመጡት አያምንም።

(2) "**ይህም ያ የቲምን በጎይል የሚገፈትረው፤...**" ማለትም፡ ብልቡ ድርቅና እና ተስፋ የሚያደርገው ምንዳም ሆነ የሚሰጋው ቅጣት ባለመኖሩ ምክንያት የማያዝን ብሎም በብርታትና ብድርቅና የሚገፈትር የሆነው፤

(3) "**. ድኻንም በማብላት ላይ የማያግባባው ሰው ነው።**" ማለትም፡ ሌላውን። እራሱም ሚስኪን የማያበላ ከሆነ ማ (ለዛቻው) ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

(4-5) "**. ወዮላቸው ለሰጋጆች።**" ማለትም፡ እነዚያ ሶላታቸውን አጥብቀው ያዥ የሆኑት፤ ነገር ግን እነሱ "**ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለኾኑት፤ (ሰጋጆች)።**" የሆኑት ናቸው። ማለትም፡ እሷኑ የሚጨፈልቋት፤ ጊዜዋን የሚተዋት፤ ማእዘኖቿን የሚያጓድሏት የሆኑት ናቸው፤ ይህም የሆነው የአሏህ ጉዳይ ስለማያሳስባቸው ነው። ከመታዘዞች ሁሉ እጅግ አሳሳቢዋን ነውና የተውት። ሶላትን መርሳት ባለቤቱ ሊወገዝበትና ሊወቀስበት የሚገባው የሆነ ጉዳይ ነው። በሶላት ውስጥ ሆኖ መርሳት ግን ከየትኛውም ሰው ከነብዩ ﷺም ሊከሰት የሚችል ነገር ነው።

(6-7) ለዚህም ነው አሏህ እነኝህን በእዩልኝ(ሪያእ)፣ በልብ ድርቀትና በርህራሄ ማጣት የገለፃቸው። እንዲህም አለ፡ "**ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዮች ለኾኑት።**" ማለትም፡ ሰዎች ስለሚያዋቸው ነው

“**የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለኾኑት (ወዮላቸው)።**” ማለትም፡ በትውስት ወይም ብስጦታ መስጠቱ የማይጎዳን ነገር ለመስጠት ጎፋግ ናቸው። እንደ የቤት እቃ፣ ባልዲ፣ መቆፈሪያና መሰል መለዋወጡ እንደቀላልና እንደባህል የሆነበት ሁሉ። እነኝህ ከስስታቸው አንፃር የዕቃ ትውስትንም ይከለክላሉ። ታድያ ከዛ በላይ በሆነው እንዴት ሆነው ነው?!

ይህች ሱራ ሚስኪንና የቲምን በመመገብ ላይ ማነሳሳት፣ በዛው ላይ ማነቃቃት፣ ሶላትን ጠብቆ መያዝ፣ በሷው ላይ መጠባበቅ፣ በሷው እና በሌሎች ስራዎችም ላይ ኒያን ማጥራት ይዛለች። መልካም በመስራት፤ የቤት እቃ፣ ባልዲ ነገርም ሆነ ኪታብ ነገር መዋዋስንና ቀለል ያሉ ነገራቶችን መለጋገስንም አካትታለች። ምክንያቱም አሏህ ይህን ያያደረጉትን ወቅሷልና። አሏህ ይበልጡን ያውቃል።



የሱረቱ አል-ከውሠር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ። 1. ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም። 2. ጠይህ (የሚጠላህ) እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው። 3.)

---

(1) ከፍ ያለው አሏህ ለነብዩ ሙሓመድ ﷺ አደረግኩልህ በሚል (በመመፃደቅ) መልኩ እንዲህ ይላቸዋል፡ “**እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ።**” ማለትም፡ በርካታ ኸይርና ታላላቅ ችሮታን፤ ከጥቅሉም አሏህ ለነብዩ ﷺ በዕለተ ትንሳኤ የሚለግሳቸው “አል-ከውሠር” የሚባል ጅረት፤ ርዝመቱ የአንድ ወር፣ ስፋቱ የአንድ ወር ያክል የሆነ፤ ውሃው ከወተት የነጣ፣ ከማር የጣፈጠ መጠጫው ያላቸው ብዛትም ድምቀትም እንደሰማይ ከዋክብቱ የሆነ፤ ከሱ አንድ ጊዜ የተጎነጨ ጥማት ለዘልአለሙ የማይነካው የሆነን ባህር ሰጠሁ እያላቸው ነው።

(2) የዋለለትን ፀጋ ባወሳለት ግዜ እንዲያመሰግንም አዘዘው። እንዲህም አለው፡ “**ስለዚህ ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም።**” እነዚህን ሁለቱን የአምልኮ አይነቶች ለይቶ ያወሳቸው ከአምልኮ በላጮቹና የመቃረቢያ ቁንጮዎቹ በመሆናቸው ነው። እንዲሁም ሶላት በልቦና እና በአካል ለአሏህ መተናነስን ያካተተች፤ በአምልኮ አይነቶች መዘዋወርን የያዘች በመሆኗ እና በእርድ ደግሞ ባርያ ዘንድ ባለው ውድ የእርድ ነገር መቀራረብን፤ ነፍስ በስስትና በውዴታው ላይ ሁና የተፈጠረችበትን ገንዘብ ማውጣት ስላለበት ነው።

(3) "**ጠይህ (የሚጠላህ)...** " ማለትም፡ አንተን ጠይ፣ ወቃሽህና አንተ ዝቅዝቅ የሚያደርግ "... **እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው።**" ማለትም፡ ከመልካም ነገር ሁሉ የተቆራረጠው፤ ስራውም የተቆረጠ መወሳቱም የተቆረጠ ነው። ነብዩ ሙሓመድማ ﷺ በርግጥም በትክክል የተሟላው ነው። ለፍጡራን ሊኖራቸው ከሚችል ከፍ ያለ መወሳት፣ የረዳትና የተከታይ ብዛት በተሟላ መልኩ ያላቸው ናቸው።

የሱረቱ አል-ካፊሩን ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በላቸው «እናንተ ከሓዲዎች ሆይ! 1. «ያንን የምትግገዙትን (ጣያት አሁን) አልግገዛም። 2. «እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም። 3. «እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም። 4. «እናንተም እኔ የምግገዛውን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም። 5. «ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ። ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ። 6.)

(1-6) ማለትም፡ ለከሃዲያን ግልፅ አድርገህ በማሳወቅ እንዲህ በላቸው "**«ያንን የምትግገዙትን (ጣያት አሁን) አልግገዛም።**" ማለትም፡ ከአሏህ ውጭ በድብቅም ሆነ በጉልህ ከሚያመልኩት መጥራራቱ ነው። "**«እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም።**" አሏህን በመገዛት በኩል ኒያችሁ የጠራ ባለመሆኑ ይህ ከሽርክ ጋ የተቆራኘው አምልኪችሁ አምልኮ የሚባል አይደለም። ይህንንም ደጋግሞ ገለፀው፤ የመጀመሪያው ድርጊቱ እንደሌለ ለመጠቆም ሁለተኛው ደግሞ ጭራሽ የማይነጠል መገለጫ ባህርይ እንደሆነ ለመጠቆም ነው። ለዛም ነው በሁለቱ ጎራዎች መካከል ለያያቸውም ልዩነታቸውንም አስቀመጠ፤ እንዲህ በማለት፡ "**«ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ። ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ።**" ልክ በሌላኛው አንቀፅ እንዲህ እንዳለው "«ሁሉም በሚመስለው መንገዱ ላይ ይሠራል። ጌታችሁም እርሱ መንገዱ ቀጥተኛ የኾነውን ሰው ዐዋቂ ነው በላቸው።" ስለዚህ እናንተም እኔ ከምሰራው የተጥራራችሁ ናችሁ እኔም እናንተ ከምትሰሩት የተጥራራሁኝ ነኝ።

የሱረቱ አል-ነስር ማብራሪያ፤ ሱራዋ መደንይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤ 1. ሰዎችንም ጭፍሮች እየኾኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤ 2. ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው። ምሕረትንም ለምነው። እርሱ ጸጸትን በጣም ተቀባይ ነውና። 3.)

(1-3) ይህች የተከበረች ሱራ የምስራች፣ በተከሰተም ጊዜ ለመልዕክተኛው ትእዛዝና ይህን ተከትሎ ለሚመጣው ጥቆማና ማመላከትን ይዛለች። የምስራቿ አሏህ መልዕክተኛውን እንደሚረዳ፣ የመካ መከፈት፣ ጠላት ከነበሩ በኋላ ከራሱ ሰዎች፣ ከረዳቶቹ ሆነው የሰዎች "**ጭፍሮች እየኾኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ**" እንደሚያይ የምትጠቁመዋ የምስራች ነች። ይህ የምስራች በተጨባጭ የታየ ነው።

ከመካ መከፈት እና ከአሏህ እርዳታ በኋላ ያለው ትእዛዝ ደግሞ አሏህ መልዕክተኛውﷺን በዚሁ ላይ እንዲያመሰግነው (ሹክር እንዲያደርስ)፣ እሱን በማመስገን እንዲያልቀውና መሃርታውንም እንዲጠይቀው ማዘዙ ነው።

ከጥቆማው በኩል ደሞ ሁለት ጥቆማዎች ይዟል። አሏህ ለዲኑ ያለው እርዳታ አሏህን (ከማይገባው ሁሉ)ማጥራት እና ከነብዩ ﷺ መሃርታን መጠየቅ በተገኘ ቁጥር ሁሉ ይዘልቃልም ይጨምራልም። ምክንያቱም ይህ ሹክር ከማድረግ በመሆኑ ነው። አሏህ ﷻ እንዲህ ይላል፡ "ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ"። በርግጥም ይህ ነገር በዚህ ህዝብ በቅን ተተኪዎቹ (ኹለፋኡ ራሺዲን) ጊዜም ሆነ ከዛም በኋላ ባሉት የተገኘ ነገር ነው። ዲነል ኢስላም የትኛውም ሃይማኖት ባልዘለቀበትም በአሏህ እርዳታ ዘላቂ ከመሆን አልተወገደም። በሌላው ያልገባውም በሱ ገብቷል፤ ከህዝቡ ከራሱ የአሏህን ትእዛዝ ከመቃረን በኩል የተከሰተው እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ። የዚያኔ በንግግር መለያየት፣ በጉዳይ መበታተን ተፈተኑ፤ የተከሰተውም ተከሰተ፤ ይህ ከመሆኑም ጋ ለዚህ ኡማ እና ለዚህ ዲን በአእምሮ ውል የማይል በህሊና ዝር የማይል ልዩ የሆነ የአሏህ እዝነትና ርህራሄ አለው። ሁለተኛው ጥቆማ ደግሞ የነብዩ ﷺ የሞት ቀጠሮ መቃረቡን ጠቋሚ ነበር፤ ይህም የነብዩ ﷺ እድሜ ከሌላው እድሜ የተለየ በላጭነት ያለው በመሆኑ አሏህ የማለበት ነው። እንደሶላት፣ ሓጅን ሌሎችም በላጭ የሆኑ ነገራቶች ደግሞ መደምደሚያቸው መሃርታ መጠየቅን በመሰሉ መሆኑ የተለመደ ነው፤ ታድያ አሏህም መልዕክተኛውን ﷺ የእድሜው መቋጫ መቃረቡን ለመጠቆም በማመስገንና መሃርታን በመጠየቅ አዘዘው። የአሏህ ሶላዋትና ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና በእድሜያቸው ከሚያገኙት በላጭ በሆነው ሁኔታ ጌታቸውን ለመገናኘት፣ ሊዘጋጁና ሊመቻቹ ዘንድ። እሳቸውም ﷺ እንደልማዳቸው የቁርአንን መልዕክት ወደ ተግባራዊነት ያዞሩትና በሶላታቸው ይሉት ነበር፤ በሱጁድም ሆነ በሩኩዓቸው *"ጌታየ ሆይ! ምስጋናም ጥራትም ለኢሏህ ሆይ ለንተ የተገባ ነው፤ መሃርታህንም ለግሰኝ።"*



የሱረቱ አል-መሰድ(ተበት የዳ) ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም። 1. ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም። 2. የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል። 3. ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን። 4. በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ ያለባት ስትኾን። 5.)

አቡ ለሃብ ማለት የነብዩ ﷺ አጎት ነው። እጅግ ጠላትነቱ የበረታና አስቸጋሪው ሰው ነበር፤ አሏህ ለጥፋት ይበለውና በዲኑም የለበትም ለዝምድናውም የማያሳስበው ነበር፤ አሏህም በእንዲህ አይነቱ እስከእለተ ትንሳኤ ድረስ በሚያዋርድ ከባድ ወቀሳ ወቀሰው፤ እንዲህም አለ

(1) "**የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ (ጠፉ፤**" ማለትም፡ እጁም ከሰረ እድለቢስ ሆነም፤ "**... (እርሱ) ከሰረም።**"

(2) "**ከእርሱ ገንዘቡ ...ምንም አልጠቀመውም።**" ያ የነበረውና ድንበር እንዲያልፍ ያደረገው "**... እና ያም ያፈራው ሁሉ**" የአሏህ ቅጣት በመጣበት ጊዜ አንዳችንም ነገር አልመከተለትም።

(3-5) "**የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል።**" ማለትም፡ እሳት ከየአቅጣጫው ታካብበዋለች፤ እሱም ሆነ "**ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትኾን።**" እሷም በበኩሏ ለአሏህ መልዕክተኛ ﷺ እጅግ ብርቱ አስቸጋሪ ነበረች። እሷም ከባሏ ጋ በወንጀልና በጠላትነት ትተባበራለች፣ ክፋትን ትነዛለች፣ የአሏህ መልዕክተኛን ﷺ ለማስቸገር እስከችሎታዋ ጥግ ድረስ ትለፋለች። ልክ አንገቱ ላይ "... **ከጭረት የኾነ ...**" ገመድ ተቋጥሮለት እንጨት በሚሰበስብ ሰው አኳኋን እሷም በጫንቃዋ ወንጀልን ትሸከም ነበር። ማለትም፡ ከቃጫ በሆነ። ወይም ደግሞ እሷ አንገቷ ላይ ከጭረት የተገመደ ገመድ ተቋጥሮላት በእሳት ውስጥም በባሏ ላይ ማገዶ ትጭንበታለች።

ያም ሆነ ይህ፡ በዚህ አንቀፅ ላይ ከአሏህ አስደናቂ ምልክቶች መካከል ይገኝበታል። አሏህ ይህን ሱራ ያወረደው አቡ ለሃብና ባልተቤቱ ሀያው ሳሉ ነበርና፤ እነሱም እሳት ውስጥ የሚቀጡ መሆናቸው የማይቀርለት ጉዳይ መሆኑንም አሳወቀን፤ ኢስላምን አለመቀበላቸውም ግድ የሚል ጉዳይ ነበር፤ ነገሩም ታድያ ግን የቅርቡንም የሩቁን የሚያውቀው ጌታ ባለው መልኩ ነበር የተከሰተው።



የሱረቱ አል-ኢኽላስ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «እርሱ አላህ አንድ ነው። 1. «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። 2. «አልወለደም፤ አልተወለደምም 3. «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።» 4.)

---

(1) ማለትም፡ "**በል**" ቁርጥ ባለ መልኩ ታምኖበት፤ ትርጉሙንም አምኖ በመቀበል፤ "**«እርሱ አላህ አንድ ነው።**" (በል)። ማለትም፡ አሃዳዊነት በሱ በቃ! በምሉእነት የተነጠለ አሃዳዊነት ያለው ነው። ያ መልካም ስሞችና የተሟላ ልኡል ባህርያት እንዲሁም ፍፁም ድርጊቶች ያሉት፤ ያም ብጤም ሆነ አምሳያ የሌለው ነው።

(2) "**«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።**" ማለትም፡ በሚፈለገው ነገር ሁሉ ታሳቢው፤ የላይኛውም ሆነ የታችኛውም አለም ባለቤት ሁሉ ጥግ በደረሰ ትህትና የሚፈልጉት፤ በባህርያቱ የተሟላ በመሆኑ ጉዳያቸውን ይጠይቁታል፤ በሃሳባቸው ሁሉ ይከጅሉታል። ያ በእውቀቱ የተሟላ "አል-ዓሊም"፤ ያ ቻይነቱ የተሟላ የሆነ "አል-ሓሊም"፤ ያ በእዝነቱ የተሟላ የሆነ እንዲሁም ሁሉንም ነገር ያካበበች እዝነት ባለቤት የሆነ "አርረሒም" ነው፤ በሌሎች ባህርያቱም እንዲሁ (የተሟላ ባህርይ ባለቤት) ነው።

(3) ከምሉእነቱም አንፃር እሱ "**«አልወለደም፤ አልተወለደምም**" በራስ መብቃቃቱ የተሟላ ነውና።

(4) "**«ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»**" ከፍ ያለው የላቀው አሏህ በስያሜውም ይሁን፤ በባህርያቱም በድርጊቱም ቢሆን (አንድም ብጤ የለውም)።

ይህች ሱራ አሏህ ከስምና ባህርያቱ አንፃር ያለውን አሃዳዊነት በሙሉ አጠቃልላ ይዛለች።



የሱረቱ አል-ፈለቅ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መክይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ። 1. «ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት። 2. «ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ፤ 3. «በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከኾኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት። 4. «ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ፤ (እጠበቃለሁ በል)።» 5.)

---

(1) ማለትም፡ ጥበቃን በመሻት መልኩ "**«በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ**" ማለትም፡ የፍሬውም የአዝርእቱም አስገኝ፤ የንጋቱም አስገኝ (በሆነው ጌታ) "**እጠበቃለሁ**" ማለትም፡ እጠጋለሁ፤ እከለላለሁ፤ አጥብቄ እይዛለሁ፤ "**በል**"።

(2) "**«ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት።**" ይህ የፈጠረውን ፍጡር ሰውንም ይሁን ጅኑንም፤ እንስሳቱንም፣ በሙሉ የሚያጠቃል ሲሆን እሷ ዘንድ ካለው ክፋት በፈጣሪዋ መጠበቅ ማለት ነው።

(3) ጥቅል አድርጎ ከገለፀ በኋላ ለይቶ አመጣ እንዲህም አለ፤ "**«ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ፤**" ማለትም፡ ሌሊቱ ሰዎችን ባጨለመ ጊዜ፤ በርካታ ክፉ መናፍስትና አስቸጋሪ እንስሳት በሚሰራጭበት ጊዜ ከሚሆነው ሁሉ።

(4) "**«በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከኾኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት።**" ማለትም፡ እነዚያ ድግምቱ ላይ በሚቋጥሩት የድግምታቸው ቋጠሮ ክሮች ላይ በመትፋት ለድግምታቸው ከሚታገዙት ሴት ደጋሚዎች ክፋት፤

(5) "**«ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ፤ (እጠበቃለሁ በል)።»**" ሓሲድ(ምቀኛ) ማለት ከተመቀኘው ሰው ያለን ፀጋ እንዲወገድ የሚመኝ ነው። ለዛም ፀጋው እንዲወገድ የሚችለውን ነገር ያደርጋል።ስለዚህም ከክፋቱ ለመዳንና ተንኮሉን ውድቅ ለማድረግ በአሏህ መጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ።

ቡዳ(የሰው አይን)ም በምቀኛ ስር የሚካተት ነው፤ ምክንያቱም የሰው አይን (አይቶ አሏህ በረካ ያድርግለት ከማይል) ከክፉ ፍጥረት የገማ ነፍስ ምቀኛ እንጅ አይመነጭምና።ይህች ሱራ ከጥቅሉም ይሁን ከዝርዝር የክፋት አይነቶች ሁሉ በአሏህ መጠበቅን አጠቃልላ ይዛለች። እንዲሁም ድግምት እውነትነት ያለው ክፋቱ የሚሰጋ በመሆኑ ከሱም ሆነ ከሰሪዎቹ የአሏህ ጥበቃ የሚያስፈልገው መሆኑንም ትጠቁማለች።



የሱረቱ አል-ናስ ማብራሪያ፤ ሱራዋ መደንይ ነች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው። (በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ። 1. «የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በኾነው። 2. «የሰዎች አምላክ በኾነው። 3. «ብቅ እልም ባይ ከኾነው ጎትጓች (ሰይጣን) ክፋት። 4. «ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከኾነው። 5. «ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል)።» 6.)

(1-6) ይህች ሱራ ከሸይጧን በሰዎች ጌታ፣ በንጉሳቸውና በአምላካቸው (አሏህ) ጥበቃ መሻትን አካትታለች። ያ የክፋቶች ሁሉ መሰረትና መሳሪያም ጭምር የሆነው፤ ያም ካለው ፊትና እና ክፋት አንፃር "**«ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከኾነው።**" ክፋትን ያስውብላቸዋል፤ እሱኑ መልካም እንደሆነ አስውቦ ያሳያቸዋል፤ እንዲያደርጉትም ፍላጎታቸውን ያነሳሳል። ከበጎ ነገርም ደግሞ ስነልቦናቸውን ይጎዳባቸዋል፤ ካለው ምንነት በተለየ መልኩ አድርጎ ያሳያቸዋል፤ እሱ ሁሌም እንዲሁ ነው ሁኔታው። ይወሰውስ ይወሰውስና መልሶ ደሞ ይደነዝዘል፤ ማለትም፡ አንድ ባርያ ጌታውን አስታውሶ ለመመከቱ በጌታው ከታገዘ ከመወስወስ ስራው ይስተጓጎላል። በመሆኑም በሰው ልጆች ሁሉ ጌታ በአሏህ ሊታገዝ፣ ጥበቃውን ሊጠይቅና ሊከለል ይገባዋል። ፍጡራን ሁሉ በጌትነቱና በንግስናው ስር ናቸው። በዛች ለሷው ሲባል በፈጠረበትም ምክንያት የሁሏንም ተንቀሳቃሽ አናት የያዘው እሱው ነው። እሷም ከሷው ማቆራረጥና በነሱና በሷ መካከል ግርዶሽ መሆን፤ አብረውት የእሳት ጓዶች ይሆኑ ዘንድ የሱ ጭፍሮች ማድረግም የሚፈልገውን ጠላታቸውን በመገፍተር እንጅ የምትሟላ አይደለችም። ወስዋስ (መወትወት) ከሰው ልጅ እንደሚሆነው ሁሉ ከሰው ልጅም ይሆናል። ለዚህም ነው፡ "**«ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል)።»**" ያለው።

ከጅምሩ እስከ ከፍፃሜው፤ በጉልሁም ሆነ በድብቁም ሁሉ ምስጋና ለሱ የተገባ ነው። ፀጋውን ሙሉ ሊያደርግልን ዘንድ አሏህን እንጠይቀዋለን። ከሱ በርካታ ፀጋ ግርዶሽ የሆነችንን ወንጀላችንንም፤ አንቀፆቹን ከማስተንተን ልባችንን ያጠፋችውን ማንዳለጥና ስሜትንም መሃርታውን ይለግሰን ዘንድ እንጠይቀዋለን። እኛ ዘንድ ባለ ክፋት እሱ ዘንድ ያለን በጎ እንደማይነፍገን እንከጅለዋለን ከሱም ተስፋ እናደርጋለን። ምክንያቱም ከከሃድያን ህዝቦች በቀር ከአሏህ ርህራሄ ተስፋ የሚቆርጥ የለምና። ከጠማሞችም በቀር ከሱ እዝነት ተስፋ አይቆርጥምና። የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በመልዕክተኛው ሙሐመድ፣ በተከታዮቹና በባልደረቦቹም ሁሉ ላይ ይስፈን፤ ዘላለሙን የተቀጣጠለ ዘላቂነት ያለው ሶለዋትና ሰላም። ምስጋናም ባጠቃላይ መልካም ነገር ሁሉ በፀጋው ሙሉ ለሚሆነው ይሁን።



የመግቢያውና የተፍሲሩ ፈተና

1. የ "አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ" ፀሃፊ ማን ነው?

O ሸይኽ ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ O ሸይኽ ሙሓመድ ቢን ዑሠይሚን O ሸይኽ ሀይሠም ሰርሓን

2. ለምንድን ነው ስለ "አሳሳቢ ትምህርቶች ለብዙሃኑ ህዝብ" የምንማማረው?

O አሳሳቢ ስለሆነች O ምክንያቱም ዑለሞች ትኩረት እንዲሰጣት አደራ ስላሉ

O ለአንድ ሙስሊም አስፈላጊ የሆኑ አሳሳቢ ነገራቶችን ስላካተተች

O ሁሉም መልስ ነው

3. ይህ ፅሁፍ የሚዳስሰው ስለ:

O አንድ ሙስሊም ከቁርአንና ከተውሒድ ጋ በተያያዘ ያለውን ሁኔታ

O የስርዓትና የስነምግባር ርእሶችን O ሙታንን ስለ መገነዝ O ስለሶላትና ዉዱእ

Oከወንጀል ስለማስጠንቀቅ O ሁሉም መልስ ነው

4. አንድ ሙስሊም ቁርአንን እንዴት እንደሚነበብ፣ እንዴት አስተካክሎ መቅራት እንዳለበት፣ እንዴት መሓፈዝ እንዳለበት መጀመር የሚገባው በ:

O ሱረቱ አል-ዓለቅ O በሱረቱ አል-ፋቲሓ O በሱረቱ አል-ኢኽላስ

5. ሰዎች ቁርአንን ከማስተንተንና በሱ ከመስራት ጋ በተያያዘ ባላቸው አቋም ወደ ሁለት ጠርዝ እና አንድ ሚዛናዊ ይከፈላሉ (እውነት – ሃሰት)

6. አንድ ተማሪ መጀመር ያለበት በየትኛው የተፍሲር ኪታብ ነው?

O ኢብን ከሢር O አስ-ሰዕዲይ O አል-ቁርጡቢይ

7. አንድ ተማሪ መጀመር ያለበት በአጫጭሮች ሲሆን በሂደት ነው ወደ ረዣዥሞቹ መሄድ ያለበት (እውነት – ሃሰት)

8. አንድ ተማሪ ከተፍሲር ኪታቦች መማርን መጀመር ያለበት በዘወትርና በመደጋገም እንዲያነብ በሚያነሳሳው በሱረቱል ቀሶስ፣ መርየምና አል-ከህፍ መሰል ሱራዎች ነው። (እውነት - ሃሰት)

9. አንድ ተማሪ ራሱ ተፍሲርን ለማንበብ የሚያስቸግረው ከሆነ ለማዳመጥ በተዘጋጁ(تفسير السعدي من تفسير للقران الصوتي አይነቱን) የኪታብ ንባብ ቅጅዎች ማዳመጡ ይመከራል (እውነት – ሃሰት)

10. ነብዩ ﷺ ቁርአን እየቀሩ ትርጉሙን አለማስተንተንን አስጠንቅቀዋል (እውነት – ሃሰት)

ከሱረቱል ፋቲሓ ማብራሪያ የተውጣጡ ጥያቄዎች

11. ሱራዋ በዚህ ስያሜ የተጠራችው ከሷም እንዳይወጣም ወደሷ እንዳይገባም በሚገታ መልኩ የታጠረች በመሆኗ ነው። (እውነት – ሃሰት)

12. ሱረቱል ፋቲሓ የተባለችበት (ተጨማሪ) ምክንያት…

……

13. ከሱረቱል ፋቲሓ ሌሎች ስያሜዎች መካከል:

O ኡሙል ቁርአን (የቁርአኑ እናት) O አስሰብዐል መሣኒ (ሰባቱ የሚደጋገሙ)

O አስ-ሶላት (ሶላቲኟ) O ሩቃ(ፈውስ) O ሁሉም መልስ ነው።

14. አሏህን በማመፅ ሳይሆን አሏህን በመታዘዝ ላይ እንኳ ቆይተን ቁርአን ከመቅራታችን በፊት የአሏህን ጥበቃ መሻት (“አዑዙ ቢላሂ” ማለትን ይመስል) ግዴታ ነው። ምንድን ነው ምክንያቱ?

……

……

15. *'አዑዙ* የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

……

16. *ለምንድን ነው ሸይጧን አረ-ረጂም(ቅጥቅጡ የተረገመው)* የሚባለው…

O የተረገመ ማለትም ከአሏህ እዝነት የተባረረ ስለሆነ O . በተወንጫፊ ከዋክብት ስለሚቀጠቀጥ O የሰው ልጅን በስሜትና በውዥንብር ስለሚቀጠቅጥ(ስለሚመታ) O ሁሉም መልስ ነው

17. **አሏህ...**

O በውዴታና በማላቅ ተመላኪ አምላክ ነው

O ከሱ ውጭ በዚህ ስያሜ የተጠራ አንድም የለም

O ለአሏህ ስያሜዎች ሁሉ መንደርደሪያ ነው

O የአሏህ ታላቁ ስያሜው ነው።

O ሁሉም መልስ ነው።

18. ***አራ-ራሕማን*** *እና* ***አራ-ረሒም*** በሚሉት ሁለቱ የአሏህ መልካም ስያሜዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

.....

.....

19. ከፍ ያለው አሏህ ፍጡራኑን የሚንከባከበው በሁለት መልኩ ነው፤ በምን እና በምን?

O ጥቅል እና ልዩ O የተገደበ እና ያልተገደበ

20. አብዛኞቹ የኑብያት ዱዓ _____ በሚል ነው።

O አሏህ ሆይ! O ያ ረብ (ጌታየ)!

21. የ *"ዲን"* እለት ማለት...

O የትንሳኤ እለት O. ሰዎች በስራቸው የሚመነዱበት እለት O ሁሉም መልስ ነው

22. **"ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።"** እጅግ ሰብሳቢውና ጠቃሚው ዱዓ ነው (እውነት –ሃሰት)

23. አድ-ዲን የሚለው የዓረብኛ ቃል የሚገልፀው

O ምንዳን O ስራን O . አንዳንዴ ስራውን አንዳንዴም ምንዳውን

24. (እንደ ዓረብኛ ስዋስው) ድርጊት ተቀባዩን ከድርጊት ፈፃሚው ማስቀደም ፋይዳው ...

O መገደብን (የተጠቀሰው ድርጊት በፈፃሚው ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑን) O ምንም

25. **'አምልኮን'** ከ **'እገዛ መሻት በፊት'** መወሳቱ _____ከ ____ እንደማስቀደም ነው:

Oጥቅል የሆነውን ነጠላ ከሆነው O የራሱን መብት ከባርያው መብት Oሁሉም

26. **"አንተን ብቻ እንግዛለን፤"** የሚለው አንቀፅ ለምንድን ነው ጥቅል በሆነ አገላለፅ የመጣው?

.....

27. **ሒባዳ (አምልኮ)** ...

O ከጉልሁም፣ ከድብቁም፣ ውጫዊም ይሁን ውስጣዊ፣ ከንግግርም ይሁን ከተግባር አሏህ የሚወደውንና የሚደሰትበትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስም ነው።

O በመውደድና በማላቅ መልኩ ትእዛዛትን በመፈፀምና ክልክላትን በመቆጠብ ለአሏህ መተናነስ ነው።

O አንዳንዴ ይህን ይፈለግበታል አንዳንዴ ደግሞ ሌላኛው ይፈለግበታል(ሀ እና ለ)

28. **"ምራን"** በሚለው የሃያሉ አሏህ ቃል የተፈለገበት ምራቻ ...

O መጠቆም እና ማመላከት O ተውፊቁን መግጠም O ሁሉም መልስ ነው

29. **"የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን "** በሚለው ቃል የተፈለገበት... O ከዚህ ህዝብ አማኝ የሆነው ሁሉ O ከነብያቶች፣ ከሲዲቆች፣ ከሸሂዶችና ከሷሊሖች የሆኑትን በጎ የዋለላቸውን

30. **"አንተን ብቻ እንግዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።"** የሚለው አንቀፅ ሸሪዓንና ቀደርን መሰብሰብን አቅፏል (እውነት – ሃሰት)

31. ከሚከተሉት መካከል የትኛዋ ነች ሌሎቹ ያላካተቱትን የቁርአን ክፍል በይበልጥ ያካተተች?

Oሱረቱል ፋቲሓ Oአየቱል ኩርሲይ Oሱረቱል ኢኽላስ

32. **"... መንገድ ምራን።"** የሚለው የአሏህ ቃል ከሚያካታቸው መካከል...

O ነብይነት የሚባለውን እውነታ ማፅደቅ O በመላ የቢድዓ እና የጥመት ባለቤት ላይ ምላሽ መስጠት O ሁሉም መልስ ይሆናል

33. **"የፍርዱ ቀን ባለቤት"** የሚለው የአሏህ ቃል ከሚያካታቸው መካከል...

O ምንዳ የሚሆነው በፍትህ እንደሆነ O አንድ ባርያ የሚሰራው ስራ በተጨባጭ የ/በራሱ እንደሆነ O ቀድመው የተጠቀሱት ሁሉ መልስ ናቸው O ምንዳ በስራ ብቻ እንደሆነ

ፈተና ከአየተል ኩርሲይ አንቀፅ ማብራርያ

34. ለአየቱል ኩርሲይ አንቀፅ ይህ ስያሜ የተሰጣት ***ኩርሲይ*** የተጠቀሰበት አንቀፅ ስለሆነች ነው (እውነት – ሃሰት)

35. በቁርአን ውስጥ ታላቋ አንቀፅ የትኛዋ ነች? O ስለእዳ የምትዳስሰዋ አንቀፅ O . አስሩ መብቶች የተወሳባት አንቀፅ Oአየተል ኩርሲይ

36. ቁርአን ከመልዕክት አንፃር ልዑል ነው (እውነት – ሃሰት)

37. ከአሏህ መልካም ስያሜዎች መካከል በአየተል ኩርሲይ ላይ የተወሱት የአሏህ ስያሜዎች ስንት ናቸው?

O አምስት O ስድስት O ሰባት

38. "**ሕያው**" የሚለው የአሏህ ስም ከምን አንፃር ምሉእነትን ይዟል…

O አካላዊ O ስልጣናዊ

39. "**ራሱን ቻይ**" የሚለው የአሏህ ስም ከምን አንፃር ምሉእነትን ይዟል…

O አካላዊ O ስልጣናዊ

40. "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" የሚሉት ቃላት በሚቆራኙበት ጊዜ ስልጣናዊ እና አካላዊ ምሉእነትን ይጠቁማሉ። (እውነት – ሃሰት)

41. "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" የሚሉት የአሏህ ስያሜዎች በቁርአን ላይ ተቆራኝተው የተደጋገሙበት ቦታ፡ …

O በሶስት ቦታ O በአራት ቦታ O በሁለት ቦታ

42. የውግዘት ባህርያትን አሏህ ከራሱ መልዕክተኛውም ከሱ እንዳወገዙት እኛም ልናወግዛቸው ግድ ነው፤ ተቃራኒው የሆነውን ምሉእነት ከማፅደቅም ጋ፤ ምክንያቱም ማውገዝ ብቻውን ምሉእነት አይደለምና። ለምሳሌ፡ ካለው የተሟላ "**ሕያው**" እና "**ራሱን ቻይ**" ማንነት አንፃር ማንገላጀትንና እንቅልፍን ከሱ እናወግዛለን (እውነት – ሃሰት)

43. አሏህ ለተደሰተበት ካልሆነ በቀር ለማንም በሸፈዓ አይፈቅድም፤ የሚደሰትም አይደለም

ከ_____ ሰዎች ቢሆን እንጅ።

O ተውሒድ O . የነብየ ﷺ ሱና ተከታይ. O የተጠቀሱት ሁሉ መልስ ናቸው

44. አሏህ ፍጡራኑን ያሳወቃቸው ሸሪዓዊም ይሁን አለማዊ እውነታ...

O ትንሽ ነው O .ብዙ ነው

45. **"ከፊታቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል" አሁን** ያለው እና የወደፊቱን ማለት ሲሆን **"ከኋላቸው ያለውም"** ማለት ያለፈ ማለት ነው። (እውነት - ሐሰት)

46. "**አል-ዓልይ (የሁሉ በላይ...")**" የሚለው የአላህ ስም ትርጉም፡

O በአካሉ O በባህርያቱ O ፍጡራንን ሁሉ አሸናፊ የሆነ O ሁሉም

47. ከመተኛቱ በፊት የሚያነበው ሰው ከአላህ ዘንድ የጠበቀ መከላከያም አለው፤ እስኪነጋም ድረስ ሸይጧን አይቀርበውም። ምንድን ነው?

O የሱራ አል-በቀራህ መጨረሻ አንቀፆች O አየተል ኩርሲይ

48. አየተል ኩርሲይን መቅራቱ ይመከራል... O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ

Oከምኝታ በፊት O ጧትና ማታ O ሁሉም መልስ ነው

የሱረቱል ዘልዘላህ ማብራርያ ፈተና

49. ሱረቱል ዘልዘላ ... O መኪይ ነች O መደንይ ነች

50. ሱረቱል ዘልዘላ በውስጧ ከያዘችው መካከል...

O ማስጠንቀቅ O ማበረታታት O ሁሉም መልስ ነው

51. "**ምድር (በኀይል) መንቀጥቀጥዋን በተንቀጠቀጠች ጊዜ፤**" የሚለው የአሏህ ቃል **«ትክክል ሜዳም ትኾናለች። በርሷ ላይ ዝቅታና ከፍታ የሌለባት»** ከሚለው ቃሉ ጋ ተነፃፃሪ ነው: (እውነት- ሃሰት)

52. "**ምድርም ሸክሟን ባወጣችም ጊዜ**" ማለት O ተራራና ኮረብታዋን O ሙታንና ድልቧን

53. ምድር በባርያዎች ላይ ከሚመሰክሩ የመስካሪዎች ጎራ መካከል አንዷ ነች። (እውነት – ሃሰት)

54. **“የተለያዩ ኾነው”** የሚለው የአሏህ ቃል የተፈለገበት…

O እያንዳንዱ ራሱን ችሎ O የሚበላለጡ ጎራዎች

55. **"የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል።..."** የሚለው የአሏህ ቃል "የሰሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ኾኖ ያገኙታል።..." እንደሚለው የአሏህ ቃል ነው (እውነት – ሃሰት)

ከሱረቱል ዓዲያት ማብራርያ ፈተና

56. ሱረቱል ዓዲያት … Oመደንይ ነች Oመክይ ነች

57. *"ዓዲያት"* የሚለው ቃል ትርጉም …

O ፈረሶች O ተንቀሳቃሽ ሁሉ Oሁሉም መልስ ነው

58. **ሱረቱል ዓዲያት** ግዴታ የሆኑ መብቶችን ያለመወጣትን ማስጠንቀቅን ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

59. የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ግለፅ:

“ዶብሐን”: ……...

“ቀድሐን”: ……...

“ነቅዐን”: ……...

“ለከኑድ”: ……...

ከሱረቱ አል-ቃሪዓህ ማብራርያ ፈተና

60. ***ሱረቱል ቃሪዓህ*** … O መክይ ነች Oመደንይ ነች

61. ከሱረቱል ቃሪዓህ ተፈላጊ ነጥቦች መካከል ከ _____ማስጠንቀቅን ይዛለች:

Oየእለተ ቂያማ አስደንጋጭ ሁኔታዎች O የዱንያ ፈተና

62. **አልቃሪዓህ** የተባለው ምኑን ነው O የዛቻ አንቀፆች O እለተ ትንሳኤ

63. የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም አብራራ:

"እንደ ተበታተነ ቢራቢሮ (ወይም ኩብኩባ)" ……

"እንደ ተነደፈ ሱፍ " .....

64. በዝህች ሱራ የተወሳው **ሚዛን** ...O ትክክኛ ሚዛን. O የፍትህ ዘይቤአዊ ገለፃ

65. "በምትወደድ ኑሮ" ማለት O ዱንያ O ጀነት

66. "መኖሪያው ሃዊያህ ናት " ማለት:

O እንደማትለየው የሆነችው እናቱ ትሆናለች O መሃል አናቱ የእሳቱ ውስጥ ማገዶ ነች።

O ሁሉም መልስ ነው

67. "እርሷም ምን እንደ ኾነች ምን አሳወቀህ?!" የሚለው ቃሉ

O የጉዳይዋን ከባድነት ለመጠቆም ነው O ጥያቄ ነው

68. አሏህ ይጠብቀንና ከእሳቲቱ ስያሜዎች መካከል:

Oአል ሃዊያህ Oጀሃነም Oአል ሑጦማህ

Oለዛ O ሰዒር Oሰቀር

Oሁሉም መልስ ነው

69. "(እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።" –ከሷ በአሏህ እንጠበቃለንና- ቃጠሎዋ ከዱንያዋ እሳት ቃጠሎ በስንት እጥፍ ትበልጣለች?

O በሰባ O በዘጠና O በዘጠና ዘጠኝ

ፈተና ከሱረት አት-ተካሡር ማብራርያ

70. ይህች ሱራ ... O መክይ ነች O መደንይ ነች

71. ይህች ሱራ በውስጧ _____ ይዛለች

O ስለሰዎች ሁኔታ መናገርን O የመፈጠራቸው አላማ ለመዘናጋታቸው ባርያዎቹን መውቀስን

72. ይህች ሱራ የተፈለገበት የአሏህ ፊት እንኳ ቢሆን መፎካከርን ትከለክላለች። (እውነት – ሃሰት)

73. ሰው ሲሞት "ወደ መጨረሻ መኖርያው ሄደ" የሚለው አገላለፅ:... O ከሞት በኋላ

መቀስቀስን ያወግዛል O ይቻላል

74. "እስከ ጎበኛችሁ ድረስ..." በሚለው ቃል ዘያሪዎች ብሎ ገለፃቸው እንጅ ነዋሪዎች ብሎ አይደለም የገለፃቸው። ለምን?

O የበርዘኽ(የቀብር) ህይወት ዋና እሳቤው ወደመጨረሻው ሃገር መሸጋገር የሆነ አገር በመሆኑ

O ከራሳቸው የሆነው የዱንያ መኖርያ ቤት የራሳቸው ወዳልሆነው የመቃብር ቤት ስለተሸጋገሩ

75. እውቀት ወደ ሶስት ይከፈላል፡ ተጨባጭ እውቀት፣ ተጨባጭ እይታ እና ተጨባጭ እውነታ (እውነት-ሃሰት)

ከሱረቱ አል-ዓስር ማብራርያ ፈተና

76. ሱረቱል ዓስር... O መካይ ነች O መደንይ ነች

77. ሱረቱል ዓስር አራት ቁምነገሮችን ትጠቁማለች፡ እውቀት፣ ባወቁት መስራት፣ ጥሪ ማድግና ትዕግስት። (እውነት – ሃሰት)

78. ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማልን በማስመልከት ትክክለኛው አገላለፅ የትኛው ነው?

O አሏህ ከፍጡራኑ በፈለገው መማል ይችላል Oፍጡራን ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማል አይችሉም O ፍጡራን ከአሏህ ውጭ ባለ አካል መማል ይችላሉ O የመጀምርያውና የሁለተኛው መልሶች ብቻ ትክክል ናቸው

79. **ትዕግስት** _____ ወደ ይከፈላል O ወደ ሁለት O ወደ ሶስት O ወደ አራት

80. ሱራዋ አራት ትዕዛዞች አሏት፤ ብሁለቱ ትዕዛዞች አንድ ባርያ ራሱን ሙሉ የሚያደርግበት ሲሆን በሌሎቹ ሁለቱ ደግሞ አንድ ባርያ ሌላውን ሙሉ የሚያደርግበት ነው። (እውነት – ሃሰት)

የሱረቱል ሁመዛህ ማብራሪያ ፈተና

81. ይህች ሱራ... O መካይ ነች O መደንይ ነች

82. "ወይል" የሚለው ቃል ትርጉም...

O ጀሃነም ውስጥ ያለ ሽለቆ O ጀሃነም ውስጥ ያለን ሸለቆ እና ከዛም በላይ ያካተተ ዛቻ

83. አል-ሃምዝ የሚባለው በቃል የሚደረገውን ሲሆን አል-ለምዝ የሚባለው በድርጊት የሚደረገውን ትንኮሳ የሚመለከት ነው። (እውነት – ሃሰት)

84. "ገንዘቡ የሚያዘወትረው መኾኑን ያስባል።!" ከሚለው ቃሉ በጎነት በእድሜ የሚጨምር መሆኑን እንረዳለን። (እውነት – ሃሰት)

85. "ምን አሳወቀህ?" ከሚለው ቃሉ የምንረዳው ነብዩ ﷺ... O ያውቋታል O አያውቋትም

86. ''የተነደደችው የአላህ እሳት ናት። '' በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃሉ ላይ የእሳት ማገዶው... O ሰዎች O ድንጋይ O ሁለቱም መልስ ናቸው

87. "በልቦች ላይ የምትዘልቅ የኾነችው።" በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃል የተፈለገው እሳቲቱ: O የሚታሰበው O ሰውነትና አልፋ ልቦና ድረስ ትዘልቃለች

የሱረቱል ፊል ማብራሪያ ፈተና

88. ሱረቱል ፊል ሱራዋ ... O መካይ ነች O መደንይ ነች

89. በየብሱ ላይ ካሉት ፍጥረቶች ሁሉ ታላቋ ፍጥረት ከአሏህ ቤቶች መካከል በአንዱ እንኳ ድንበር እንዳታልፍ ትሰጋለች፤ የሰው ልጅ ደግሞ ለስጋቱ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። (እውነት – ሃሰት)

90. ነብዩ ﷺ የተወለዱበት አመት በአረቦች የ_____ አመት ይባላል። O የዝሆን O የሃዘን O የድርቅ

91. ይህች ሱራ ከነብዩ ﷺ መላክ በፊት የነበረ ከተለምዶ ውጭ የሆነ ለሳቸው ሲባል የተገለፀ ነብያዊ ተአምሮች የሚካተት ነው። (እውነት – ሃሰት)

92. የተከታዮቹን ሃረጎች ማብራሪያ ግለፅ:

"...መንጎች የኾኑን ዎፎች..."……

"... እንደ ተበላ አዝመራ..." ……

ከሱረቱል ቂረይሽ ማብራሪያ ፈተና

93. ***ሱረቱል ቂረይሽ***...O መክይ ነች O መደንይ ነች

94. ይህች ሱራ ከ____ ሱራ ጋ ቁርኝት አላት O አል-ካፊሩን O አል-ፊል O አን-ናስ

95. የቂረይሾች ጉዞ በክረምት ወደ ሻም በበጋ ደግሞ ወደ የመን ነበር። (እውነት – ሃሰት)

96. አሏህ የመካን እና የሰዎቹን ክብር በሌሎች ዓረቦች ልቦና ዘንድ እስኪያከብሯቸውና እስከማይጋረጡባቸው ድረስ አልቋቸዋል። O በመካ ሳሉ O በመካም ጉዞም ላይ ሆነው

97. አሏህ ጌትነቱን ከካዕባ ጋ አቆራኝቶ ያመጣው ላለው ክብር እና በላጭነት እንጅ እሱ የሁሉም ጌታ ነው። (እውነት – ሃሰት)

98. **“ስለዚህ የዚህን ቤት (የከዕባን) ጌታ ይግገዙ።።”** የሚለው ቃል አገላለፅ ፍጡርን ከክብር አንፃር ወደ ፈጣሪ ማስጠጋት ነው። (እውነት – ሃሰት)

የሱረቱል ማዑን ማብራሪያ ፈተና

99. ሱረቱል ማዑን... O መክይ ነች O መደንይ ነች

100. **"أَرَأَيْتَ الَّذِي يُكَذِّبُ بِالدِّينِ"** በሚለው ከፍ ያለው አሏህ ቃል “ዲን” በሚለው የተፈለገበት... O ከሞት በኋላ መቀስቀስ እና መመንዳት Oግዴታንና መብቶችን ማውገዝ

101. “**فَذَٰلِكَ الَّذِي يَدُعُّ الْيَتِيمَ**” በሚለው የአሏህ ቃል '**يَدُعُّ** ” ማለት... O የሚተው O በጭካኔ የሚገፈትር

102. የቲም የሚባለው _____ የሞተበት ነው። O አባቱ O እናቱ

103. የቲም የሚባልበትም ... O ለአቅመ አዳም እስካልደረሰ O ቢያድግም

104. በሶላት ውስጥ መርሳት ባለቤቱ ሊወቀስበትና ሊወገዝበት የሚገባ የሆነው ሲሆን ሶላትን መርሳት ግን ከየትኛውም ሰው ሊከሰት የሚችል ጉዳይ ነው። (እውነት – ሃሰት)

105. ሪያእ(ይዩልኝ ይስሙልኝ) ኢስላማዊ ፍርዱ... O የተፈቀደ O የተወገዘ

O የተከለከለ(ሓራም) O ትንሹ ሽርክ O ትልቁ ሽርክ

106. በዚህ ሱራ ውስጥ ለሌሎች በጎ መዋልን የሚያበረታታ አለበት። (እውነት – ሃሰት)

107. በአንቀፁ "الْمَاعُونَ" ("ትውስት")ተብሎ የተወሳው …

Oመጣቀሚያ እቃ O መዋዋሱና መለጋገሱ ተለምዶ የሆነ ሁሉ

የሱረቱ አል-ከውሠር ማብራሪያ ፈተና

108. ሱረቱ አል-ከውሠር… O መከይ ነች O መደንይ ነች

109. አል-ከውሠር የተባለው … O ጅረት ነው O ብዙ መልካም ነገርና ታላቅ ፀጋ ነው

110. አሏህ እነኝህን ሁለቱን የአምልኮ አይነቶች -ሶላትና እርድን- ለይቶ ያመጣቸው ከአምልኮ በላጮቹ እና ታላላቅ መቃረቢያዎች በመሆናቸው ነው። (እውነት – ሃሰት)

111. "شَانِئَكَ" ማለት… O የሚጠላህ O የሚወቅስህ O የሚያሳንስህ Oሁሉም

112. "…እርሱ በእርግጥ (ዘሩ) የተቆረጠው ነው።" የሚለው የላቀው አሏህ ቃል የነብዩ ﷺ ወዳጅ የሆነ ሰው ትውስታ እና ውዳሴ እንደሚቀርለት ይጠቁማል። (እውነት – ሃሰት)

113. ለነብዩ ﷺ በርካታ ረዳቶች እና ተከታዮች እንደሚኖሯቸው በሱራዋ ውስጥ ጥቆማ አለባት። (እውነት – ሃሰት)

የሱረቱል ካፊሩን ማብራሪያ ፈተና

114. ሱረቱል ካፊሩን … O መከይ ነች O መደንይ ነች

115. ሱረቱ አል-ካፊሩን ከሱረቱል ፋቲሓ በኋላ በ_____ ሶላት በመጀመሪያው ረከዓ መቅራቱ ይመከራል።

O ሱብሒ ሱና O በመግሪብ ሱና O በጡዋፍ ጊዜ በሚሰገድ ሱና

O በዊትር O ሁሉም መልስ ነው

116. ከሽርክ ጋ የተቆራኘ አምልኮ… O ያልተሟላ አምልኮ

O አምልኮ አይባልም

117. "በል" በሚለው የተፈለገው ለ____ ነው። O ለነብዩ ﷺ

O ለነብዩም ﷺ በንንግሩ ሊፈለግበት ለሚያመቸውም ሁሉ

118. አልካፊሩን የተባሉት…

O የነብዩ ﷺ ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑት እንደ ክርስቲያንና አይሁድ መሰል ሁሉ

O የመካ ከሃዲያን

119. ይህች ሱራ ከሽርክ እና ጓዶቹ በልቦና፣ በአንደበትና በአካል በተጨባጭ መጥራራትን ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

120. በሱራው ውስጥ (የአንዱ አንቀፅ) መደጋገሙ…

O ካፋሩን ለማጠንከር ነው

O የመጀመሪያው የድርጊቱ አለመከሰትን የሚገልፅ ሲሆን የሁለተኛው ደግሞ መሰረታዊ መገለጫ ባህርይ እንደሆነ ለመጠቆም ነው።

የሱረቱ አል-ነስር ማብራርያ ፈተና

121. ሱረቱ አል-ነስር … O መካይ ነች O መደንይ ነች

122. ይህች ሱራ በውስጧ የምስራች፣ መረጃ፣ ትእዛዝና ጥቆማ ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

123. አሏህ ለዚህ ህዝብ(ኡማ) እንዲሁም ለዚህ ዲን ከሚታሰበው በላይ እና በአእምሮ ውል ሊል በማይችልበት መልኩ እዝነትና ርህራሄ አለው። (እውነት - ሃሰት)

124. በዝች ሱራ የነብዩ ﷺ የሞት ቀጠሮ እየተቃረበ እየተጠጋ መሆኑን ጥቆማ ይዛለች። (እውነት – ሃሰት)

125. የዚህን ሱራ ጭብጥ ተግባራዊ በማድረግ መልኩ ነብዩ ﷺ በሱጁዳቸው እና በሩኩዓቸው "سبحانك اللهم ربنا وبحمدك اللهم اغفرلي)" ማለትን ያበዙ ነበር። (እውነት – ሃሰት)

የሱረቱ አል-መሰድ ማብራርያ ፈተና

126. ሱረቱ አል-መሰድ … O መካይ ነች O መደንይ ነች

127. አቡ ለሃብ …

O የነብዩ ﷺ አጎት ነው O ከነብዩ ﷺ ጋ ዝምድና የለውም

128. እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ ሲወቀስ ይኖራል…

O አቡ ለሃብ ብቻ O ከነብዩ ﷺ ጋ ጠላትነት የመሰረተ ሁሉ

129. የተከታዮቹን ቃላት ትርጉም ግለፅ:

"تبت" ..... :تَبَّت

"ما كسب" ..... ማ ከሰብ

"جيدها" ..... :ጂዲሃ

"مسد" ..... :መሰድ

130. ይህች ሱራ አቡ ለሃብንና ባልተቤቱ ከአሏህ ተአምራት መካከል ይዛለች፤ ሁለቱም አልሰለሙም!(እውነት –ሃሰት)

የሱረቱ አል-ኢኽላስ ማብራርያ ፈተና

131. ሱረቱ አል-ኢኽላስ … O መካይ ነች O መደንይ ነች

132. ሱረቱ አል-ኢኽላስ በዚህ ስያሜ የተጠራችበት ምክንያት …

O ጥርት ባለ መልኩ ስለአሏህ ብቻ ስለምትገልፅ O የሚቀራትን ከሸርክ ስለምታጠራው

Oሁለቱም

133. ይህች ሱራ ከምንዳ አንፃር _____ ትስተካከላለች

O የቁርአኑን ግማሽ O የቁርአኑን ሩብ O የቁርአኑን አንድ ሶስተኛ

134. ሱረቱ አል-ኢኽላስ ከሱረቱል ፋቲሓ በኋላ በ_____ ሶላት በሁለተኛው ረከዓ መቅራቱ ይመከራል።

O ሱብሒ ሱና O በመግሪብ ሱና O በጡዋፍ ጊዜ በሚሰገድ ሱና

O በዊትር O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O በእንቅልፍ ሰአት O ሁሉም መልስ ነው

135. ሶስቱም የተውሒድ አይነቶች እስኪረጋገጡ ድረስ ሱረቱ አል-ካፊሩንና ሱረቱ አል-ኢኽላስን ቀንም ሌትም መቅራቱ ይመከራል። (እውነት – ሃሰት)

136. ሱረቱ አል-ኢኽላስ በይበልጥ ይዘታ...

O ተውሒድ አል-ኡሉሂያህ O ተውሒድ አል-ሩቡቢያ እና ተውሒድ አል-አስማእ ውሲፋት

137. "በል" ሲል ___ማለቱ ነው። O በቃል ብቻ O በቃል፣ በተግባርም በእምነትም

138. "በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።" ሲል በጌትነት፣ በአምላክነት እና በስምና ባህርያት ያለውን ብቸኛ ነው ማለቱ ነው። (እውነት – ሃሰት)

139. "«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።" ሲል ____ ማለቱ ነው።

O ለሁሉም ነገር ተፈላጊው O ያ ለራሱ ሁኖ የሌላውም ሁሉ ብቸኛ መጠጊያ የሆነ

O በአለቃነቱ፣ በጌትነቱ፣ በአምላክነቱ፣ በስምና ባህርያቱ የተሟላ የሁሉ አሳዳሪ የሆነ Oሁሉም

140. ልጅ ወይም ወላጅ አለው ብሎ ወደ ኋያሉ አሏህ ማስጠጋት ትልቁ ክህደት ነው። (እውነት – ሃሰት)

የሱረቱ አልፈለቅ ማብራርያ ፈተና

141. ሱረቱ አልፈለቅ ... O መክይ ነች O መደንይ ነች

142. ሱረቱ አልፈለቅን መቅራቱ ይመከራል በ...

O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O ልትተኛ ስትል O ሁሉም መልስ ነው

143. የተከታዮቹን ቃላት ግለፅ:

أعوذ: ..... *ኣዑዙ*

الفلق: ..... *ኣልፈለቅ*

غاسقٍ: ..... *ጋሲቂን*

وقبَ: ..... *ወቀብ*

النَّفَّاثات: ..... *ኣጉ ነፋሣት*

العُقَد: ..... *ኣልዑቀድ*

حاسدٍ: ..... *ሓሲዲን*

144. ይህች ሱራ በውስጧ ... ይዛለች። O ጥቅል በሆነ መልኩም ይሁን በዝርዝር የአሏህ ጥበቃን መሻት O የሲሕርን እውነትነት O ሁሉም

የሱረቱ አን-ናስ ማብራርያ ፈተና

145. ሱረቱ አን-ናስ ... O መክይ ነች O መደንይ ነች

146. ሱረቱ አን-ናስ መቅራቱ ይመከራል...

O ከግዴታ ሶላቶች በኋላ O በእንቅልፍ ጊዜ Oሁሉም መልስ ነው

147. 'አል-ሽናስ' ማለት ምን ማለት ነው?

.....

ሁለተኛው ትምህርት

ሁለተኛው ትምህርት-የኢስላም ማእዘናት

የአምስቱ ማዕዘናት ማብራርያ፡ የመጀመሪያውና ታላቁ ዓምድ - ‘‘ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ የለም ፣ መሐመድም ﷺ የአላህ መልእክተኛ ነው’’። የሚለው የምስክርነት ቃል ነው። ትርጉማቸውም ወደ ኋላ ከ‘‘ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ የለም’’ ቅድመ ሁኔታዎች ጋር ይብራራል ።

ትርጉሙ-‘‘إِلَٰهَ ’’ የሚለው ከአላህ ሌላ የሚመለኩትን ሁሉ የሚያወግዝ ነው። “ اللهَ إِلَّا ” ማለት ደግሞ አምልኮን ለአላህ ብቻ የሚያፀድቅ ነው።

የ ‘‘ اللهَ إِلَّا إِلَٰهَ ’’ ቅድመ መስፈርቶች ደግሞ፡

1 -እውቀት፡ ድንቁርናን የሚጋፈጥ። 2 - እርግጠኛነት፡ ጥርጣሬን የሚጋፈጥ።

3- ኢኽላስ፡ ሽርክን የሚጋፈጥ 4- እውነተኝነት፡ ውሸትን የሚጋፈጥ

5- ጥላቻን በሚጋፈጥ ውዴታ 6- መጎተት፡ መተውን የሚጋፈጥ

7 - መቀበል፡ ማፈግፈግን የሚጋፈጥ 8- ከአላህ ሌላ በሚመለኩ ነገሮች ሁሉ መካድ።

ይህም በቀጣዮቹ ሰንኞች ተጠቃልሎ እናገኘዋለን፡

እውቀት፣ እርግጠኝነት፣ እንዲሁም ኢኽላስህ

እውነተኝነት፣ ውዴታ፣ ለትእዛዙም መጎተትህ

ተቀብሎ አፅድቆ በሌላው ተመላኪ መካድህ

ይህ ነው ተፈላጊው የእምነት መሰረትህ።

እንዲሁም በሙሐመድ መልዕክተኝነት መመስከር ግድ የሚያስብላቸው ግዴታዎች ደግሞ፡ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፣ ባዘዙትም መታዘዝ፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉትም መራቅ እና እሳቸው በደነገጉት እንጅ አሏህን አለማምለክ ናቸው። ከዚያም ለተማሪው ቀሪዎቹን የኢስላም ማዕዘናት ይብራራሉ። እነሱም፡ ሶላት፣ ዘካ፣ የረመዷንን ወር መፆም፣ መንገዱን ለቻለ በተከበረው የአሏህን ቤት ሐጅ ማድረግ ናቸው።

የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

የ "“لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ”" ማእዘናት

ማውጣዝ: "በእውነት የሚመለክ የለም..."

ከአሏህ ውጭ የሚመለከውን ሁሉ ያወግዛል

(በጣኦት መካድ)

ማፅደቅ: "... ከአሏህ በቀር"

አምልኮን ለአሏህ ብቻ ያፀድቃል

(በአሏህ ማመን)

ይህች ከአሏህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው የለም የምትለው የኢኽላስ ቃል ሁለት ቅድመ መስፈርቶች አሏት፤ እነሱም ማፅደቅና ማውገዝ ናቸው።

የ “ላ ኢላሃ ኢላ አላህ” ቅድመ ሁኔታዎች ማብራርያ

የ ”ላ ኢላህ ኢለሏህ” ሁኔታ እንደ ቁልፍ ጥርሶች ነው። ”ላ ኢላሃ ኢለሏህ” ደግሞ በርግጥም የጀነት ቁልፍ ነች። ቁልፍም ጥርሶች ከሌለው በስተቀር አይከፈትም። በቁርአንና በሃዲስ ውስጥ የሚገኘውን “ላ ኢላሃ ኢላ አላህ” ለሚለው ማንኛውም እንዲህ እንዲህ አለው ተብሎ ምንዳ የተወሰበት ሁሉ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎችን በተጨባጭ ማረጋገጡ ላይ የተመረኮዘ ነው። ቅድመ ሁኔታዎቹም ስምንት ናቸው፡

1- ትርጉሚን ማወቅ፡ ተቃራኒውም ትርጉሚን አለማወቅ ነው። ትርጉሚን የማያውቅን ሰው አትጠቅመውም። ስለሆነም እስልምናን ለመቀበል ለሚፈልግ ሰው ትርጉሙን ማወቅ ይጠበቅበታል። ነብዩ ﷺ ”ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው አምላክ አለመኖሩን እያወቀ የሞተ ጀነት ገባ።” ብለዋል። (ሙስሊም ዘግበውታል)

2 - እርግጠኛነት - ማለትም መቶ በመቶ (ያለጥርጥር)። አንድ ሰው ከአላህ ሌላ ባሉ አማልክት መካድ እንዳለበት አንድ በመቶ እንኳ ቢጠራጠር ወይም ቢያመነታ እሱ/እሷ ሙስሊም አይደለም/ችም። አንድ ሰው ስለነዚያ የነብዩ ﷺ ጥሪ የደረሳቸው አይሁዶች እና ክርስቲያኖች ክህደት የሚጠራጠር ከሆነ ሙስሊም አይደለም። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል-“እኔ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እና እኔም የአሏህ መልዕክተኛ መሆኔን እመሰክራለሁ። በእነዚህ ሁለት የምስክርነት ቃላት የማይወላዳ ሆኖ ጌታውን አሏህን የሚገናኝ አንድም ባርያ የለም ጀነት የገባ ቢህን እንጅ።” (ሙስሊም ዘግበውታል)

3- ኢኽላስ: መቶ በመቶ ለአሏህ ሊሆን፤ ምንም አይነት ይዩልኝ ወይም ይስሙልኝ ካለው ወይም ከአላህ ሌላ የሚያመልክን አይጠቅምውም ።

ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል-"በምልጃዬ በጣም እድለኛ የሆነው ሰው‹ ላ ኢላሃ ኢላ አላህ › ብሎ ከልቡ በኢኽላስ የሚመሰክር ሰው ነው ።" (ቡኻሪ)

4- እውነተኝነት-እንደ ሙናፊቆች አይነቱ ዋሽቶ የሚልን ሰው አትጠቅመውም። ነብዩﷺ እንዲህ ብለዋል-‹ላ ኢላሃ ኢለሏህ (ከአሏህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው የለም) መሐመድም የአሏህ ባርያ እና መልዕክተኛ ናቸው ብሎ ከልቡ የሚመሰክር የለም፤ አሏህ ከእሳት እርም የሚለው ቢሆን እንጅ።" (ቡኻሪ እና ሙስሊም)።

5- ውዴታ፡ አንድ ሰው አሏህን ሊወድ እና አንድንም እንደሱ ላይወድ ነው። በተጨማሪም አንድ ሰው አላህ እንዲወደድ ያዘዘውን ነገር ሁሉ መውደድ አለበት እና ተቃራኒውም ጥላቻ ነው። ለዚህም ነው ኢስላምን ከሚያፈርሱ ነገራቶች የሚመደበው። መልእክተኞች ይዘውት ከመጡት አንዳችንም ነገር መጥላት ቢሰራበትም እንኳ ከሃዲ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል-" ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አልሉ። ..." (አል-በቀራ 165)።

6- መጎተት፡ ይህም ማለት በሷው መስራት ግዴታ ነው ማለት ነው። በሷው የማይሰራን ሰው አትጠቅመውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል "በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።" (አን ኒሳእ 65)

7- መቀበል፡ አንድ ሰው በመልእክቱ፣ በተግባሩም ሆነ በእምነቱ መቀበል አለበት። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል "እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ። እኛ ለዕብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉም ነበር። "(35-36)

8- መካድ: ማለትም ከአሏህ ውጭ የተመለከ ሁሉ አምልኮው ውድቅ ነው። ከአሏህ ውጭ ሊመለክ የሚገባው የለምና።

ማሳሰቢያ፡

የኢኽላስ የምስክርነት ቃል ማመኑ፣ መናገሩ እና በተግባር ማዋሉ የግድ ነው።

የመውደድ(ፍቅር) አይነቶቹ

ተፈጥሯዊ ፍቅር

አሏህን ከመውደድ በፊት እስካልተቀደመ ድረስ የሚፈቀድ ነው። ለምሳሌ: ልጅን እና ባለቤትን መውደድን ይመስል።

የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ ''**እኔ እሱ ዘንድ ከልጅ፣ ከወላጁም ሆነ ከመላው የሰው ልጅ በላይ እሱ ዘንድ የተወደድኩ እስካልሆንኩ ድረስ አላመነም።** ''

ለአሏህ ብሎ መውደድ

ይህ ግዴታ ብሎም ታማኝ የኢማን ዘለበት ነው።

አሏህ ﷻ እንዲህ ብሏል: "*የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው።* ..." (48:29).

ከስር ባሉት አራት ነገራቶች ይገለፃል:

- **አሏህ ዘንድ የተወደዱ ድርጊቶች ያም እንደ ተውሒድ ያለውን ሸሪዓ ይዞት የመጣውን ሁሉ ማለት ነው።**
- **በሱ ሰሪዎች፡ እንደ ነቢያት ፣ ሩሱሎች፣ መላእክቶች ፣ ሱሓቦችና እና እያንዳንዱ የተውሒድ ሰው።**
- **ለአላህ የተወደዱ ጊዜያት፡ እንደ ለይለቱል ቀድር እና የእያንዳንዱ ምሽት አንድ ሶስተኛ ክፍል ያሉትን ይመስል።**
- **እንደ መካ እና መዲና ያሉ አላህ ዘንድ የተወደዱ ቦታዎች።**

ከአሏህ ጋ (እኩል) ማፍቀር

ይህ ከትልቁ ሽርክ ነው። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል **"ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ኾነው የሚይዙ አልሉ።"** (አል በቀራ :165).

የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

ሙሐመዱን ረሱሉሏህ በሚለው የምስክርነት ቃል “ዓብዱህ(ባርያው ናቸው)” ስንል ምን ማለታችን ነው?

እርሱ ከፍጥረቱ ሁሉ እጅጉን በላጩ የአሏህ ባርያ ነው። ለአላህ የሚገባውን አምልኮ በፍጹም ያረጋገጠ ብቸኛ ነው።

እሱ በ‹ጌትነት› ፣ በአምልኮም ሆነ በአላህ ስሞች እና ባህሪዎች ውስጥ ምንም ድርሻ ስለሌለው ﷺ ሊመለክ የሚገባው አይደለም ማለት ነው።

ለአሏህ ተገቢ የሆነው ተገዥነት (ማጎብደድ) አይነቶቹ፡

የልዩ ልዩ የሆነው

ይህ ደግሞ የመልዕክተኞች _ዓለይሂሙ ሶላት ወሰላም_ ለአሏህ ያላቸው ታዛዥነትን የሚጠቁም ነው። **"... እርሱ በብዙ አመስጋኝ ባሪያ ነበርና።"** (አል ኢስራእ 3) ይህች ወደ ባርያዎች የተጠጋችዋ የተገዥነት አይነት የልዩ ልዩ ነች። ምክንያቱም የነኝህን መልዕክተኞች ተገዥነት ጋ የሚፎካከር አንድም አካል የለምና።

ልዩ የሆነው

ይህ አጠቃላይ የታዛዥነት ማጎብደድ ነው: ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል " **የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚኼዱት... ናቸው"(**አል ፉርቃን 63). ይህ በድንጋጌዎቹ አሏህን የተገዛን ሁሉ ያጠቃልላል።

ጥቅል የሆነው

ይህ የአጠቃላይ ፍጥረት ለአሏህ ﷻ ጌትነት (አሸናፊነት) ያላቸው ማጎብደድ ነው። ከፍ ያለው አሏህ እንዲህ ይላል፡ **(በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም)** (መርየም 93). በዚህም አጠቃላይ ሙእሚኑም ከሃዲውም ይካተታል።

የነብዩ ﷺ አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ

እሳቸው-መሐመድ ኢብኑ ዓብዱላህ ኢብኑ ዓብዱል-ሙጦሊብ ኢብን ሀሺም ፣ ሃሺም ከቁርይሽ ሲሆን ፣ ቁረይሽም ደግሞ ከዓረቦች የመጣ እንዲሁም አረቦችም ደግሞ ከኢስማዒል ኢብኑ ኢብራሂም አል-ኸሊል (የአሏህ ተወዳጅ) ናቸው። ዓለይሂሙ ሶላት ወሰላም

ዘራቸው

የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

ውልደት	እሳቸው የተወለዱት በመካ፤ በወርሃ ረቢዐል አወል ነው። በህይወት የኖሩት ለ63 አመት ሲሆን ከዚህም 40ውን ከነብይነት በፊት 23 አመቱ ደግሞ ነብይ እና ረሱል ሆነው ነው። እሳቸው ወላጅ አልባ ሆነው ነበር ያደጉት። ወላጅ አባታቸው ከመወለዳቸው በፊት የሞቱ ሲሆን በአያታቸው ዓብዱል ሙጦሊብ ሃላፊነት ስር ሆኑ። ከአያታቸው ሞት በኋላ ደግሞ አጎታቸው አቡ ጧሊብ ነው ያሳደጋቸው።
መላካቸው	እሳቸው ﷺ ወደ ሁለቱም ከባባዶች የሰው ልጅና አጋንንት ነው የተላኩት። የሳቸው ተልዕኮ መልእክት ደርሶት በሳቸው ያላመነ ግን ማንም ይሁን ማን ከእስልምና የሚያወጣውን አይነት ትልቁ ክህደት ላይ ያረፈ ካፊር ነው።
ጥሪያቸው	የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ ወደ ተውሒድ፣ ወደ መልካም ባህሪ እና ወደ መልካም ስነምግባር ነው ጥሪ ያደረጉት። ከአላህ ሌላን ከማምለክ፣ ከመጥፎ ሥነምግባር እና ከመጥፎ ተግባራት አስጠንቅቀዋል።
የኢስራእ እና ሚዕራጅ ጉዞ	እሳቸው ﷺ ከመካ ወደ በይተል መቅዲስ አርገዋል። ከዚያም ወደ ሰባተኛው ሰማይ አርገው አሏህም አናግሯቸው እዛው ባሉበትም አምስቱ የሶላት ወቅቶች ተደንግጎባቸዋል።
ሂጅራ እና ሞት	እሳቸው ﷺ ከመካ ወደ መዲና ተሰደው እዚያው ሞተው በምእመናን እናት ዓኢሻ(ረዲየሏሁ ዓንሃ) ቤት ውስጥ ተቀበሩ።
ተልዕኳቸው	አላህ ዲኑን በሳቸው አሟልቷል። ተልዕኪቸውን ግልጽ በሆነ መልእክት አስተላልፈዋል። አደራቸውን ተወጥተዋል። ህዝባቸውን መክረዋል፤ በየትኛውም የትግል አይነት በአሏህ መንገድ እውነተኛውን ትግል ታግለዋል። በመሆኑም ማንም ቢሆን በዚህ ሃይማኖት ውስጥ ማንኛውንም አይነት አዲስ ነገር ሊያክል አይመቸውም።

የሁለተኛው ትምህርት ማብራርያ

ሰባት ናቸው: በድር፣ ኡሑድ፣ አልኽንደቅ፣ ኸይበር፣ የመካ መከፈት፣ ተቡክና ሑነይን ናቸው።	አሳሳቢ የሚባሉት ዘመቻዎቻቸው
አል ቃሲም ፣ ኢብራሂም ፣ አብዱሏህ እሱም ነው ጦይቡ ጧሂር የሚባለው፣ ዘይነብ ፣ ሩቅያ፣ ኡም ኩልሡም፣ ፋጢማ ይባላሉ። ከፋጢማህ ውጭ ሌሎቹ ሁሉም እሳቸው በህይወት እያሉ የሞቱ ናቸው። ፋጢማም የሞተችው ከሳቸው ሞት ከስድስት ወር በኋላ ነው። አሏህ ሁሉንም መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና	ልጆቻቸው ሰባት ናቸው
ኸዲጃ ፣ ዓኢሻህ ፣ ሰውዳህ ፣ ሓፍሷ ፣ ዘይነብ አል ሂላሊያህ ፣ ኡሙ ሰላም ሂንድ ፣ ዘይነብ ቢንት ጀሕሽ ፣ ጁወይሪያ ቢንት አል ሓሪሥ ፣ ሶፊያ ቢንት ሑየይ ፣ ኡሙ ሓቢባ ረምላ ፣ ረይሓናህ ቢንት ዘይድ እና መይሙናህ ቢንት አል ሓሪሥ። አሏህ ሁሉንም ስራቸውን ይውደድላቸውና።	12ቱም ባልተቤቶቻቸው
እናታቸው አሚናህ ቢንት ወህብ፣ ሡወይባህ የአጎታቸው አቢ ለሃብ ነፃ የወጣች አገልጋይ፣ ሓሊማህ ቢንት አቢ ዙአይብ አስ-ሰዕድያህ (ረዲያሏሁ ዓንሃ)።	አሳቸውን ﷺ ያጠቡ
በሱረቱል ዓለቅ ላይ ያሉት ተከታዮቹ አንቀፆች: "**አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም።** 1. **ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።** 2. **አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤** 3. **ያ በብርዕ ያስተማረ።** 4. **ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን።** 5."	መጀመርያ ወደ እሳቸው ﷺ የወረዱት የቁርአን አንቀፆች
ከወንዶች አቡበከር አስ-ሲዲቅ ሲሆኑ ከሴቶቹ ደግሞ የአማኞች እናት ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ እንዲሁም ከልጆች ዓልይ ኢብኑ አቢ ጧሊብ። ከአገልጋዮች ዘይድ ኢብኑ ሓሪሣህ እና ከባሪያዎ ደግሞ ቢላል ኢብን አቢ ረባሕ ናቸው። አሏህ ሁሉንም መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና።	መጀመርያ በሳቸው ﷺ ያመነ

እሳቸው ﷺ 4 ጊዜ ሁሉንም በተለያየ አመት በወርሃ ዙል-ቀዒዳህ ሓጅ አድርገዋል። በአስረኛው አመተ ሂጅራ አንድ ጊዜ ያም የመሰናበቻውን ሓጅ ሓጅ አደረጉ።	የሳቸው ﷺ ሓጅና ዑምራቸው
ከፍ ያለው አላህ ለመልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ይላቸዋል: "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።"(አል ቀለም 4) አላህ ስራዋን ይውደድላትና የምእመናን እናት ዓኢሻም እንዲህ ብላለች: "ስነምግባራቸው ቁርአን ነበር።"	ስብእናቸው ﷺ
ኢብኑ አል ቀይም –አላህ ይዘንለትና እንዲህ ብሏል- በሁለቱም አገር ውስጥ የአንድ ሰው ደስታና ስኬት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ ጋር የተገናኘ ከሆነ እራሳቸውን ለሚመክሩ እና ስኬታማ ለመሆን እንዲሁም ደስተኛ ለመሆን ለሚወድ ሁሉ ከማያውቁት በማይሆንበትና በሚለይበት እንዲሁም በተከታዮቻቸው፣ በጭፍሮቻቸው እና በጓዶቻቸው ጎራ በሚሰለፍበት መልኩ ስለ መመርያቸው፣ ስለታሪካቸውና ስለጉዳያቸው ማወቁ የግዱ ነው። ሰዎችም በዚህ ረገድ ይለያያሉ፡ ትንሽ የሚያውቅ አለ፤ ብዙ የሚያውቅም አለ፤ የተነፈገም አለ፤ መበላለጡ አሏህ ለፈለገው የሚሰጠው የአሏህ ችሮታ ነው። አላህም የታላላቅ ችሮታዎች ባለቤት ነው።	ታሪካቸውን የመማር አስፈላጊነቱ

ሶስተኛው ትምህርት

የኢማን ማእዘናት

የኢማን ማእዘናት ስድስት ናቸው፡ እነሱም- በአላህ ማመን፣ በመላእክቱ፣ በመፃህፍቱ፣ በመልዕክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀን ማመን እና በበጎውም ሆነ በክፉ ቀደር ከአሏህ መሆኑን ማመን ናቸው።

ኢማን እንደ ሸሪዓህ ያለው ፍች

ኢማን በአንደበት የሚባል፣ በልቦና እምነት ተደርጎ የሚያዝ እና በአካልም በልቦናም የሚተገበር ነው። አሏህን በመታዘዝ የሚጨምር በማመፅም የሚቀንስ ነው። ማስረጃውም፡ -

በአንደበት የሚገለፅ ለመሆኑ: የአሏህ ﷺመልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል: **“(የኢማን) ከፍተኛ ደረጃዋ ላ ኢላሃ የሚለው ቃል ነው።”**

በአካል የሚተገበር ለመሆኑ: የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል **“(የኢማን) ዝቅተኛ ደረጃዋ አስቸጋሪን ነገር ከምንገድ ማስወገድ ነው።”**

በልቦናዊ ተግባር የሚገለፅ ለመሆኑ: የአሏህ ﷺመልእክተኛ እንዲህ ብለዋል **“ሐያእም ከኢማን ነው”** (ሙስሊም)

ኢማን እንደሚጨምር ማስረጃው: ተከታዩ የአሏህ ቃል ነው: **"ማንኛችሁ ነው= ይህች (ምዕራፍ) እምነትን የጨመረችለት?”**(አትተውባ 124)

እንደሚቀንስ ማስረጃው : የአሏህ መልዕክተኛ ﷺ ቃል ነው **“ከአእምሮም ሆነ ከዲን ቅናሽ ... አላየሁም”** (ቡኻሪይና ሙስሊም)

የሶስተኛው ትምህርት ማብራርያ

ኢማን የሚጨምርባቸው ምክንያቶች

- ተውሒድን በተለይም የስምና ባህርያቱን አሃዳዊነት ማጥናት
- ለአሏህ ታዛዥነትን ማብዛት
- ከወንጀል መታቀብ
- ስለፍጥረታቱ ማስተንተን

ኢማን የሚቀንስባቸው ምክንያቶች

- ተውሒድን በተለይም የስምና ባህርያቱን አሃዳዊነት ማጥናትን መተው
- አሏህን መታዘዝ መተው
- ወንጀልን መዳፈር
- ስለፍጥረታቱ ማስተንተንን መተው

ስድስቱ የኢማን ማእዘናት

- በአሏህ ማመን
- በመላእክቶች ማመን
- ባወረዳቸው መፃህፍቶች ማመን
- በመልዕክተኞች ማመን
- በእለተ ፍፃሜ ማመን
- በቀደር በበጎውም በክፉውም ማመን

የመጀመርያው ማእዘን: በአሏህ ማመን

- በስምና ባህርያቱ ማመን
- በአሏህ ጌትነት ማመን
- በአሏህ አምላክነት ማመን
- በአሏህ ህልውና ማመን: ይህም በአራት መልኩ የሚሆን ነው:
  - **በተደነገገው**
    ኢብን ቀይም አሏህ ይዘንላቸውና በቁርአን ውስጥ የትኛዋም አንቀፅ የለችም ወደ አሏህ ብቸኝነት የምትጠቁም ብትሆን እንጅ።
  - **በተፈጥሯዊ ማንነት**
    የአሏህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል:
    “ተወላጅ ሁሉ በተፈጥሯዊ ማንነቱ ላይ ሆኖ ይወለዳል ወላጆቹ አይሁድ ወይም ክርስትያን ወይም ደሞ መጁሲይ ያደርጉታል እንጅ። ”(ቡኻርይ እና ሙስሊም)
  - **በተጨባጩ**
    በችግርና መከራ ሆነህ እጆችህን ወደ ሰማይ ከፍ አድርገህ፡ “ያ ረብ!” ስትል ይህ ችግርና መከራ በአሏህ ፍቃድ ተወግዶ ታገኘዋለህ።
  - **እንደ አእምሮ**
    እንደ አእምሯዊ አስተሳሰብ ምንም አይነት ግኙኝት ያለ አስገኝ ፍጥረትም ያለ ፈጣሪ ሊገኝ መቻሉን ሊቀበለው የሚችል አይደለም። **“ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?”** (አጥ-ጡር 35)

ሁለተኛው ማእዘን፡ በመላእክቶች ማመን

መላእክቶች፡ በማይዳሰሰው አለም ያለ ራሱን የቻለ አለም ነው። አሏህ ክብርሃን የፈጠራቸው፤ የማያምፁት ታዛዦች፤ መናፍስትም **“ቅዱሱ መንፈስ”** (አል በቀራ 87) አካልም **“መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፤...ክንፍ አድራጊ ለሆነው...”** (ፋጢር 1) አእምሮና ልቦናም **“ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጸም ጊዜ (ተማላጆቹ) «ጌታችሁ ምን አለ?» ይላሉ። ...”** (ሰባእ 23) እንዳላቸው እናምናለን። በነሱ ህልውናም ሆነ አሏህ ስለነሱ(እንደ ጅብሪል፣ ሚካኤልና ኢስራፊል ባለው) ከስያሜዎቻቸው ባሳወቀንም ስለ ባህሪዎቻቸውም **“አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም። የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።”** (ተሕሪም 6) ያለንን ስለስራዎቻቸውም ባሳወቀን እናምናለን።

ስለመላኢኮች (ሃላፊነት) በግል ከተነገረን መካከል

ከነዚህም መካከል ስምንቱ የዓርሽ ተሸካሚዎች፣ ወሕይ የማድረስ ሃላፊነት ያለው ጅብሪል፣ በዝናብ በኩል ሃላፊነቱ ያለበት ሚካኤል፣ በአጠቃላይ በነሱ እና ስለነሱ በጥቅሉም ይሁን በዝርዝር በመጣው እናምናለን።

ሶስተኛው ማእዘን፡ በመፃህፍቱ ማመን

ዘይቢያዊ ሳይሆን በትክክል የአሏህ ቃል መሆናቸውን፤ ከሱ የተወረዱ እንጅ የተፈጠሩ አለመሆናቸውን፤ አሏህ ከእያንዳንዱ ረሱል ጋ መፅሃፍ እንዳወረደ፤ በነሱ፣ ስለነሱ ስያሜ፣ መረጃ እና እስካተሻረ ድረስ ፍርድ ጥቅልም ይሁን በዝርዝር በመጣው እናምናለን። ቁርአንም ደሞ ከሱ በፊት የመጡትን (ተውራት/ኦሪት፣ ኢንጂል/ወንጌል፣ ዘቡር/መዝሙር፣ የኢብራሂምና የሙሳ ሱሑፎች) መፃህፍቶችን ሁሉ እንደሻረ እናምናለን።

አራተኛው ማእዘን፡ በመልዕክተኞች ማመን

ከአምላክነት መለያ ማንነት ምንም ድርሻ የሌላቸው የሰው ልጆች መሆናቸውን፤ የሚያመልኩ እንጅ የማይመለኩ መሆናቸውን፤ አሏህ እንደላካቸው እና ወሕይም እንዳወረደላቸው፤ በተአምራትም እንዳጠናከራቸው፤ እነርሱም አደራቸውን እንደተወጡ፣ ኡማውንም እንደመከሩ እንዲሁም በአሏህም መንገድ ትክክለኛውን ትግል እንደታገሉ ማመናችን ግዴታ ነው።

በነሱ፤ አሏህ ስለነሱ በጥቅሉም በዝርዝርም ስለስማቸው፣ ስለባህርያቸውና ስለነሱ በነገረን ሁሉ እናምናለን። የነብያቶች መጀመርያ አደም፣ የረሱሎች መጀመርያም ኑሕ፣ የነብያቶችም የረሱሎችም መደምደምያ ደግሞ ሙሐመድ መሆናቸውን፤ ከሱ በፊት የነበሩ ድንንጋጌዎች ሁሉ በሙሐመድ ሸሪዓ እንደተሻሩ፤ ከነሱም የቆራጥነት ባለቤት የተባሉትም በሁለት ሱራዎች (ሹራ እና አሕዛብ) የተጠቀሱት አምስቱ መሆናቸውን እናምናለን። ሶለዋቱሏሂ ወሰላሙሁ ዓለይሂም።

አምስተኛው ማእዘን፡ በመጨረሻው ቀን ማመን

ነብዩ ﷺ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው በነገሩን ሁሉ ማመንን የሚያጠቃልል ነው። የቀብር ፈተናን፤ በጥሩምባ መነፋቱ፤ የሰዎች ከቀብራቸው መነሳት፤ ሚዛን፤ የስራ መዝገብ፤ ሲራጥ፤ ሓውድ፤ ሸፋዓህ፤ ጀነት፤ ጀሃነም፤ የምእመናን ጌታቸውን በእለተ ትንሳኤ እና በጀነትማየታቸው፤ እና በሌሎችም በስሜት ህዋሳት ስለማይደረስባቸው የነገሩንን ሁሉ ይመስል።

ስድስተኛው የኢማን ማእዘን: በመጥፎውም በደጉም ቀደር ማመን

ማወቅም መፃፉ መፍለግና መፍጠሩ እሱው ነው ክንውኑ ሂደት የፍጡሩ

በሚለው ስንኝ አራቱም እርከኖች ይገኛሉ።

ማወቁ:

ጥራት ይገባውና አላህ ሁሉንም ነገር በጥቅሉም በዝርዝርም እንደሚያውቅ ማመን: "... **(ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል።...**" (አልበቀራ 255).

መፃፉ:

አላህ ሁሉም ነገር እስከዕለተ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ክንውን ሁሉ እንደፃፈው ማመን: ማስረጃውም ተከታዩ የአሏህ ቃል ነው፡ "**በሰማይና በምድር ውስጥ ምንም የተደበቀ ነገር የለም ገላጭ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ ያለ ቢኾን እንጅ።**" (ነምል 75).

መሻት:

አላህ የሻው እንደሚሆን አላህ ያልሻው ደሞ እንደማይሆንና ባርያም የራሱ ነፃ ፍላጎት እንዳለው ነገር ግን ከአላህ መሻት ስር መሆኑን ማመን: "**አሏህ የሻውን እንጅ የምትሹ አይደላችሁም**" (አትተክዊር :29)

መፍጠር:

የሰው ልጆችም ሌላውም ከድርጊቶቹ ጋ አላህ የፈጠረው መሆኑ፤ ማስረጃውም

"**«አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን።»** (አስ-ሷፋት 96)"

አራተኛው ትምህርት

የተውሒድ አይነቶች እና የሽርክ አይነቶች

ተውሒድ ሶስት ክፍሎች አሉት: **የጌትነት አሃዳዊነቱ፣ አምላካዊ አሃዳዊነቱ እና በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነቱ**

የጌትነት አሃዳዊነቱ: ጥራት ይገባውና አሏህ ሁሉንም ነገር የፈጠረ መሆኑን፣ የሁሉም ነገር አስተናባሪ መሆኑን እንዲሁም በዚህም ተጋሪ የሌለው መሆኑን ማመን ነው።

የአምልኮ አሃዳዊነቱ: ጥራት ይገባውና በእውነት ተመላኪው እርሱ መሆኑን፤ በዚህም ተጋሪ እንደሌለው ማመን ነው። ይህም ነው ደግሞ የ *"ላ ኢላሃ ኢላ ሏህ"* ትርጉም። ምክንያቱም ትርጉሟም ከአሏህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም ነውና። በመሆኑም የአምልኮ አይነቶች ባጠቃላይ ከሶላት፣ ከፆም እና ሌሎችም ለአሏህ ብቻ ማጥራቱ ግዴታ ነው። አንዳችንም ነገር ከሱ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ የሚፈቀድ አይደለም።

በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነት: ይህ ደግሞ በተከበረው ቁርአን፣ ሶሒሕ በሆኑ ሓዲሦች ስለአሏህ ስምና ባህርያት በወረደው ሁሉ ለአሏህ ብቻ ያለምንም ተጋሪ ጥራት ይገባውና ለሱ ልቅና በሚገባው መልኩ ማፅደቅና ማመን ነው። ይህም ያለማዛባት፣ ውድቅም ባለማድረግ፣ ዝርዝር ሁኔታም ውስጥ ባለመግባት እና ባለማመሳሰል ነው። በተከታዩ የአሏህ ቃል በመስራት መልኩ: **"በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።(1) «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። (2) «አልወለደም፤ አልተወለደምም (3) «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»(4)** (አል ኢኽላስ 1-4) እንዲሁም ተከታዩ የአሏህ ቃል **"የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።"** (ሹራ 11)

አንዳንድ ዑለሞች ተውሒድን ወደ ሁለት ከፍለውታል፤ ይህም አሏህ በስምና ባህርያቱ ያለውን አሃዳዊነት በጌትነቱ ባለው አሃዳዊነት ስር በመክተት ሲሆን በዚህም ላይ መተቻቸት የለለበት ነው። ምክንያቱም ሁለቱም የፈለጉበት ነገር ግልፅ ነውና።

የሽርክ አይነቶችም ሶስት ናቸው: **ትልቁ ሽርክ፣ ትንሹ ሽርክ እና ድብቁ ሽርክ ናቸው።**

ትልቁ ሽርክ: የስራን መበላሸት እና በዛው ላይ ሆኖ ለሞተም ደግሞ እሳት ውስጥ መዘውተርን ግድ ያደርጋል። ልክ ከፍ ያለው አሏህ እንዳለው፡ **"ባጋሩም ኖሮ ይሠሩት የነበሩት ከነሱ በታበሰ ነበር።"** (አልአንዓም 88) እንዲህም ብሏል: "**ለከሓዲዎች በነፍሶቻቸው ላይ በክህደት የሚመሰክሩ ሲኾኑ የአላህን መስጊዶች ሊሠሩ አይገባቸውም። እነዚያ ሥራዎቻቸው ተበላሹ። እነሱም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።"** (አት-ተውባ17) በዛው ላይ ሆኖ ያለ ተውባ የሞተም አሏህ መሃርታ አያደርግለትም ጀነትም በርሱ ላይ እርም ነች። ልክ አሏህ እንዳለው፡ **"አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል።"** (አን-ኒሳእ 48) ጥራት ይገባውና እንዲህም ብሏል: **"እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።"** (አል ማኢዳህ 72)

ከአይነቶቹም: ሙታንንና ጣኦታትን መማፀን፣ በጭንቅ ጊዜም እነሱን ድረሱልኝ ማለት፣ ስለትን ወደነሱ ማቅረብ፣ እርድንም ለነሱ ማቅረብ እና ሌሎችም።

ትንሹ ሽርክ: ይህ ደግሞ በቁርአንና በሓዲሥ ጥቅስ ሽርክ በሚል ስያሜ የተጠራ ሆኖ ነገር ግን ከትልቁ ሽርክ ያልሆነ ነው። እንደ በአንዳንድ ድርጊቶች ላይ ይዩልኝ ይስሙልኝ ማለት፣ ከአሏህ ውጭ ባለ አካል እንደመማል፣ "የአሏህ እና የአንተ ፍላጎት ከታከለበት(እኩል በሚያደርግ ገለፃ)" ማለት እና ሌሎችም። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ ነው " 'ከምፈራላችሁ ሁሉ እጅጉን የምፈራላችሁ ትንሹ ሽርክ ነው'፤ ስለዛም (ምንነት) ተጠየቁ፤ 'ሪያእ(እዩልኝ ስሙልኝ) ነው' አሉ። "

እንዲሁም የነብዩ ﷺ "ከአሏህ ውጭ ባለ የትኛውም አካል የማለ በርግጥም አጋርቷል" የሚለው ቃላቸው።

እንዲሁም የሳቸው ﷺ "የአሏህ እና የእከሌ ፍላጎት ከሆነ አትበሉ፤ ነገርግን የአሏህ ፍላጎት ከሆነ ከዚያ የእከሌ በሉ" የሚለው ቃላቸው። አቡ ዳውድ ሶሒሕ በሆነ ዘገባ ከሑዘይፋ ኢብኑል የማን ዘግበውታል።

ይህ አይነቱ ከእስልምና ያስወጣል ወይም ደሞ በእሳት ውስጥ ዘውታሪ ያደርጋል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ግዴታ የሆነውን የተውሒድ ምሉእነት ያናጋል።

ሶስተኛው አይነት ደግሞ: ድብቁ ሽርክ ነው። ይህም ነብዩ ﷺ ተከታዩን ያሉበት ነው: " **‘እኔ ዘንድ ከመሲሑ ደጃል በላይ እጅጉን የምፈራላችሁን አልነግራችሁምን?’** አሏቸው እነርሱም: ‘እንዴታ የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ!’ አሉ እሳቸውም: **"ድብቁ ሽርክ፡ አንድ ሰው ለሶላት ይቆማል፤ ሶላቱንም ያሳምራል ግን እሱን የሚመለከተው ሰው ስላየ ነው።"**

ሽርክ ወደ ሁለት ብቻም ሊከፈል ይችላል፡ ትልቁ እና ትንሹ ተብሎ። ድብቁ ሽርክ ደግሞ ሁለቱንም ሊያጠቃልል የምችል ነውና።

ከትልቁ ሽርክ ሊይርፍ ይችላል፤ እንደሙናፊቆቹ ሽርክ፤ ምክንያቱም እነሱ ውዳቂ የሆነ እምነታቸውን ይደብቃሉና። ከዚያም ለሰው ሲታዩ ኢስላምን ያሳያሉ፤ ይዩልኝ ይስሙልኝ በሚል ስሜት ወይም ደሞ በራሳቸው ላይ ስለሚሰጉ።

በትንሹ ሽርክም ላይ ሊያርፍ ይችላል፤ እንደ ይዩልኝ ይስሙልኝ ያለው፤ ልክ ባሳለፍነው የማሕሙድ ኢብኑ ለቢድ አልአንሷርይ ሓዲሥ ላይ፤ እንዲሁም የአቢ ሰዒድ ሓዲሥም ላይ እንደተወሳው። አሏህ የተውፊቁ ባለቤት ይግጠመንና።

የአራተኛው ትምህርት ማብራርያ

የክልክላቶች አይነት፡

ትልቁ ሽርክ:

ይህ ከፍተኛው ነው።

ትንሹ ሽርክ:

ከትልቁ ሽርክ ያነሰ ከከባባድ ወንጀሎች ግን የከፋ ነው።

ከባባድ ወንጀሎች:

መርገም፣ ከራሕመት መባረር፣ ወይም ከሰሪው መጥራራትን የመሰለ መቀጣጫ የመጣበት ወይም ደግሞ “ከካፊሮች ነው” ወይም “ከሙሽሪኮች ነው” “ከሙእሚኖች አይደለም” የተባለበት ወይም ደሞ በአስቀያሚ እንስሳት የተመሳሰለበት ነው።

ትናንሽ ወንጀሎች:

ይህ ደንጋጊው (አሏህና መልዕክተኛው) ከልክሎት ልዩ የሆነ መቀጣጫ ያላስከተለበት ነው።

ከባባድ ወንጀሎች:

ፍርዱ

ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ ተውባ ማድረጉ ግድ ነው: "ሙሽ አውራጅ ሴት ከሞሞታ በፊት ተውባ አድርጋ ካልተመለሰች..." (ሙስሊም)

ደረጃዎቿ

ነብዩ እርስ በራሱ ይበላለጣል ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ:

"ከከባዶቹ ከባዱን አልነግራችሁምን? ..." (ቡኻሪይ እና ሙስሊም ዘግበውታል)

የድርጊቱ ፈፃሚ ፍርዱ

-እምነቱ የቀነሰ ሙእሚን ነው። ወይም ደሞ በእምነቱ አማኝ በፈፀመው ከባድ ወንጀል አመፀኛ ነው።

-እሱ ዘንድ ባለው መልካም ስራ ልክ ይወደዳል እሱ ዘንድ ባለው ከባድ ወንጀል ልክ ይጠላል።

-ወንጀሉን በሚዳፈርበት ሁኔታ ላይ አብረውት አይቀማመጡም።

ብዛቷ?

በቁጥር የተገደበ ባይሆንም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መርህ የተገደበ ነው።

በትንሹ እና በትልቁ ሽርክ መካከል ያለው ልዩነት

ትልቁ ሽርክ

1. ከኢስላም መንገድ ያስወጣል
2. ስራን ሁሉ ያበላሻል
3. ተውባ ሳያደርግ ለሞተ ለዘላለሙ እሳት ውስጥ ዘውታሪ ያደርገዋል
4. ለሚመለከተው ሙስሊም ባለስልጣን ደሙንና ገንዘቡን የተፈቀደ ያደርግበታል
5. በማስረጃ ከባዱ መሆኑ የተጠቆመበት
6. ሰበብ ለሆነ ነገር በፍጥረተ አለሙ ላይ ድብቅ የሆነ ማስተናበር አለው ተብሎ ከታመነ
7. በዛው ላይ ሆኖ ከሞተ መሃርታ አይደረግለትም
8. ተውባ ካደረገ አሏህ ተውባውን ይቀበለዋል፤ በሁለት አጋጣሚዎች ላይ ካልሆነ በቀር፤ የፀሃይ በስተምዕራብ በኩል መውጣትና ጣእረ ሞት / ሞት አፋፍ ላይ ሲሆን።

ትንሹ ሽርክ

1. ከኢስላም መንገድ አያስወጣም
2. ስራን ሁሉ ባያበላሽም የተቀላቀለበትን ስራ ብቻ ለይቶ የሚያበላሽ ነው።
3. ዘላለሙን ጀሃነም ውስጥ ለመዘውተር ምክንያት አይሆንም
4. ባለስልጣን ደሙንና ገንዘቡን የተፈቀደ አያደርግበትም
5. በማስረጃ ትንሹ መሆኑ የተጠቆመበት
6. ሰበብ ያልሆነ ነገር ሰበብ ተደርጎ ሲያዝ
7. ወደ ትልቁ መዳረሻ የሆነ ሁሉ ከትንሹ ይመደባል
8. በሸሪዓህ ሽርክ መሆኑ ቢጠቆምም ነገር ግን ትልቁ መሆኑን በማይገልፅበት መልኩ የተገለፀ ከትንሹ ሽርክ ነው፤ ከትልቁ እንደሚመደብ የሚጠቁም ተጓዳኝ እስከሌለው ድረስ።

አምስተኛው ትምህርት

ኢሕሳን

የኢሕሳን ምሰሶው: አሏህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ ምክንያቱም አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።

ኢሕሳን አንድ ምሰሶ እና ሁለት እርከኖች አሉት

የእይታ አምልኮ(ሚቢደቱል ሙሻሀዳህ)

(አምልኮውን ከማጣጣም ጋ) አላህ ዘንድ ላለው ወዶ፣ ከጅሎና ናፍቆ የሚደረግ አምልኮ ነው፤ የነብያቶችና የመልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም አምልኮ ነው: ልክ ነብዩ ﷺ **"...አመስጋኝ ባርያ መሆን የለብኝምን!"** እንዳሉት። ሌሎችም ሊደርሱበት የሚችሉት ደረጃ ነው

የቁጥጥር አምልኮ (ሚቢደቱል ሙራቀባህ)

(የሚቆጣጠር እንዳለ አስቦ) በፍርሃትና በስጋት የሚደረግ አምልኮ ሲሆን የትኛውም ሙስሊም ከዚህ ደረጃ አይወጣም።

ተውሒድ ነክ ፈተና

1. ዲነል ኢስላም በጥቅሉ ስንት እርከኖች አሉት? O ሶስት O አራት O አምስት

2. የኢስላም ማእዘናት ስንት ናቸው? O አምስት O ስድስት O ሰባት

3. ኢስላም ከኢማን ከፍ ብሎ ያለ እርከን ነው። (እውነት - ሃሰት)

4. **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** የምትለዋ የኢኽላስ የምስክርነት ቃል ስንት ማእዘን ነው ያላት?

O ሰባት O ስምንት O ሁለት

5. የ **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ቅድመ መስፈርቶች ስንት ናቸው?

O ስምንት O ሰባት O አምስት

6. እውቀት ከ **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ቅድመ መስፈርቶች ሲሆን የሚፈለግበት ትርጉምም:

O አንድን ነገር ተጨባጭ ሁኔታውን ማግኘት O ከአሏህ ውጭ በእውነት የሚመለክ አለመኖሩ

7. የመልዕክተኛው ﷺ ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑ ሰዎች ያላቸውን (የክህደት) ፍርድ የተጠራጠረ…

O ትልቁን ክህደት ፈፅሟል O ጥርጣሬው ከእርግጠኝነቱ የሚያመዝን ከሆነ ካፊር አይሆንም

8. በሙሉ ልብ መቀበል ከ **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ቅድመ መስፈርቶች መካከል ነው ሲባል…

O ቃሉን O ድርጊት ነክ የሆነውን

O እምነቱን O ሁሉንም

9. ይዩልኝ ይስሙልኝ በ **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ቢሆንም በምዕዋት ላይ እንዳለው ይዩልኝ ይስሙልኝ ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ ነው። (እውነት – ሃሰት)

10. ልቡ ሳያምንበት በቃል ደረጃ **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ያለ ሰው …

O የተውሒድ ሰው ነው O ያላመነ ሙስሊም ነው

O ትልቁ ክህደት ያለበት ከሃዲ ነው O ደካማ ኢማን ያለው ነው

11. አንድ ሰው አሏህን እንደሚወደው ወይም እኩል በሆነ መልኩ ነብዩንም ﷺ ቢወድ:

O ትልቁ ክህደት ውስጥ ገብቷል O ትንሹን ክህደት ክዷል O ከከባባድ ወንጀሎች አንዱን ፈፅሟል

12. መውደድ ስንት ክፍሎች አሉት? O አራት O ሶስት O ሁለት

13. ለአሏህ ብሎ መውደድ ለድርጊቱ፣ ለሰሪው፣ ለጊዜም ለቦታም የሚሆን ነው። (እውነት – ሃሰት)

14. ከአሏህ ጋ (እኩል) መውደድ ኢስላማዊ ፍርዱ…

O ትንሹ ሽርክ ነው O ግዴታ ነው O ትልቁ ሽርክ ነው

15. ለአሏህ ብሎ መውደድ ፍርዱ…

O የተፈቀደ ነው O ግዴታ ነው O ትልቁ ሽርክ ነው

16. የሰዎች አምላኪነት(ዑቡዲያ) ስንት ክፍሎች አሉት? O 2 O 3 O 4

17. ከሃድያንን ጨምሮ ፍጥረታት ሁሉ በአሏህ አሸናፊነት ስር ያሉ ባርያዎቹ ናቸው። (እውነት – ሃሰት)

18. **"ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ"** ብሎ ድርጊታዊ በሆነው በኩል ሙሉ በሙሉ ቢተወው፤ ባይሰግድ፣ ባይፆም ወይም የትኛውንም አይነት አምልኮ ባይፈፅም (ይህች የ 'ላ ኢላሃ ኢላ አሏህ' ቃሉ)፡

O ትጠቅመዋለች O አትጠቅመውም

19. "ባርያውና መልዕክተኛው" የሚለው በሸሃዳ ላይ ያለው ቃል ባርያው ነው ስንል የማይመለከ፤ መልዕክተኛው ነው ስንል ደግሞ የማያስተባብሉት የሚለውን ጠቋሚ ነው። (እውነት – ሃሰት)

20. "ሙሐመድም ባርያውና መልዕክተኛው ናቸው" በሚለው የምስክርነት ቃል ተመርኩዘን ባዘዙት መታዘዝ እና የተናገሩትን አምኖ መቀበል … ነው ያልነው ይህ:

O ትርጉሚ ነው O ግድ የሚለው መልዕክቷ ነው

21. ከጌትነት መገለጫዎች መካከል አንዳች ነገርን ለነብዩ ﷺ የሚያደርግ ሰው የሳቸውን ባርያ የመሆን የምስክርነት ቃሉን አልሰጠም። (እውነት – ሃሰት)

22. የነብዩ ﷺ ምጡቅ መገለጫ የሳቸው _____ መሆን ነው።

O የአሏህ መልዕክተኛ O ባርያውና መልዕክተኛው O የነብያቶች መደምደሚያ

23. "በኢስላም አዲስ መጤ(ቢድዓ)ን አምጥቶ መልካም እንደሆነች አድርጎ የሚያያት ሰው ነብዩ ሙሐመድ ﷺ በተልዕኳቸው ሸፍጥ ሰርተዋል እያለ ነው። ምክንያቱም አሏህ እንዲህ ብሏልና **"ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡**"(አልማኢዳህ 3) ስለዚህ የዚያኔ ዲን ያልሆነ ዛሬ ላይ ዲን አይሆንም።". ይህ የ _____ ቃል ነው?

O ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ O ኢብን ባዝ O ኢማም ማሊክ

24. ነብዩ ሙሐመድ ﷺ የነብዩ _____ ዝርያ ናቸው። O ኢስሓቅ O ኢስማዒል

25. ክፍት ቦታ ሙላ: ነብዩ ﷺ የተወለዱት በ ..... አመት በ ..... ከተማ ነው። እድሚያቸውም ..... ነበር። ከዚህም ..... አመቱን ነብይ ከመሆናቸው በፊት ሲሆን ..... አመቱን ደግሞ ነብይ እና መልዕክተኛ ሆነው ነው። በ ..... ሱራ ነብይ ሆነው በ ..... ደግሞ ረሱልነትን ተጎናፀፉ።

26. ነብዩ ﷺ የተላኩት ወደ: O ህዝባቸው O ሰው ልጆች O ወደ ሰው ልጆችም ወደ ኢጋንንቱም

27. ሚዕራጅ ማለት የነብዩ ﷺ ከመካ ወደ በይቱል መቅዲስ ያደረጉት ጉዞ ነው። (እውነት – ሃሰት)

28. ነብዩ ﷺ በስደት የተጓዙት ወደ...

O ጧኢፍ O ኢትዮጵያ O መዲና O ሁሉም

29. የነብዩ ﷺ አሳሳቢ የሚባሉት ዘመቻዎቹ ስንት ናቸው?

O አንድ O ሁለት O ሶስት O አራት O አምስት

30. የነብዩ ﷺ ልጆች ስንት ናቸው?

O ሶስት O አራት O ሰባት

31. ነብዩ ﷺ የመሰናበቻ ሓጅ አድርገዋል፤ ይህም ከዛ በፊትም ሓጅ ማድረጋቸውን ይጠቁማል። (እውነት – ሃሰት)

32. የነብዩን ﷺ ታሪክ መማር ...

O ግዴታ ነው O የተወደደ ነው O የተፈቀደ ነው

33. ክፍት ቦታዎቹን ሙላ: ኢማን እንደሸሪዓዊ ፍቹ በ ..... የሚባል፤ በ ..... እምነት ተደርጎ የሚያዝ፤ በ ..... የሚተገበር ነው። በ ..... የሚጨምር ሲሆን በ ..... የሚቀንስ ነው።

34. የኢማን ማእዘናት በቁጥር ስንት ናቸው?

O ስድስት O አምስት Oአራት

35. በአሏህ ማመን እንድናምን ግድ የሚያስብላቸው ነገራቶች አሉ። ስንት ናቸው?

O አራት O ሶስት O ሁለት

36. የአሏህን ህልውና የሚጠቁሙ ማስረጃዎች በጥቅሉ ...

O አራት ናቸው O በቁጥር ሊገለፁ አይችሉም

37. ሚካኤል ዝናብ የማውረድ ኃላፊነት የተጣለበት መላኢካ ነው። (እውነት – ሃሰት)

38. ልቦና ያላቸው መላኢኮች ናቸው እንጅ መላኢኮች ልቦና የላቸውም። (እውነት – ሃሰት)

39. አሏህ ስማቸውን ያሳወቀን መፃህፍቶች ብዛት ስንት ናቸው?

O ስድስት O አራት O ሰባት O ብዙ

40. በሁሉም ነብያቶች ላይ አሏህ መፅሃፍን አውርዷል። (እውነት – ሃሰት)

41. የመጀመሪያው ረሱል አደም ነው። (እውነት – ሃሰት)

42. ሙሐመድ ﷺ ረሱል እንጅ ነብይ አይደሉም። (እውነት – ሃሰት)

43. ከመልዕክተኞች መካከል የቆራጥነት ባለቤት የተባሉት ስንት ናቸው?

O አምስት O አራት O ብዙ

44. በመጨረሻው ቀን ማመን ሰዎች ከቀብራቸው እስከመቀስቀስን ጨምሮ ከሞት በኋላ በሚሆነው ሁሉ ማመንን ያጠቃልላል። (እውነት – ሃሰት)

45. በቅዱና በቀደር ማመን የራሱ እርከኖች አሉት፤ ስንት ናቸው?

O አራት O አምስት O ሶስት

46. አሏህ ነገራቶች ከመከሰታቸው በፊት ያውቃልን? (አዎ – አይ)

47. አሏህ ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ ያውቃልን? (አዎ – አይ)

48. አሏህ ሰዎች የሚያደርጉትን ሁሉ በፅሁፍ አስፍሮታልን? (አዎ – አይ)

49. ባርያ የፈለገውን የሚያደርግበት ነፃ ፍላጎትና መሻት አለው። (እውነት – ሃሰት)

50. የባርያዎች ስራቸው ፍጡር ነውን? (አዎ – አይ)

51. ተውሒድ ወደ _____ ይከፈላል።

O ወደ ሁለት O ወደ ሶስት O ወደ አለመግባባት የሚያመራ አይደለም

52. በትልቁ ሽርክ እና በትንሹ ሽርክ መካከል ካሉ ልዩነቶች መካከል አምስቱን ጥቀስ።

1- ……..

2-……..

3-……...

4-……...

5-……...

53. ከትልቁም ከትንሹም ሽርክ አምስት ምሳሌዎችን ጥቀስ

ትልቁ ሽርክ	ትንሹ ሽርክ
……	……
……	……
……	……
……	……
……	……

54. የእምነት ኒፋቅ ከመንገዱ የማያስወጣ ትንሹ ሽርክ ላይ የሚመደብ ነው። (እውነት – ሃሰት)

55. ኢሕሳን የሚያጠቃልለው

O አንድ ማእዘን O ሁለት ማእዘናት

ስድስተኛው ትምህርት

የሶላት ቅድመ መስፈርቶች

ሶላት ዘጠኝ ቅድመ መስፈርቶች አሉት:

1. ኢስላም 2. (የአእምሮ) ጤንነት 3. ተምይዝ (ክፉውን ከደጉ መለየት መቻል)
4. ርክሰትን ማስወገድ 5. ነጃሳን ማስወገድ 6. ሃፍረተ ገላን መሸፈን
7. የሶላት ጊዜው መግባቱ 8. ወደ ካዕባ መቅጣጨት 9. ኒያ

የመጀመርያው ቅድመ መስፈርት: ኢስላም

ተቃራኒው ክህደት ነው፡ አላህን የሚሰድብ ወይም አምልኮን ከአሏህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሚሰጥ ቢሰግድ ተውባ አድርጎ ወደ አሏህ እስካልተመለሰ ድረስ ሶላቱ ውድቅ ነው።

ሁለተኛው መስፈርት: የአእምሮ ጤንነት

ተቃራኒው እብደት ሲሆን ስካርም እዚሁ ለመካተት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ሶስተኛው ቅድመ መስፈርት: መለየት መቻል

ይህ ሲባል ለአቅመ ተቃራኒ ዖታ መድረስ ማለት አይደለም። ይልቅ ትርጉሙ በነገሮች መካከል መለየት መቻል ማለት ነው፤ በሌላ አገላለፅ ጥያቄ እና መልስን ያውቃል። የተወሰነ ዕድሜ ገደብ የለውም። ብዙውን ጊዜ ግን ዕድሜ 7 ዓመት ሲኮን ነው ነገራቶችን መለየት የሚቻለው። የህፃን ልጅ ሶላት ትክክለኛ የሚሆነው መቼ ነው? ነገራቶችን መለየት ከቻለ ነው። ማለትም እንደምሳሌ ጥያቄ እና መልስን ማወቅ ከቻለ፤ እሳትና ውሃን መለየት ከቻለ ማለት ነው። ካልሆነ ግን ሶላቱ ውድቅ ነው።

አራተኛ ቅድመ መስፈርት: ርክሰትን ማስወገድ

የሚከተሉትን ያጠቃልላል:

ትልቁ ርክሰት

ገላን በመታጠብ የሚወገድ ነው።

ትንሹ ርክሰት

ዉዱእ በማድረግ የሚወገድ ነው።

አምስተኛ ቅድመ መስፈርት: ነጃሳን ማስወገድ

ሲባል ከሰውነት ፣ ከቦታ እና ከልብስ ማስወገድ ነው። አንድ ሰው እሱ ላይ ነጃሳ ኖሮበት እያወቀ፣ እሱን ማስወገድ የሚችል እና የሚያስታውስ ሆኖ ሳለ ከሰገደ ሶላቱ ውድቅ ነው።

ነጃሳን ማስወገድ በሦስት ምድቦች ይከፈላል፡

ከባድ:

ይህ የውሻ ነጃሳ ነው።

ነብዩ ﷺ የውሻ ለሃጭ ያረፈበትን እቃ ሰባት ጊዜ የመጀመርያውን በአሸዋ እንዲታጠብ አዘዋል።

ሙስሊም ዘግበውታል

ቀላል:

መጭመቅ ሳይጠበቅበት ውሃ በማፍሰስ ያውም በማርከፍከፍ ይወገዳል። ይህ ምግብ ያልጀመረ ህፃን ልጅ ሽንት፣ መዘይንና መንይን የሚመለከት ነው። ምንም እንኳ ጡሃራ ቢሆንም ነብዩ ﷺ እርጥብ ሲሆን ውሃ ያርከፈክፉበታል ደረቅ ከሆነ ደግሞ ይፈገፍጉት ነበር።

መካከለኛ:

በማጠብ የሚወገድ ሲሆን ያም ውሃን ከማፍሰሱ ጋ በመጭመቅ ነው። ይህ መካከለኛና ከባድ ላልሆነው የሚሆን ነው። የወንድም ሆነ የሴት ሽንት እና ሌሎች ነጃሳዎችን የሚመለከት ነው።

ነጃሳ ነገራቶች

የሰዎች ሽንት እና አይነምድር፤ እንዲሁም ስጋቸው የማይበሉ እንስሳት ሽንትና ኩሬያቸውም ነጃሳ ነው። እንደ ድመቶች ፣ በቅሎ እና አህያ የመሳሰሉትን ለመጠንቀቅ አስቸጋሪ ከሆኑት እንስሶች በቀር የአውሬዎች ሁሉ ኩሬ እና ሽንትም ነጃሳ ነው። የእርድ ደም / ማለትም፡ እንስሶች ሲታረዱ የሚፈሳቸው ደም፣ ከሁለቱ የመፀዳጃ ሽለቆዎች የሚወጣ ደምም እንዲሁ ነጃሳ ነው። ከሰው ልጅ ሬሳ እና ነፍስ (የሚፈስ ደም) የሌላቸው፣ እንዲሁም የባህር ሙታኖችና አንበጣ ሲቀሩ ሌሎቹ ሙታኖችም ነጃሳ ናቸው።

ስድስተኛው ቅድመ ሁኔታ: ሃፍረተ ገላን መሸፈን

ሃፍረተ ገላ ሲባል ሶስት አይነት ነው:

ከባዱ:

የጉርምስና ዕድሜ ላይ የደረሱ ሴቶች ሃፍረተ ገላ፣ ከፊቷ በስተቀር መላውን ሰውነት መሸፈን ትሸፍነው፤ በባዕድ ሰዎች ፊት ከሆነች ደግሞ እሱንም መሸፈን ይኖርባታል።

ቀላሉ:

እድሜያቸው እንደ ከሰባት እስከ አስር ዓመት ያሉ ወንድ ልጆች ሃፍረተ ገላ፤ ቢያንስ ሁለቱ ብልቶች መሸፈን አለባቸው።

መካከለኛ:

በሁለቱ ከተጠቀሱት በስተቀር፤ ከእምብርት እስከ ጉልበት ድረስ መሸፈን ተገቢ ነው። ትከሻዎችን መሸፈን እና ሙሉ በሙሉ ለመልበስ የበለጠ ከመሆኑም ጋ።

ሰባተኛው ቅድመ መስፈርት: የሶላት ሰአት መግባቱ

ሶላት ጊዜው ከመግባቱ በፊትም ሆነ ካለፈም በኋላ ትክክል አይሆንም። ለበቂ ምክንያት ሲባል ከሌላኛው የሶላት ወቅት ጋ አቆራኝቶ ለመስገድ ካልታሰበ በቀር። ሆን ብሎ ማዘግየቱን ካሰበ ግን ወንጀለኛ ይሆናል።

ስምንተኛው ቅድመ መስፈርት፡ ወደ ቂብላ መቅጣጨት

ከነዚህም በጉዞ ወቅት የሚሰገዱ የሱና ሶላቶች ልዩ ናቸው፤ በሚጓዝበት ጊዜ ሲሰግድ መጓጓጥው በዞረችበት አቅጣጫ ሁሉ ነውና የሚሰግደው። ለምሳሌ- በጊዜያችን በአውሮፕላን ውስጥ ሲሰገድ።

በተጨማሪም ፣ መቅጣጨት የተሳነውና ጠላትን የሚሰጋ ሰውም እንዲሁ ፍርዱ የተለየ ነው።

ዘጠነኛው ቅድመ ሁኔታ፡ ኒያ

ቦታዋ ልብ ውስጥ ነው። በቃላት መግለጹ መጤ(ቢድዓ) ነው። አንድ ሰው ከሶላቱ ከተወሰነ ጊዜ በፊት (እንደሚሰግድ) ቢያስብ ወይም የጊዜውን ግዴታ ለመስገድ በሚል (ጥቅል በሆነ) መልኩ ቢያስብ እንኳ ሶላቱ ተቀባይነት ያለው ነው።

አሳሳቢ ጥቆማዎች

1- ሆን ብሎ፣ ባለማወቅ አሊያም በመርሳት ቅድመ ሁኔታን መተው ተቀባይነት የለውም ፤ አንድ ሰው ባለማወቅ ወይም ረስቶ ነጃሳ እያለበት ቢሰግድ ግንሶላቱ ትክክል ነው፤ ምክንያቱም ይህ ከመተው አይነቶች እንጅ ከማድረግ አይነቶች አይደለምና።

2- ቅድመ ሁኔታዎች ከአምልኮው ውጭም በፊትም ይሆናሉ። የአምልኮው ተግባር እስኪጠናቀቅ ድረስ መገኘታቸው ግን የግድ አስፈላጊ ነው።

ሰባተኛው ትምህርት

የሶላት ማእዘናት

የሶላት ማእዘናት አስራ አራት ናቸው:

1- ከተቻለ መቆም 2- ተክቢረተል ኢሕራም (በሶላቱ መጀመርያ “አሏሁ አክበር” ማለት)

3- ሱረቱል ፋቲሓ(አልሓምዱ)ን መቅራት 4- ሩኩዕ መውረድ 5- ከሩኩዕ በኋላ መልሶ መቆም 6- በሰባቱ የሰውነት አካላት ሱጁድ ማድረግ 7- ከሱጁድ በኋላ መልሶ መነሳት

8- በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ 9- በእያንዳንዱ ክንዋኔ ላይ ሁሉ መረጋጋት

10- እያንዳንዱን ማእዘን በተራው ማድረግ 11- የመጨረሻው ተሸሁድ

12- ለተሸሁድ(አተሕያቱ) መቀመጥ 13- በነብዩ ﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድ

14- በሁለቱም በኩል ማሰላመት

<u>የመጀመርያው ማእዘን፡ ከተቻለ መቆም</u>

ተጨማሪ ሶላቶች:

አንድ ሰው ቁጭ ብሎ የሚሰግድ ከሆነ ሶላቱ ትክክለኛ ነው። ሆኖም አጅሩ ግን ቆሞ ከሚሰግደው ሰው ግማሽ ነው። አንድ ሰው ተኝቶ ቢሰግድ ደግሞ ተቀምጦ ከሚሰግደው ግማሹን አጅር ያገኛል።

የግዴታ ሶላቶች:

በግዴታ ሶላቶች ደግሞ መቆሙ ምሰሶ ነው። አንድ ሰው በጭራሽ መቆም ካልቻለ ወይም መቆም ቢችልም ነገር ግን ትኩረት ማድረግ የማይችል ከሆነ ግዴታነቱ ይቀርለታል። አንድ ሰው ከሶላቱ የተወሰነውን ክፍል እንኳ መቆም ከቻለ መቆም ይኖርበታል።

ሁለተኛው ማእዘን፡ ተክቢረተል ኢሕራም

“አሏሁ አክበር” ከሚለው ቃል ውጭ አያብቃቃም።

ሶስተኛው ማእዘን፡ ሩቲሓ(አልሓምዱ) መቅራት

በእያንዳንዱ ረከዓ ውስጥ በዝምታም ሆነ ጮክ ብሎ በሚሰገደው ሁሉ አንቀፆቿን፣ አናባቢዎቿን፣ ቃላቶቿን እና ፊደላቶቿን አሟልቶ በቅደም ተከተል መቅራቱ የግድ ነው።

አንድ ሰው ኢማሙን ያገኛቸው ሩኩዕ ላይ ሆኖ ከሆነ ብቻ ትቀራለች።

ዘጠነኛው ማእዘን፡ በእያንዳንዱ ክንዋኔ ላይ ሁሉ መረጋጋት

መረጋጋቱ በእያንዳንዱ ማእዘን ላይ በሚባለው ዚክር ነው የሚረጋገጠው።

አሳሳቢ ጥቆማዎች

ማእዘኖቹ በአምልኮ ውስጥ ያሉ ናቸው። ከማእዘናቶቹ መካከል አንዳቸውንም ሆን ተብሎ፣ ባለማወቅ ወይም ደግሞ በመርሳት ከተተወ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም። በሱጁድ ሰህው (የመርሳት ሱጁድም) የሚጠገን አይደለም። በሰአቱ ማእዘን የተወበትን ሶላት እንዲደግም ይታዘዛል። አንድ ሰው ሁሉንም ማእዘናትን እያጓደለ ለሰገደባቸው ቀደም ያሉ ሶላቶች ግን ባለማወቁ (ከተጠያቂነት ነፃ በሆነ መልኩ) ዑዝር ይኖረዋል። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሶላቱን ያበላሸውን ሰውየ ሰውየው የተወው ከሶላት ማእዘናት አንዷ የሆነችውን መረጋጋት ከመሆኑም ጋ በወቅቱ የያዘውን ሶላት እንጅ ሁሉንም ሶላት እንዲደግም አላዘዙምና። ። አላህ ይበልጡን ዐዋቂ ነው።

ስምንተኛው ትምህርት

የሶላት ዋጅቦች(ግዴታዎች): የሶላት ግዴታዎች ስምንት ናቸው

1- ከተክቢረተል ኢሕራም(የመጀመርያው “አሏሁ አክበር”) ውጭ ያሉት ተክቢራዎች (አሏሁ አክበር) ሁሉ

2- ለኢማሙም ይሁን ለተከታዮቹ *"ሰሚዐሏሁ ሊመን ሓሚዳህ"* ማለታቸው።

3. እያንዳንዳቸው *"ረበና ወለከል ሓምድ"* ማለታቸው

4. በሩኩዕ ጊዜ *"ሱብሓነ ረብየል ዓዚም"* ማለት

5. በሱጁድ ጊዜ *"ሱብሓነ ረቢየል አዕላ"* ማለት

6. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል *"ረቢ ግፊርሊ"* ማለት

7. የመጀመርያው ተሸሁድ 8. ለተሸሁድ መቀመጥ

አሳሳቢ ጥቆማዎች

ሩኩዕ ላይ ‘‘ሱብሓነ ረብየል ዓዚም’’ በሚለው ቃል ማለቱ ግዴታ ነው። ከዚያም ከነብዩ ﷺ በመጡ ሌሎች አባባሎች ማለቱ ይመከራል። እንደዚሁም በተመሳሳይ ሱጁድ ላይ እያለ ‘‘ሱብሓነ ረቢየል አዕላ’’ በማለት ከዚያም በሌላ ከነብዩ ﷺ በመጡ መጨመሩ አስፈላጊ ነው።

ዘጠነኛው ትምህርት

ተሸሁድ (አት-ተሕያቱ)

የተሸሁድ ፍቹ - "ምስጋና፣ ሶለዋት እና መልካም ሁሉ ለአሏህ የተገባ ነው። አንተ ነብይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይሁን የአላህ እዝነት እና በረከቱም እንዲሁ በአንተው ላይ ይሁን፤ ሰላም በእኛ ላይ፣ በደጋግ የአላህ ባሪያዎችም ላይ ይሁን። ከአላህ ውጭ በእውነት ሊመለክ የሚገባው እንደሌለ ሙሐመድም የአሏህ ባርያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።"

ከዚያም ለነቢዩ ﷺ ሶለዋት በማውረድ ለሳቸው በረካን በመሻት መልኩ ዱዓ የሚያደርግ ሲሆን እንዲህ ይላል፤ ‹አላህ ሆይ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ሶለዋትህን እንዳወረድከው በሙሐመድና በቤተሰቦቹም ላይ ሶለዋትህን አውርድ። አንተ በእርግጥ የላቀ ምስጋና የሚገባህ ነህና። አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እንደባረክከው በመሐመድ እና በመሐመድም ቤተሰቦች ላይ በረካህን አውርድ። በርግጥ አንተ የላቀ ምስጋና የሚገባህ ነህና።"

ከዛም በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ ከጀሃነም ቅጣት፣ ከቀብር ቅጣት፣ ከህይወት እና ሞት ፈተና እና ከመሲሑ ደጃል ፈተና የአሏህን ጥበቃ ይለምናል: - "አሏህ ሆይ! ከጀሃነም ሥቃይ በአንተው እጠበቃለሁ ፣ ከመቃብር ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፣ ከሕይወት እና ከሞት ፈተናዎች በአንተው እጠበቃለሁ፣ ከደጃልም ፈተና በአንተው እጠበቃለሁ።" (ቡኻሪ እና ሙስሊም)።

ከዚያም ከዱዓዎች አማርጦ በሻው በተለይም ከነብዩ ﷺ ማስረጃ ባላቸው ይማፀናል። ከነዚህም፡ "አሏህ ሆይ! አንተን በማስታወስ፣ በማመስገንና ባማረ መልኩ እንድገዛህ አግዘኝ። አሏህ ሆይ! እኔ ራሴ በእጅጉ በድያለሁ፤ ወንጀልን ደግሞ ከአንተው ውጭ የሚምር የለም፤ በመሆኑም ከአንተው ዘንድ የሆነ መሃርታህን ለግሰኝ፤ መሃሪው እና አዛኙ አንተው ነህና።"

በዙህር፣ ዓሱር፣ መግሪብ እና ዒሻእ ሶላቶች ላይ ግን ከመጀመሪያው ተሸሁድ ካለ በኋላ ለሦስተኛው ረከዓህ ይቆማል። በዚህ በኩል የመጡ ሓዲሦች ካላቸው ጥቅል መልዕክት ከተሸሁዱ ጋ በነብዩ ﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድን ካከለበት በላጭ ይሆንለታል።

አስረኛው ትምህርት

የሶላት ተጨማሪ ሱናዎች

1- የመክፈቻ ዱዓእ

2- ቆሞ ሳለ፣ ከሩኩዕ በፊት እና ከዛም በኋላ የቀኝ እጅን መዳፍ በግራ እጅ ላይ አሳርፎ ደረት ላይ ማድረግ

3- በመጀመርያው ተሸሁድ፣ ወደ ሩኩዕ ሲወረድ፣ ከሩኩዕ ቀና በሚባልበት ጊዜ እና ከመጀመርያው ተሸሁድ ወደ ሁለተኛው ተሸሁድ በሚሸጋገሩበት ጊዜ ጣቶችን ዘርግቶ በትከሻ ወይም በጆሮ ትይዩ እኩል አድርጎ ሁለቱን እጆች ማንሳት

4. በሩኩዕ እና በሱጁድ ጊዜ የሚባለውን ከአንድ ጊዜ በላይ ማለቱ

5. ከሩኩዕ ቀና ካሉ በኋላ *"ረበና ወለከል ሓምድ"* ከሚለው በላይ መጨመሩ፤ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል *"ረቢ ግፊርሊ"* ከሚለው በኋላ ያለ የድግግሞሽ ጭማሪ

6- በሩኩዕ ጊዜ ጭንቅላትን ከጀርባ ጋ እኩል ለጥ ማድረጉ

7- በሱጁድ ጊዜ ክርናችንን ከጎናችን ማራቅ፤ ሆድን ከታፋ ማራቅ እና ታፋን ደግሞ ከባት ማራቅ

8- በሱጁድ ጊዜ ክርንን ከመሬት ማንሳት

9- በመጀመርያው ተሸሁድ እና በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጫን የግራ እግር ውስጠኛው ክፍል ላይ አሳርፎ የቀኝ እግርን ተረከዝ ተክሎ መቀመጥ።

10- ሶስትና አራት ረከዓ በሚሰገድባቸው ሶላቶች በመጨረሻ ተሸሁድ ጊዜ ተወሩክ በሚባለው አቀማመጥ መቀመጥ፤ ያም፡ መቀመጫን መስገጃው ላይ አሳርፎ የግራ እግርን በተከልነው የቀኝ እግር ተረከዝ ስር ማሸሎክ

11- በመጀመርያውና በሁለተኛው ተሸሁድ ጊዜ ከሚቀመጥበት ጊዜ አንስቶ እስከ ተሸሁድ መጨረሻ ድረስ ባለው ጠቋሚ ጣትን መጠቆም እና በዱዓም ጊዜ ማንቀሳቀስ።

12- ለነብዩና ለቤተሰቦቻቸው፤ ለነብዩ ኢብራሂምና ለቤተሰቦቻቸውም ﷺ በመጀመርያው ተሸሁድ ጊዜ ሶለዋትና በረካን ከአሏህ እንዲወርድላቸው አሏህን መማፀን።

13- በመጨረሻው ተሸሁድ ጊዜ ዱዓእ ማድረግ

14- በፈጅር ሶላት፣ በጁሙዓህ ሶላት፣ በሁለቱ ዒዶች ሶላት፣ በሶላተ ኢስቲስቃእ(ዝናብ እንዲመጣ የሚሰገድ ሶላት) በዒሻእ እና በመግሪብ የመጀመርያዎቹ ሁለት ረከዓዎች ላይ ጮክ ብሎ መቅራት

15- በዙህር እና በዓሱር እንዲሁም በመግሪብ ሶላት ደግሞ በሶስተኛው ረከዓ በዒሻእ ሶላትም በመጨረሻዎቹ ሁለት ረከዓዎች በዝግታ መቅራት

16- ከፋቲሓ በኋላ ጨምሮ መቅራት

ከጠቀስናቸው ውጭ ያሉ ሌሎች በሶላት ውስጥ የሚደረጉ ሱናዎችንም ከመጠባበቅ ጋ፤ ከነዚህም፡ ሲጋጁ ኢማም ይሁን ተከታይ አልያም ብቻውን የሚሰግድም ቢሆን “ረበና ወለከል ሓምድ” ካለ በኋላ የሚጨምረው ሱና ነው። እንዲሁም፡ በሩኩዕ ጊዜ ጣቶችን ለያይቶ ታፋዎቹ ላይ ማስቀመጡ ይገኝበታል።

የመክፈቻ ዱዓእ

“አሏሁመ ባዒድ በይነ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወል መግሪብ አሏሁመ ነቂነ ሚነል ኸጧያ ከማዩነቀ ሠውቡል አብየዱ ሚነ ደነስ አሏሁመግሲልነ ሚን ኸጧያየ ቢልማኢ ወሠልጂ ወልበረድ”

“አላህ ሆይ ፣ በምስራቅና በምእራብ መካከል እንዳደረግከው ርቀት በእኔና በኃጢያቶቼ መካከል ያለውንም ርቀት እንዲሁ አድርግ። ከኃጢአቶቼም በውሃ ፣ በበረዶ እና በብርድ እጠበኝ።” (ቡኻሪ እና ሙስሊም) ወይም ደግሞ *"ሱብሓነከሏሁመ ወቢሓምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላኢላሃ ገይሩክ”*ትርጉሙ “አሏህ ሆይ! ምስጋና ይገባህና ጥራት የተገባህ ፍፁም ነህ፤ ስምህ ልቅና የተገባው ነው፤ ማንነትህ ከፍ ያለ ነው፤ ከአንተም ውጭ በእውነት የሚመለክ የሌለ ጌታ ነህ።"

አስራ አንደኛው ትምህርት

ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች

ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች ስምንት ናቸው:

1- ከማስታወስ እና ከማወቅም ጋ መናገር - የረሳ ወይም የማያውቅ ግን ሶላቱ ውድቅ አትሆንበትም።

2- ሳቅ። 3- መብላት። 4- መጠጣት 5- የሃፍረተ ገላ መገለጥ 6- ከቂብላ አቅጣጫ በብዙ መንሻፈፍ።

7- እየሰገደ እያለ ተከታታይ የሆነ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ማድረግ 8- ዉዱእ ማፍረስ

<u>የመጀመርያው አፍራሽ:</u> ከማስታወስ እና ከማወቅም ጋ መናገር

ኢማሙ ሲረሳ ወይም በቁርዓን ሲሳሳት ለመርዳት ካልሆነ በስተቀር ::

በሶላት ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ሁኔታ

የተከለከሉ እንቅስቃሴዎች:	የተወገዙ እንቅስቃሴዎች:	የተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች:	የሚፈለጉ እንቅስቃሴዎች:	ግዴታ የሆኑ እንቅስቃሴዎች:
እንደ መብላት ያሉ ብዙ አላስፈላጊ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች።	ትንሽ እንደ መዞር ያሉ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን።	ዒምን እንደ ማከክ ያሉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች።	የሶፍ ክፍተቶች መዝጋትን የመሰሉ ሶላትን ሙሉ ለማድረግ አሰፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች::	የሶላቱ ትክክለኛነትን የሚወስኑ ነጃሳን እንደ ማስወገድ የመሰሉ እንቅስቃሴዎች።

አስፈላጊ ጥቆማዎች

የሶላት ቅድመ ሁኔታዎች፣ ማእዘናት፣ ግዴታዎቹንና ሱናዎቹን አሳልፈናል። ልዩነታቸውስ ምንድን ነው?

<table>
<tr><th>ሱና</th><th>ግዴታ</th><th>ማእዘን</th><th>ቅድመ ሁኔታ</th></tr>
<tr><td colspan="3">በአምልኮው ምንነት ውስጥ የሚካተት ነው</td><td>ከአምልኮው ምንነት ውጭ ነው</td></tr>
<tr><td colspan="3">ከአምልኮው ክፍሎች በሆነው ክፍል ብቻ የተገደበ ነው</td><td>በመላ አምልኮው ዘላቂ ነው</td></tr>
<tr><td>አለማወቁ፣ መርሳቱም ሆነ ሆን ብሎ መተው ዑዝር ይሆንለታል</td><td>ሆን ብሎ እስካልሆነ ድረስ አለማወቁ ወይም መርሳቱ ዑዝር ይሆነዋል</td><td colspan="2">አለማወቁ፣ መርሳቱም ሆነ ሆን ብሎ መሆኑ ለመቅረቱ (ዑዝር) በቂ ምክንያት አይሆንም</td></tr>
<tr><td></td><td>በሱጁደ ሰህው የሚጠገን ነው</td><td>በሱጁደ ሰህው አይጠገንም</td><td>የመርሳት ሱጁድ (ሱጁደ ሰህው) አይደረግለትም</td></tr>
</table>

የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

ሱጁደ ሰህው (የመርሳት ሱጁድ)

የሱጁደ ሰህው ምክንያቶች ሶስት ናቸው:

ጥርጣሬ:

ለምሳሌ አንድ ሰው የሰገደው ሁለት ወይንስ ሶስት መሆኑን ከተጠራጠረ፤ ይህ ሁለት አይነት ነው:

መቀነስ:

ለምሳሌ ከሶላቱ ግዴታዎች መካከል አንዳች ነገር አልፎበት ቢቀንስ

መጨመር:

አንድ ሰው ሩኩዕ ወይም ሱጁድ ወይም መቆምን ወይም መቀመጥን ቢጨምር

በአምልኮው ውስጥ የሆነ ጥርጣሬ:

ጥርጣሬው ብዙ ከነበረ ዞርም አይልለትም፤ ትንሽ ከሆነ ግን እሱ ዘንድ አመዛኝ ብሎ በሚያስበው ላይ ተንተርሶ ቀሪውን ይገነባል። እሱ ዘንድ አማካኝ ሆኖ ከታየው ደግሞ ቢያንስ በሚለው ላይ ተንተርሶ ቀሪውን ይገነባል።

አምልኮውን ካጠናቀቀና ከቋጨ በኋላ መጠራጠር:

እንዲህ አይነቱን እርግጠኛ እስካለሆነ ድረስ ቦታም የሚሰጠው አይሆንም።

ጥቆማ:

- አንድ ሰው በሱጁደ ሰህው ከረሳ አንዳችም ነገር ሳይጠበቅበት ሶላቱ ትክክለኛ ነው።
- አንድ ሰው ማእዘን የሆነን ነገር ከረሳ እሷኑ እስኪያመጣት እና ኋላም ሱጁደ እህው እስኪሰግድ ድረስ ሶላቱ ትክክል አትሆንም።
- አንድ ሰው ግዴታ የሆነን ነገር ረስቶ ትቶ ቦታውንም ካለፈው የመርሳትን ሱጁድ (ሱጁደ ሰህው) ይወርዳል።

የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ

- በመጀመርያ አንድ ሙስሊም በቤቱ ሆኖ (ዉዱእ በማድረግ) ንፅህናውን ጠብቆ ጥሩውን መልበስ አለበት
- በእግሩም ይሁን በመጓጓዣ በእንቅስቃሴው እርጋታንና ስርዓትን ተላብሶ፤ ማለትም፡ ሳይጣደፍ፣ ግራ ቀኝ ሳይውረገረግ እንዲሁም ድምፁን ከፍ ሳያደርግ መሄድ ይኖርበታል
- (የለበሰውን ልብስ ሰብስቦት ከነበረ የልብሱን እጅጌ መዘርጋት ይኖርበታል)




- አንዴ መስጅድ ከደረሰ ጫማዎቹን አውልቆ በተመደበላቸው ቦታ ያስቀምጣል፤ ዱንያ ነክ ነገሩንም እዛው ይጥላል፤ በመስጅድ ውስጥ መሸጥ፣ መለወጥና የጠፋን እቃ አፋልጉኝ ብሎ ማወጅ ሓራም ነው።

- በሚገባበት ጊዜ ቀኝ እግሩን በማስቀደም እንዲህ ይላል: ***"ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመፍተሕሊ አብዋበ ራሕመቲክ"*** እንዲሁም ሲወጣ ደግሞ የግራ እግሩን አስቀድሞ እንዲህ ይላል: ***"ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመ ኢኒ አስአሉክ ሚን ፈድሊክ"***

- ወደ ውስጥ ከገቡ በኋላ ወንዶች በፊት ለፊት ካሉት ሶፎች ይሆናሉ ሴቶች ደግሞ ከኋለኞቹ ሶፎች ይሆናሉ
- ሶላቱ ተጀምሮ ከነበረ አንድ ሰው ‹ አላሁ አክባር › በማለት ኢማሙ በማንኛውም ሁኔታ ላይም ቢሆን መቀላቀል አለበት። ኢማሙን ያገኛቸው ቆሞ ወይም ሩኩዕ ላይ ከሆነ እንደሙሉ ረከዓ ይቆጠርለታል። ኢማሙ ሶላቱን ሲያጠናቅቅ ዘግይቶ ኢማሙን የተቀላቀለው ሰው ይነሳና ያመለጠውን ያጠናቅቃል።

- አንድ ሰው ወደ መስጊድ ሲገባ እና ሶላቱ ገና ካልተጀመረ ከሶላቱ በፊት የሶላቱን ተያያዥ ሱና መስገድ አለበት። ሶላቱ ከፊት የተቆራኘ ሱና ከሌለው ግን አንድ ሰው መስጊድ ውስጥ ከመቀመጡ በፊት (የገባው ወደ መስጅድ በመሆኑ) እንዲሁ ሁለት ረከዓ መስገድ አለበት።
- አንድ ሰው ሲገባ ሶላቱ ካልተጀመረ እንዲጀመር በሚል ሰአቱን መመልከት አልያም ጉሮሮውን በማፅዳት የመስጅዱን ክብር መዳፈር የለበትም።
- ኢማምም ሆነ ብቻውን የሚሰግድ ሰው ሲሰግድ ከለላ(ሱትራ) ነገር ከፊት ለፊቱ ማድረጉ ይመከራል። ኢማሙ ከፊት ለፊቱ ሱትራ ካደረገ ግን ከኋላው ለሚሰግዱት ሰዎች በቂያቸው ነው።






- በቆመበት ጊዜ በእግሮቹ መካከል ያለው ርቀት ሳይበልጥም ሳያንስም በትከሻዎቹ መካከል እንዳለው ርቀት መሆን አለበት። የእግሮቹን ጫፍ ደግሞ ቀጥ አድርጎ ወደቂብላ አቅጣጫቶ መቆም አለበት።







- አንድ ጊዜ የሶላቱን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከፈጸመ በኋላ እጆቹን በጆሮዎቹ ወይም በትከሻዎቹ ትይዩ ወደ ላይ ከፍ በማድረግ “አሏሁ አክባር” ይላል። የመዳፎቹን ውስጠኛ ክፍል ወደ ቂብላ ያቅጣጫል።



- ከዚያም የቀኝ እጁን መዳፍ በግራ እጁ ጀርባ እና አንጓ ውጫዊ ክፍል ላይ ያሳርፈዋል፤ ወይም በቀኝ እጁ የግራ እጁን አንጓ ይይዛል።



- አይኑንም ወደ ሱጁድ ማረፊያ ቦታ ላይ ያሳርፋል፤ ወደ ሌላ ቦታም አይዟዟርም።



- ከዚያም በአንደኛው ረከዓ ላይ ብቻ "የመክፈቻ ዱዓእ" ማድረጉ ይመከራል፤ ከነብዩ ﷺ በመጡ የተለያዩ ሶላቶች "የመክፈቻ ዱዓዎችን" በመለዋወጥ ማለቱ የተሻለ ይሆንለታል።

- ከዚያም ከነብዩ ﷺ በመጡ "አዑዙ ቢላሂ ሚነ -ሸ -ሸይጧኒ -ር- ራጂም" ን በመሰሉ መጠበቂያ ቃላት በአሏህ ይጠበቃል።

- ከዚያም ‹ቢስሚላሂ -ር- ራሕማኒ -ር- ራሒም› ይላል።


- ከዚያም ፋቲሓን ከአናባቢዎቿ፣ ቃላቶቿ፣ ፊደላቶቿ እና አናቅፆቿ ጋ አሟልቶ በትክክል ይቀራል።

- ከዚያም እንደገና የመጠበቂያ ቃላትን(አዑዙ ቢላህን) ሳይጨምር ከቁርአን የገራለትን መቅራቱ ይመከራል። የሱራው መጀመርያ ላይ ከሆነ የሚቀራው ብቻ ቢስሚላህ ይበል።

- ከዚያም ከሶላቱ መጀመርያ ጋር በተመሳሳይ መልኩ እጆቹን ከፍ አድርጎ "አሏሁ አክበር" ብሎ ሩኩዕ ይወርዳል።

- የእጆቹን ክርን ሳያጥፍ ጉልበቶቹን በመዳፉ ይዞ፤ ጀርባውን ከጭንቅላቱ በስትክክል አድርጎ ያንበድዳል።

- በግዴታ አንድ ጊዜ "ሱብሓነ ረቢየል ዓዚም" ይላል። ከነብዩ ﷺ ከመጡ ሌሎች ዱዓዎችም መጨመሩ ይመከራል።



- ከዚያም ካጎበደደበት እጆቹን በጆሮዎቹ ወይም በትከሻዎቹ ትይዩ አድርጎ ከፍ እያለ ተስተካክሎ ከመቆሙ በፊት ‘‘ሰሚዐሏሁ ሊመን ሓሚዳህ’’ ይላል።

- ተስተካክሎ ሲቆም ደግሞ “ረበና ወለከል ሓምድ” ይላል።

- ከዚያም እጆቹን ከፍ ሳያደርግ በሰባቱ የሰውነት ክፍሎቹ [በግንባሩ ከአፍንጫው ጋ፣ ሁለት የእጅ መዳፎቹ፣ ሁለት ጉልበቶቹ፣ የሁለት እግር ጣቶቹ ውስጠኛው ክፍሉ] ሱጁድ ያደርጋል።

- እጅና ብብቱ እንዳይገናኙ፤ ብብቱ እና ታፋውም፤ ታፋውና ባቱም እንዳይገናኙ ከፈትፈት ያደርገዋል፤ የእጆቹን ክርንም ከመሬት ያነሳል።



- አንድ ጊዜ “ሱብሓነ ረቢየል አዕላ” ማለት የግድ ነው። ሌሎች ከነብዩ ﷺ በመጡ ዱዓዎች መጨመሩ ይወደድለታል፤ በፈለገው ዱዓ መማፀንም የሚፈቀድለት ቢሆንም ከነብዩ ﷺ በመጡ ዱዓዎች ማለቱ በላጭ ይሆንለታል።

- ከዚያም ‹አላሁ አክባር› በማለት መቀመጫን የግራ እግር ውስጠኛው ክፍል ላይ አሳርፎ የቀኝ እግርን ጣቶች ወደ ቂብላ በማቅጣጨት ተረከዝን በመትከል “ኢፍቲራሽ” የሚባለውን አይነት አቀማመጥ ይቀመጣል። የእጆቹን መዳፍ በታፋዎቹ ላይ ያደርጋል። ይህ አቀማመጥ ከባለ ሶስት እና አራት ረከዓ ሶላቶች የሁለተኛው ተሸሁድ ውጭ ባሉ አቀማመጦች ላይ ሁሉ የሚቀመጠው አቀማመጥ ነው። በዚህ በተጠቀሰው የሁለተኛ ተሸሁድ ላይ ግን የግራ እግሩን በቀኝ እግሩ ስር በማሸሎከ “ተወሩክ” የሚባለውን አይነት አቀማመጥ ነው የሚቀመጠው።



- ከዚያም አንድ ሰው "አላሁ አክባር" በማለት እንደመጀመርያው ሱጁድ ይወርዳል።

- ከዚያም "አሏሁ አክባር" በማለት ለሁለተኛው ረከዓ በመነሳት ከተክቢረተል ኢሕራም እና ከመክፈቻው ዱዓእ ውጭ በመጀመርያው ረከዓ ያደረገውን ሁሉ ያደርጋል።

- ሁለተኛውን ረከዓ ካጠናቀቀ በኋላ ለተሸሁድ ይቀመጣል።

- ጠቋሚ ጣቱን በመዘርጋት የመካከለኛውን ጣቱን ደግሞ ከአውራ ጣቱ ጋ አያይዞ ክብ አድርጎ ጠቋሚ ጣቱን እያንቀሳቀሰ ዱዓውን ያደርጋል።

- አት-ተሕያቱን ማለቱ የግድ ነው።

- የሁለት ረከዓ ሶላት ከሆነ ደግሞ ከተሸሁዱ በኋላ የሚባለውን በኢብራሂም ላይ የሚደረገውን ሶለዋት ይላል፤ ከአራቱም ደግሞ የአሏህን ጥበቃ ይለምናል: **"አሏሁመ ኢኒ አውዙበከ ሚን ዓዛቢ ጀሃነም፤ ወአውዙ ቢከ ሚን ዓዛቢል ቀብር ወአውዙቢከ ሚን ፊትነቲ ደጃል፤ ወአውዙቢከ ሚን ፊትነቲል መሕያ ወልመማት"** ይላል ትርጉሙም: "አሏህ ሆይ! ከእሳት ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከመቃብር ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከዳጃልም ቅጣት በአንተው እጠበቃለሁ፤ ከሕይወትና ሞት መከራዎች በአንተው እጠበቃለሁ"።

ከዚያም በፊለገው መልኩ ዱዓ ያደርጋል፤ በላጭ የሚሆንለት ግን “**አሏሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ዒባደቲከ**” ትርጉሙም “አሏህ ሆይ! አንተን በማስታወስ፣ በማመስገንና አምልኮየን ለአንተው በማሳመር ላይ አግዘኝ።” በመሰሉ ከነብዩ ﷺ በመጡ ዱዓዎች ማለቱ ነው።



- ከዚያም ጭንቅላቱን ብቻ በማንቀሳቀስ በትከሻው ሳይዞር፤ ጭንቅላቱንም ወደ ላይም ወደ ታች ሳያደርግ በእጁም ጥቆማ መስጠት ሳይጠበቅበት ወደ ቀኝና ግራ ያሰላምታል።



- ሶላቱ ባለ 3 ወይም 4 ረከዓ ሶላት ከሆነ የመጀመሪያውን ተሸሁድ ካለ እና እንደተጨማሪ ደግሞ ኢብራሂምይ ሶለዋት ካለ በኋላ ይነሳል ።
- "አላሁ አክባር" ብሎ 3ኛውንም ረከዓ ይሰግዳል፤ ባለ ሶስት ረከዓ ሶላት ከሆነ ለመጨረሻው ተሸሁድ ይቀመጣል። ባለ አራት ረከዓ ከሆነ ደግሞ አንዲቷንም ይጨምራትና ለመጨረሻው ተሸሁድ ይቀመጣል።
- ኢብራሂምይ የሆነውን ሶለዋትም ይልና፡ "አሏሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢ ጀሃነም፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢል ቀብር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲ ደጃል፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲል መሕያ ወልመማት" በማለት ከአራቱ የአሏህን ጥበቃ ይማፀናል። ከዚያም በመረጠው ሁሉ መማፀን ይችላል፤ በላጭ የሚሆንለት ግን "አሏሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ዒባደቲክ" ቢል ነው።
- የግዴታ ሶላት ከሆነ ከሶላት በኋላ የሚባሉትን ከነብዩ ﷺ የመጡ ዚክሮችን ማለቱ የተወደ ይሆንለታል።
- **"አስታግፊሩሏህ! አስታግፊሩሏህ! አስታግፊሩሏህ! አሏሁመ አንተ ሰላም ወሚንከ ሰላም፤ ተባረክተ ያዘል ጀላሊ ወልኢክራም"**
- ከዚያም እንዲህ ይላል ‹ሱብሐነሏህ፤ አል ሓምዱላላህ፤ አላሁ አክባር" እያንዳንዳቸውን 33 ጊዜ ካለ በኋላ ሁሉም በድምር 99 ጊዜያት ይሆናሉ። ከዚያም በ "ላ ኢላሃ ኢለሏሁ ዋሕደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሓምዱ ወሁዋ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" 100 ኛውን ይሞላል። ትርጉሙም "ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው ምንም ነገር የለም ፤ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ ነው ፣ ግዛቱ የእርሱ ነው፤ ምስጋናም ለእርሱ ነው፤ እሱም በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነው።»
- ከዚያም አያተል-ኩርሲይ **"አሏሁ ላ ኢላሃ ኢላ ሁወል ሓዩል ቀዩም..."** (ገጽ 11) ፣ ሱራ አል ኢኽላስ/ **"ቁል ሁወሏሁ አሓድ... "** (ገጽ.33) ፣ ሱረቱል ፈለቅ **"ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ..."** (ገጽ.34) ፣ እና ሱረቱን-ናስ **"ቁል አዑዙ ቢረቢናስ..."** (ገጽ 36) ያነባል ። (**ል.በ.** ገጽ 11,33 ፣ 34 እና 36 ማለት በዚህ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡበት ነው)።

አስፈላጊ ጥቆማ -

- ከሶላት ትክክለኛነት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል በሶላቱ ውስጥ መሸፈን ያለባቸውን የሰውነት ክፍሎች መሸፈን አንዱ ነው። በሶላቱ ወቅት እነዚህ ክፍሎች እንዳልተገለጡ ማረጋገጥ አለበት፤ ካልተሸፈኑ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም ::



- ከኢማሙ ጋር የሚሰግደው አንድ ሰው ብቻ ከሆነ ያ ሰው በቀኝ ጎኑ መቆም አለበት። አንድ ሰው ከሌላው ጎን ሆኖ ሲሰግድ እንደሚቆመው ወደፊትም ወደኋላም ሳይል አብሮት መቆም አለበት።



ሶላቶች በጥቅሉ

ስም	ኢስላማዊ ፍርዱ	ጊዜው	ረከዓዎቹ	ማብራርያ
የጁሙዓ ሶላት	ግዴታ	በዙህር ሰአት	2	ጁሙዓ ጮክ ተብሎ በሚቀራ የሚሰገድ፤ በሦስት ወይም ከዚያም በላይ በሆኑ ወንዶች ሊከናወን የሚችል ነው።
የፀሃይ ግርዶሽ ሶላት	ማህበሰባዊ ግዴታ (ፈርዱን ኪፋያ)	ግርዶሹ ሲከሰት	2	በእያንዳንዱ ረከዓ ላይ ሁለት ሩኩዕ በማድረግ ጮክ ብሎ በሚቀራ ሶላት የሚከናወን ነው።
የዊትር ሶላት	እጅግ ጠንካራ ሱና	ከዒሻእ ሶላት በኋላ እስከ ፈጅር ድረስ	ከ 1-11	ያም የሚከናወነው ወይ፡ - አንዲት ረከዓ ብቻ፤ - ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ የሚቀመጥበት ሶስት ተከታታይ ረከዓዎች፤ ወይም ደግሞ ሁለት ረከዓዎችን ይሰግድና ካሰላመተ በኋላ አንድ ረከዓ ይጨምራል፤ - ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ በመቀመጥ አምስት ተከታታይ ረከዓዎች፤ - ለመጨረሻ ተሸሁድ ብቻ በመቀመጥ ሰባት ተከታታይ ረከዓዎች፤ - በስምንተኛው ለተሸሁድ በመቀመጥ ሳያሰላምት ለዘጠነኛው ተነስቶ የሚጨምርበት እናም ተሸሁድ ካለም በኋላ የሚያሰላምትበት፤ - ሁለት ሁለት እያደረገ በመስገድ አንዲት ረከዓ ብቻዋን በመስገድ ዊትር የሚያደርግበት ነው።

የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

የፈጅር ሱና	እጅግ በጣም ጠንካራ ሱና	ከሱብሒ ሶላት በፊት	2	በ 1 ኛው ረከዓ ሱረቱል ካፊሩንን ይቀራል እና በ 2 ኛው ረከዓ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስን ይቀራል።
የዝሁር ሱና	ተወዳጅ ሱና	ከዝሁር በፊት አራት እና ከዝሁር በኋላ ሁለት ረከዓ	4 እና 2	ሁለት ሁለት ረከዓ በመከፈል
የመግሪብ ሱና	ተወዳጅ ሱና	ከመግሪብ በኋላ	2	በ 1 ኛው ረከዓ ሱረቱል ካፊሩንን ይቀራል እና በ 2 ኛው ረከዓ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስን ይቀራል።
የሚሻ ሱና	ተወዳጅ ሱና	ከሚሻ በኋላ	2	
ተራዊሕ	ተወዳጅ ሱና	ከሚሻ በኋላ እስከ ፈጅር ድረስ	ከ 2 - 10	
ተሕየተል መስጅድ (መስጅድ ስለገባህ የሚሰገድ)	ግዴታ	መስጅድ በገባህ እና ከመቀመጥህ በፊት	2	
ሶላተ ዱሓ	ተወዳጅ ሱና	ፀሃይ ከፍ ካለችበት ጀምሮ እስከ ዙህር ድረስ	2-8	
ሶላተል ኢስቲኻራ (አሏህ የማማከር ሶላት)	ተወዳጅ ሱና	በየትኛውም ጊዜ	2	ከማሰላመቱ በፊት የኢስቲኻራ ዱዓውን ያደርጋል

የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

ሶላተል ኢስቲስቃእ (ዝናብ እንዲመጣ የሚሰገድ ሶላት)	አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተወዳጅ ሱና ነው	ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ	2	በአንደኛው ረከዓ ልክ እንደ ዒድ ተክቢራ ተክቢረተል ኢሕራምን ጨምሮ ሰባት ጊዜ “አሏሁ አክበር” ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ አምስት ጊዜ “አሏሁ አክበር” ይላል። ይህ ግን የመሸጋገሪያን ተክቢራ አይጨምርም።
የዒድ ሶላት	ተወዳጅ ሱና	ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ	2 ረከዓ እና 2 ኹጥባ	በአንደኛው ረከዓ ተክቢረተል ኢሕራምን ጨምሮ ሰባት ጊዜ “አሏሁ አክበር” ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ አምስት ጊዜ “አሏሁ አክበር” ይላል። ይህ ግን የመሸጋገሪያን ተክቢራ አይጨምርም።

ልቅ የሆነ የሱና ሶላት መስገድ የሚከለከልባቸው ጊዜያት

1 .ኀህ ከቀደደ ጀምሮ ፀሃይ የዘንግን ያህል ከፍ እስከምትልበት ጊዜ ድረስ

2 .ከዓሱር ሶላት ጀምሮ ፀሃይዋ እስክትጠልቅ ድረስ

3 .የፀሃይ ከመሃል አናት መሆን ጀምሮ ዘንበል እስክትል ድረስ

ስለሶላት ፈተና

1. ሶላት ስንት ቅድመ ሁኔታዎች አሉት? O 9 O 11 O 8
2. ሙስሊም ካልሆነ በስተቀር ማንም ስለማይሰግድ ‹እስልምናን› እንደሶላት ቅድመ ሁኔታ መቁጠር ስህተት ነው (እውነት – ሃሰት)
3. 'የመለየት ዕድሜ' ማለት የጉልምስና ዕድሜ ማለት ነው። (እውነት – ሃሰት)
4. 'ነጃሳ ነገሮችን ማስወገድ' አካልን ፣ ልብሶችን እና ቦታውን ሁሉ ይመለከታል (እውነት – ሃሰት)
5. የአሳማ ነጃሳነት: O ከባድ O መካከለኛ
6. ከፈሰሰ ገላን መታጠብ ግዴታ ስለሚያደርግ የዘር ፈሳሽ(መንይ) ርኩስ ነው። (እውነት – ሃሰት)
7. ውሃን በመርጨት እና በማጠብ መካከል ምንም አይነት ልዩነት የለም (እውነት – ሃሰት)
8. ከመታረዱ በፊት የሞተ እንስሳ ሁሉ ነጃሳ ነው (እውነት – ሃሰት)
9. የውሻን ነጃሳ ለማስወገድ አፈርን በዘመናዊ (እንደሳሙና) ባሉ ማፅጃዎች መጠቀም በቂ ነው። (እውነት – ሃሰት)
10. መግባት መውጣት የሚያበዙ ለመጠባበቁ አስቸጋሪ የሆኑ እንስሳት ሲሆን ነው፤ ለምሳሌ፡ ድመት ለአንዳንዶቹ ጡሃራ ሁና ለሌሎች ግን ነጃሳ ልትሆን ትችላለች። (እውነት – ሃሰት)
11. 'እስትንፋስ' የሌለው ነገር' ስንል “እስትንፋስ” የተባለው “ነፍስ” ለማለት ነው። (እውነት – ሃሰት)
12. በደም ሥሮች ውስጥ የሚቆይ ደም... O ነጃሳ O ጡሃራ
13. የሶላት ማእዘናት ስንት ናቸው O 14 O 9 O 8
14. የመጀመሪያ ተክቢር ማለት እጆችን ከፍ ማድረግ ማለት ነው (እውነት – ሃሰት)
15. አንድ ሰው ማእዘንን ረስቶ ከዘነጋ ፣ የመርሳት ሱጁድ መስገድ ብቻ ነው የሚጠበቅበት (እውነት – ሃሰት)
16. ሶላት ስንት ግዴታዎች አሉት? O 8 O 14 O 9

17. አንድ ሰው "ሱብሓነ ረቢየል አዕላ" የሚለውን ቢያንስ አንድ ጊዜ ማለቱ ግዴታ መሆኑን ከማወቁም ጋ "ሱቡሕ ቁዱስ ረቡል መላኢከቲ ወሩሕ" ብሎ ቢናገር ሶላቱ ውድቅ ነው። (እውነት–ሃሰት)
18. የቀኝ እጅን መዳፍ በግራ እጅ ጀርባ እና አንጓው ላይ ማድረጉ የተደነገገ ነው። (እውነት – ሃሰት)
19. በለሊቱ ክፍለ ጊዜ በሚሰገዱ እና የሚድ ሶላቶችን በመሰሉ መሰብሰብ የተደነገገባቸው ሶላቶች ቁርአንን ጮክ ብሎ መቅራቱ የተደነገገ ነው። (እውነት – ሃሰት)
20. ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ስንት ናቸው? O 8 O 9 O 14
21. ተወሩክ የሚባለውን አይነት አቀማመጥ የምንቀመጠው በ _____ *ተሸሁድ* ነው።

O1ኛው O መጨረሻው O ሁሉም

22. "ረበና ወለከል ሓምድ" ካልን በኋላ "ወሹክር" ጨምሮ *"ረበና ወለከለ ሓምዱ ወሹክር"* ማለት…

O የተከለከለ O የተወደደ O የተፈቀደ

23. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል: "ረቢግፊርሊ ወሊዋሊደየ" ማለት the 2 prostrations is…

O የተፈቀደ O የተከለከለ O የተወገዘ

24. በሱጁድ ጊዜ ክርንን ምድር ላይ ማድረግ …

O የተከለከለ O የተወደደ O የተወገዘ

25. የሱጁደ ሰህው(የመርሳት ሱጁድ) ምክንያቶቹ ብዛት ስንት ናቸው? O 2 O 3 O 4
26. ድርጊቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ጥርጣሬ ተፅእኖ የለውም፤ ጥርጣሬ የሚበዛበት ሲሆንም እንዲሁ (እውነት – ሃሰት)
27. የፊጅር ሶላት ሱና በሌላው የግዴታ ሶላት ጋ ተቆራኝተው ከሚመጡ የሱና ሶላት አምሳዮቿ የምትለየው፡ በበላጭነቷ፣ በቀላልነቷ፣ ባሏት ልዩ ተመርጠው የሚቀሩ ሱራዎች፣ በጉዞም ላይ

ለመሰገድ ያላት ተጠባቂነት፣ በቤት በሚሰገድበት አጋጣሚ ደግሞ ከተሰገደች በኋላ ጋደም ማለት የሚበረታታ በመሆኗ ነው። (እውነት – ሃሰት)

28. የተከታዮቹን ቁምነገሮች ኢስላማዊ ፍርድ አብራራ:

ጉዳዩ	ፍርዱ
ዲኑን የሰደበ ሰው ሶላት	
በስካር ላይ ያለ ሰው ሶላት	
በአልዝሃይመር በሽታ የተጠቃ ሰው ሶላት	
የህፃን ልጅ ሶላት	
ረስቶ ዉዱእ ሳያደርግ ሰገደ	
ረስቶ በተነጀሰው ልብሱ ሰገደ	
የላም ሽንት	
የአሞራ ሽንት	
ተፋዎቹ ሳይሸፈኑ ሰገደ	
ረስቶ ጊዜው ሳይደርስ ሰገደ	
በፕሌን ውስጥ ሰገደ	
በጥቅሉ የጊዜውን ግዴታ በሚል ኒያ(ሃሳብ) ሰገደ	
ተቀምጦ ሰገደ	
ፋቲሓን መቅራት ዘነጋ	
(ዘግይቶ በመምጣቱ) ኢማሙን ያገኛቸው ሩኩዕ ላይ ነው	
ሶላት ላይ መጣደፍ	
ከሰገደ በኋላ ብዙ ጥርጣሬን ተጠራጠረ	
ተክቢረተል ኢሕራም ካደረገ በኋላ ስለውዱኡ ተጠራጠረ	

የአስራ አንደኛው ትምህርት ማብራርያ

ረስቶ ሩኩዕ ጨመረ	
ተክቢረተል ኢሕራምን ተወው	
የመጀመርያውን ተሸሁድ ተወው	
የመጨረሻውን ተሸሁድ ተወው	
የሰገደው ሶስት ወይንስ አራት የሚለውን ተጠራጠረ	
ከሰገደ በኋላ ተጠራጠረ	
በሚሰግድበት ጊዜ ተጠራጠረ	
ሱጁደ ሰህው(የመርሳት ሱጁድ) ላይ ሳለ ተጠራጠረ	
በሚሰግድበት ጊዜ ረስቶ ተናገረ	
ሰግዶ ከጨረሰ በኋላ እንጅ ልብ ሳይለው ሃፍረተ ገላው ተገልጦ ሰገደ	
ወደ ሶላት ከመሄድ በፊት ገና ቤት ውስጥ ሳሉ ንፅህናን መጠበቅ	
መስጅድ ውስጥ መሻሻጥ	
መስጅድ ውስጥ የገንዘብ ምንዛሬ ማድረግ	
ኢማሙን የመጨረሻው ተሸሁድ ላይ አገኛቸው	
በሶላት ጊዜ በፊትለፊትህ ሱትራ(ከለላ ነገር) ማድረግ	
ቀላል እንቅስቃሴ ማድረግ	
ብዙ የሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ	
ሶላትን በተጣደፈ መልኩ መስገድ	
በተሸሁድ ጊዜ ኢብራሂምይ የሆነውን ሶለዋት ማድረግ	
ሶላት ላይ ሳሉ መናገር	
ሶላት ላይ ሳሉ መንቀሳቀስ	
ፋቲሓን(አልሓምዱ ሊላህን) መቅራት ረሳ	

የጁሙዓህ ሶላት	
የዊትር ሶላት	
[መስጅድ ስለገባህ] ተሕየተል መስጅድ መስገድ	

29. የቅድመ ሁኔታ(ሸርጥ)፣ ማእዘን(ሩክን)፣ ግዴታ(ዋጅብ) እና ሱና ልዩነቱን ጥቀስ:

ቅድመ ሁኔታ	ማእዘን	ግዴታ	ሱና

አስራ ሁለተኛው ትምህርት

የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች

የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች አስር ናቸው:

1- ኢስላም 2- የአእምሮ ጤነኛ መሆን 3- መለየት የሚችልበት እድሜ ላይ መሆን 4- ኒያ (ትክክለኛ የሆነ ሃሳብ) 5- ፍርዷን ይዞ መዝለቅ፤ እስኪጨርስ ድረስ ማቋረጧን ላያስብ 6- ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች መሃል ላይ አለማቋረጣቸው 7- ከዛ በፊት ኢስቲንጃእ(ሃፍረተ ገላን በውሃ ማፅዳት) ወይም ኢስቲጅማር(ሃፍረተ ገላን በደረቅ ነገር ማፅዳት) ማድረግ 8- የውሃው ጡሃራ እና ሓላል መሆን 9- የውሃ ወደ ቆዳ ተደራሽ መሆን ሊያቅብ የሚችልን ነገር ማስወገድ 10- በየጊዜው ውዱእ የማፍረስ ችግር ላለበት ሰው የጊዜው መግባቱ

<u>የአንዳንዶቹ ቅድመ ሁኔታዎች ማብራርያ</u>

- “ፍርዷን ይዞ መዝለቅ፤ እስኪጨርስ ድረስ ማቋረጧን ላያስብ" ሲባል ዉዱእ የማድረግ ሃሳቡ እስከመጨረሻው ድረስ ዘላቂ ይሁን ማለት ነው።
- "ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች መሃል ላይ አለማቋረጣቸው" ሲባል እንደምሳሌ የግመል ስጋ እየበላ ውዱእ ማድረግ የለበትም፤ ወይም እየሸና፤ ይልቅ ውዱእ ማድረጉን ከመጀመሩ በፊት ውዱእን የሚያፈርሱ ነገራቶች አቋርጦ ሊሆን ይገባዋል።
- "ከዛ በፊት ኢስቲንጃእ(ሃፍረተ ገላን በውሃ ማፅዳት) ወይም ኢስቲጅማር(ሃፍረተ ገላን በደረቅ ነገር ማፅዳት) ማድረግ" ሲባል ከዚህ ተነጥሎ የሚወጣው ውዱእ የሚያድረግበት ምክንያት በአየር ምክንያት(ፈስቶ) ከሆነ፣ በእንቅልፍ ምክንያት ከሆነ፣ የግመል ስጋ በልቶ ከሆነ ብቻ የተለየ ህግ ይኖረዋል።

- "የውሃው ጡሃራ እና ሓላል መሆን" ሲባል ነጃሳ በሆነ ወይም በተዘረፈ ውሃ መሆን የለበትም ለማለት ነው።

- "የውሃ ወደ ቆዳ ተደራሽ መሆን ሊያቅብ የሚችልን ነገር ማስወገድ" ሲባል እንደቡሆ እና የጠፍር ቀለም ያሉ ነገራቶችን ማስወገድ ለማለት ነው። ምክንያቱም እነኝህ ውሃ ወደሰውነት እንዳይደርስ ያግዳሉና።

ሱነኑል ፊጥራ (ተፈጥሯዊ ሱናዎች)

ከተፈጥሯዊ ሱናዎች መካከል

1- **ግርዛት**: ለወንድ ልጅ ግዴታ ሲሆን ለሴት ልጅ ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተወደደ ነው።

2-5- **ቀድሞ ቀመስን(በአፍንጫና በላይኛው ከንፈር መካከል ያለውን የፂም ክፍል) ማሳጠር፣ ጥፍር መቁረጥ፣ የብብትን ፀጉር መንቀል፣ በሃፍረተ ገላ ያለውን ፀጉር መላጨት፡** ከአነስ –ረድየሏሁ ዓንሁ- በተላለፈ ሓዲሥ እንዲህ ይላል: **"ነብዩ ﷺ ቀድሞ ቀመስን ለማሳጠር፣ ጥፍርን ለመቁረጥ፣ የብብትን ፀጉር ለመንቀል እና በሃፍረተ ገላ ያለውን ፀጉር ለመላጨት ከአርባ ለሊቶች በላይ እንዳንተወው የጊዜ ገደብ አደረጉልን።"**

6- **ፂምን ማፋፋት**: It ፂምን ማሳደግ ፍርዱ ግዴታ ሲሆን፤ መላጨቱ ከከባባድ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው።

7- **ሲዋክ:** ልዩ የሆነ አትክልት ዛፍ ተጠቅሞ ጥርስን ማፅዳት ነው። መሰረታዊ ፍርዱ የተወደደ በተለይም ደግሞ በተከታዮቹ አጋጣሚዎች፡ በውዱእ ጊዜ፣ በሶላት ጊዜ፣ ቤት በሚገባበት ጊዜ፣ ቁርአን በሚቀራበት ጊዜ፣ ከምኝታ በሚነሱበት ጊዜ፣ ለሞተ ሰው(ሌሎች ሊያፀዱለት) እና የአፍ ጠረን በሚቀይርበት ጊዜ ይበልጥ ጠንካራ ሱና ነው።

አስራ ሶስተኛው ትምህርት

የውዱእ ግዴታዎች

የውዱእ ግዴታዎች ስድስት ናቸው:

1- ፊትን ማጠብ፣ መጉመጥመጥንና መሰርነቅን(አፍንጫን በውሃ ማፅዳት) ያቀፈ ነው።

2- ክርንን ጨምሮ ሁለቱንም እጆች ማጠብ

3- ጆሮን ጨምሮ መላ ራስን ማበስ

4- ቁርጭምጭሚትን ጨምሮ ሁለቱንም እግሮችን ማጠብ

5- ቅደም ተከተላቸውን መጠበቅ

6- ማከታተል

ፊትን፣ ሁለት እጆችን፣ ሁለቱንም እግሮችን እንዲሁም መጉመጥመጥንና መሰርነቅም ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠቡ የተወደደ ነው። የነኝህ ግዴታቸው ግን አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ራስን ማበስ ግን ከነብዩ ﷺ የመጡ ሶሒሕ ሐዲሦች እንደሚጠቁሙን መደጋገሙ የተወደደ አይደለም።

የተረጋገጠው ማከታተል

ውዱእ የሚያደርግ ሰው አንድን አካል ሲያጥብ ከበፊቱ ያጠበው አካል እስኪደርቅ ድረስ ባለማዘግየቱ የሚሆን ነው።

አስራ አራተኛው ትምህርት

ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች

ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች ስድስት ናቸው:

1- ከሁለቱ መፀዳጃዎች የወጣ ነገር ሁሉ

2- ከሌላ የሰውነት አካልም ቢሆን የወጣ ፀያፍ ነጃሳ ነገር ሁሉ

3- በእንቅልፍም ይሁን በሌላ ህሊናን መሳት

4- የፊትም ይሁን የኋላ ሃፍረተ ገላን ያለግርዶሽ መንካት

5- የግመል ስጋ መብላት 6- (አሏህ ይጠብቀንና) ከኢስላም መቀልበስ

አሳሳቢ ጥቆማ:

ጀናዛን(ሟችን) ማጠብን በማስመልከት: ትክክል የሚሆነው ውዱእን አይፈርስም የሚለው ነው። ይህን የሚያመላክት ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የበርካቶቹ ዑለሞች ቃል ነው። ነገር ግን የአጣቢ እጅ ያለ ግርዶሽ የሟችን ብልት ከነካች ግን ውዱእ ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል። ማድረግ የሚጠበቅበት ግን በግርዶሽ ተጠቅሞ ካልሆነ በቀር የሟችን ብልት አለመንካት ነው።

እንዲሁም **ሴትን ልጅ መንካት**[1] ከዑለሞች ጠንከር ያለውን ቃል በመመርኮዝ በስሜትም ይሁን ከስሜት ውጭ መሆኑ ልዩነትና ገደብ ሳይኖረው አንዳች ነገር እስካልወጣው ድረስ ውዱእ የሚያፈርስ አይደለም። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ባለቤታቸውን ስመው ውዱእ ሳያደርጉ ሰግደዋልና። "...ሴትንም የነካችሁ ብትኾኑ..." (አልማኢዳህ 6) የሚለው ደግሞ የተፈለገበት ይበልጥ ለእውነት ቅርብ በሆነው የዑለሞች ቃል መሰረት ዖታዊ ግንኙነት ነው። ይህም የነኢብኑ ዓባስ እንዲሁም ሌሎች ቀደምትም ኋላ ከመጡ ታላላቅ ተተኪዎችም የመረጡት ቃል ነው።

[1] ልብ በል፡ ከሴት ልጅ ጋ ወይም ከተቃራኒ ፆታ ጋ ያለ መስተጋብር **መገደቡ**ም ሆነ ተቃራኒ ፆታን ሰላም ማለት **የማይቻለው** ተቃራኒ ፆታን ሰላም ማለት ዉዱእን ስለሚያፈርስ አይደለም። [ተርጓሚው]

ውዱእ ከሚያፈርሱት የከፊሎቹ ማብራርያ

"ከሁለቱ መፀዳጃዎች የወጣ ነገር ሁሉ" ሲባል በልቁ ነው፤ እንደ ሽንት፣ ሰገራ፣ መንይ (የዘር ፈሳሽ)፣ መዝይ(ጠረን የለሹ ነጭ ፈሳሽ)፣ ወድይ(ከሽንት በኋላ የሚወጣው ፈሳሽ አይነት)፣ ፈስ፣ ጠጠርም ቢሆን፣ ደም፣ ትል ነገር፣ የወር አበባ ደም እና የወሊድ ደም ሁሉ ማለት ነው።

"ከሌላ የሰውነት አካልም ቢሆን የወጣ ፀያፍ ነጃሳ ነገር ሁሉ" ያለውን በማስመልከት ይበልጥ ሚዛን የሚደፋው የዑለሞች ቃል ሽንትና ሰገራ ነክ ነገር ካልሆነ በቀር ውዱእ አያፈርስም የሚለው ነው።

"በእንቅልፍም ይሁን በሌላ ህሊናን መሳት" ሲባል እንቅልፍ በመሰረቱ ውዱእ የሚያፈርስ ሆኖ አይደለም። ይሁን እንጅ አየር(ፈስ) ለማውጣ አመች ነው። በመሆኑም ከሱ አንዳች ነገር እንዳልወጣ እርግጠኛ መሆን የሚችልበት ሁኔታ ላይ ከነበረ ውዱእ አፍርሷል ሊባል አይችልም።

"የፊትም ይሁን የኋላ ሃፍረተ ገላን ያለግርዶሽ መንካት": የሚለውን በማስመልከት አሏህ ይዘንለትና ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ በመንካት ብቻ ውዱእ ማድረጉ የተወደደ እንጅ ግዴታ እንዳልሆነ ሚዛን የሚደፋ አቋም መሆኑን አብራርተዋል።

የውዱእ አደራረግ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ

-ውዱእ ለማድረግ ሲፈልግ “ቢስሚላህ” ይበል።

- ከዚያም በውሃ አድርጎ ሁለት እጆቹን ሶስቴ ያጥባል

- ከዚያም በቀኝ እጁ ውሃ ዘግኖ ለመጉመጥመጥ ወደ አፉ በማስገባት በኮሸኮሸው ደግሞ ወደ አፍንጫው በመሳብ ከዚያም ደግሞ የግራ እጅ ጠቋሚ ጣቱን ከአውራ ጣቱ ጋ አድርጎ ከአፍንጫው እንዲወጣ ያደርገዋል፤ ይህንንም ሶስት ጊዜ ይደጋግመው።

- ከዚያም ፊቱን ሶስቴ ያጥበዋል፤ ፊት ሲባል ገደቡ ቁመቱ ከተለምዶው የራስ ፀጉር መብቀያ ወደታች እስከ አገጭና ፂም ጫፍና ጠርዝ ድረስ ሲሆን ወደ ጎን ደግሞ በሁለቱ ጆሮዎች መካከል ነው።

- ከዚያም ከቀኝ እጁ ጀምሮ ግራ እጁን በማስከተል ሁለት እጆቹን ክርኑንም ጨምሮ ሶስቴ ያጠባቸዋል።


- ከዚያም ከግንባሩ ጀምሮ ማጅራቱ ድረስ አብሶ ድጋሚ በመመለስ አካኋን ራሱን ያብሳል።

- ከዚያም ሁለቱን ጠቋሚ ጣቶቹን ጆሮው ውስጥ በመክተት ጆሮውን ያብሳል።

- ከዚያም እግሮቹን ከቁርጭምጭሚቱ ጋ ሶስቴ ያጥባል።







-ውዱእ ማደረጉን ሲያጠናቅቅ እንዲህ ይላል *"አሸሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ወአሸሃዱ አነ ሙሓመደን ዓብዱሁ ወረሱሉሁ"* [2] በቲርሚዝይ ዘገባ ደግሞ እንዲህ የሚል ጭማሪ ይገኛል *"አሏሁመ ጅዓልኒ ሚነተዋቢነ ወጅዓልኒ ሚነል ሙተጠሂሪን"*[3]

ከተደነገገው ልክ በላይ መጨመር ያለው ፍርድ

በውዱእ ጊዜ ከተደነገገው በላይ መጨመር አይፈቀድም። ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብን ይመስል፣ ከክርን በላይ ትከሻ ድረስ ማጠብን ይመስል፣ ወይም ከቁርጭምጭሚት በላይ ባትን ማጠብ ይመስል፣ወይም ራስን ሲያብሱ ማጅራትን ጨምሮ ማበስ ይመስል።



[2] ትርጉሙም "ከአሏህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አለመኖሩን እና ተጋሪ የሌለው ብቸኛ መሆኑን እመሰክራለሁ፤ እንዲሁም ሙሐመድም ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ"

[3] ትርጉሙም፡ አሏህ ሆይ! ወዳንተ ከሚመለሱት አድርገኝ፤ ከሚጥራሩትም አድርገኝ።

ከንፅህና ጋ ተያያዥ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች

የመጀመርያው: ጡሃራ (መጥራራት)

'ተየሙም'

አካልን ወይም ከፊሉን ለመታጠብ የሚያስፈልገው ሊገኝ ባለመቻሉ ወይንም ቢኖርም እንኳ መጠቀሙ የሚያሰጋ በመሆኑ ውሃን መተካት ነው። በመሆኑም አፈር ውሃን የሚተካ ይሆናል ማለት ነው።

የተየሙም ምንነት

ተየሙምን በማሰብ “ቢስሚላህ” ይላል። ከዚያም ንፁህ የሆነው ምድር ላይ እጁን ያሳርፍና በዚያው በመዳፎቹ የእያንዳንዱን መዳፍ ጀርባ እና ፊቱን ያብሳል።



እጁን መሬት ላይ ሲያሳርፍ ጣቶቹን ከፈትፈት ማድረጉ የተደነገገ አይደለም፤ የመዳፎቹን ጀርባ ሲያብስም ጣቶቹን መፈልፈል አይጠበቅበትም።



ግዴታ የሆነው ገላን መታጠብ ሁኔታው

መታጠብንና ከጀናባ መጥራትን በልቡ ሊያስብ ይገባዋል፤ ከዚያም "ቢስሚላህ" ይበልና በስስም ይሁን በብዙም ፀጉር ስር ያለን ሁሉ በማዳረስ በመጉመጥመጥ እንዲሁም በመሰርነቅ መላ ሰውነቱን ይታጠብ።

በትጥበት ጊዜ ተወዳጅ የሆኑ ነገሮች

በመጀመርያ ሃፍረተ ገላውን መታጠብ፤ ከዚያም ሁለት እጆቹን፤ ከዚያም ለሶላት እንደሚያደርገው ውዱእ ያድርግ፤ የፀጉሮቹን ስሮች ማዳረስ፤ ከዚያም በቀኝ በኩል አጥቦ በግራ በኩል ይታጠብና ከዚያም ሁለት እግሮቹን ይታጠባል።

ትጥበትን ግድ የሚያደርጉ ነገሮች

1- ጀናባ: ወይ በግንኙነትም ይሁን በሌላ ምክንያት የዘር ፈሳሽ በመፍሰሱ አልያም ደግሞ የሁለቱ ጥንዶች ብልት ስለተነካካ ብቻም ይሆናል።

2- የወር አበባ ደም ወይም የወሊድ ደም ስለፈሰሰ

3- ሸሂድ (ለዲነል ኢስላም ልቅና የተሰዋ) ካልሆነ በቀር በሌላ ከሞተ

4- ካፊር እስልምናን ከተቀበለ

በሁለት ካልሲዎች(ኹፎች) ላይ የማበስ ቅድመ ሁኔታዎች

ኹፎቹ ወይም ካልሲዎቹ ጡሃራ መሆን አለባቸው።

ኹፎቹን ሲያጠልቃቸው በጡሃራ (እግሮቹ) መሆን አለበት፤ ማለትም፡ ውዱእ ሲያደርግ ሁለት እግሮቹን ካጠባቸው በኋላ (ያጠለቃቸው) መሆን አለበት።

በካልሲዎቹ ላይ ማበሱ ለትንንሽ ርክሰት (ለውዱእ ማፍረስ) እንጅ በጀናባ ወይም ገላን መታጠብ ግድ ለሚያስብል ነገር መሆን የለበትም።

ካልሲዎቹ አብዛኛውን የእግሩን ክፍል የሚሸፍኑ መሆን አለባቸው።

ማበሱ በሸሪዓው በተገደበው የጊዜ ልኬት ገደብ ውስጥ መሆን ይኖርበታል። ይህም መንገደኛ ላልሆነ አንድ ቀን ከለሊት (24 ሰዓት) ሲሆን፤ ለመንገደኛ ደግሞ ሶስት ቀን ከለሊቱ (72 ሰአታት) ያህል ነው። ሰአት ቆጠራው የሚጀምረው ውዱእን አድርጎ ካጠለቃቸው በኋላ ውዱእን አፍርሶ ለአዲሱ ውዱእ መጀመርያ ካበሰበት ሰአት ነው።

በኹፎቹ(ካልሲዎቹ) ላይ የሚታበስበት አኳኋን?

እጁን ከእግሩ ጠርዞች ጀምሮ እስከባቱ ድረስ ማሳለፍ ነው። ማለትም የሚታበሰው ክፍል የኹፉ (የካልሲው) የላይኛው ክፍል ነው ለማለት ነው። ስለዚህም እጆቹን ከእግሮቹ ጣቶች እስከ ባቱ ድረስ ብቻ ያንሸራትታል። ይህ ማበስ በሁለቱም እጆቹ አንድ ላይ ከሁለቱም እግሮቹ ላይ ነው የሚሆነው። ማለትም ቀኝ እጁ እግሩ እግሩን የምታብስ ስትሆን በዛው ቅፅበት የግራ እጁም የግራ እግሩን የምታብስ ትሆናለች ማለት ነው። ልክ ሁለቱን ጀሮዎቻችንን በምናብስበት መልኩ ማለት ነው። ምክንያቱም ከሱና የምንረዳው ጉልሁ መልዕክት ይህንኑ ነውና።

ከማበስ ጋ ተያያዥነት ያላቸው ቁምነገሮች

1- የማበስ ጊዜው ከተቋጨ አልያም የታበሰበት ከወለቀ ጡሃራው እንዳለ ነው፤ ውዱኡ አልፈረሰም።

2- በቀዳዳ ኹፍ (ካልሲም) ላይ ማበስ ይቻላል፤ እንዲሁም ባለው ቀዳዳ ምክንያትም ይሁን በስስነቱ ቆዳን የሚያሳይም (እንዲሁ ለማበስ መጠቀም ይቻላል)።

የመፀዳዳት ስነ-ስርዓቶች

<u>ተወዳጅ የሆኑ:</u>

-ወደ መፀዳጃ ቤቱ ሲገባ ግራ እግሩን በማስቀደም እንዲህ ማለቱ "***ቢስሚላሂ አሏሁመ ኢኒ አውዙቢከ ሚነል ኹቡሢ ወልኸባኢሥ***". (ትርጉም፡ በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፤ አሏህ ሆይ! ከወንድም ሆነ ከሴት አጋንንት ባንተው እጠበቃለሁ።)

-ሲወጣ ደግሞ ቀኝ እግሩን በማስቀደም "***ጹፍራነከ***" ማለቱ (ትርጉም፡ መሃርታህን ጌታየ)

<u>ግዴታው</u>፡ በአጥር ነገር አልያም በሌላ መከለል፤ ገላጣ መሬት ላይ ከሆነ ደግሞ ከሰው ራቅ ማለቱ

<u>የማይፈቀድለት:</u>

-በመንገድ ላይ፣ ሰዎች በሚቀማመጡበት ቦታ፣ በምታመርት ዛፍ ስር፣ ወይም ሰዎችን ሊያስቸግር በሚችል ቦታ እንዲሁም በረጋ ውኃ ላይ መፀዳዳት፤

-በሚፀዳዳበት ጊዜ ጀርባውን አልያም ፊቱን ለቂብላ መስጠት፤

- ብልቱን በቀኝ እጁ መንካት፤

-አሏህን ማውሳት፤

ተፀዳድቶ እንዳጠናቀቀ ወይ በውኃ ያጥበዋል ወይም ደግሞ በደረቅ ነገር ያፀዳዋል(ኢስቲጅማር)፤

<u>የኢስቲጅማር (በደረቅ ነገር የማፅዳት) ቅድመ መስፈርቶች:</u>

- ሶስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ መጥረግ፤ ይህ ሲባል ግን በአንድ ማፅጃ ተመሳሳይ ቦታ (ደጋግሞ) መጥረግ የለበትም።

- ማፅጃው በራሱ ፅዱ መሆን አለበት። ይህም ድንጋዩ ወይም መሃረቡ መልሶ ደረቅ በመሆኑ ሊታወቅ ይችላል።

- ኢስቲጃምር የሚደረገው በነጃሳ ነገር፣ እንደምግብ ባለ ክብር ነገር፣ ወይም በአጥንት እንዲሁም በእንስሳ ኩስ መሆን የለበትም።

የሸንቱ ፍንጣሪ በልብሱ ላይ አልያም በሰውነቱ ላይ እንደማያርፍ እንዲሁም ሃፍረተ ገላው ለእይታ እንደማይጋለጥ ለተማመነ ቆሞ መሸናት ይፈቀድለታል፤ “... **ነብዩ ﷺ ወደ ሰዎች መፀዳጃ ቦታ መጥተው ቆመው (ሽንታቸውን) ሲፀዳዱ አይቻቸዋለሁ።**” (ቡኻሪይ እና ሙስሊም)

ከንፅህና ጋ የተያያዙ ጥያቄዎች

1. ውዱእ ስንት ቅድመ መስፈርቶች አሉት? O 9 O 10 O 8

2. ውዱእ የማድረግ ግዴታዎች: Oአራቱ የሰውነት ክፍሎች O ከቅደም ተከተልና ማከታተልን በተመለከተ ያስቀደምነው።

3. ውዱእን የሚያፈርሱት ነገራቶች ብዛት ስንት ነው? O 6 O 5 O 8

4. ከሚከተሉት ውዱእን የሚያፈርሰው የትኛው ነው:

O የግመል ስጋ O የሚዳቋ ስጋ O የሆድ ድምፅ O አየር(ፈስ)

O እንቅልፍ O ሬሳ ማጠብ O ሴትን መንካት

5. የተየሙምን ሁኔታ አብራራ:

……

……

……

6. የትጥበትን አካኋን አብራራ:

……

……

……

7. የተከታዮቹን ነጥቦች ኢስላማዊ ፍርድ አብራራ:

ነጥቡ / ጉዳዩ	ኢስላማዊ ፍርዱ
ኒያን በቃል ማለት	
ውዱኡን ሲያደርግ ኒያው(ሃሳቡ) ለአንድ ሶላት ብቻ ነበር፤ ነገር ግን በዚያው ከዛ(ከአንዱ) በላይ ሶላቶችን ሰገደበት	
ውዱኡን ሲያደርግ ኒያው ቁርአን ለመቅራት ነበር፤ ግን ሰገደበት	
ውዱኡን በሚያደርግበት ሰአት ውዱእ የማድረጉ ኒያው (ሃሳቡ) ተቋረጠ	
ውዱኡን ካደረገ በኋላ ውዱእ የማድረጉ ኒያው (ሃሳቡ) ተቋረጠ	
ውዱእ አደረገና በባቱ ላይ ሊጥ ተመለከተ	
የግመል ስጋ እየበላ ውዱእ አደረገ	
በተሰረቀ ዉኃ ውዱእ አደረገ	
ኢስቲንጃእ ወይም ኢስቲጅማር ከማድረጉ በፊት ውዱእ አደረገ	
ለጆሮዎቹ እንደአዲስ ዉኃ ዘገነ	
ጭንቅላትን ሶስት ጊዜ ማበስ	
አንዳድ ጊዜ ብቻ እያጠቡ ውዱእ ማድረግ	
ዉዱእ በሚያደርጉበት ጊዜ ሶስት ሶስት ጊዜ ማድረግ	
ውዱእ በሚያደርጉበት ጊዜ ሁለት መዳፎችን መታጠብ	
ፂምን እየፈለፈሉ ማጠብ	
በውዱእ ጊዜ እያሹ መታጠብ	
መታጠብ ያለበትን በማበስ ብቻ መብቃቃት	
ፀጉርን መታጠብ	
መዳፎችን በውኃ ቋቱ ውስጥ ማስገባት	

በውዱእ ጊዜ ቀኝን ማስቀደም	
የውዱእ አካላትን ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብ	
ባትን ማጠብ	
ከዋና በኋላ ቀጥታ ሰገደ	
ገላውን ከታጠበ በኋላ ውዱእ ሳያደርግ ሰገደ	

ሁለተኛው : ዘካ

ሁለት አይነት ነው:

ዘካቱል ፊጥር

ይህ ዘካተል ፊጥር የምንለው ነው። በእያንዳንዱ ሙስሊም ትልቅም ይሁን ትንሽ፤ ወንድም ይሁን ሴት፤ ጨዋም ይሁን ባርያ ላይ ሁሉ ግዴታ ነች።

ዘካቱል ማል

ይህች ከእስልምና ማእዘናት ሶስተኛዋ የሆነችዋ የዘካ አይነት ነች። ይህች በእያንዳንዱ ጨዋ ሆኖ የሃብት መጠኑ በሸሪዓ የተወሰነውን የኒሷብ ልኬት የደረሰ ሁሉ ላይ ግዴታ ነች። ከምድሪቱ ለወጣ፤ እንዲሁም ኒሷቡ እንደሚፋፋ እና እንደ የንግድ ትርፍ ላለው መሰረቱን ይዞ ለሚያድግ አይነቱ አመት ለመሙላቱ ጊዜው የሚቆጠርለት በመሰረቱ ላይ ተንተርሶ ለሆነው ካልሆነ በቀር፤ ይህ የኒሷብ ልኬት መጠኑ ደርሶም ሙሉ አንድ አመት እስካልሞላው ድረስ በሃብቱ ላይ የዘካ ግዴታ የለበትም።

ይህም አራት አይነት ነው:

የንግድ ቁስ፡

ለሽያጭና ለግዥ የተጋለጠ ሁሉ

ከመሬት የሚወጣ

ፍራፍሬና ቡቃያ

የደለቦች የቤት እንስሳ

ለሙሉ አመት ወይም አመት ሊባል በሚችል በነፃነት የሚንከባከቧት፤ የቤት እንስሳ (በሂሙቱል አንዓም) ሲባል ግመል፣ ከብት እንዲሁም በግና ፍየልን ማለታችን ነው።

ወርቅና ብር

ወርቅና ብር(ሲልቨር) እንዲሁም ሌላም እንደነሱ ሆኖ የግብይት መሳርያ የሆነ፤ የወርቅ ኒሷብ 20 ሚሥቃል[85 ግራም] ሲሆን የ(ሲልቨር)ብር ኒሷብ 200 ዲርሃም [595 ግራም] ነው።

የዘካ ገንዘብ ባለቤቶች፡

1. **ድሆች /ፉቃራእ:** እነኝህ ማለት አንዳችም ነገር የሌላቸው፤ ቢያገኙም ከሚያስፈልጋቸው ጥቂቱን እንጅ የማያገኙ ችግረኞች ናቸው።

2. **ሚስኪኖች** : እነኝህ ማለት ከሚያስፈልጋቸው አብዛኛውን ወይም ግማሹን የሚያገኙ ናቸው። ለምሳሌ፡ አጠቃላይ አመታዊ ፍጆታ (ተደምሮ ለግለሰብ) 12000 ነው ብለን ብናስብ ድሃ ማለት እሱ ዘንድ ሊኖር የሚችለው (ቢደመር) 6000 ወይንም ከዚያ በታች የሆነ ማለት ሲሆን ሚስኪን ማለት ደግሞ እሱ ዘንድ ሊኖር የሚችለው 6000 ወይንም ከዚያ በላይ ነገር ግን 12000 የማይሞላ ማለት ነው። ይህም (አመት ያልነው) ሚስኪንንም ሆነ ድሃን የምንሰጠው በአመት አንድጊዜ ስለሆነ ነው፤ ዘካም ግዴታ የሚሆነው በአመት አንዴ ነውና።

3. **የዘካ ሰራተኞች:** እነዚህም ሰብሳቢዎቹ፣ ጥበቃዎቹ፣ በማከፋፈሉ የተመደቡት፣ የሙስሊሞቹ መሪ በሾመላቸው ሹም ይከናወናል። እነኝህ ስለድህነታቸው መገለፅ እንደቅድመ መስፈርት አይሆንም ይልቅ ሃብታሞች እንኳ ቢሆኑም የራሳቸው ድርሻ አላቸው።

4. **ልቦናቸው የተዘነበሉትን:** እስልምና እንደሚቀበሉ ተስፋ የተጣለባቸው ወይም ሸራቸውን ለማቀብ ወይም ደግሞ ኢማንን ለማጠናከር።

5. **ጫንቃዎችን ለማስለቀቅ:** እነኝህም:

ሀ. ራሱን ከአለቃው በገንዘቡ ነፃ የሚያወጣ ሙስሊም

ለ. ሙስሊም ባርያን ነፃ ለማውጣት

ሐ. ሙስሊም እስረኛን ነፃ ለማውጣት

የባርያው አለቃ አንድን ባርያ ነፃ ቢለቀውና ዘካ ነው ብሎ ቢያስብ አይፈቀድለትም።

6. **እዳ ላይ ያሉ:**

ሀ. በሰዎች መካከል ለማሸማገል ብሎ እዳ ውስጥ የገባን

ለ. ለራሱ ሲል እዳ ውስጥ የገባ

አንድ ድሃን ያበደረ ሰው ዘካን አስቦ እዳውን ቢምረው የዘካ ግዴታውን ተወጣ ማለት አይደለም።

7. **<u>በአሏህ መንገድ ለሚታገል:</u>** ለዘማቾችም ይሁን ለሚያስፈልጋቸው ትጥቅ ማሟላትንም ያካትታል።

8. **<u>ለመንገደኛም</u>**: ስንቁ የተቋረጠበት ለሆነ መንገደኛ ወደ ሃገሩ ሊያደርሰው የሚያስችለውን ያክል ይሰጠዋል።

ከነኝህ ከተዘረዘሩት ለአንዳቸው ብቻ በመስጠት መብቃቃትም ይቻላል። ዘካ ለሃብታምም ሆነ መስራት ለሚችል ብርቱ አይፈቀድም፤ እንዲሁም ለነብዩ ﷺ ቤተሰቦች ማለትም ለሃሺም ዘር እና ለነርሱው ባርያዎችም የተፈቀደች አይደለችም፤ የዘካ ገንዘቡን በሚያወጣበት ጊዜ በሱ ስር ለሆኑትና ጣጣቸውን ሊሸፍንላቸው ግዴታ የተጣለበትን ሰዎች ቢሰጥም አይፈቀድለትም፤ ለካፊርም የተፈቀደች አይደለችም። ተእማሪ በሆነ ሶደቃ ግን ለነኝህም ሆነ ለሌሎችም መስጠት ይፈቀዳል፤ ነገር ግን ይበልጥ ጠቀሜታዋ ዘርፈ ብዙ በግ=ሆነ ቁጥር ይበልጥ የተሟላች ነች።

አስፈላጊ ገለፃዎች

-***ቢንት መኽድ*** እድሜዋ ከአንድ አመት በላይ የሆናት ግመል ነች፤ በዚህ ስያሜ ልተራ የቻለችበትም ምክንያትም ከእናቷ ጫና አንፃር ነው።

- ***ቢንት ለቡን*** ሁለት አመቷ የሞላት ግመል ነች፤ በዚህ ስያሜ የተሰየመችውም እናቷ ባለወተት ስለሆነች ነው።

- ***ኦል-ሒቃህ*** ሶስት አመት የሞላት ግመል ነች፤ በዚህ የተሰየመችውም የግመል ኮረዳ ስለሆነች ነው።

-***ኦል-ጀዘዓህ*** እድሜዋ ከአራት አመት በላይ የሆናት ነች፤ በዚህም የተሰየመችው የፊት ጥርሷ የምትሰበረውና የምትወድቀው በዚህ እድሜዋ ስለሆነ ነው።

-***ኦት-ተቢዕ*** ወይንም ***ኦት -ተቢዓህ*** እድሜዋ አንድ አመት የሞላት ጥጃ ነች።

- ***ኦል-ሙሲንናህ*** እድሜዋ ሁለት አመት የሞላት ጊደር ነች።

የዘካ መጠን

የገንዘቡ አይነት	(ዘካ እንዲወጣበት) አመት መሙላቱ	ኒሷብ (የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት)	የዘካው መጠን
የደለበች የቤት እንስሳ (በሂመቱል አንዓም) [ግመል፣ ከብት፣ በግና ፍየል]	ቅድመ መስፈርት ነው	ቀጣዩን ሰንጠረዥ ተመልከት	ቀጣዩን ሰንጠረዥ ተመልከት
ከመሬት ከሚወጣ	ቅድመ መስፈርት አይደለም	300 ሷዕ (≈900 ኪሎ ግራም ገደማ)	ከዝናብ ወይም ከተፈጥሮ ምንጭ በተገኘ ውኃ አሊያም መሬቱ እርጥበታማ በመሆኑ ከበለፀገ 1/10
			በመስኖ ውኃ ከበለፀገ 1/20
			በሁለቱም መንገድ ከበለፀገ ሩብ ቀረሽ ለአንድ አስረኛ ይለግሳል
ከመገበያያ ገንዘብ	ቅድመ መስፈርት ይሆናል	85ግራም ወርቅ ወይም 595 ግራም ሲልቨር/ብር	የአንድ አስረኛ ሩብ
ከግብይት እቃዎች	ቅድመ መስፈርት ይሆናል	ከወርቅና ከብር ለድሆቹ ይበልጥ አመች በሆነው በመመርኮዝ ይወሰናል	የአንድ አስረኛ ሩቡ

የሳኢማ (ለመደለብ የተመደቡት በግ፣ ከብት፣ ግመል ፣ ፍየል) ኒሷብ እና የዘካው መጠን

የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

ከብት እና ጎሽ			ባለ አንድም ባለሁለትም ሻኛ ግመል			በግና ፍየል		
ዘካ የሚወጣው	መጠኑ		ዘካ የሚወጣው	መጠኑ		ዘካ የሚወጣው	መጠኑ	
	ከ	እስከ		ከ	እስከ		ከ	እስከ
ተቢዕ (አመት የሞላው ወንድ ወይም ሴት ከብት /ጥጃ)	30	39	1 በግ/ፍየል	5	9	1 በግ/ፍየል	40	120
			2 በግ/ፍየል	10	14			
ሙሲና (ሁለተኛ አመቷ የሆነች ጊደር)	40	59	3 በግ/ፍየል	15	19	2 በግ/ፍየል	121	200
			4 በግ/ፍየል	20	24			
2 ተቢዓ /ጥጃ	60	69	1	25	35	3 በግ/ፍየል	201	300
			1 ቢንተ ለቡን	36	45	ከዚያ በኃላ ለ 100 በግ/ፍየል 1 በግ/ፍየል		
ለየ 30ው, 1 ጥጃ ለየ 40ው, 1 ጊደር			ሒቃህ	46	60	ተከታዮቹ እንደ ዘካ ሊሆኑ አይወሰዱም: ከሲታ፣ አራስ ወይም ለመውለድ የቀረበች፣ ኮርማ እና በጣም ምርጥ የሆነ እንዲሁ ነውረኛ ገንዘብ ለዘካ አይወሰዱም		
			ጀዝዓህ	61	75			
			2 ቢንተ ለቡን	76	90			
			2 ሒቃህ	91	120			
			3 ቢንተ ለቡን	121	129			
			ለየ 40, 1 ቢንተ ለቡን. ለየ 50, 1 ሒቃህ					

የዘካ ፈተና

1. ሃብት በ …… የጊዜ አቆጣጠር ሙሉ አንድ አመት እስካልሞላው ድረስ የዘካ ግዴታ የለም።

O ዓመተ ሂጅራ(በኢስላማዊ) O ዓመተ ልደት(እኤአ/እሐአ) O ልዩነት የለውም

2. አመት መሙላት ለ …… የገንዘብ አይነት ዘካ መውጣት ቅድመ መስፈርት አይሆንም

O ማእድን O ከመሬት ለሚወጣ (ቡቃያ) O ሁሉም መልስ ይሆናል

3. የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት በወርቅ …

O 85 ግራም O 595 ግራም O 95 ግራም

4. የገንዘቡ ለዘካ ብቁነት ሸሪዓዊ ልኬት በብር (ሲልቨር) …

O 200 ዲርሃም O 595 ግራም O ሁሉም መልስ ይሆናል

5. በሂመቱል ኦንዓም ሲባል ግመል፣ ከብት፣ ጎሽ እንዲሁም በግና ፍየልን ያጠቃልላል

(እውነት – ሃሰት)

6. ፍራፍሬዎች የዘካ ግዴታ የለባቸውም (እውነት – ሃሰት)

7. ሳኢማ ማለት… O ዋጋዋ ውድ የሆነች O ለአመትና ከዚያም በላይ የደለበች

8. በተፈቀደ የምትታገድ ሲባል … O ጥሩ ጥሩውን የምትቀለብ O ባላባት የሌላት

9. ሚስኪኖች ከተወሱ ድሆችም በስሩ ይጠቃለላሉ (እውነት – ሃሰት)

10. ድሃ ሲሰጥ ሊሰጥ የሚገባው ለ …… የሚበቃውን ያክል ነው

O ለ 1 አመት O ለ 1 ወር

11. የዘካ ሰራተኞች ማለት …

O በዘካው ዙርያ የሚሰሩት ሰራተኞች በሙሉ O አስተዳዳሪው የሾማቸው ብቻ

12. የተከታዮቹን ዘካ መጠን ቀምረህ አስቀምጥ ፡

የገንዘቡ አይነት	የዘካው መጠን	ግዴታ የማይኖርበት ትራፊ ገንዘብ ካለ (ወቅስ)
100 ዲርሃም (የብር ሳንቲም)		
300 ዲናር (የወርቅ ሳንቲም)		
400 ዲርሃም (የብር ሳንቲም)		
80 ግራም ወርቅ		
500 ግራም ብር(ሲልቨር)		
30 በጎች/ፍየሎች		
60 በጎች/ፍየሎች		
565 በጎች/ፍየሎች		
4 ግመሎች		
17 ግመሎች		
449 ግመሎች		
30 ከብቶች		
49 ከብቶች		
77 ከብቶች		
99 ከብቶች		
20 ሚልዮን ሪያል		
40 ሪያል		
45679 ሪያል		
255 ሷዕ ስንዴ		

13. እስልምና ይቀበላል ተብሎ ተስፋ የሚይደረግበት ካፊርም “ልቦናቸው ለተዘነበሉ” በተባሉት ይካተታል (እውነት – ሃሰት)
14. የባርነት አለቃው ከባርነቱ ነፃ ያለው ባርያ ከዘካ ይሰጠዋል (እውነት – ሃሰት)
15. አንድ ባለሃብት ያበደረውን ገንዘብ ከ(ዘካ ከሚገባው) ተበዳሪው ገንዘቡን ጠየቀና ከፊሉን እዳውን እንደተወለትና ያም ዘካ መሆኑን አሳወቀው፤ ይህ ድርጊቱ ትክክል ነው። (እውነት – ሃሰት)
16. 'በአሏህ መንገድ ለሚታገሉ' ሲባል መስጅድ መገንባትን የመሰሉ የቪይር አቅጣጫዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። (እውነት – ሃሰት)
17. የወርቅና ብር እንዲሁም ሌሎች መገበያያዎች የዘካ ገንዘብ የሚቀመረው ለ 40 እያካፈሉ ነው። (እውነት – ሃሰት)
18. በሚደለቡ(ሳኢማ) እንስሶች ላይ ዘካ ግዴታ ሲሆን በሚሰሩና በሚቀለቡ እንስሶች ላይ ግን ግዴታ አይደለም። (እውነት – ሃሰት)
19. አትክልትና ፍራፍሬ መጠናቸው የዘካ ግዴታነት ልኬት(ኒሷብ) ላይ ከደረሱ ዘካ ሊወጣባቸው ግዴታ ነው። (እውነት – ሃሰት)
20. በጥረት ከበለፀገ አትክልትና ፍራፍሬ የሚወጣው የዘካ መጠን 1/20 ነው። (እውነት – ሃሰት)
21. ወርቅ የዘካ ግዴታነት ልኬቱን ከደረሰ ዘካ ይወጣበታል፤ መጠኑም 20 ሚስቃል ነው። (እውነት – ሃሰት)
22. ከሚከተሉት ዘካ ግዴታ የሚሆንባቸውን አክብብ

O ዶሮ O ሱቅ O የተቀለበች እንስሳ

O የደለበ ግመል O የተምር ማሳ O ከወርቅ 25 “*ሚሰቃል*”

23. *“ሃብሪያ”* የምትባለው ሁለት አመት የሞላ ከብት ነች። (እውነት – ሃሰት)
24. በጊዜያችን ያሉት የመገበያያ ገንዘቦች ዘካ የሚሰላው በ …… መሰረት ላይ ነው።

O በመገበያያ ቁሶች O በወርቅ ወይ በብር (ሲልቨር) ኒሷብ ተመን

O በወርቅና ብር(ሲልቨር) ኒሷብ ተመን

25. በጊዜያችን ያሉት የመገበያያ ገንዘቦች ዘካ መጠን O 0.025 O $1/20^{ኛ}$

26. የ 80 ግራም ወርቅ ዘካ መጠን …

O 2 ግራም O 4 ግራም O ዘካ የለበትም

27. መኖርያ ቤቶች ዘካ ይወጣባቸዋል (እውነት – ሃሰት)

28. ጉዞ የወጣ ሁሉ ኢብኑ ሰቢል ስለሆነ ዘካ ይሰጠዋል (እውነት – ሃሰት)

ሶስተኛ: ፆም

በቋንቋ ደረጃ መታቀብ ማለት ሲሆን፤ በሸሪዓ ደረጃ ደግሞ ከትክክለኛው ጎህ መቅደድ ጀምሮ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ከመጠጥና ከሌሎችም የሚያስፈጥሩ ነገራቶች መታቀብ ማለት ነው።

የፆም ማእዘናት

1- ኒያ

2- ከሚያስፈጥሩት ነገራቶች መታቀብ

ግዴታ ለሆነው ፆም ኒያ

ከለሊት ማለትም ከፈጅር በፊት ጀምሮ ለግዴታ ፆም ኒያ ማድረግ የግድ ነው። ገና በወርሃ ረመዷን መግቢያ የተቋጠረ ኒያ(ሃሳብ) በቂ ነው። ቦታዋ ልብ ሲሆን ቃሏን በአንደበት አውጥቶ መናገሩ ቢድዓ ነው።

ተጨማሪ ለሆነ ፆም የሚደረግ ኒያ

የሚያስፈጥርን ነገር እስካላስቀደመ ድረስ በየትኛውም ሰአት ኒያውን ቢያስብ ይሆናል። ነገር ግን ኒያውን ከቋጠረበት ሰአት ጀምሮ ነው አጅሩ ሊታሰብለት የሚችለው።

የፆም አይነቶች

ግዴታ:

የረመዷን ወር፣ የከፋራ እና የስለት ፆም

ተጨማሪ:

ከነኝህ ውጭ ያለ ፆም ሁሉ

የፆም ግዴታነት ቅድመ መስፈርቶች

1- ሙስሊም መሆን 2- ጤነማ አእምሮ ያለው መሆን

3- ለአቅመ አዳም መድረስ፡ ለአቅመ አዳም ካልደረሰ እንዲፆምም ይበረታታል አስተዳዳሪውም ያዘዋል፤

4- በአገሩ ላይ መሆን: ፆም በመንገደኛ ላይ ግዴታ አይደለም፤ የማያጨናንቀው እስከሆነ ድረስ ግን ቢፆም በላጭ ይሆንለታል ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እንዲሁ ነውና ያደረጉት፤ እንዲሁም በአስቸኳይ ከተጠያቂነት መፅዳትም ተፈላጊ በመሆኑ፤ ለግለሰቡም የገራ በመሆኑ እና የረመዷንን ችሮታምለማግኘ ሲባል

5- አካላዊ ጤንነት 6- ከወር አበባ እና ከወሊድ ደም መፅዳት

የበሽታ አይነቶች ከፆም አንፃር

ማገገሙ ተስፋ የማይደረግበት በሽታ

መፆም የተሳናቸው ሽማግሌም በዚሁ የሚጠቃለሉ ሲሆን መፆሙ ግዴታ አይሆንበትም ነገር ግን ለእያንዳንዱ ቀን ሚስኪን ያበላል። ወይ በቀናቶቹ ልክ ቆጥሮሚስኪኖችን በመሰብሰብ ይመግባል፤ አልያም ደግሞ በቀናቶቹ ልክ ለእያንዳንዱ ሚስኪን 510 ግራም (በነብዩ ጊዜ የነበረው ሷዕ ሩ) ምርጥ ስንዴ ሊልክ ነው። እንደ ስጋ ወይም ዘይት አይነት የሚያባላውን ቢጨምርበት መልካም ይሆንለታል።

ማገገሙ ተስፋ የሚጣልበት ሆኖ እያለ ለመፆም ግን አስቸጋሪ የሆነ

እንደ የወር አበባዋ ላይ ያለች፣ በወሊድ ደም ያለች፣ አጥቢ እና ሙሳፊር ያሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ከዚህ ባገገመ ጊዜ ያፈጠረባቸውን ቀናቶች ቀዷ ፁሞ ያካክሳል። ከማገገሙ በፊት ህይወቱ ካለፈች ይቅር ይባልለታል።

የረመዷን ወር መግባቱ የሚረጋገጠው በምንድን ነው?

ወይ የረመዷን ጨረቃ ከታየች፤ አለበለዚያ የሸዕባንን ወር ሰላሳ መሙላት ነው።

ፆምን የሚያፈርሱ ነገሮች?

1- ሆን ብሎ መብላት ወይንም መጠጣት፤ ዘንግቶ ከሆነ ፆሙ ልክ ነው(ይቀጥል)።

2- ግንኙነት መፈፀም፤ ግንኙነቱን የፈፀመው በወርሃ ረመዷን በቀኑ ክፍለጊዜ እስከሆነ ድረስ ከባድ የሆነችዋ ከፋራ ሊያወጣ ግዴታው ነው። ይህም ባርያ ነፃ ማውጣት፤ ይህን የማይችል ከሆነ ደግሞ ሁለት ወር በተከታታይ ሊፆም ነው፤ ይህን የማይችል ከሆነ ደግሞ ስሳ ሚስኪን ማብላት ይኖርበታል።

3- ወይ በመነካካት፣ ወይ በመሳም፣ ወይ በማቀፍ ወይም በመሳሰሉት አማካኝነት የዘር ፈሳሽ ማፍሰስ

4- እንደምግብ መርፌ ያለ በምግብ እና መጠጥ ምትክ የሚሆን፤ ከምግብ መርፌ ውጭ ያለው መርፌ አያስፈጥርም

5- በዋግምትና በመሳሰሉት አማካኝነት ደም መፍሰስ፤ ለምርመራ የሚሰጥ ደም ግን አያስፈጥርም

6- ሆን ብሎ ማስታወክ

7- የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ፍሰት

አንዳንድ ለፆመኛ የሚፈቀዱ ነገራቶች

ምራቅን መዋጥ፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ምግብን በምላስ መቅመስ፤ ትጥበት፤ ሲዋክ፤ ሽቶ እና ራስን ማርጠብ።

በፆም የሚበረታቱ

1. ሱሑርን መብላት **2.** ሱሑርን ዘግየት ማድረጉ **3.** ማፍጠርን ማፍጠኑ **4.** በእርጥብ ተምር ማፍጠር፤ ከሌለ ደግሞ በየትኛውም ተምር ማፍጠር፤ ብዛቱ ለሁለት የማይከፈልን ቁጥር ቢሆን ይመረጣል። ይህንንም ካላገኘ የሆነ ያክል ውኃ መጎንጨት፤ ምንም ካላገኘ ደግሞ ማፍጠሩን በልቡ በማሰብ ያፈጥራል። **5.** ፆሙን በሚይዝበት እና በሚያፈጥርበት ሰአት ዱዓእ ማድረግ **6.** ምፅዋት ማብዛት **7.** የለሊት ሶላትን ለመስገድ መጣጣር **8.** ቁርአን መቅራት **9.** ለሚዘልፍህ ሰው "ፆመኛ ነኝ" ማለት **10**. ዑምራ ማድረግ **11.** የመጨረሻዎቹን 10 ለሊቶች ኢዕቲካፍ ማድረግ **12.** ለይለቱል ቀድርን ማደን

በፆም የሚወገዙ

1. ውዱእ በሚደረግበት ጊዜ አፍን እና አፍንጫን ጥግ ድረስ ማጠብ
2. አስፈላጊነቱ ባልታመነበት አጋጣሚ ወጥ መቅመስ

ፆመኛ የተከለከላቸው ነገሮች

1. አክታን መዋጥ [ፆሙን ባያስፈጥረውም]
2. ምናልባት በዛ ምክንያት ወደሌላ እንደማይገባ በራሱ ለማይተማመን ሰው ሚስቱን መሳሙ
3. ማበል [ያም ከረመዷን ውጭ ባሉ ጊዜያቶችም የተከለከሉ ነገሮችን መፈፀም]
4. ቂላቂልነት [ያም መጃጃልና ቅጥ ያጣ መሆን ማለት ነው]
5. ዊሷል [ሳያፈጥር አከታትሎ መፆም]

ተጨማሪ ፆም

1- የረመዷንን ወር አሟልቶ ለፆመ አስከትሎ ቢቻል በሁለተኛው ቀን ከሸዋል ወር 6 ቀን መፆም

2- ሓጅ ላይ ላልሆነ ሰው የዓረፋን ቀን መፆም

3- የዓሹራ ቀንን ከአስራ አንደኛውና ከአስራ ሁለተኛው ቀንጋ ደርቦ መፆም

4- ሰኞና ሃሙስን መፆም፤ በተለይም ሰኞ መፆም

5- ከየወሩ ሶስት ቀን መፆም፤ በተለይም በሂጅሪ አቆጣጠር 13ኛ ፣ 14ኛን እና 15ኛ ን ቀን መፆም

6- አንዳንድ ቀን እየዘለሉ መፆም 7- አሏህ ያከበረውን የሙሓረምን ወር መፆም

8- የዙልሒጃን 9ኛ ቀን መፆም

9- የሸዕባንን ወር መፆም፤ ይሁን እንጅ አይሞላውም

የተወገዘው ፆም

እለተ ጁምዓን፣ ቅዳሜን ወይንም እሁድን በፆም መነጠል የተወገዘ ነው። የነጠለው ዓረፋ በመሆኑ ወይም መሰል ምክንያት ከሆነ ግን ችግር የለውም።

የተከለከለ ፆም

1- የረጀብን ወር በፆም መነጠል

2- በሚዶ እለት መፆም

3- የጥርጣሬውን ቀን (ረመዷን መሆኑ የሚያጠራጥር) መፆም፤ ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት ፆሞች አንዱን ሲፆም ከነበረና ባጋጣሚ ካልገጠመ በቀር

4- በሓጅ ስርአት እርድ ለማቅረብ የተሳነው ካልሆነ በቀር አያመ ተሽሪቅን (ከሚደል አድሓ/ዓረፋ በኋላ ያሉት ሶስት ቀናት) መፆም

5- ለዘላለሙ በየቀኑ ሳያቋርጡ መፆም

ፆምን ቀዷ(ያመለጠህን መመለስ) ከማውጣት ጋ ተያያዥ የሆኑ ህግጋት

- አከታትሎ መፆሙ የሚበረታታ ነው
- ልክ ከዒዱ እለት በኋላ ማስከተሉ ተገቢ ነው
- የአንዱን ረመዷን ቀዷ ፆም ወደሌላኛው ረመዷን አቅራቢያ ድረስ ማዘግየት አይፈቀድም
- በቂ ምክንያት ሳይኖረው ካዘገየው ወንጀለኛ ይሆናል፤ ይሁን እንጅ ያልፆመውን ቀዷ ከማድረግ ውጭ ሌላ ግድ የሚለው ነገር የለም።

ዘካተል ፊጥር

ትልቅም ሆነ ትንሽ፤ ወንድም ሆነ ሴት፤ ባርያም ይሁን ጨዋ ሆኖ የረመዷን ወር የመጨረሻዋ ቀን ጸሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ሙስሊም ሆኖ የመቆየትን እድል የተሰጠው ሁሉ መስጠት ያለበት የዘካ አይነት ነው። ፀሃይዋ ከገባችበት ሰአት ጀምሮ የዒዱን ቀን መስጠት ይኖርበታል። ይህም በራሱም ሆነ በሌላው የቤተሰቡ አባላት በመሰረታዊነት ከሚቀለቡት ትርፍ ከሆነው በእያንዳንዱ አንድ ሷዕ ይመፀውታል። ማህፀን ላይ ላለ ሽል ደግሞ በሱ ስም መስጠቱ ግዴታም ባይሆን የሚበረታታ ነው። ከተደነገገባቸው ጥበቦች መካከል:

- ለፆመኛው ዛዛታና መንዘላዘል ማጥርያው ነች
- ድሆችና ሚስኪኖች የዒድ እለት ጠያቂ የሰውን ከጃይ ከመሆን ታብቃቃቸዋለች

ዘካተል ፊጥር ስለሚሰጥበት ጊዜ

የተከለከለ ጊዜ
ከዒድ ሶላት በኋላ

የሚበረታታው ጊዜ
ከፈጅር በኋላ ከሶላተል ዒድ በፊት

የሚፈቀደው ጊዜ
ከዒዱ እለት በአንድ ቀን ወይንም በሁለት ቀን ቀደም ብሎ

የዘካተል ፊጥር መጠኑ

የሰው ልጅ ከሚመገበው 1 ሷዕ እህል፤ ብር ነገር አያብቃቃም። የ 1 ሷዕ መጠኑ ማለት ደግሞ በጥሩ ስንዴ 2 ኪሎ ከ 40 ግራም ማለት ነው።

የዒድ ሶላት

በነፍስ ወከፍ ደረጃ በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ ግዴታ (ፈርዱል ዓይን) ነች። የምትሰገድበት ወቅትም ፀሃይ የዘንግን ያክል ከፍ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ መሃል አናት እስከምትሆንበት ጊዜ ድረስ ነው። ያመለጠችበት ደግሞ ቀዷ ሊያወጣት አይችልም። ሱናው ከህንፃ ውጭ በሆነ የተንጣለለ ሜዳ ላይ ቢሰገድ ሲሆን ነገር ግን መስጅድ ውስጥ መስገዱም የተፈቀደ ነው። ከዒድ ሶላት በፊት ብዛቱ ዊትር(ለሁለት የማይካፈል) የሆነ መጠን ያለውን ቴምር ቢበላም፤ ንፅህናውን ጠብቆ ከሽቶውም ተቀባብቶ ከልብሱም ምርጡን ለብሶ ቢሄድ፤ መንገዱንም ሲሄድ ባንዱ መንገድ ሂዶ ሲመለስ መንገዱን ቀይሮ ቢመለስ ሱና ይሆንለታል። አንድ ሙስሊም ሌላኛውን እንደ “ተቀበለሏሁ ሚና ወሚንኩም ” በመሰለ ዒዱን በተመለከተ እንኳን አደረሰህ ቢለው ችግር የለውም። በእለተ ዒድ ለሊትና ጸሃይዋም እስክትጠልቅ ድረስ በአምስቱ የሶላት ወቅቶች ከየሶላቱ በኋላ ልቅ የሆነውን ተክቢራ ማለቱ ሱና ነው። የሚባለውም: “አሏሁ አክበር! አሏሁ አክበር! ላ ኢላሃ ኢለሏህ፤ ወሏሁ አክበር! አሏሁ አክበር! ወሊላሂል ሐምድ” ነው። አሰጋገዱም: ከኹጥባው በፊት ሁለት ረከዓ የሚሰገድ ሲሆን በመጀመርያው ረከዓ ልክ ተክቢረተል ኢሕራም እንዳለ ስድስት ጊዜ “አሏሁ አክበር!” ይላል፤ በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ ለመቆም ብሎ አሏሁ አክበር ካለው ውጭ አምስት ጊዜ አሏሁ አክበር በማለት ነው።

ስለፆም ፈተና

1. የፆም ማእዘናት ስንት ናቸው? O 2 O 3 O 4

2. ፆም ግዴታ የሆነው በማን ላይ ነው?

ሀ. .....

ለ. .....

ሐ. .....

መ. .....

3. በሽታ ሁሉ ከፆም ያቅባል። (እውነት – ሃሰት)

4. የተከታዮቹን ጉዳዮች ኢስላማዊ ፍርድ ጥቀስ:

ጉዳዩ	ኢስላማዊ ፍርዱ
መፆሙን የወሰነው(የነየው) ከፈጅር በኋላ ነው	
ያለ ኒያ ቢፆም	
የልጅ ፆም	
የሙሳፊር(የመንገደኛ) ፆም	
በወሊድ ደም ያለች ሴት ፆም	
የ(የተሳነው ሰው) ደካማ ሽማግሌ ፆም	
ፆሞ እያለ ቢበላ	
ፆመኛ ምግብ መርፌ ቢተከልለት	
የአይን ጠብታ ለፆመኛ	
ፆመኛ ማደንዘዣ ቢወጋ	
ፆመኛ ቢታገም	

የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

ማስታወክ	
ምራቅን መዋጥ	
ፆመኛ ምግብ ቢቀምስ	
ፆመኛ ቢተኛ	
ፆመኛ ገላውን ቢታጠብ	
ራስን ማቀዝቀዝ	
ሲዋክ ለፆመኛ	
እጣን	
የሱሑር ወቅት	
በምንድን ነው ሱሑር የሚታሰረው	
በምንድን ነው የሚፈጠረው?	… … … … … … .. ካላገኘ… … … … … … … … … … .. ካለገኘ ደግሞ … … … … … … … .. ካላገኘ ……. ያፈጥራል።
የተራዊሕ ሶላት	
በረመዷን ወር ዑምራ ማድረግ	
ፆመኛ ሆኖ አፍን ሲያጥቡ ጥግ ድረስ ማፅዳት	
ፆመኛ ሆኖ መሳም	
ዊሷል (ሳያፈጥሩ) አከታትሎ ለሁለት ቀናት መፆም	
ከሸዋል ወር ለ 6 ቀናት መፆም	
የዓረፋን ቀን መፆም	

የጥርጣሬን ቀን (ረመዷን መሆን አለመሆኑ ያልተረጋገጠን ቀን) መፆም	
የዒድን ቀን መፆም	
ከዒድ አልአድሓ በኋላ ያሉትን ሶስት ቀናት መፆም	
የሙሐረምን ወር መፆም	
የረጀብን ወር መፆም	
ሁልጊዜ በየቀኑ እያከታተሉ መፆም	
የጁምዓን ቀን መፆም	
ቀዷን እስከሌላኛው ረመዷን ማዘግየት	

የአስራ አራተኛው ትምህርት ማብራርያ

አራተኛ: ሓጅ

ሓጅ ከእስልምና ማእዘናት 5ኛው ማእዘን ነው። ሙስሊም፣ ጤናማ አእምሮ፣ ለአቅመ አዳም/ሄዋን መድረስ፣ ጨዋ መሆን እና መቻል የሚሉትን መስፈርቶችን ባሟላ ላይ ሁሉ ግዴታ ነው። ሴት ልጅ ሓጅ ለማድረግ ጉዞ መውጣት የሚጠበቅባት ከሆነ መሕረም የሆነ ሰው አብሯት መሆኑ ተጨማሪ መስፈርት ነው። የሓጅ ማእዘናት አራት ናቸው:

ኢሕራም

ሓጅን ለመጀመር የሚደረገው ኒያ ሲሆን ያ ማለት ተልቢያን ወይም ደግሞ የሓጅን ሽርጥና ግልድሙን ማድረግ ማለታችን አይደለም፤

ዓረፋ ላይ መገኘት

ጊዜውም ከዙልሒጃ 9ኛው ቀን የፀሃይ መዘንበል ጀምሮ እስከ የሚዱ እለት ፀሃይ መውጫ ድረስ ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል: "***ሓጅ ማለት ዓረፋን ነው***"

ጡዋፈል ኢፋደ

የዚያራው ጡዋፍ፤ ይህም በዓረፋ ሜዳ ላይ ከመቆም በኋላ የሚሆን ሲሆን ጡዋፈል ቁዱምን ማለት አይደለም።

በሁለቱ ተራሮች መካከል ሰዕይ ማደረግ

በሰፋ እና መርዋ ተራሮች መካከል ዱብዱብ ማለት፤ አሏህ እንዲህ ይላል: "**በርግጥ ሰፋ እና መርዋ ከአሏህ ምልክቶች ናቸው።**" (2:158).

የስርአተ ሓጅ አይነቶች

ተመቱዕ

በሓጅ ወራት ዑምራን ኒያ አድርጎ ካጠናቀቀ በኋላ ይፈታና በዛው አመት ለሓጅ ኢሕራም ያደርጋል። ሃድይ (እርድ) ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ቂራን

ሓጅና ዑምራን አንድላይ ኒያ ያደርግና ሁለቱንም በየተራ ያከናውናል። ሃድይ (እርድ) ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ኢፍራድ

ሓጅን ብቻ ኒያ ያደርግና ሓጁን ብቻ ያከናውናል

የሓጅ ግዴታዎች

ከነኝህ ግዴታዎች መካከል አንዱን የተወ በመስዋእት ሊጠግነው ግዴታው ነው፤ ይህም በሓረም ታርዳ ለመካ ድሆች የምትከፋፈል በግ ወይም ፍየል ነች። ከሷ ሊበላ ግን አይፈቀድለትም።

ከሚቃቱ (ከመግቢያው አንፃር ለኢሕራም በተወሰነለት ቦታ) ሆኖ ኢሕራም ሊያደርግ

በቀኑ ከፍለ ጊዜ በዓረፋ ሜዳ ለተገኘ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ መቆም

ሙዝደሊፋ ላይ መቆየት

የአያመ ተሸሪቅ ሌሊቶችን በሚና ላይ መቆየት

ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር

ጠጠሮቹን መወርወር

ከሓጅ ወራት ውጭ እንኳ ቢሆንም መካን ለቆ ሊወጣ ባለበት ጊዜ የመሰናበቻውን ጡዋፍ ማድረግ፤ የወር አበባዋ ወይም የወሊድ ደም ላይ ካለች ሴት በቀር።

የሓጅ እና የዑምራ መቼት (ሚቃት):

ቦታ

-***ዙልሑሊይፋ*** ለመዲና እና በመዲና በኩል ለሚያልፉ ሰዎች
-***አልጁሕፋህ*** ከሻም፣ ለግብፆችና ለሞሮኮዎች
-***ቀርነል መናዚል*** ለነጅዶች
-***የለምለም*** ለየመኖች
-***ዛቱ ዒርቅ*** ለዒራቆች

ጊዜው

የሓጅ ወራቶች ናቸው: ***ሸዋል፣ ዙልቃዒዳህ,*** እና ***ዙልሒጃህ***

የጊዜ መቼቱ ሓጅን ነው እንጅ የሚመለከተው ዑምራ ለማድረግ የተገደበ ጊዜ የለውም።

ተወዳጅ የሓጅ ክንውኖች

ነጩን የሓጅ ሸርጥና ግልድም መልበስ	ለኢሕራም መተጣጠብና ሽቶ መቀባት
ከኢሕራም ጀምሮ እስከ ጀመረቱል ዓቀባ የጠጠር ውርወራ ድረስ ተልቢያ (ለበይክ ኣሏሁመ ለበይክ ...) ማለት	የኢሕራምን ኒያ ከማለት በፊት ጥፍርንም ሆነ መቆረጥ ያለበትን ፀጉር መቁረጥ
ተመቱዕ አይነቱን የሓጅ ስርአት ለሚያደርግ ሰው በጡዋፈል ቁዱም እና በዑምራ ጡዋፍ የመጀመርያዎቹ ሶስት ዙሮች በሶምሶማ ይዞራል። ሶምሶማ ስንል ዱብዱብ ማለት ወይም እጅግ ፈጣን እርምጃ ማለታችን ነው።	የኢፍራድና የቂራን ስርአተ ሓጅ ለሚያደርግ ሰው ጡዋፈል ቁዱም ማድረግ
ሙዝደሊፋ እንደደረሰ ዒሻን ወደ መግሪብ አምጥቶ ጀምዕ ተቅዲም በማድረግ ይሰግዳል	ተመቱዕ አይነቱን የሓጅ ስርአት ለሚያደርግ ሰው በበጡዋፈል ቁዱም እና በዑምራ ጡዋፍ ኢድጢባዕ አይነቱን አለባበስ ይለብሳል፤ ይህም ቀኝ ትከሻውን ገልጦ መልበሱ ነው
ሓጂረል አስወድን መሳም	የዓረፋን ለሊት ሚና ላይ ማሳለፍ
ከፈጅር ጀምሮ ፀሃይ ልትጠልቅ እስከምትቃረብበት ጊዜ ድረስ ሙዝደሊፋ ላይ በተለይም መሽዓረል ሓረም ላይ መቆም፤ መላ ሙዝደሊፋም ግን መቆሚያ ነው።	

በኢሕራም የተከለከሉ ነገሮች

ዘጠኝ ናቸው: የራስ ቅልንም የሌላ አካልንም ፀጉር መላጨት፤ ጥፍርን መቁረጥ፤ ለወንዶች የራስ ቅልን በሆነ ነገር መሸፈን፤ በሆነ የሰውነት ቅርፅ የተሰፉ ልብሶችን መልበስ፤ ለሴት ልጅ ኒቃብ ወይንም ጓንት መልበስ፤ ሽቶ መቀባት [ሽታ ያለው ሳሙናም እንዲሁ]፤ የየብስ አደን ማደንና መግደል፤ ለራሱም ይሁን ለሌላ ኒካሕ ማሰር፣ ግንኙነት መፈፀም ወይም ከባለቤትህ ጋ መተሻሸት የተከለከሉ ናቸው። ዘንግቶ ወይ ባለማወቅ ወይም ደግሞ ተገዶ ከነኝህ ነገራቶች መካከል አንዱን የፈፀመ አንዳችም ነገር የለበትም፤ ምናልባት አደን ማደን ካልሆነ በቀር እንደዛ ያደረገ በልቁ “ፊድያ” የማድረግ ግዴታ አለበት። ሆን ብሎ የፈፀመ ግን ከልክላቶች አራት አይነት ናቸው:

ፊድያ የማይጠበቅበት

ለራሱም ይሁን ለሌላ ሰው ኒካሕ ማሰር፤ ከባለቤት ጋ መተሻሸትም እንዲሁ ነገር ግን የዘር ፈሳሽ በሚያወጣ መልኩ ካልሆነ ወይም ካላወጣ ማድረግ የሚጠበቅበት ነገር ባይኖርም ተውባ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

አምሳያውን ፊድያ ማቅረብ ያለበት

የየብስ አደንን መግደልና ማደን፤ የገደለ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መስዋእት ማቅረብ ይኖርበታል። ይህም : በግ ወይ ፍየል፣ ወይ ከብት ወይ ግመል ሚዛናዊየሚባሉ ሰዎች ባስቀመጡት መልኩ

ከባድ ፊድያ የሚጠበቅበት

ግንኙነት መፈፀም : ከመጀመርያው ተሕሊል በፊት የፈፀመ ከሆነ ሐጁ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል፤ ነገር ግን ይቀጥላል አያቋርጥም፤ በሌላኛው አመት ይደግመውና መስዋእትንም ያቀርባል።

ፊድያው የ ”እዛ” ፊድያ የሆነ

ይህ ቀሪው ክልከላን ያጠቃልላል፤ ፊድያው ደግሞ በምርጫ ይሆንለታል : ወይ ሶስት ቀን መፆም፣ ለእያንዳንዱ ሚስኪን ግማሽ ሷዕ እያደረገ ስሳ ሚስኪን መመገብ፣ ወይም ደግሞ በሓረም ድሆች መካከል የምትከፋፈል የሆነችን በግ/ፍየል ማረድ።

የሓጅ ቀናት ስያሜ

እለተ ተርዊያህ (የመጠጫ ቀን) : ይህም 8ኛው ቀን ይህም የተባለበት ውኃ ወደ ሚና ያግዙ የነበሩ ከመሆናቸው አንፃር ነው።	የዓረፋ ቀን ወይም ወቅፋህ: ይህም 9ኛው ቀን ነው።	የዒድ እለት የእርዱ ቀን፤ ይህም 10ኛው ቀን ነው።	እለተ “ቀር” ይህም 11ኛው ቀን ነው።	ቀዳሚው እለተ “ነፈር” ይህም 12ኛው ቀን ነው።	ሁለተኛው እለተ “ነፈር” ይህም 13ኛው ቀን ነው።

ለይለቱ ጁመዕ የሚባለው የስብስቡ እለት የዒድ እለት ነው። ይህም የተባለው ሰዎች በዓረፋ ከቆሙ በኋላ የሚሰባሰቡበት ቀን በመሆኑ ነው። ምክንያቱም በዘመነ ጃሂሊያ የመካ ሰዎች ወደ ዓረፋ አይወጡምና ነው።

በሓጅ ሂደት ለየት ባለ መልኩ ዱዓእ የሚደረግባቸው 5* ቦታዎች

በ 9ኛው ቀን በእለተ ዓረፋ ፀሃይ ካዘነበለች ጀምሮ እስክትጠልቅ ድረስ።	ሙዝደሊፋ ላይ የዘጠነኛው ቀን ፈጅር እስከ ፀሃይ መውጫ አቅራቢያ	ከዒድ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ከትንሹና መካከለኛው የጠጠር ውርወራ በኋላ	ጡዋፍ በምናደርግበት ጊዜ	በሰፋና መርዋ መካከል ሰዕይ በምናደርግበት ጊዜ

የሓጅና ዑምራ ማብራርያ

ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን –አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ብለዋል:

ክቡር ሓጅ አድራጊ ሆይ! ለኢሕራም ወደ ተዘጋጀው ቦታ ከደረሱ በኋላ ገላዎን ይታጠቡ፤ ወንዶች በሰውነትዎ ፣ በጭንቅላትዎ ወይም በጢምዎም ላይ ሽቶ ይቀቡ። ከዚያም በሚያደርጉት ስርአተ-ሓጅ መሰረት [ለምሳሌ "ተመቱዕ" ከሆነ የሚያደርጉት] ለዑምራ ኢሕራም በማድረግ ተልቢያ እያሉ ወደ መካ ይሂዱ፤ በተከበረው ካዕባ ሲደርሱ ለዑምራ 7 ዙር ጡዋፍ ያድርጉ። ከካዕባ አንፃር ቅርብም ይሁን ሩቅ ሆኖ በመስጊዱ ውስጥ እስከሆነ ድረስ በማንኛውም ቦታ ጡዋፎን ማድረግ እንደሚችሉ ይወቁ። ሆኖም በሰው ጭንቅንቅ ካልተቸገሩ ወደካዕባው መጠጋቶ የተሻለ ነው። በጣም የተጨናነቀ ከሆነ ግን ራቅ ይበሉ። ምስጋና ለአሏህ ይገባውና በዚህ ረገድ ነገሩ የተጣበበ አይደለም።

አንዴ ጡዋፎን ካጠናቀቁ በኋላ ከመቃሙ ኢብራሂም - ዓለይሂ ሰላም- በስተጀርባ ሁለት ረከዓ ሶላት ይስገዱ። ከተቻለ ተጠግተው መስገድ፤ ካልቻሉ ደግሞ መቃሙ ኢብራሂም በእርሶ እና በካዕባ መካከል እስከሆነ ድረስ የትም ቢሆን መስገድ ይችላሉ። ከዚያ ወደ የዑምራ "ሰዕይ" ይሂዱ እና ከ "ሰፋ" ይጀምሩ። 7 ቱን ዙሮች ካጠናቀቁ በኋላ ከመላው ጭንቅላቶ ላይ ፀጉር ይከርክሙ፤ በብዙዎች ድርጊት ተታለው ከጭንቅላቶ የሆነ ክፍል ላይ ብቻ ፀጉር መቁረጥ በቂ አይደለም።

በዙል ሒጃ 8ኛ ቀን ገላዎን ይታጠቡ፤ ወንዶችም ሽቶ ይቀቡ። እርስዎ ካረፉበት ለሓጅ ኢሕራም ያድርጉ። ወደ ሚና ሄደው ዙህርን፣ ዓስርን፣ መግሪብን፣ ዒሻን እና ፈጅርን ይስገዱ። ሶላቶቹን ያሳጥሩ እንጅ ጀምዕ አያድርጉ። ምክንያቱም ነቢያችን ﷺ ሶላትን በሚና እና በመካ ሲሰግዱ ያሳጥሩ ነበርንጅ አያጣምሩም ነበርና። በእለተ ዓረፋህ ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ ለአሏህ በመተናነስ ተልቢያህን እያሉ ወደ ዓረፋ ይሂዱ። ከዚያም የዙህርንና የዓስርን ሶላት በዓረፋህ ጀምዕ በማድረግ ሁለት ሁለት ረከዓ አድርገው ይስገዱ።

ከዚያም አላህን በመማፀን እና በመለመን ይጠመዱ፤ ከውዱእ ውጭ ላለመሆን የተቻለዎትን ሁሉ ይሞክሩ፤ ወደ ቂብላም ይቅጣጩ፤ ያ የተደነገገው ተራራው ከኋላዎ ቢሆንብዎም እንኳ ቂብላዎን መቅጣጨቶ ነውና። የዓረፋን ድንበሯን እና የተዘጋጁትን ምልክቶች በጥንቃቄ ያስተውሉና በዚያ ውስጥ መሆኖን እርግጠኛ ይሁኑ፤ ምክንያቱም ብዙዎች ዓረፋ ውስጥ መቆም ሲኖርባቸው ከሷ ውጭ እየቆሙ ነውና። በዓረፋ ለማይቆም ደግሞ ሓጅ የለውም፤ ነብያችንም ﷺ **"ሐጅ ዐረፋ ነው"** ብለዋልና። መላ ዓረፋ ደግሞ ምስራቋም፣ ምዕራቧም፣ ሰሜኗም ሆነ ደቡቧ ሁሉ ከውርና ሸለቆ በቀር መቆሚያ ነው። ነቢያችን ﷺ **"እኔ እዚሁ ቆሜያለሁ፤ እናም በዓረፋ በየትኛውም ቦታ መቆም ትችላላችሁ።"** ብለዋልና።

ፀሐይ መጥለቋን ካረጋገጡ በኋላ ለአሏህ በመተናነስ ተልቢያህን እያሉ ወደ ሙዝደሊፋ ያቅኑ። ነብያችሁ ﷺ እንዳዘዟችሁ መረጋጋትን አጥብቃችሁ ያዙ፤ በርግጥም ኮ ነብዩ ﷺ የግመሏን ልጓም አጥብቀው ከዓረፋ ሲሄዱ ግመሏም ከመረጋጋቷ አንፃር ራሷ ኮርቻቸውን የሚነካበት አጋጣሚም ነበረ። የተከበረው እጃቸውን እያወዛወዙም ***"ሰዎች ሆይ! እርጋታን ተላበሱ። እርጋታን ተላበሱ።"*** ይሉ ነበር።

ሙዝደሊፋ ከደረሱ በኋላ መግሪብንና ዒሻእን ሰግደው እስከ ፈጅር ድረስ እዚያው ይቆዩ፤ ነብያችን ﷺ ከፈጅር በፊት ከሙዝደሊፋ ተነስቶ መጓዝን ለማንም አላገሩም፤ ምናልባት ደካሞች ካልሆኑ በቀር እነሱም በሌሊቱ መገባደጃ አካባቢ ነው የሚጓዙት። ፈጅርን ከሰገዱ ወደ ቂብላ ተቅጣጭተው አሏህን በማላቅ "አሏሁ አክበር" ማለትን ያብዙ፤ ያመስግኑት፤ ወጋገኑ ፈንጥቆ ሊነጋጋ እስኪል ድረስ ይለምኑት፤ ከዚያም ፀሃይዋ ከመውጣቷ በፊት ወደ ሚና ይንቀሳቀሱ። ከዚያም 7 ጠጠሮችን ለቅመው ከመካ ቀጥሎ የመጨረሻ ወደሆነው ወደ ጀመረቱል ዓቀባህ በመሄድ በእያንዳንዱ ውርወራ "አሏሁ አክበር!" እያሉ ከፀሐይ መውጣት በኋላ ለአሏህ በመተናነስና እሱኑ እያላቁ 7ቱን ጠጠሮች ይወርውሩ።

ጠጠሮችን የመወርወሩ አስፈላጊነት አላህን ለማክበር እና እርሱን ለማስታወስ መሆኑን ይወቁ። ጠጠሮቹን ሲወረውሩ በጉድጓዱ ውስጥ መውደቃቸው ግዴታ ሲሆን ችካሉን መምታቱ ግን መስፈርት አይደለም። ጠጠሮቹን መወርወርን ካጠናቀቁ እርድዎን ይሰዉ። ለኡዱሒያ የሚያብቃቃ መስዋእት ካልሆነ በቀር ለሃድይም አያብቃቃም። እርስዎን ወክሎ አንድ ሰው እንዲሠዋ መሾሙ የተፈቀደ ነው። ከእርዱ በኋላ ራስዎን ይላጩ፤ ሲላጩም መላ ራስዎን መሆን ይኖርቦታል፤ ከፊሉን ላጭተው ከፊሉን መተው አይፈቀድሎትም። ሴቶችም ከፀጉራቸው ጫፎች የጣት አንጓ ያህል ይቆርጣሉ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የመጀመርያው ተሓሉል (በሓጁ ስነስርአት ምክንያት የተከለከሉትን ሓላል የሚሆንሎት ሁኔታ) ላይ ነዎት፤ የተለመዱ ልብሶችንም ለመልበስ ጥፍሮትንም ለመቁረጥ ሽቶንም ለመቀባት ነፃ ነዎት፤ ነገር ግን ከባለቤትዎ ጋር ግንኙነት አይፈቀድሎትም። ከዚያም ከዙህር ሶላት በፊት ወደ መካ ይውረዱ፤ ለሓጅ ጡዋፎንም ሰዕዮንም ያድርጉ። ከዚያም ወደ ሚና ተመልሰው ጡዋፎን እና ሰዕዮን በማድረጎ ፀጉሮን ከመላጨቶም ጋ የጠጠር ውርወራውን በማድረግ የሁለተኛው ተሓሉል ላይ ነዎት። በዚህም ከባለቤቶ ጋ መገናኘትን ጨምሮ የተፈቀደ ይሆናል።

ሰዎች ሆይ! አንድ ሓጅ አድራጊ በዒድለት አራት ስርአተ ሓጅን ይፈፅማል፤ እነሱም፡ ጠጠር መወርወር፣ ከዚያም እርድ፣ ከዚያም መላጨት፣ ከዚያም ጡዋፍና ሰዕይ ናቸው። የተሟላው ቅደም ተከተል ይህ ነው። ነገር ግን ከፊሉን ከከፊሉ ቅደም ተከተል አዛብተው እንደሆን፤ ለምሳሌ እርድን ከመፈፀምዎ በፊት ራስዎን ቢላጩ ችግር የለውም፤ ጡዋፍንና ሰዕይን ወደሚና እስኪዘልቁ ድረስ ቢያዘገዩትም ችግር የለውም፤ እርዱንም አዘግይተው በአስራ ሶስተኛው ቀን ወደ መካ በሄዱ ጊዜ ቢያደርጉትም ችግር የለውም፤ በተለይም ደግሞ አስፈላጊና የተሻለ ሆኖ ከተገኘ።

የ11ኛውን ሌሊት በሚና ያሳልፉት። ፀሃይዋ ዘንበል ካለች በኋላ ሶስቱንም የጠጠር ውርወራዎችን ከትንሹ ጀምረው ከዚያም መካከለኛው ከዚያም ደግሞ ትልቁ አለት ላይ የጠጠር ውርወራዎን ያድርጉ። እያንዳንዱ ውርወራዎ ሰባት ሰባት ጠጠር፤ በእያንዳንዱ ውርወራዎም “አሏሁ አክበር!” እያሉ ይሁን። በእለተ ዒድ የውርወራ ሰአቱ ለሚችል ሰው ፀሃይዋ ከወጣችበት ሰአት ጀምሮ፤ ለደካሞች ደግሞ በሌሊቱ መገባደጃ ሲሆን የመጨረሻ ሰአቱ ደግሞ ፀሃይዋ እስክትጠልቅ ነው። ከዒዱ በኋላ ሰአቱ ደግሞ ፀሃይዋ ዘንበል ካለችበት ጀምሮ ፀሃይዋ እስከምትጠልቅበት ድረስ ነው። ፀሃይዋ ዘንበል ከማለቷ በፊት አይፈቀድም፤ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ብዙ መጨናነቅ ካለ ግን በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ውርወራውን ማድረግ ይፈቀዳል። ከእድሜ አንፃር ወይም ከህመም አንፃር መወርወር የሚሳነው ሰው በሱ ምትክ ሆኖ የሚወረውርን መወከል ይችላል። ተወካይም ለራሱም ለሌላም እዛው በቆመበት አከታትሎ መወርወር ይችላል፤ ነገር ግን ለራሱ በመወርወር ይጀምራል። በአስራ ሁለተኛው ቀን ውርወራዎን ካደረጉ ሓጅዎን ቋጭተዋልና ከፈለጉ መሄድ፤ ከፈለጉ ደግሞ አስራ ሶስተኛውን ለሊት እዛው አሳልፈው የቀጣዩ ቀን ፀሃይ ዘንበል ካለች በኋላ ሶስቱንም የጠጠር ውርወራ ማድረግ ይችላሉ፤ ይህ የተሻለው ነው። ምክንያቱም ነቢዩ ﷺ ﷺ ያደረጉት እንዲሁ ነውና።

መካን ለቀው ሊወጡ ከሆነ የመሰናበቻውን ጡዋፍ ያድርጉ። በወር አበባና በወሊድ ደም ያሉ ግን የመሰናበቻ ጡዋፍ አይጠበቅባቸውም፤ ወደመስጅዱ በር መምጣታቸውም ሆነ እዛው መቆማቸው የተደነገገም አይደለም።

የሓጅ ጥያቄዎች

1. ሓጅ ግዴታ የሚሆነው በማን ላይ ነው?

ሀ. .....

ለ. .....

ሐ. .....

መ. .....

ሠ. ሴት ከሆነች በተጨማሪ.....

2. የሓጅ ማእዘናት ስንት ናቸው? O 2 O3 O4

3. ኢሕራም ከሓጅ ማእዘናት አንዱ ሲሆን ይህም የሓጅ ሽርጥንና ግልድሙን መልበሱ ነው። (እውነት – ሃሰት)

4. ጡዋፈል ኢፋደ ከ ጡዋፈል ዚያራ የተለየ እና የመጀመርያው ሩክን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሱና ነው። (እውነት – ሃሰት)

5. ነብዩ ﷺ ሶስት ጊዜ ነው ሓጅ ያደረጉት። (እውነት – ሃሰት)

6. አንድ ሰው ሓጅ የማድረግ አቅም እንዳገኘ ወድያውኑ ሓጅ ግዴታ ይሆንበታል። (እውነት – ሃሰት)

7. የመዲና ሰዎች ኢሕራም የሚያደርጉት ከየለምለም ነው። (እውነት – ሃሰት)

8. ዑምራ ከጊዜ አንፃር መቼቱ ረመዷን ላይ ነው። (እውነት – ሃሰት)

9. በተከታዮቹ አረፍተ ነገር ያሉ ክፍት ቦታዎችን ሙላ: ሓጅና ዑምራ .... ከእድሜ ልክ ..... ግዜ ነው። ሓጅን ሲያከናውን ..... እና ..... ላይ ያላረፈ ልክ እናቱ እንደወለደችው ሆኖ ከወንጀሉ ይላቀቃል። እጅግ መልካም የሆነ ሓጅ ከ ..... ውጭ ምንዳ የለውም።

10. የመካ ሰዎች ከተንዒም ነው ኢሕራም የሚያደርጉት። (እውነት – ሃሰት)

11. ሴት ልጅ ሓጅ ስታደርግ ነጩን ልብስ ትለብሳለች። (እውነት – ሃሰት)
12. ሓጅ ለሚያደርግ ሰው ሸቶ በ ..... ያደርጋል በ.....አያደርግም።
13. ለሴት ልጅ ተለምዷዊ የሆነው የተሰፋ ልብስ አይፈቀድላትም። (እውነት – ሃሰት)
14. በኢሕራም ጊዜ ቀበቶ መታጠቅ አይፈቀድም። (እውነት – ሃሰት)
15. ሴቶች በኢሕራም ጊዜ .....ም .....ም አይለብሱም።
16. ኢድጢባዕ የተሰኘውን ቀኝ ትከሻ የሚገለጥበት የአለባበስ አይነት የሚበረታታው በ...

O በጡዋፈል ዑምራ O በጡዋፈል ቁዱም(የመግቢያው ጡዋፍ)

O የዚያራ ጡዋፍ O በመጀመርያውና በሁለተኛው ጡዋፍ ብቻ O ሁሉም መልስ ነው

17. ሰዕይ በሚያደርግበት ጊዜ በከባድ ፍጥነት መሆን ይኖርበታል። (እውነት – ሃሰት)
18. ሰዕይ የሚጀመረው ከ..... ሲሆን የሚጠናቀቀው ደግሞ በ ..... **ነው።**
19. ሓጅ የሚያደርጉ ሰዎች ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት ነው ከዓረፋ ሜዳ የሚንቀሳቀሱት። (እውነት – ሃሰት)
20. በዓረፋ ሜዳ መቆም ከሓጅ ግዴታዎች መካከል አንዱ ግዴታ ነው። (እውነት – ሃሰት)
21. የሓጅ ስነስርአት በ ..... እለት ጀምሮ በ ..... እለት ነው የሚጠናቀቀው።
22. በዓረፋ ተራራው ላይ መውጣቱ የተደነገገ አይደለም። (እውነት – ሃሰት)
23. እርድ መሰዋት ለሙተመቲዕ እና ለቃሪን ግዴታ ሲሆን ለሙፍሪድ ሱናው ነው። (እውነት – ሃሰት)
24. ተልቢያን ማለት የሚያቆመው በዒድ እለት የጀመረቱል ዓቀባ የጠጠር ውርወራ ነው። (እውነት – ሃሰት)
25. አንድ ሓጅ አድራጊ ጠጠር ሲወረውር ጠጠሩ ምሰሶውን ሳይነካ በጉድጓዱ ቢያርፍም ውርወራው ትክክል ነው። (እውነት – ሃሰት)
26. አንድ ሓጅ አድራጊ በአስረኛው ቀን ሶስቱንም የጠጠር ውርወራ ነው የሚወረውረው። (እውነት – ሃሰት)

27. ከዒድ በኋላ ባሉት ሶስት ቀናት ጠጠር የሚወረወረው ከፀሃይ መዘንበል ጀምሮ ነው። (እውነት – ሃሰት)
28. በጀመረተል ዓቀባህ ጠጠር ከተወረወረ በኋላ ዱዓእ ማድረጉ የተደነገገ ነው። (እውነት – ሃሰት)
29. ጡዋፈል ኢፋዷን ከመካ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ ቢያዘገየው ከመሰናበቻው ጡዋፍ ያብቃቃዋል፤ እንዲሁም ጡዋፈል ኢፋዷ በ ..... እና በ ..... ካልሆነ በቀር ልክ እንደ የዑምራው ጡዋፍ ነው።
30. ቂራን የሚያደርግና ሙፍሪድ ..... ሰዕይ የሚያደርጉ ሲሆን ሙተመቲዕ ደግሞ ..... ነው ሰዕይ የሚያደርገው።
31. የተከታዮቹን ድርጊቶች ኢስላማዊ ብይን አስቀምጥ:

ድርጊት	ብይኑ
ንኡሱ ሓጅ [ዑምራ]	
መሕረም የሌላት ሴት ሓጅ ብታደርግ	
እዳ እያለበት ሓጅ ቢያደርግ	

አስራ አምስተኛው ትምህርት

ለሁሉም ሙስሊም የተደነገጉ በሆኑ ስነምግባር ማጌጥ

ከነዚህም: እውነተኝነት፣ አደራ መጠበቅ፣ ጥብቅነት፣ አይነ አፋርነት፣ ጀግንነት፣ ቸርነት፣ ቃልን መጠበቅ፣ አሏህ ሓራም ካደረገው ነገር ሁሉ መጥራት፣ መልካም ጉርብትና፣ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው በተቻለ መጠን መርዳት እና ከነዚህም ውጭ ያሉ ቁርአንና ሓዲሥ ጥቆማ የሰጠባቸውን መልካም ስነምግባሮች ሁሉ።

አሳሳቢ ማስታወሻዎች

- (እውነተኝነት) ከአሏህ ጋ በቃልም፣ በድርጊትም በእምነትም ደረጃ ታማኝ ሆኖ መገኘት፤ ከአሏህ ባርያዎችም ጋ ታማኝ ሆኖ መገኘት፤ የዚህ ተቃራኒ ውሸት ነው።
- (አደራ መጠበቅ) የሰው ልጅ የተሸከማት የሆነች ታላቅ ሃላፊነት ነች፤ የኺያና (ማበል) ተቃራኒ ነች።
-(ጥብቅነት) ያም ከሓራም መታቀብ ማለት ነው።
- (አይነ አፋርነት) መልካምን ለመስራት የሚያነሳሳና ፀያፍን ከማድረግ የሚያቅብ ባህሪ ነው።
- (መልካም ጉርብትና) ይህ ግድ ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል አይንን ሰበር ማድረግ፣ የጎረቤትን ነውር አለመከታተል ተጠቃሾች ናቸው።
- (እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው መርዳት) ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል: **"በዱንያ ከአንድ አማኝ አንድ ችግሩን ያቃለለ አሏህ ከሱ የአኼራ ችግሮች አንድ ችግሩን ያቃልልለታል፤ ለተጨናነቀ ያግራራ አሏህ በዱንያም በአኼራም ያገራለታል፤ የአንድን ሙስሊም ነውር የሸፈነ አሏህ በዱንያም በአኼራም ነውሩን ይሸፍንለታል፤ የአሏህ ባርያ ወንድሙን በመርዳት ላይ እስከሆነ ድረስ አሏህም እሱኑ በመርዳት ላይ ነው።"** ሙስሊም ዘግበውታል

አስራ ስድስተኛው ትምህርት

ኢስላማዊ ስርአቶችን መላበስ

ከነዚህም: ሰላምታ መስጠት፤ ፈገግታ፤ በቀኝ እጅ መብላትና መጠጣት፤ ሲጀምሩ በአሏህ ስም ይሁን፤ በልተው ሲያጠናቅቁ በማመስገን ይሁን፤ ሲያስነጥሱ ማመስገን፤ አስነጥሶ አሏህን ያመሰገነን አሏህ ያዝንለት ዘንድ አሏህን መለመን፤ ህመምተኛን መጠየቅ፤ ሶላተል ጀናዛን ለመስገድ መከተልና መቅበር፤ መስጅድም ቤትም ሲገባም ሲወጣም ያሉ ሸሪዓዊ ስርአቶችን መጠበቅ፤ ጉዞ በሚወጣበት ጊዜ ያሉ አዳቦችን መጠበቅ፤ ከወላጆችም ጋ፣ ከቤተ ዘመድም ጋ፣ ከጎረቤቶችም ጋ፣ ከትልቁም ከትንሹም ጋ ስርአትን መላበስ፤ የተወለደለትን የእንኳን ደስ ያለህ ምኞትን መግለፅ፤ ያገባን ከአሏህ በኩል በረካ እንዲያገኝበት አሏህን መማፀን፤ ሃዘን ላይ ያለን ማፅናናት እና ሌሎችም ኢስላማዊ የሆኑ በመልበስም በማውለቅም ጊዜ ያሉ በመጫማትም ያሉ ስርአቶችን ሁሉ መጠበቅ።

አሳሳቢ ማስታወሻዎች

"ሰላምታ መስጠት" ሲባል መለዋወጥ ለማለት ነው። የተሟላ የሆነው: "አሰላሙ ዓለይኩም ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ" የሚለው ሲሆን ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰላምታን ትሰጣለህ፤ ሰላምታን ለሰጠውም ሁሉ ትመልስለታለህ።

"በቀኝ እጅ መብላትና መጠጣት" የተባለው ግዴታ ሲሆን፤ በሶስት ጣት ቢሆንና በቀኝ እጅ መስጠትና መቀበሉ ደግሞ የሚበረታታ ነው።

"ሲጀምር በአሏህ ስም ይሁን" ሲባል "ቢስሚላህ" ይበል ለማለት ነው።

"ሲያጠናቅቅ ማመስገኑ" ሲባል ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ "አልሓምዱ ሊላሂ ል-ለዚ አጥዓመኒ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሓውሊን ሚኒ ወላ ቁዋህ" ትርጉሙም "የኔ ሃይልም ብልሃትም ሳይታከልበት ይህንን ላበላኝና ላጠጣኝ አሏህ ምስጋና ይገባው"

-ከፊት ለፊቱ ባለው ሊበላና ምግቡንም ላያነውር የተደነገገ ነው።

ሲያስነጥሱ አሏህን ማመስገን ሲባል "አልሓምዱ ሊላህ" ይበል ለማለት ነው።
አስነጥሶ አሏህን ያመሰገነን አሏህ ያዝንለት ዘንድ አሏህን መለመን ሲባል "የርሓመከሏህ" ይበለው ለማለት ነው። ከዚያም ያስነጠሰው "የህዲኩሙሏሁ ወዩስሊሑ ባለኩም" ብሎ ይመልስ።
ህመምተኛንም ይጠይቅ ሲባል ይጠይቀው፤ አመች በሆነ አጋጣሚ እየተመላለሰ ዚያራውንም ያብዛ፤ ሂዶ ግን ቆይታውን አያርዝመው ከአሏህም እዝነት ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ እንዲገባም አያድርገው።
ሶላተል ጀናዛን ለመስገድ መከተልና መቅበር ሲባል ወንዶችን ነው እንጅ ሴቶችን አይመለከትም።
መስጅድም ቤትም ሲገባም ሲወጣም ያሉ ሸሪዓዊ ስርአቶችን መጠበቅ ሲባል መስጅድ ሲገባ ቀኝ እግሩን አስቀድሞ ሊገባና እንዲህም ሊል ነው፡ "ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመፍተሕሊ አብዋበ ራሕመቲክ" ትርጉሙም "በአሏህ ስም! ሶላትና ሰላምም በአሏህ መልእክተኛ ላይ ይስፈን፤ አሏህ ሆይ! የእዝነት በሮችህን ክፈትልኝ።" ከዛ በሚወጣበት ጊዜ ደግሞ ግራ እግሩን በማስቀደም እዲህ ይበል፡ "ቢስሚላሂ ወሶላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላሂ አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ" ትርጉሙም "በአሏህ ስም! ሶላትና ሰላምም በአሏህ መልእክተኛ ላይ ይስፈን፤ አሏህ ሆይ! ከችሮታህ እለምንሃለሁ።" ቤትን በማስመልከት ደግሞ ሲገባም ሲወጣም በቀኝ እግሩ ሲሆን ሲወጣ እንዲህ ይላል፡ "ቢስሚላሂ ተወከልቱ ዓለሏሂ ወላ ሓውላ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ አሏሁመ ኢኒ አዑዙቢከ አን አዲለ አው ኡዶለ አው አዚለ አው ኡዘለ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ አው አጅሂለ አው ይጅሀለ ዓለየ" ትርጉሙም "በአሏህ ስም፤ በአሏህም እመካለሁ፤ በአሏህ እንጅ ሃይልም ብልሃትም ያለው የለም፤ አሏህ ሆይ! በሌሎች ምክንያት ከመጥመምም ሆነ በኔው ምክንያት ሌሎች ከመጥመማቸውም ባንተው እጠበቃለሁ፤ ወይም ከመንዳለጥም ሌሎችን ከማንዳለጥም፤ ሌሎችን ከመበደልም በሌሎች ከመበደልም፤ ከመጃጃልም ሌሎች በኔ ከመጃጃላቸውም ባንተው እጠበቃለሁ።" ሲገባ ደግሞ እንዲህ ይበል "አሏሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸይረል መውሊጂ ወኸይረል መኽረጂ ቢስሚላሂ ወለጅና ወቢስሚላሂ ኸረጅና ወዓለሏሂ ረበና ተወከልና" ትርጉሙም "አሏህ ሆይ! ሰላማዊ መግባትንና ሰላማዊ መውጣትን እለምንሃለሁ፤ በአሏህ ስም ገባን በአሏህም ስም ወጣን፤ በጌታችን አሏህም ተመካን።" በማለት ቤት ውስጥ ላሉት ሰላምታን ይሰጣል።
ያገባን ከአሏህ በኩል በረከ እንዲያገኝበት አሏህን መማፀን ሲባል "ባረከሏሁ ለኩማ ወባረከ ዓለይኩማ ወጀመዓ በይነኩማ ፊ ኸይር" ብሎ ማለት ነው።
ሃዘን ላይ ያለን ማፅናናት ሲባል በሶስት ቀን ገደብ ነው፤ ከዛ መጨመር አይገባም።

አስራ ሰባተኛው ትምህርት

ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች ማስጠንቀቅ

ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች መራቅና ማስጠንቀቅ

ከነዚህም: ሰባቱ አውዳሚና አጥፊ ወንጀሎች ይገኙበታል። እነዚህም: በአሏህ ማጋራት፣ ድግምት፣ ተገቢ በሆነ ሸሪዓዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር አሏህ ክብር ያደረጋትን ነፍስ ማጥፋት፣ ወለድ መብላት፣ የየቲምን ገንዘብ መብላት፣ በፍልሚያ ጊዜ ማፈግፈግ፣ ጥብቅ የሆነችን ዝንጉ ሴትን ስም በዝሙት ማጠልሸት።

ከነዚህም: ወላጆችን መጨቆን፣ ዝምድናን መቁረጥ፣ የውሸት ምስክርነት፣ የውሸት መሃላ፣ ጎረቤትን ማስቸገር፣ ከደም መቃባት ጋ በተያያዘ፣ ከገንዘብ ጋ፣ ከክብር ጋ በተያያዘ ሰዎችን መበደል፤ አስካሪ መጠጥ፣ ቁማር መጫወት፣ ሃሜት፣ ነገር ማዋሰድ፣ ከዚህም ውጭ አሏህ ወይም መልዕክተኛው ﷺ የከለከሏቸው ነገሮች ሁሉ።

አሳሳቢ ማስታወሻዎች

“ሽርክ” ሲባል ትልቁንም ትንሹንም ሽርክ የሚያጠቃልል ነው።

“ድግምት” ሲባል እንደመስተፋቅር እና መስተፃርር መሰልንም የሚያካትት ሲሆን ያንን ያደረገ ወይም ያንኑ የወደደ ካፊር ይሆናል። ወደነሱ መሄድም ይሁን ድረገፃቸውን መጎብኘት የተከለከለ ነው። እንዲሁም የድግምት ጣብያዎችን መከታተልም ሆነ ጥንቆላዎቻቸውን የሚለቁባቸውን መፅሄቶችንና ጋዜጦቻቸውን ማንበብም የተከለከለ ነው። ድግምትን በድግምት ለመፍታት መጣርም ተገቢ አይደለም። ይልቅ ሸሪዓዊ በሆነ ሩቃ እና በዱዓእ እንዲሁም ዋግምትን በመሰሉ የተፈቀዱ በሆኑ ህክምናዎች ይፈወሳል እንጅ።

"ተገቢ በሆነ ሸሪዓዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር አሏህ ክብር ያደረጋትን ነፍስ ማጥፋት" ተገቢ በሆነ ሲባል ከሶስቱ አንዱን ለማለት ነው: እነሱም "ነፍስ ላጠፋ ነፍሱ ይጠፋል፤ አግብቶ የሚያውቅ ዝሙት ሲፈፅም፤ ዲኑን ትቶ ከሙስሊሞች ስብስብ የተገነጠለ"። ናቸው።

"የቲም" ሲባል ለአቅመ አዳም ከመድረሱ በፊት አባቱ የሞተበት ማለት ነው።

"በፍልሚያ ጊዜ ማፈግፈግ" ሲባል በአሏህ መንገድ ለመታገል የዘመቱትን ለማለት ነው።

"ጥብቅ የሆነችን ዝንጉ ሴትን ስም በዝሙት ማጠልሸት" ሲባል ጨዋ ሴቶችን ለማለት እንጅ ያገቡትን ብሎ ለመነጠል አይደለም የተፈለገበት።

"የውሸት መሃላ" ስንል ከአሏህ ውጭ ባሉት መማላንም ያጠቃልላል፤ ልክ በነብዩ ﷺ መማል፤ ወይም በክብራቸው ወይንም በህይወታቸው ወይንም በጥበቃቸው ወይንም በመሳሰሉት መማልንም ያጠቃልላል።

"ቁማር መጫወት" ሲባል ማሸነፍና መሸነፍ ያለበትን ጨዋታ ሁሉ እንደሎተሪ ያለውንም ጭምር

"ሃሜት" ሲባል ነብዩ ﷺ በዚህ መልኩ ገልፀውታል "ወንድምህ በሚጠላው መልኩ ማውሳትህ ነው"

"ነገር ማዋሰድ" ሲባል በሰዎች መካከል ወሬ ማመላለስ ማለት ነው

የውድድሮችና ፉክክሮች ብይን

ከማስያዣ ጋ የሚፈቀድ: የፈረስ፣ የግመል፣ የቀስት ውርወራ ውድድር፤ ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና:

“በቀስት፣ በግመል ውድድርና በፈረስ ውድድር ካልሆነ በቀር ማስያዝ መወዳደር አይቻልም”

ሙሉ በሙሉ ሐራም የሆነ:

ሃረድ (ዳይስ መሰል ጨዋታ) ቼዝ እና መሰል ጨዋታዎች

አስይዘህ ከሆነ የተከለከለ ሳታስይዝ ግን የተፈቀደ: ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት ጨዋታዎች ሁሉ።

አስራ ስምንተኛው ትምህርት

ሙትን መገነዝና በሱም ላይ መስገድ እና መቅበር

የዚህ ማብራርያው እንደሚከተለው ነው:

<u>በመጀመርያ</u>: ሞት አፋፍ ላይ ያለን "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" እንዲል ቃሉን ማስያዝ፤ ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና **"ሙታኖቻችሁን ላ ኢላሃ ኢለሏህ አስይዟቸው"** "ሙታኖቻችሁን" ሲባል ሞት አፋፍ ላይ የተጣዱትን እነኝህም የሞት ምልክት ጎልቶ የሚታይባቸው የሆኑት ናቸው።

<u>ሁለተኛ</u>: መሞቱ ከተረጋገጠ አይኖቹ እንዲጨፈኑ ይደረግና ፂሙም ይቋጠራል፤ ከነብዩ ﷺ የመጣው ሱና ይህን የሚያመልክት ነውና።

<u>ሶስተኛ</u>: የሙስሊም ሬሳ ከሆነ ማጠቡ ግዴታ ነው። ምናልባት መስዋእት ሆኖ በጦር መስክ ሸሂድ የሆነ ካልሆነ በቀር፤ ይህ አይታጠብምም አይሰገድበትምም ይልቅ ከነልብሱ ነው የሚቀበረው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ የኡሑድ ዘመቻ ሸሂዶችን አልሰገዱባቸው አላሳጠቧቸውምና።

<u>አራተኛ</u>: የሙት አተጣጠብ ሁኔታው: ሃፍረተ ገላው ይሸፈናል፤ ከዚያም ከፍ ተደርጎ ይያዝና ከሆዱ በኩል ለስለስ ባለ መልኩ ጫን ይደረጋል፤ ከዚያም አጣቢው/ዋ እጅ ላይ ብጣሽ ጨርቅ ነገር ይጠቀለልና በዚያው ያሸዋል። ከዚያም ሬሳውን የሶላት ውዱእ እንደሚደረገው ውዱእ ያስደርገዋል፤ ከዚያም የሙቱን ጭንቅላትና ፂም በውኃና በቁርቁራ ዛፍ ወይም መሰል ነገር አድርጎ ያጥበዋል፤ ከዚያም በቀኙ በኩል ካጠበ በኋላ በግራው በኩል ያጥበዋል፤ ከዚያም ለሁለተኛና ለሶስተኛም ጊዜ እንዲሁ አድርጎ ያጠበዋል፤ በሆዱ አካባቢ ባጣበው ቁጥር ከስር አንዳች ነገር የሚወጣው ከሆነ አፅጅው ቦታውንም በጥጥ ነገር ይዝጋው፤ አሁንም አላቆም ካለ ግን በአንዳች አፈር ነገር ወይም ዘመን አመጣሽ በሆነ ህክምናዊ ስሪት፤ ማለት እንደፕላስቲክና መሰል በሆነ ነገር ይዝጋው።

ውዱኡም ይደገምለት፤ ሶስቴ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ወደ አምስቴ ወይንም ወደሰባት ጨመር ተደርጎ ይታጠብ። ከዚያም በልብስ ነገር ያደራርቁት። በየመገጣጠሚያዎቹም ላይ፣ (ማለትም በብብቶቹ እና በታፋው ውስጥ) በሱጁድ አካላቶቹ፣ ከተቻለ ደግሞ መላ አካላቱንም ሽቶ ቢቀባው መልካም ነው። ከፈኑም በዕጣን ነገር ማጠን፤ ቀድሞ ቀመሱ ወይንም ጥፍሩ የረዛዘሙ ከሆኑ ይቀነጠባል። ቢተወውም ግን ችግር የለውም። ፀጉሩ መወገድ አይኖርበትም፤ ሃፍረተ ገላው አይላጭም፤ (ያልተገረዘ ከነበረ) አይገረዝም ምክንያቱም ይህን የሚያመላክት ማስረጃ የለምና፤ ሴት ከሆነች ደግሞ ፀጉሯ ሶስት ጉንጉን ተደርጎ በጀርባዋ ይለቀቃል።

<u>አምስተኛ</u>: ሙትን መከፈን: ለወንድ በላጭ የሚሆነው ልክ ነብዩ ﷺ ላይ እንደተደረገው ቀሚስና ዒማማ (ጥምጣም) ሳይታከልበት በሶስት ነጫጭ ልብስ ተደርጎ መከፈኑ ሲሆን ታዳጊ ሴት ልጅ ደግሞ በቀሚስና በሁለት ፎጣ ተደርጋ ነው የምትከፈነው።

በሁሉም ላይ ግዴታ የሆነው መላ ሰውነትን የሚሸፍን አንድ ልብስ ነው። ሚቹ በሓጅ ስርአት ኢሕራም ላይ ያለ ከሆነ በውሃና በቁርቁራ ዛፍ ይታጠብና በሸርጡና በፎጣው ወይም መሰል በሆነ ነገር ይከፈናል። ራሱና ፊቱ ግን አይሸፈንም፤ ሽቶም አይቀባም ምክንያቱም የውመል ቂያማ ተልቢያውን እያለ ነውና የሚቀሰቀሰው። ልክ ከነብዩ ﷺ ሶሒሕ በሆነ ሓዲሥ እንደመጣው።

በሓጅ ኢሕራም እያለች የሞተችዋ ሴት ከሆነች ግን የምትከፈነው እንደሌሎቹ ሴቶች ነው። ነገር ግን ሽቶ አትቀባም፤ ፊቷንም በኒቃብ እጆቿንም በጓንት አትሸፈንም፤ ነገር ግን ፊቷንም ሆነ እጆቿን በተጠቀለለችበት ከፈን ነው የምትሸፈነው። የሴትን ልጅ አከፋፈን ሁኔታን በማስመልከት ቀደም ብለን ባብራራነው መልኩ ማለት ነው።

ስድስተኛ: ከማንም በበለጠ ለመገነዝ ተገቢ የሚሆነው አደራ የተጣለበት ሲሆን ከዚያም አባት፤ ከዚያም አያት፤ ከዚያም ካለው የዝምድና ቅርበት አኳያ እየታየ ይሆናል። ይህ ወንድን በማስመልከት ነው።

ሴትን በማስመልከት ደግሞ ከማንም ይበልጥ ተገቢ የምትሆነው ሚቹ አደራ የጣለችባት ስትሆን ከዚያም እናት፤ ከዚያም ሴት አያቷ ከዚያም ካላት የዝምድና ቅርበት አኳያ እየታየ ይበልጥ በዝምድና የምትቀርባት ሴት ትገንዛታለች። የትዳር አጋሮች ደግሞ እርስ በራሳቸው ይተጣጠባሉ። ምክንያቱም አቡበክር ሲዲቅን ያጠበቻቸው ባለቤታቸው ነችና፤ እንዲሁም ዓልይም ባለቤታቸውን ፋጢማን ያጠቡት ራሳቸው ናቸውና።

ሰባተኛ: በሚች ላይ ሶላት መስገድ: "አሏሁ አክበር!" የሚለው አራት ጊዜ ነው። ከመጀመርያው ተክቢራ በኋላ ፋቲሓን (አልሓምዱ) ይቀራል፤ አብሮ አንዲት አጠር ያለች የቁርአን ሱራ ወይንም አንድ ሁለት አንቀፅ ቢያክልባት መልካም ነው። ኢብኑ ዓባስ በዘገበውና ከነብዩ ﷺ ከመጣው ሶሒሕ ሓዲሥ አንፃር፤ ከዚያም በነብዩ ﷺ ላይ ልክ ሶላት ላይ እንደሚባለው አድርጎ ሶለዋት ያወርዳል፤ ለሶስተኛ ጊዜ "አሏሁ አክበር!" ካለ በኋላ እንዲህ በማለት ዱዓእ ያድርግ **"አሏሁመ-ግፊር ሊሓይና ወመይቲና፡ ወሻሂዲና ወጋኢቢና፡ ወሶጊሪና ወከቢሪና፡ ወዘኩሪና ወኡንሣና፡ አሏሁመ መን አሕየይተሁ ሚና ፈአሕይሂ ዓለል ኢስላም፡ ወመን ተወፈይተሁ ሚና ፈተወፈሁ ዓለል ኢማን፡ አሏሁመ-ግፊር ለሁ ወርሓምሁ ወዓፊሂ፡ ወዕፉ ዓንሁ፡ ወአክሪም ኑዙለሁ፡ ወወሲዕ መድኸለሁ፡ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወሠልጂ ወልበረዲ፡ ወነቂሂ ሚነልኸጣያ ከማ ዩነቀ-ሥ-ሠውቡል አብየዱ ሚነደነስ፡ ወአብዲልሁ ኸይረን ሚን ዳሪሀ፡ ወአህለን ኸይረን ሚን አህሊሀ፡ ወአድኪልሁል ጀነተ፡ ወአዒዝሁ ሚን ዓዛቢል ቀብሪ፡ ወዓዛቢ-ን-ናሪ ፡ ወፍሰሕ ለሁ ፊቀብሪሀ፡ ወነዊር ለሁ ፊሀ፡ አሏሁመ ላተሕሪምና አጅረሁ ወላ ቱዲለና ባዕደሁ"** ትርጉሙም፡

ትርጉሙም **“አሏህ ሆይ! ለህያዋኑም ለሙታኑም ምህረትህን ለግስ፤ በቅርብም በሩቁም ላለው፣ ለትልቆቻችንም ለትንሾቻችንም፣ ለወንዶቻችንም ለሴቶቻችንም ምህረትህን ለግስ። አሏህ ሆይ! ከኛ መካከል ህያው ያደረግከውን ኑሮውን በኢስላም አድርግለት፤ ከኛ መካከል ሞት የወሰንክበትን ሞቱን በኢማን አድርግለት፤ አሏህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰው፣ እዘንለትም፣ ጠብቀውም፣ ይቅር በለውም፣ መኖርያውንም የተከበረ አድርግለት፣ መግቢያውንም አስፋለት፣ በውኃ በበረዶና በቀዝቃዛ እጠበው፣ ልክ ነጭ ልብስ ከጉድፍ እንደሚፀዳው ሁሉ ከወንጀሉም አፅዳው፤ ከሃገሩ የተሻለ ሃገር፣ ከቤተሰቡ የተሻለ ቤተሰብ ተካለት፤ ጀነትንም አስገባው፣ ከቀብር ቅጣትም ጠብቀው፣ ከእሳት ቅጣትም ጠብቀው፣ ቀብሩንም አስፋለት፣ ውስጡንም አብራለት፣ አሏህ ሆይ! አጅሩንም አትንፈገን ከሱ በኋላም አታጥምመን።”** ከዚያም ለአራተኛ ጊዜ አሏሁ አክበር ካለ በኋላ በቀኙ በኩል ብቻ አንድ ጊዜ በማሰላመት ያጠናቅቃል።

ከእያንዳንዱ ተክቢራ ጋ እጁን ማንሳቱ የሚበረታታ ነው።

ሚች ሴት ከሆነች እንዲህ ነው የሚለው “አሏሁመ-ግፊር ለሃ... ” *[ማለትም በዱዓው ወንድ ጠቋሚ የሆነውን መጨረሻቸው “... ሁ” የሚል መቋጫ ያላቸውን ቃላቶች እየቀየረ ሴትን በሚገልፀው “... ሃ” በሚል ይተካዋል እላይ በተጠቀሰው ምሳሌ መሰረት፤ የሚያውቅን ሰው ቢጠይቁ በተሻለ መልኩ ይረዳዎታል]*

ሚኾቹ ሁለት ከሆኑ እንዲህ ነው የሚለው “አሏሁመ-ግፊር ለሁማ... ” እያለ ሁለትን ጠቋሚ በሆነ የዓረብኛው ምእላድ ይቀጥላል\

ሚኾቹ ከዚህ በላይ ከሆኑ ደግሞ እንዲህ ነው የሚለው “አሏሁመ-ግፊር ለሁም... ” እያለ ብዛትን ጠቋሚ በሆነ የዓረብኛ ምእላድ ነው ዱዓውን የሚያደርገው።

ሚቹ ጨቅላ ህፃን ከሆነ ምህረትን ከመለመን ይልቅ እንዲህ ነው የሚባልለት “አሏሁመ-ጅዓልሁ ፈረጠን ወዙኽረን ሊዋሊደይሂ፡ ወሸፊዐን ሙጃነን፡ አሏሁመ ሠቂል ቢሂ መዋዚነሁማ፡ ወአዕዚም ቢሂ ኡጁረሁማ፡ ወአልሒቅሁ ቢሷሊሒ ሰለፊል ሙእሚኒን፡ ወጅዓልሁ ፊከፋለቲ ኢብራሂም ዓለይሂ-ስሶላቱ ወ-ስ-ሰላም ወቂሂ ቢራሕመቲከ ዓዛበል ጀሒም” ትርጉሙም “አሏህ ሆይ! ለወላጆቹ የሚያሰናዳ እና ድልብ አድርገው፤ ተቀባይነት ያለውም አማላጅ፤ አሏህ ሆይ! በሱ ምክንያትም የወላጆቹን ሚዛን የሚያመዝን፤ በሱ ምክንያትም አጅራቸው ከፍ የሚልላቸው፤ የቀደሙትን ደጋጎችንም የሚቀላቀል አድርገው፤ በኢብራሂም ዓለይሂ ሰላም ስር ከሚሆኑትም አድርገው፤ በእዝነትህም የጀሃነምን እሳት ከምትጠብቃቸውም አድርገው።”

ሱናው ኢማሙ በወንድ ላይ ከሆነ የሚሰገደው በራስጌው ልክ፤ በሴት ላይ ከሆነ የሚሰገደው በስትክክል መሃል ሆኖ መቆሙ ነው። በርከት ያሉ ከሆኑ የሚሰገድባቸው ወንዱ ሚች በኢማሙ በኩል ተደርጎ ሴት ሚች ደግሞ በስተቂብላ መሆን፤ ከነሱ መካከል ጨቅላዎች ካሉ ደግሞ ወደ ቂብላው በኩል ጨቅላ ቀዳሚ ይሆንና ከዚያም ሴት ከሱ ቀጥላ ከዚያም በድጋሚ ጨቅላው ይደረጋል። የወንድ ህፃን ልጅ ራስ በወንድ ራስ በስትክክል ሲሆን የሴት ልጅ አዋቂም ይሁን ህፃን ሽምጥ ደግሞ በወንዱ ራስ እስትክክል ይሆናል። ሰጋጆችም ባጠቃላይ ከኢማሙ በስተጀርባ ይሆናሉ፤ ምናልባት ብቸኛ ሆኖ ከኢማሙ በኋላ ለመቆም ቦታ ያላገኘ ካልሆነ በቀር ይህ በቀኙ በኩል ነው የሚቆመው።

<u>ስምንተኛ</u>: የሙት አቀባበር አኳኋን: የሚበረታታው ቀብሩን እስከሽምጥ አካባቢ ድረስ ጥልቅ አድርጎ ከበስተቂብላውም በኩል ወደ ጎን መቆፈር ነው። ሚችም በቀብሩ በተቆፈረለት ላሕድ በቀኙ እንዲተኛ ይደረጋል፤ የከፈኑ ቋጠሮም ይፈታና ግን ሳይወልቅ እንዲሁ ይተዋል። ሚች ሴትም ትሁን ወንድ ፊቱ አይገለጥም። ከዛም ጡብ(ብሎኬት ነገር) ይተከልለትና አፈር እንዳይዘልቅበት ይመረጋል፤ ጡብ ካልተገኘ ጣውላ አልያም ድንጋይ ወይም ደግሞ አፈር ማቀብ የሚችል እስከሆነ ድረስ ሌላ እንጨት ማድረግም ይቻላል። ከዚያም አፈሩ በላዩ ላይ ይለቀቃል፤ የዚህኔ እንዲህ ማለቱ የሚበረታታ ነው። **"ቢስሚላሂ ወዓላ ሚለቲ ረሱሊላሂ"** ትርጉሙም "በአሏህ ስም! በመልዕክተኛውም ጎዳና" ቀብሩም የስንዝርን ያክል ወደላይ ጉብ ይደረጋል። አሞቺ ከሆነ ችካል ነገር በላዩ ላይ ይተከልበትና ወኋም ይርከፈከፍበታል።

ቀባሪዎቹ በቀብሩ ሳሉ ለሚቹ ዱዓእ ቢያደርጉለት የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሚችን ቀብረው ካጠናቀቁ በኋላ ቆመው እንዲህ ይሉ ነበርና **"ለወንድማችሁ መሃርታን ለምኑለት፤ ፅናትን ይለግሰው ዘንድም አሏህን ተማፀኑለት፤ ምክንያቱም አሁን መጠየቁ ነውና።"**

ዘጠነኛ: ሶላተል ጀናዛ ያልሰገደበትም ካለ ከተቀበረ በኋላም ቢሆን ሊሰግድበት የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ይህን አድርገዋልና፤ ይሁን እንጅ ይህ የሚሆነው ጊዜው እስከወርና ከወር ባነሰ የጊዜ ገደብ ነው። ጊዜው ከዚህ ካለፈ ግን በሟቹ ላይ መስገዱ የተደነገገ አይደለም። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ሟች ከተቀበረ ወር ከሞላው በኋላ በሟች ላይ ሰግደዋል የሚል የተዘገበ የለምና ነው።

አስረኛ: የሟች ቤተሰብ ለእድምተኛው ምግብ ማሰናዳታቸው የተፈቀደ አይደለም። ምክንያቱም ሱሓብዩ ጀሪር ቢን ዓብዲላህ አልበጀሊይ (በሶሓቦች ጊዜ ስለነበረው) እንዲህ ብሏል **"በሟች ቤተሰብ መሰባሰብና ከተቀበረም በኋላ ምግብ ማሰናዳትን ከሙሾ ማውረድ እንቆጥረው ነበር።"** ነገርግን ለራሳቸው አልያም እንግዳ ሆነው ለመጡባቸው መስራታቸው ችግር የለውም። እንዲሁም ዘመድና ጎረቤት ደግሞ ለሟች ቤተሰብ ምግብ መስራታቸው የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ከሻም በኩል የጃዕፈር ቢን አቢ ጣሊብ መርዶ በመጣላቸው ጊዜ ቤተሰቦቹን ለጃዕፈር ቤተሰቦች ምግብ እንዲያሰናዱ አዘው ነበርና ነው። እንዲህም ብለው ምክንያት አዘል መልዕክትን ተናግረዋል **"... የሚጠምዳቸው ነገር መጥቶባቸዋል ... "** የሟች ቤተሰብም ጎረቤቶቻቸውን ወይም ሌሎችን ጠርተው ከመጣላቸው ምግብ አብረው እንዲቋደሱ ቢያደርጉ ችግር የለውም። እስካሁን በምናውቀው ለዚህ በሸሪዓ የተገደበ ጊዜ እንደሌለው ነው።

አስራ አንደኛ: ለሴት ልጅ ከሶስት ቀን በላይ ሃዘን ላይ ሆና ልትቀመጥ የተፈቀደ አይደለም፤ ምናልባት ሟቹ ባሏ ካልሆነ በቀር፤ ሟቹ ባሏ ከሆነ ግን ለአራት ወር ከአስር ቀን ሃዘንተኛ ሆና ልታሳልፍ ግዴታዋ ነው። ምናልባት ነፍሰጡር ከሆነች ግን የሃዘንተኛ ጊዜዋ በወለደችበት ጊዜ የሚነሳ ይሆናል። ይህም ከነብዩ ﷺ ከመጡ የተረጋገጡ ሶሒሕ ሓዲሦች አንፃር ነው።

ወንድ ከሆነ ግን ለዘመድም ይሁን ወይም ለሌላ ለማንም ብሎ ሃዘንተኛ ሆኖ ሊቀመጥ አይፈቀድለትም።

<u>አስራ ሁለተኛ</u>: ለወንዶች በየጊዜው እየሄዱ ቀብር እየዘየሩ ለሟችም ዱዓእ አድርገው፤ ምህረትን ከአሏህ ተማፅነው በሞትና ከሞት በኋላ ባለው ሁኔታ ተግሳፅን ቀስመው መምጣታቸው የተደነገገ ነው። ምክንያቱም ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና "ቀብርን ዘይሩ ከሞት በኋላ ያለውን ህይወት ታስታውሳችኋለችና።" ባልደረቦቻቸውንም ቀብርን ለመዘየር በሚሄዱበት ጊዜ እንዲህ እንዲሉ ያስተምሯቸው ነበር። **"አሰላሙ ዓለይኩም አህለ ዲያሪ ሚነል ሙእሚኒነ ወልሙስሊሚን ወኢና ኢንሻአሏሁ ቢኩም ላሒቁን ነስአሉሏሃ ለና ወለኩሙል ዓፊያህ የርሓሚላሁል ሙስተቅዲሚነ ሚና ወልሙስታእኺሪን"** ትርጉሙም "እናንተ ከሙእሚንም ከሙስሊምም መካከል የሆናችሁ የቀብር ነዋሪዎች ሆይ! አሏህ ባለው ጊዜ እኛም እናንተኑ የምንቀላቀል ነን፤ ለኛም ለእናንተም አሏህ ይቅር ባይነቱን ይለግስ ዘንድ እንማፀነዋለን፤ ከኛ መካከል ቀዳሚ የሆኑትንም የዘገዩትንም አሏህ መሃርታውን ይለግስ።"

ሴቶች ግን ቀብርን መዘየራቸው ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም ነብዩ ﷺ **"ሴት የቀብር ዘያሪዎችን ረግመዋል"** እንዲሁም የቀብር ዚያራ ቢያደርጉ ምናልባት የሚፈተኑበት ነገር እና የትእግስት እጦትም ሊኖር ይችላልና።

እንዲሁም ሟች ወደ ቀብር ሲሄድ ጀናዛውን መከተልም አይፈቀድላቸውም፤ ምክንያቱም ነብዩ ﷺ ከዚህ ከልክለዋቸዋልና። መስጅድ ውስጥ ሆነ አልያም በሌላ ቦታ ሆነው በጀናዛው ላይ መስገድ ግን ለወንዱም ለሴቷም ባጠቃላይ የተፈቀደ ነገር ነው።

መሰብሰቡ የገራልን ይህን ይመስላል፤ ወሶለሏሁ ወሰለመ ዓላ ነብይና ሙሓመዲን ወአሊሂ ወሷሕቢህ

ቀብርን የመዘየር አይነቶች

የተደነገገው ዚያራ

ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት አስታውሶ መገሰፅን ሊያቅድ፤ ምንም አይነት ነገር ሳይሰንቅ ሊሆን፤ ለሱም ሆነ ለሌሎች ሚኾች ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ ዱዓእ ሊያደርግላቸው አቅዶ የተነሳ እና ሸሪዓው የሚቃወመውን አንዳችም ነገር ከማድረግ የሚቆጠብ ከሆነ ነው።

መጡ የሆነው ዚያራ

ቀብሩ ላይ ሆኖ አሏህን ለማምለክ አቅዶ የተነሳ እንደሁ ነው።

ሸርክ ያለበት ዚያራ

የቀብሩን ባለቤት(ሚቹን) ራሱን ለመለመን አቅዶ የተነሳ እንደሆነ ነው።

ስለ መገነዝና ስለ ስርአት ፈተና

1. ስርአትና ሸሪዓዊ አደቦችን መጠበቅ ከሙስሊም ባህርያት ናቸው። (እውነት – ሃሰት)
2. ሃይማኖቴ ከከፎውች ጋ እንድወዳጅና ደጋጎችን እንድርቅ ያዘኛል። (እውነት – ሃሰት)
3. ኢስላም ከአስተናጋጆችና ከሰራተኞችም ጋ በመልካም መስተጋብር እንድንኗኗር ነው ያስተማረኝ። (እውነት – ሃሰት)
4. በምላሱም በእጁም ሌሎችን አዛ የሚያደርግን ሰው እወዳጃለሁ። (እውነት – ሃሰት)
5. የሰደበኝን ሰው መልሸ በመስደቤ ያስደስተኛል። (እውነት – ሃሰት)
6. የሚያስፈልጋቸውን እና ደካሞችን እንዳግዝ ነው ኢስላም ያስተማረኝ። (እውነት – ሃሰት)
7. አንድ ሙስሊም በሌላኛው ሙስሊም ላይ ካለው ሐቅ መካከል በታመመ ጊዜ ሊጠይቀውና አሏህ እንዲፈውሰውም ዱዓእ ሊያደርግለት ነው። (እውነት – ሃሰት)
8. የጎረቤትን ሚስጥር መፈላፈል ከአማኞች ባህሪ ነው። (እውነት – ሃሰት)
9. አሏህ ዘንድ ከማንም በበለጠ ተወዳጁ ከማንም በላይ ሰዎች ጠቃሚ የሆነው ነው። (እውነት – ሃሰት)
10. ከቤት ሲወጣ የሚባለው ዚክር እንዲህ ነው “ቢስሚላሂ ወለጅና ወቢስሚላሂ ኸረጅና ወዓላ ረበና ተወከልና” (እውነት – ሃሰት)
11. ባስነጠስኩ ጊዜ “የርሓመከሏህ” ላለኝ እኔ የምለው “የህዲኩሙሏሁ ወዩስሊሑ ባለኩም” ነው። (እውነት – ሃሰት)
12. አሏህን ማስታወስ አንድን ሙስሊም ከከፋት ትጠብቀዋለች ወደ አሏህም ታቃርበዋለች። (እውነት – ሃሰት)
13. ኢስላማዊ ወንድምህን ወይንም እህትሽን የመውደድህ/ሽ ምልክቱ ምንድን ነው?

.....

14. የኢማንህን መዳከም ከሚያመላክቱ ነገራቶች መካከል ሙስሊም ወንድምህን መመቅኘት ይገኝበታል። (እውነት – ሃሰት)
15. ሙሓባን የሚያመጡ ሰበቦችን ጥቀስ/ሽ።

.....

16. ከሚያሰክሩ ነገራቶች የተከለከለው ኽምር ተብሎ የሚጠራውን ነው። (እውነት – ሃሰት)
17. በሚጠጡትና በሚበሉበት ላይ መተንፈስ የተወገዘ ነው። (እውነት – ሃሰት)
18. ምግብ በልተው እጅን ከመታጠብ በፊት ጣትን መላስ የሚበረታታ ነው። (እውነት – ሃሰት)
19. በአመጋገብም ይሁን በመጠጥ እንዲሁም በአለባበስ መካከለኛ መሆን ተፈላጊ አካሄድ ነው። (እውነት – ሃሰት)
20. ከሰዎች መካከል ጀናዛን ለማጠብ፣ በሱ ላይ ለመስገድና ለመቅበር ይበልጥ ተገቢ የሆኑ በቅድሚያ ... ... ከዚያም.... ... ...ከዚያም ... ... ከዚያም ... .
21. የሟችን እዳ መክፈል ... ...

O ግዴታ ነው O የሚበረታታ ነው O የተፈቀደ ነው

22. ሟችን መቅበር ብይኑ ... ... O የሚበረታታ ነው O ግዴታ ነው O ፈርዱ ኪፋያ ነው (ማህበራዊ ግዴታ) ነው
23. ሞት አፋፍ ላይ ያለን “ላ ኢላሃ ኢለሏህ” እንዲል ማስደረግ ብይኑ... ... O ግዴታ ነው O የሚበረታታ ነው O የተከለከለ ነው
24. ሙታን በሚታጠቡበት ጊዜ ላያጥቡ ነገር በቦታው መገኘት ብይኑ ... .

O የተከለከለ ነው O የተፈቀደ ነው O የተወገዘ ነው

25. የከፈኑ ቋጠሮ የሚፈታው ሟቹን በቀብሩ ጉድጓድ ካስገቡት በኋላ ነው። (እውነት – ሃሰት)
26. ባልና ሚስት አንዱ ሌላኛውን አያጥብም፤ ምክንያቱም ኒካሓቸው በሟች ሞት ምክንያት ውድቅ ሆኗልና። (እውነት – ሃሰት)

27. … … … … ያለውን ወንድም ሴትም ሊያጥቡ ይችላሉ።
28. በሚች ላይ መስገድን ያመለጠው ……. መስገድ ይችላል፤ ይህም የሚሆነው ግን በ…….. የጊዜ ገደብ ነው።
29. በሚች ላይ ማልቀስ ልቅ በሆነ መልኩ የተፈቀደ ነው። (እውነት – ሃሰት)
30. ሚች ቀብሩ ውስጥ በተዘጋጀለት ላሕድ ቂብላን ተቅጣጭቶ ነው እንዲጋደም የሚደረገው። (እውነት – ሃሰት)

ርእስ ማውጫ

የሸይኹ መግቢያ ማብራሪያ 3

የመጀመሪያው ትምህርት: ሱረቱ -ል- ፋቲሓ እና አጫጭር ሱራዎች 4

ከ"ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ሯሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን" የተወሰኑ ቅንጫቢዎች 6

የመግቢያውና የተፍሲሩ ፈተና 27

ሁለተኛው ትምህርት-የኢስላም ማእዘናት 43

ሶስተኛው ትምህርት: የኢማን ማእዘናት 51

አራተኛው ትምህርት: የተውሒድ አይነቶች እና የሽርክ አይነቶች 56

አምስተኛው ትምህርት: ኢሕሳን.....61

ተውሒድ ነክ ፈተና 62

ስድስተኛው ትምህርት: የሶላት ቅድመ መስፈርቶች.....67

ሰባተኛው ትምህርት: የሶላት ማእዘናት.....71

ስምንተኛው ትምህርት: የሶላት ዋጅቦች(ግዴታዎች) 73

ዘጠነኛው ትምህርት: ተሸሁድ (አት-ተሕያቱ) 74

ማውጫ

አስረኛው ትምህርት: የሶላት ተጨማሪ ሱናዎች 75

አስራ አንደኛው ትምህርት: ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶች 77

አስፈላጊ ጥቆማዎች 78

የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ.....80

ሶላቶች በጥቅሉ.....90

ስለሶላት ፈተና 93

አስራ ሁለተኛው ትምህርት: የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች.....98

አስራ ሶስተኛው ትምህርት: የውዱእ ግዴታዎች 100

አስራ አራተኛው ትምህርት: ውዱእ የሚያፈርሱ ነገራቶች.....101

የውዱእ አደራረግ ሁኔታ ስእላዊ ማጠቃለያ.....103

ከንፅህና ጋ ተያያዥ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች.....106

ንፅህና ነክ ጥያቄዎች 110

ሁለተኛው : ዘካ 113

ዘካ ነክ ጥያቄዎች 118

ሶስተኛ: ፆም.....122

ማውጫ

ፆም ነክ ጥያቄዎች.....129

አራተኛ: ሓጅ.....132

የሓጅና ዑምራ ማብራርያ.....137

የሓጅ ጥያቄዎች 140

አስራ አምስተኛው ትምህርት: በኢስላማዊ ስነምግባር ማጌጥ 143

አስራ ስድስተኛው ትምህርት: ኢስላማዊ ስርአቶችን መላበስ.....144

አስራ ሰባተኛው ትምህርት: ከሽርክና ከመሳሰሉት ወንጀሎች ማስጠንቀቅ 146

አስራ ስምንተኛው ትምህርት: ሙትን መገነዝ.....149

ስለ መገነዝና ስለ ስርአት ፈተና 157

ማጣቀሻ መፃህፍት

[1]. ቁርአነል ከሪም

[2] "ተይሲር አል-ከሪሙ-ር-ራሕማን ፊ ተፍሲሪ ከላም አል-መናን" የታላቁ ሸይኽ ዓብዱ-ር-ራሕማን አስሰዕዲይ

[3]. “ሶሕሕ ቡኻሪይ” የእውቁ ዓሊም ኢማም አቢ ዓብዲላህ ሙሓመድ ቢን ኢስማዒል አልቡኻሪይ

[4]. “ሶሒሕ ሙስሊም” የእውቁ ዓሊም ኢማም አቢል ሑሰይን ሙስሊም ቢን አልሓጃጅ

[5] “ሸርሒል ሙምቲዕ ዓላ ዛዲል ሙስተቅኒዕ” የታላቁ ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን

[6]. “አል ቀውሉል ሙፊድ ዓላ ሸርሒ ኪታቡ ተውሒድ” የታላቁ ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን አሏህ ሁሉንም መሃርታውን ይለግሳቸውና።

ثواب لوالدها / مبارك عبد العزيز الحساوي رحمه الله، ووالدتها / بدرية محمد الحشتي عفا الله عنها
وقف لله، لا يجوز بيعه
በነዓ የሚታደል የወቅፍ አትም
دار الامل الخيرية

ይህ ነው እስልምና

هذا هو الإسلام

ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ማብራሪያ

شرح أسئلة القبر الثلاثة

የአራቱ መሰረታዊ ህጎች ማብራሪያ

شرح القواعد الأربع

ከእስልምና የሚያስወጡ ነገሮች ማብራሪያና ማስጠንቀቅያ

تحذير أهل الإيمان بأشياء تخرج المسلم من الإسلام



በአማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ
مترجم باللغة الأمهرية

شرح فضيلة الشيخ
هيثم بن محمد جميل سرحان

የክቡር ሸይኽ ሀይሰም ብን ሙሀመድ ጀሚል ሰርሀን ማብራሪያ

هيثم سرحان
الموقع الرسمي للشيخ
www.alsarhaan.com

ይህ ነው እስልምና
የክቡር ሸይኽ ሀይሰም ብን ሙሀመድ ጀሚል ሰርሀን ማብራሪያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው፤ እናመሰግነዋለን፣ እገዛውን እንጠይቀዋለን፣ መሃርታውን እንለምነዋለን፣ ከነፍሳችን ክፋትና ከክፉ ስራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራውን የሚያጠም የለውም፤ ያጠመመውንም የሚመራ የለውም፤ ከአላህ ውጭ (በእውነት) የሚመለክ እንደሌለ ብቸኛና ተጋሪ የሌለው መሆኑንና ሙሓመድም ﷺ ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በመቀጠል፡

የትንታኔው መግቢያ

የዚህ ፅሁፍ ደራሲ

ሸይኹል ኢስላም፤ የተውሒድ ጥሪ የተሃድሶ መሪ(ሙጀዲድ)፤ ኢማም ሙሓመድ ቢን

ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ፤ በቅፅል ስማቸው አቡ-ል-ሑሰይን (ይባላሉ)።

በዑየይና መንደር በ1115 ዓ. ሒ. ተወልደው በ1206 ዓ. ሒ. ሞቱ።

ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማረው?

- ምክንያቱም አሏህ እኛን የፈጠረበት ምክንያት ስለሆነ
- በሱው ቢሆን እንጅ አላህ ስራን ስለማይቀበል
- ተውሒድ ያለው ካልሆነ በቀር ጀነት ስለማይገባ
- ምንዳን ለማብዛት ምክንያት ስለሆነ
- ኃጢአትን ለማሰረዝ ምክንያት ስለሆነ
- ለመመራትና ለተረጋጋ ደህንነት ምክንያት ስለሆነ
- ለውስጣዊ መረጋጋት ምክንያት ስለሆነ
- የነብዩን ﷺ አማላጅነት ለማግኘት ምክንያት ስለሆነ

በመጀመርያውኑ ይህንን ትምህርት ለማስተማር የተመረጠበት ምክንያት

የደጋግ ቀደምቶቻችን እና ሌሎች የአህሉ ሱና ወልጀማዓህ ሙሁራኖቻችን በዚህ ታላቅ ፅሁፍ ትኩረት የሰጡበት ምክንያት ካለው ጥቅምና የጎላ ፋይዳው አኳያ ነው። ይህች አንድ እውቀት ፈላጊ የሆነ ሰው መስመሩ አድርጎ ሊጓዝ የሚችልባትና ሸሪዓዊ እውቀቱንም የሚገነባባት መርሆ ነች። እኛም በዚሁ አካሄዳቸው አርአያ አድርገን እንይዛቸዋለን ከቴያቸውንም እንከተላቸዋለን።

ይህ ኪታብ *(በጥቅሉ የሸይኹ ኪታቦች)* ከተከታዮቹ ምክንያቶች አንፃር ይለያል

- ግልፅና ቀላልነቱ
- (ከፅሁፉ የምንረዳቸውን) ቁምነገሮችን ከማስረጃቸው ጋር በመጥቀስ
- ቁምነገሮችን በቅደም ተከተላቸውና ቁጥር ካስቀመጠላቸው በኃላ ትንታኔ በመስጠቱ
- ፅሁፎቹን ለሚያነብም ሆነ ለሚያዳምጥ ሰው ዱዓ በማብዛቱ


የሶስቱ መሰረቶች ፍች

ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ መልኩ ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ማለት ነው።

- ጌታህ ማን ነው?
- ሃይማኖትህ ምንድን ነው ?
- ነብይህ ማን ነው?

ሶስቱን መሰረቶች በመማራችን የምናገኘው ፍሬ ምንድን ነው?

አንተኮ ሶስቱን መሰረቶች ከተማርክ፣ ከዚያም በስራ ላይ ካዋልካቸው፣ ከዚያም ወደነሱው ጥሪ ካደረግክ፤ ከዚያም በእወቀቱ፣ በስራው ላይና ጥሪ በማድረጉ ላይ ትእግስትን ከተላበስክ ለቀብር ጥያቄዎች -በአላህ ፍቃድ- ምላሽ ትሰጣለህ።


የሶስቱ መሰረቶች ፅሁፍ (ጥቅል) ማውጫ
ይህ ፅሁፍ ወደ አምስት ክፍሎች ይከፈላል። እነሱም
1.አራቱ ቁምነገሮች (ሱረቱ-ል ዓስር)
2 .ሶስቱ ቁምነገሮች (የተውሒድ ክፍሎች)
3. ተውሒድን የማስተማር አሳሳቢነት
4. ሶስቱ መሰረቶች (የቀብር ጥያቄዎች)
5. መደምደሚያ

1.አራቱ ቁምነገሮች

- እውቀት
- በሱው መስራት
- ወደሱው ጥሪ ማድረግ
- በዛው ላይ ለሚያጋጥም ጫና መታገስ

2.ሶስቱ ቁምነገሮች

- 1.[አላህ] በጌትነቱና በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነት
- 2. በአምላክነቱ ያለው አሃዳዊነት
- 3. ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች (በልቦና፣ በአንደበትና በአካል) መጥራራት

3.ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት

ተውሒድን ለምን እንማራለን? በሚለው ጥያቄ ላይ ምላሽ የተሰጠበት።

4. ሶስቱ መሰረቶች

ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ መልኩ ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ናቸው።

- ጌታህ ማን ነው?
- ሃይማኖትህ ምንድን
- ነብይህ ማን ነው?

5. ማጠቃለያ

የሸይኹ “ሰዎች ከሞቱ በኃላ ይቀሰቀሳሉ” ከሚለው እስከመጨረሻው።

በመጀመሪያ: አራቱ ቁምነገሮች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩሃ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው (1)

እወቅ–አላህ ይዘንልህና- (2) እነሆ አራት ቁመነገሮችን መማር ግዴታ ነው:

በመጀመርያ እውቀት: ያም አላህን ማወቅ፣ ነብዩን ﷺ ማወቅና ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ ነው።

ሁለተኛ: በሱው መስራት (3)".

(1) ሸይኹ ፅሁፉን በቢስሚላህ የጀመሩበት ምክንያት

- በአላህ መፅሃፍና በነብያቶች (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር
- ከሱ በፊት ፅሁፎቻቸውን በቢስሚላህ መጀመር ልምዳቸው በነበሩ ቀደምትና ዑለሞች ከመከተል አንፃር
- በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

(2) ቀደም ብለን እንደጠቆምነው ከአዘጋጁ ልምድ አንፃር ለእውቀት ፈላጊዎች ዱዓእ ማድረጉን መጀመሩ ነው። ይህ ደሞ የሚከተሉትን ጥቆማዎች ይሰጣል:

- የአህለ ሱና ወልጀማዓህ ዑለሞች በተማሪዎቻቸው ላይ ያላቸው እዝነት
- ዲነል ኢስላም በመሰረቱ በእዝነት ላይ የተገነባ ስለመሆኑ

እውቀት: ሲባል እውነትን በማስረጃው ማወቅ ማለት ነው፤ ተቃራኒው አላዋቂነት ነው።

(3) በእውቀትና በተግባሩ መካከል ስላለው ቁርኝት የሚከተለው ተብሏል: "እውቀት ተግባርን ጥሪ ያደርግለታል፤ ምላሽ ከሰጠው ይቀጥላል፤ አለበለዚያ ግን ይተወዋል።" ተግባር ያልተቆራኘው እውቀት ፋይዳቢስ ነው። ካወቀ ሊሰራ ግድ ይለዋል አለበለዚያ ግን የአይሁዶች ተመሳሳይነት አለበት። ምክንያቱም አይሁዶች እወቀቱም ቢኖራቸው ተግባሩ የላቸውምና {ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል።} (አል በቀራህ 146)

አስቀድሞ እሳት የምትቀጣጠልባቸው ሶስት ናቸው። ከነሱም ተምሮ እውቀት ያካበተ ዓሊም ሆኖ በሱም ያልሰራበት:

እውቀት ኖሮት በእውቀቱ ያልሰራበት ከጣኦት አምላኪ በፊት ቅጣቱ አለበት

[ወደ አላህ ለሚደረግ] ጥሪ የሚቆምበት ግዴታ የሆኑ መሰረቶችና ቅድመ መስፈርቶች አሉት፤ አሳሳቢ ከሚባሉትም፡

ጥሪው ጥርት ባለ መልኩ የአላህን ፊት ብቻ ተፈልጎበት ሊሆን ይገባዋል	ጥሪው ሸሪዓዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል	ጥሪው በጥበብ እና በትእግስት ሊሆን ይገባዋል	ጥሪ የሚደረግላቸውን ሰዎች ሁኔታ አሚልቶ የጠበቀ ሊሆን ይገባዋል	**ሶስተኛ:** ወደሱው ጥሪ ማድረግ


ለነዚህ ቅድመ መስፈርቶች ማስረጃው...

ከፍ ያለው አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡ **{«ይህች መንገዴ ናት። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን። ጥራትም ለአላህ ይገባው። እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም» በል።} (ዩሱፍ-108)**

«ይህች መንገዴ ናት... » ጥቆማው ነብዩ ﷺ ይዘውት የመጡትን ሸሪዓ የሚያመለክት ነው። "السبيل" ሲባል መንገዱን ነው።

«... ወደ አላህ እጠራለሁ... » ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርግ ሰው ሲባል ጥርት ባለ መልኩ የአላህን ፊት ፈልጎ ሰዎችን ወደ አላህ ለማድረስ የሚጣራው ነው።


«... በግልጽ ማስረጃ ላይ... » "በሲራ" ሲባል እውቀት ማለት ነው። እዚጋ የሚከተሉትን ማወቅን ያካትታል:



ሸይኹ እንዲህ ለማለት የፈለጉ ይመስላል፤ አውቀህ የምትሰራ ከሆንክ ነብዩ ﷺ ፣ ሶሓቦችና ቀደምት ደጋግ አበው በነበሩበት ልትጓዝ ይገባሃል፤ አላህ ያለው **{«ይህች መንገዴ ናት። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን።}** ነውና። ስለዚህም ጥሪ (ዳዕዋ) ማድረግ የግድ ነው።

አራተኛ: በዛው ላይ ለሚያጋጥም ጫና መታገስ፡ (1) ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: « **{በጊዜያቱ እምላለሁ። (1) ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው። (2) እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ። (3) » }** » **(አል ዓስር:1-3)** (2)

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና «ልክ ለነብያቶችና ለሩሱሎች እንደተከሰተባቸው ሁሉ ይህንን መንገድ ለሚከተልም አንዳንድ ጉዳዮች ይከሰቱበታልና ትእግስት የግድ ነው።» ለማለት የፈለገ ይመስል ከዳዕዋ (ወደ አላህ ጥሪ ማድረግ) በኃላ ትእግስትን ጠቀሰ።





(2) ሸይኹ አራቱን ቁምነገሮች ከጠቀሰ በኃላ ማስረጃቸውን ከቁርአን ጠቀሰ፤ ያም ሱረቱል ዓስር ነው። ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ቁመነገርን ባወሳ ቁጥር ማስረጃውንም አቆራኝቶ ያመጣል።

ለምን?

እውቀት ፈላጊን ከተጎታችነት ይልቅ (በማስረጃ) ተከታይነት ላይ ከመከትከት አንፃር	ተማሪው በተቃራኒዎቹ ላይ የሚመልስበት ማስረጃ ይኖረው ዘንድ	ተማሪው ሕግጋቶችን ከመሰረታዊ ማስረጃቸው ከማውጣጣት (ኢስቲንባጥ ከማድረግ) አንፃር ችሎታ ይኖረው ዘንድ

(1) አላህ ይዘንለትና ሃሳቡ ይህች ሱራ ብቻዋን ለፍጡራን ያውቁ፣ ይተገብሩ፣ ጥሪ ሊያደርጉና ሊታገሱ ዘንድ በቂ የሆነች ማሰረጃ ነች ነው።

እንዴት ነው ታድያ ከዚህ ሁሉ ሱራ ጋ ሲሆንስ? ቁርአን በሙሉው (ውዝር የማያሰጥ) ማስረጃ ነው።

(2) በሓዲሥ ዘርፍ የሙእሚኖች መሪ በሶሒሐል ቡኻሪይ ኪታቡ ላይ "ባብ: እውቀት ከንግግርም ከተግባርም ቀዳሚ ስለመሆኑ" ብሎ ርእስ ቋጠረለትና ማስረጃውንም ጠቀሰ። ስለዚህ ከንግግርም ከተግባርም በፊት እውቀት ቀዳሚ መሆኑ የማያወላዳ ነው።

ያለእውቀት መስራት ትክክል ሊሆን አይችልም፤ አለበለዚያ ከክርስትያኖች ጋር የሚመሳሰልበት ሆነ ማለት ነው።

ኢማሙ ሻፊዕይ -አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ይላሉ: "አላህ በፍጡራኖቹ ላይ ከዚች ሱራ ውጭ ማስረጃን ባያወርድ ኖሮ (ለተልዕኮው) በቂያቸው በሆነች ነበር።" (1)

ኢማሙል ቡኻሪይም -አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ይላሉ: "ባብ: እውቀት ከንግግርም ከተግባርም ቀዳሚ ስለመሆኑ" ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን።»** (ሱረቱል ሙሓመድ 19) ከንግግርም ከተግባርም እውቀትን አስቀደመ። (2).

ሁለተኛ: ሶስቱ ነጥቦች

አላህ ይዘንልህና እወቅ: እነሆ እነኝህን ሶስቱን ነጥቦች አወቆ በነሱው መስራት በሁሉም ወንድም ሆነ ሴት ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው። **(1)**

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ይህን የፅሁፉን ክፍል ለተማሪው ዱዓ በማድረግ ጀመረው። ሸይኹ አላህ ይዘንለትና በኡሱሉ ሠላሣህ ኪታቡ ለተማሪው ሶስት ጊዜ ዱዓእ ያደርግለታል፤ በመጀመሪያ በአራቱ ቁምነገሮች መንደርደሪያ፣ ከዚያም እዚሁ ሶስቱን ነጥቦች ሲጠቅስ፣ ሶስተኛው ደሞ በሚከተለው አረፍተ ነገር ውስጥ፤ "እወቅ: አላህን ለመታዘዝ ቅኑን ይምራህና፤ ቀና የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ እከ..."

ሶስቱን ነጥቦች ከማብራራታችን በፊት መንደርደሪያ

ተውሒድ

ከቋንቋ አንፃር: ወሐደ፣ ይወሒዱ፣ ተውሒደን ከሚል ስርወ ቃል የመጣ ሲሆን፤ "ወሐደ-ሸይእ" ሲባል ብቸኛ ማድረግን የሚጠቁም ቃል ነው።

ከሸሪዓ አንፃር: አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ብቸኛ በሆነባቸው በጌትነቱ፣ በአምልኮት እና በስምና ባህርያቱ መነጠል ማለት ነው።

ተውሒድ ወደ ሶስት ይከፈላል

ተውሒደ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ): አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በድርጊቶቹ ብቸኛ ማድረግ። ወይም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በመፍጠሩ፣ በንግስናውና በማስተናበሩ ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው።

ተውሒደል ኡሉሂያ (በአምልኮ አሃዳዊነቱ): አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ።

ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነቱ): አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ራሱን በኪታቡ ወይም በነብዩ ﷺ አንደበት በሰየመበትና በገለፀበት መልኩ ብቸኛ ማድረግ። ይህም ከተሕሪፍ (ማዛባት)፣ ከተዕጢል (ውድቅ ማድረግ) ፣ ከተክይፍ (ዝርዝር ሁኔታ ሳንሰጥ) እና ከማመሳሰል ውጭ በሆነ መልኩ ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅ፣ ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ነው።

*ስምና ባህርያቱን በማስመልከት በቁርአንና በሓዲሥ በመጣው የምንገደብበት ተውቂፍይ (እገዳ የተጣለበት) ነው። ይህም የሚሆነው:

አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ራሱን በኪታቡ ወይም ነብዩ ﷺ ለአላህ ያፀደቁትን በማፅደቅ እና...

አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ በኪታቡ ከራሱ ያወገዘውን ወይም ነብዩ ﷺ ከአላህ ያወገዙትን በማውገዝ ነው። ለምሳሌ: « {... ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።...} (አል-በቀራህ 255) {... ድካምም ምንም አልነካንም።...} (ቃፍ 38) »

ይህም ከተሕሪፍ (ማዛባት)፣ ከተዕጢል (ውድቅ ማድረግ) ፣ ከተክይፍ (ዝርዝር ሁኔታ መስጠት) እና ከማመሳሰል ውጭ በሆነ መልኩ ነው።

የመጀመሪያው ነጥብ: አላህ እኛን ፈጠረን፣ ሲሳይም ለገሰንና እንዲሁ በከንቱ አልተወንም፤ ይልቅ መልእክተኛ ላከልን፤ እሱን የታዘዘ ጀነት ገባ፤ እሱን ያመፀውም ጀሀነም ገባ። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:
« {እኛ በእናንተ ላይ መስካሪ መልዕክተኛን ወደእናንተ ላክን። ወደ ፈርዖን መልዕክተኛን እንደላክን። (15) ፈርዖንም መልክተኛውን አመጸ፤ ብርቱ መያዝንም ያዝነው። (16)} » (አል-ሙዘሚል 15-16). (1)

“የሶስቱ ነጥቦች” ማጠቃለያ

- አንደኛው ቁምነገር: ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ) እና ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (የስምና ባህርይ አሃዳዊነቱ)
- ሁለተኛው ቁምነገር: ተውሒዱል ኡሉሂያ (አምልኳዊ አሃዳዊነቱ)
- ሶስተኛው ቁምነገር: ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና በመጀመርያዋ ቁምነገር የጌትነት አሃዳዊነቱንና የስምና ባህርይ አሃዳዊነቱን (በሚከተለው መልኩ) አፀናባት፤ “አላህ እኛን ፈጠረን፣...” ሲል አል-ኻሊቅ (ፈጣሪ መሆኑን) ፤ “ሲሳይም ለገሰን” ሲል አር-ረዛቅ (ሲሳይ ለጋሽ) ፤ “እንዲሁ በከንቱ አልተወንም...” ትእዛዝና ክልከላ የሌለባቸው ከንቱዎች (አላደረገንም)፤ “ይልቅ መልእክተኛ ላከልን” ።

አላህ መልዕክተኞችን (ዓለይሂሙ ሰላም) የመላኩ አላማ

- በፍጡራኖች ላይ ሑጃ [ተልዕኳዊ ማስረጃ] ከማቆም አንፃር፤ «{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።}» (አል-ኢስራእ 15)
- ከርህራሄ አንፃር: « (ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።) » (አል-አንቢያእ 107)

ሁለተኛው ነጥብ: አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም፤ ቅርብ መላኢካም ሆነ የተላከ ነብይም እንኳ ቢሆን (እንዲጋራው አይፈልግም)፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:

« {እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ። } » (አል-ጅን 18)

በሁለተኛዋ ቁምነገር አምላክነትን ለአሏህ ማፅደቅን ይዛለች:

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና "አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም" ፤ ይህ አገላለፅ በዓረብኛው ያለው የቃላት አሰካክ በዓረብኛው የስዋሰዋዊ ህግ መሰረት እያንዳንዱን ከሱ ውጭ ያለውን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። ነብይ፣ ወልይ፣ ጅንይ፣ መላኢካ፣ ደግ ሰው፣ ሌላ ሌላም የሆነ ይሁን (የሚያጠቃልል ነው) ።


ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **« {እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)።} »** (አል-ጅን 18)

"...المَساجِدَ..."ወይም "... መስጊዶችም... " የተባለውን በማስመልከት ሶስት የተለያየ ግን ማስማማት የሚቻል (የ ዑለሞች) ቃል አለ:

አላህ እንዲመለክበት በሚል የተገነቡ መስጅዶች	የሱጁድ አካላቶች	መሬት ; "መሬት (በሙሉ) መስጅድና ንፁህ ተደረገችልኝ" (ቡኻሪይ)

{... የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)።}(አል-ጅን 18)
"...አንድንም..." ወይም "...أَحَدًا" ሲል ይህም አገላለፅ በዓረብኛው ያለው የቃላት አሰካክ በዓረብኛው የስዋሰዋዊ ህግ መሰረት ከሱ ውጭ ያለውን በሙሉ እያንዳንዱን የሚያካትት ነው። ለዚህም ነው ኢማሙ አላህ ይዘንላቸውና በሁለተኛዋ ቁምነገር መንደርደርያ "አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም" ያለው። ማለትም ማንም ይሁን: ነብይም፣ ወልይም፣ ጅንይም ይሁን ሷሊሕ።

ሶስተኛዋ ቁምነገር ላይ አላህ ይዘንለትና ሸይኹ ከሽርክም ሆነ ከሽርክ ሰዎች መጥራራት ግዴታነቱን ግልፅ አደረገ።



1. **በልቦና**: ካፊሮችን፣ በዓላቸውንም ሆነ ሌሎች ዝግጅቶቻቸውን በተለይም እነሱ ዘንድ የሚገኙ ሽርክና ቢድዓዎቻቸውን ልትጠላ ነው።

2. **በአንደበት**: {«እኔ ከምትግዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ፡፡»} (ዙኽሩፍ 26)

{በላቸው «እናንተ ኩሓዲዎች ሆይ! (1)«ያንን የምትግዙትን (ጣዖት አሁን) አልግዛም፡፡(2) «እናንተም እኔ የምግዛውን (አምላከም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም፡፡(3) «እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም፡፡(4) «እናንተም እኔ የምግዛውን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም፡፡(5) «ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ፡፡ ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ፡፡(6)}» (አል-ካፊሩን 1-6)

3. **በተግባር**: የእምነት መገለጫቸው በሆኑ ክብረ በአላቶቻቸውም ይሁን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶቻቸው ወይም በአለባበሳቸው ባለመጋራት የሚሆን ነው።

ሶስተኛው ነጥብ: መልእክተኛውን ﷺ የታዘዘና የአላህን አሃዳዊነት ያፀደቀ ሰው አላህንና መልእክተኛውን ﷺ የሚከራከሩትን ሰዎች የቅርብ ቅርብ እንኳ ቢሆኑ ሊወዳጅ አይፈቀድለትም። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:

«በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም። እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል። ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል። ከሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ያገባቸዋል። አላህ ከእነርሱ ወዷል። ከእርሱም ወደዋል። እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው። ንቁ! የአላህ ሕዝቦች እነርሱ ምኞታቸውን የሚያገኙ ናቸው።» (አል-ሙጃደላህ 22)

ሶስተኛ: ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት

አላህ ለታዛዥነቱ ቀናውን ይምራህና እወቅ ሐኒፍ የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ እኮ:

አምልኮህን ጥርት አድርገህ አላህን ልትገዛው ነው፤ አሏህ የሰው ልጆችን በሙሉ ያዘዘበትና የፈጠረበት አላማም ለዚሁ ነው። ልክ አላህ በሚከተለው መልኩ እንዳለው: « **{ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።}** » **(ዛርያት 56) (1)** "لِيَعْبُدُونِ" ወይም **"ሊግገዙኝ"** ሲል (በአምልኮ) ብቸኛ ሊያደርጉኝ ማለት ነው። (2)

አላህ ያዘዘበት ትልቁ ጉዳይ ተውሒድ ሲሆን ያም አላህን በአምልኮ ብቸኝነቱን ማረጋገጥ ነው። **(3)** አላህ የከለከለው ትልቁ ጉዳይ ደግሞ ሽርክ ነው፤ ያም አንዳች ነገር ከአላህ ጋ መጣራት ማለት ነው።

ሐኒፊያ

ከቋንቋ አንፃር: "الحنف" ወይም "አል-ሐነፍ" ከሚለው የመጣ ሲሆን ትርጉሙም መዘንበል ማለት ነው።

ከሸሪዓ አንፃር: ከሸሪዓ አንፃር ደግሞ ሸሪካ ከማድረግ ይልቅ ወደ ኢኽላስ፣ ተውሒድና ኢማን ያዘነበለች መንገድ ናት። **«...ለአላህ ታዛዥ ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘንባይ...»** (ነሕል 120) ማለትም ወደ አላህ ተቅጣጭቶ ለሽርክ ጀርባውን የሰጠ ማለት ነው። "الحنيف" ሁልጊዜም ወደ ተውሒድ እየተመለሰ ከሽርክ የሚርቅ ነው።

(3) እዚጋ ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ተውሒድን ለምን እንደምንማር ያብራራልናል፤ አሳሳቢነቱንም ቀደም ብለን ጠቅሰናል።

ቀደም ብለን በመግቢያው ላይ እንደጠቀስነው የተውሒድ ፍች

ከቋንቋ አንፃር: ወሐደ፣ የወሒዱ፣ ተውሒደን ከሚል ስርወ ቃል የመጣ ሲሆን፤ "ወሐደ-ሸይእ" ሲባል ብቸኛ ማድረግን የሚጠቁም ቃል ነው።

ከሸሪዓ አንፃር: ከሸሪዓ አንፃር: አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ብቸኛ በሆነባቸው በጌትነቱ፣ በአምልኮት እና በስምና ባህርያቱ መነጠል ማለት ነው።

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና « لِيَعْبُدُونِ ወይም "ሊግገዙኝ"» ሲል (በአምልኮ) ብቸኛ ሊያደርጉኝ ማለት ነው።" ይላል፤ ይህ ደሞ ኢብኑ ዓባስ ረድየሏሁ ዓንሁማ እንደሚከተለው ያሉት ንግግር ነው። "አምልኮ ሁሉ በቁርአን ትርጉሙ ተውሒድ ነው።" **"واعبدوا الله"**(النساء ٣٦) **"... አላህን አምልኩ..."**(አን-ኒሳእ 36) ማለትም "... ብቸኛ አድርጉት..." **"እናንተ ሰዎች ሆይ!... ጌታችሁን ተገዙ"** (አል-በቀራ 21) "... እናንተ ሰዎች ሆይ! ...በብቸኝነት ተገዙ" ማለት ነው።

አራተኛ: ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ሶስት የቀብር ጥያቄ ይዘት ያላቸውን ሶስቱን መሰረታዊ መርሆዎች በመግለፅ ጀመረ፤ (አስቀድሞ) የኡድማጭን ወይም የአንባቢን ትኩረት በጥያቄ ካነቃቃ በኃላ ምላሹን ሰጠ።

(2) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና አምልኮ የሚገባው ጌታ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን በመግለፅ የመጀመርያውን መሰረት አብራራ፤ ማስረጃውንም ተከታዩን የቁርአን አንቀፅ ጠቀሰ: «ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1) የሚመለከው ደሞ ጌታ ነው።

"የሰው ልጅ ሊያውቃቸው ግድ የሚሉ ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ምንና ምን ናቸው?" ከተባልክ እንዲህ በል፡
"አንድ ባርያ ጌታውን፣ ዲኑንና ነብዩ ሙሐመድን ﷺ ማወቁ ነው።" **(1)**
«ጌታህ ማን ነው? » ከተባልክ "ጌታየ ያ በፀጋው እኔንም የተንከባከበኝ መላው አለምንም የሚንከባከበው አሏህ ነው፤ እሱኑ ነው የማመልከው ሌላ የማመልከው የለኝም።" በል። ማስረጃውም ከፍ ያለው አላህ በሚከተለው መልኩ ያለው ነው: «ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1) **(2)**
ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ (በአንቀፁ ላይ በተገለፀው) ዓለም (ውስጥ የሚካተት) ነው። እኔም የዚህ አለም አንዱ ነኝ። **(3)**.

«ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1)

ይህች አንቀፅ ሶስቱንም የተውሒድ አይነቶችን አካታለች

«"الحمد"ምስጋና" ...» ተውሒዱል አስማእ ወሲፋትን(በስምና ባህርያቱ ያለውን አሃዳዊነት) ይዟል	« "الله" "ለአላህ ይገባው"...» ተውሒዱል ኡሉሂያ (በአምልኮ አሃዳዊነቱ)ን ይዟል	«"ربّ" "የዓለማት ጌታ ለሆነው"...» ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱን) ይዟል

(3) ማለትም ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ ፍጡር ነው፤ ፍጡር እስከሆንክ ድረስ ደሞ ጥራት ይገባውና በጎ የዋለልኝን ፈጣሪ ምስጋና ላቀርብለት የግድ ነው።

“ጌታህን በምን አወቅክ?” ብትባል “በምልክቶቹና በፍጥረታቱ” በል። ከምልክቶቹም ሌሊትና ቀን፤ ፀሀይና ጨረቃ፤ ከፍጥረታቱ ደሞ ሰባቱ ሰማያት፣ ሰባቱ ምድሮች በውስጣቸውም ያለው በመካከላቸውም ያለው ይገኝበታል።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው።: «ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው። ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ። ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ። ። እርሱን ብቻ የምትግዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)።» (ፉሲለት 37) እንዲሁም ተከታዩ ቃሉ: «ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው። ከዚያም በዐርሹ ላይ ተደላደለ። (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል። ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)። ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው። የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ።» (አል አዕራፍ 54) **(1)**.

የሚመለከው ጌታ ነው፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።(21) (እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው። እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።» (አል በቀራህ 22) **(2)**.

ኢብኑ ከሢር አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ “እነኝህን የፈጠረ ለአምልኮ ተገቢ የሆነው እሱው ነው።” **(3)**.

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ወደ አምላክ ህልውና ጠቋሚ የሆኑ አለማዊ ምልክቶችንና ፍጥረታትን ማውሳት ጀመረ፤ ከአላህ ውጭ ጌታ፣ ፈጣሪም ተመላኪም እንደሌለ የሚያፀኑ ምልክቶችን። ቀደም ብለን በመግቢያው ላይ እንዳወሳነው ለነዚህም ከቁርአን ማስረጃዎችን አጣቀሰ።

እያንዳንዱ ፍጥረት ጥራት ይገባውና ከፍ ወዳለው አምላክ ህልውና ጠቋሚ የሆነ ምልክት ነው። ነገር ግን ሸይኹል ኢስላም ሙሐመድ ቢን ዓብዱል ወሃብ አላህ ይዘንለትና በፍጥረታትና በ(ተአምራዊ) ምልክቶች መካከል ልዩነትን በሚጠቁም መልኩ ገለፃቸው፤ ምክንያቱም ልክ እንደ ቀንና ሌሊት መፈራረቅ አይነት “አል-አያህ (ተአምራዊ ምልክቶች)” ይለዋወጣሉና ነው፤ የሚለዋወጥ ደሞ ከማይለዋወጠው በላይ የበረታ ጥቆማ ሰጭ ነው።

(2) ይህች አንቀፅ ሱረቱል በቀራህ ላይ የምትገኝ አንቀፅ ነች፤ ስለዝች አንቀፅ አንዳንድ ዑለሞች በቁርአን የመጀመርያው ጥሪ «እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! ...» የሚለው እንዲሁም የመጀመርያው ድርጊታዊ ትእዛዝ «...ተገዙ...» ማለትም “ብቸኛ አድርጉ” የሚለው በአንቀጿ ላይ እንዳለ ያፀናሉ። «(...እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።» በሚል ከሸርከ የሚከለከለው የመጀመሪያው ክልከላም በአንቀፁ ላይ እንዳለ ሁሉ።

(3) በጌትነቱ አሃዳዊነት የፀደቀለት በአመልኮም አሃዳዊነቱ ሊፀድቅለት ይገባል።

ሸይኹ ከኢብኑ ከሢር ቃል በኃላ ልቦናዊና አካላዊ የሆኑ የአምልኮ አይነቶችን ለእያንዳንዱ ተግባር በሚከተለው መልኩ ከማስረጃዎቻቸው ጋ በማውሳት አስከተለ፤



አላህ ያዘዘባቸው የሆኑ የአምልኮ አይነቶች (1) እንደ ኢስላም፣ ኢማን(እምነት)፣ ኢሕሳን፣ እንዲሁም ዱዓእ፣ ፍርሃት(ኸውፍ)፣ ተስፈኝነት፣ መመካት፣ መከጀል(አር-ረግባህ)፣ መሸሽ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ)፣ መተናነስን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ)፣ እውቀት ላይ የተመረኮዘ ፍርሃት(አል-ኸሸየህ)፣ ተፀፅቶ መመለስ፣ እገዛን መሻት፣ ጥበቃን መሻት፣ ከጭንቅ ገላጋይን መሻት፣ እርድ ማቅረብ፣ ስለትና ሌሎችም አላህ ያዘዘባቸው የሆኑ የአምልኮ አይነቶች ሁሉ ለአለማት ጌታ ለአላህ የሚገቡ ናቸው። ማስረጃውም: «እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፡፡ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)፡፡» (አል-ጅን 18).

ከነዚህም አንዲትስ`ኳ ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሰጠ ሙሽሪክና ካፊር ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: « {ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው ምርመራው እጌታው ዘንድ ብቻ ነው፡፡ እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም፡፡} » (አል-ሙእሚኑን 117) በሓዲሥም ‘‘ዱዓእ የአምልኮ አስኳል ነው። ’’ የሚል ይገኝበታል።ከፍ ያለው አላህም እንዲህ ይላል: «{ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡}» (ጾፊር 60)



ይህ ተጠሪ በፍጥረተ አለሙ ላይ ድብቅ እንቅስቃሴ እንዳለው፣ ጥቅምን ሊያመጣ ወይም ክፋትን ሊያስቀር የሚችል ተደርጎ የሚታመን ከሆነ ግን ይህ ሽርክ ይሆናል።

ል. በ: እየተማርን ያለነው ፍርድ ስለድርጊቱ ነው እንጅ በድርጊቱ ፈፃሚ ላይ ስላለው ፍርድ ግን ሑጃ (ማስረጃ) ሊቆምለትና (ፍርዱን ከመስጠት) የሚያቅብ ነገር ሊወገድ ይገባዋል።

ድርጊት ፈፃሚው ላይ አማኝ ነው ካፊር የሚለውን ፍርድ መስጠት የሚችሉት ዑለሞች ናቸው።

ሰበቦችን በማስመልከት ሰዎች ያላቸው እምነት ወደ ሶስት ይከፈላል

ጥራት ይገባውና አላህ ሰበብ ያደረገውን ነገር እንደሰበብነቱ የሚያምኑም እንደሰበብም አድርገው የሚይዙት፤ ይህ **ትክክለኛው** ነው።

ጥራት ይገባውና አላህ ሰበብ ያላደረገውን ነገር እንደሰበብ የሚያምኑና እንደሰበብም አድርገው የሚይዙት፤ ይህ **ትንሹ ሽርክ** ነው።

ሰበብን በራሱ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችልና ጥቅም መምጣቱም ክፋት መወገዱም በሱው እንደሆነ አድርገው የሚያምኑ፤ ይህ **ትልቁ ሽርክ** ነው።

ሸሪዓዊ ሰበቦች

ሸሪዓውን የጠበቀ ሩቃን ይመስል፤ አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ህመምን ለማስወገድ ሩቃን ሸሪዓዊ ሰበብ አድርጎታል።

ግኡዝ ሰበቦች:

መድኃኒቶች አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ለፈውስ ሰበብ አድርጎታል።

"ዱዓእ የአምልኮ አስኳል ነው።" የሚለው ሓዲሥ ዶዒፍ ቢሆንም "ዱዓእ ራሱ አምልኮ ነው።" የሚል ሌላ የነብዩ ﷺ ሶሒሕ ሓዲሥ አለ።

ዱዓእ ራሱ አምልኮ እንዴት ሊሆን ይችላል?

«{ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሽነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡}» **(ጋፊር 60)** የሚለው አንቀፅም ለዚህ ጥቆማ ይሰጣል። ጥራት ይገባውና «...መግገዛት...» ብሎ ነው የጠራው፤ ይህ ደሞ የዱዓእን ዒባዳነት ጠቋሚ ነው።

ለኸውፍ (ፍርሃት/ሲባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...አትፍሩዋቸውም:: ምእምናንም እንደኾናችሁ ፍሩኝ። » (አሊ ዒምራን 175) **(1)**.

ለተስፈኝነት (ሲባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ:: በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው::» (አልከህፍ 110) **(2)**.

(1) ፍርሃት (ኸውፍ): ሊያጠፋ ወይም ሊጎዳ የሚችል ነገር ይከሰታል በሚል ስጋት የሚመጣ ስሜት ነው።

ጥራት ይገባውና አሏህ የሸይጧን ጓዶችን መፍራት ከልከሎ እሱን ብቻ እንድንፈራው አዟል።



(2) ረጃእ (ተስፈኝነት): ለማግኘቱ ቅርብ የሆነን ወይም ሩቅም ቢሆን የቅርቡን ያክል ቦታ ለሚሰጠው ነገር ያለ ልባዊ ፍላጎት።

መተናነስና ራስን ማዋረድን የታከለበት ተስፋ ጥራት ይገባውና ለአላህ እንጅ አይገባም፤ ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ ሽርኩን አክበር ላይ የሚመደብ ነው።

የሚወደስ የሆነ ተስፋ የሚጣልበትም ለአላህ ትእዛዝ ታዛዥ ሆኖ ምንዳውን ተስፋ ላደረገ አልያም ከወንጀሉ ተፀፅቶ ተመልሶ መፀፀቱን ተቀባይነት ማግኘቱን ተስፋ ላደረገ ነው። ስራ ያልታከለበት ተስፋ ግን ራስን መሸንገልና ከንቱ ምኞት ነው።



ለተወኩል (መመካት/ሚባዳ መሆን) ማስረጃው: **«ምእመናንም እንደኾናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ»** (አል-ማኢዳህ 23) እንዲሁም: **«በአላህምላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው።»** (ጦላቅ 3) **(1)**.

ለ አር-ረግባህ (መከጀል)፣ **(2)** መሸሸ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ) እና **(3)** ራስን ማዋረድን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ) **(4)** ማስረጃቸው: **«{...እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ። ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ።»** (**አል-አንቢያእ 90**) **(2)**

(2) መከጀል (አር-ረግባህ): ተወዳጅ ወደሆነው ነገር ለመድረስ መውደድ

(3) መሸሸ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ): ከድርጊት ጋ የተቆራኘ ከሚፈራው ነገር የሚያርቅ ፍርሃት ነው።

(4) ራስን ማዋረድን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ): ለአላህ ሸሪዓዊም ይሁን ዓለማዊ ለሆነ ፍርዱ እጅን በሰጠ መልኩ ለአላህ ልቅና ማጎብደድና መዋራድ ማለት ነው።

◆ ወደ አላህ መንገድ የገባ ሰው በሚያጠፋው መልኩ አንዱን ካንዱ ሳያስበልጥ ፍርሃትንና ተስፋን ሊሰንቅ ይገባዋል፤ ፍርሃትም ተስፋም እንደ ሁለት ክንፍ ሁነው እሱ ዘንድ ሊኖሩ ግድ ነው።

አል-ኽሽየህ (ሲባዳ ስለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...አትፍሯቸውም፤ፍሩኝም...» (አል-በቀራህ 150) **(1)** (ወደ አላህ ተፀፅቶ) መመለስ (ሲባዳ ስለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ።» (አል-ዙመር 54) **(2).** እገዛ መሻት (ሲባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡ ፡» (አል-ፋቲሓ 5) በሐዲሥም ተከታዩን እናገኛለን "እገዛን ከፈለግክ በአላህ ታገዝ።" (ቲርሚዚይ)**(3)** ጥበቃ መሻት (ሲባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ።» (አል-ፈለቅ 1) እንዲሁም «በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ።» (አን-ናስ 1) **(4)** ኢስቲቻዛ (ከጭንቅ ገላጋይን መሻት/ሲባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «ከጌታችሁ እርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ... ለናንተ የተቀበላችሁን (አስታውሱ)።»(አል-አንፋል 9) **(5)** ለእርድ (ሲባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:: ««ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል። (162«ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)።» (አል-አንዓም 162-163). ከሐዲሥም "**ከአላህ ውጭ ላለ አካል(ታላቅነት ብሎ) ያረደ በአላህ ተረግሟል።**" (ሙስሊም) **(6).**

(1) አልኽሽየህ (እውቀት ላይ የተመሰረተ ፍርሃት): የሚፈራውን አካል ታላቅነትና የስልጣን ሙሉነት በማስመልከት እውቀት ላይ የተመረኮዘ ፍርሃት ነው።

(2) (ወደ አላህ) መመለስ: ትእዛዛቱን በመፈፀምና ክልከላውን በመቆጠብ ወደ አላህ መመለስ፤ «...وَأَنِيبُوا...» «...**ተመለሱ**...» «...ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ።» (አል-ዙመር 54) ማለትም ጉዳይህን ለአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ በመስጠት፤ ምክንያቱም ባርያ ነህና ባርያ ደሞ ለጌታው (እጅ እግሩን) ሊሰጥ ግድ ነው። ጌታው ደሞ አላህ ነው። ልክ ነብዩ ﷺ በሚከተለው መልኩ እንዳሉት "ጌታ አላህ ነው።"

(3) እገዛን መሻት(አል-ኢስቲዓናህ): እገዛ መፈለግ ማለት ነው። « {አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።» (አል-ፋቲሓ 5) በዚህ አንቀፅ የዓረብኛው አገላለፅ በስዋስዋዊ ህጉ መሰረት ገደብ የሚያስቀምጥ አገላለፅ ነው **{تقديم ما حقه التأخير يفيد الحصر}** እንደሚባለው ማለት ነው። ማለትም አንገዛም አንተን ቢሆን እንጅ፤ እርዳታን አንለምንም አንተን ቢሆን እንጅ ማለት ነው።

(4) ጥበቃን መሻት: መጠበቅን መፈለግ ማለት ነው። ያ ማለት ከሚሸሽ ነገር ከለላ መፈለግ «أعوذ» «**አዑዙ**» ማለት "እጠበቃለሁ፣ እከለላለሁ" ማለት ነው።

(5) አል-ኢስቲቻዛህ (ከጭንቅ የሚገላገልን መሻት): ከጭንቅና ከውድመት መዳንን መፈለግ ማለት ነው።


✪ አራቱን: እገዛን መሻት፣ ጥበቃን መሻት፣ ከጭንቅ ገላጋይን መሻትና አማላጅነት(ሽምግልና) አራት መስፈርቶች ከተሟሉባቸው ከፍጡራኖች መፈለግ የተፈቀዱ ናቸው፤ በህይወት ካለ ሊሆን ይገባል፣ ያለና የቀረበ ሊሆን ይገባል፣ ቻይ ሊሆን ይገባዋል እና ሰበብ ተደርጎ ሊያዝ ይገባዋል።

(6) እርድ ማቅረብ: ለየት ባለ መልኩ ደም በማፍሰስ ህይወት መቅጠፍ።




ስለት (ሲባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «(ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ። መከራው ተሰራጪ የኾነንም ቀን ይፈራሉ።» (አል-ኢንሳን 7)

ል. በ.: እርድን በማስመልከት ተጨማሪ ማብራሪያ በአላህ ፍቃድ ኪታቡ ተውሒድ ላይ ይመጣል።



ል. በ.: ስለት ዝርዝሩ በአላህ ፍቃድ ወደፊላ ኪታቡ ተውሒድ ላይ የሚመጣለት የሆነ ዓይነት፣ ቅድመ መስፈርቶችና ማሰረዣ(ከፋራ) አለው።



ሸይኹ እነኝህን የሲባዳ አይነቶች መጥቀሱ ከመገደብ አንፃር ሳይሆን እንደምሳሌ ነው ምክንያቱም ያልተወሱ በርካታ የሲባዳ አይነቶች አሉና። ጭብጡ ሃሳብ ከነዚህ ሲባዳዎች መካከል አንዳች ነገር ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ በርግጥም ትልቁን ሽርክ ፈፅሟል ነው።

ሁለተኛው መሰረታዊ መርሆ: ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ (ነው)። ያም ለአላህ በተውሒድ እጅ እግርን መስጠት፣ በታዛዥነት ለሱ ተጎታች መሆን፣ ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት።

ሶስት እርከኖች አሉት: ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን፤ እያንዳንዱ እርከንም ማእዘን አለው።

የመጀመርያው እርከን: ኢስላም **(1)**

የእስልምና ማእዘናት አምስት ናቸው። የ "ላ ኢላሀ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱለሏህ" የምስክርነት ቃል **(2)** ፣ ሶላትን ስርአቷን አሟልቶ መስገድ፣ ዘካን ማውጣት፣ ረመዷንን መፆምና የአላህን ቤት ሓጅ ማድረግ ናቸው።


(1) ሸይኹ ሁለተኛው መሰረት ላይ ወጣ፣ ያም አንድ ባርያ ዲኑን ማወቁ ነው። በሚከተለው መልኩ ዲነል ኢስላምን ማስተዋወቅን ጀመረ:

የመጀመርያው እርከን ኢስላም

ያም ለአላህ በተውሒድ እጅ እግርን መስጠት፣ በታዛዥነት ለሱ ተጎታች መሆን፣ ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት።

"ኢስላም" ለሚለው ቃል ፍቹ ይህ ነው፤ ጉዳይህን ለአላህ ልትሰጥ ማለት ነው። ምክንያቱም ባርያ ነህና ባርያ ደሞ ለጌታው (እጅ እግሩን) ሊሰጥ ግድ ነው። ጌታውም አላህ ነው። ልክ ነብዩ ﷺ "ጌታ አላህ ነው።" እንዳሉት ማለት ነው።

ከዚያም ዲንን ወደ ሶስት እርከን ከፈሉት:



(2) የእስልምና ማእዘናት አምስት ናቸው። የመጀመሪያው

የ "ላ ኢላሀ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱለሏህ" የምስክርነት ቃል ነው።

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና “ላ ኢላሀ ኢለሏህ” ን የምስክርነት ቃል ማስረጃ አድርጎ ጠቀሰ፤ ትርጉሙንም አብራራ። ያም: “ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም” ማለት ነው።

የኢኽላስ ምስክርነት ተከታዮቹን ልታካትት ግድ ነው

- ማውገዝ
- ማፅደቅ

“ላ ኢላሀ” በሚለው ቃል “ነፍይ” የምንለው ወይም ደሞ ማውገዝ ይገኝበታል

“ኢለሏህ” በሚለው ቃል ደሞ “ኢሥባት” የምንለው ወይም ደሞ ማፅደቅ ይገኝበታል

ይህ አይነቱ አገላለፅ መገደብንና ማፅደቅን ይጠቁማል። ምክንያቱም ሒባዳን በተገደበ መልኩ ለአላህ ብቻ በማፅደቅ ከሌላው የሚያጠራ አገላለፅ ነውና።

ለዚህም ነው ሸይኹ አላህ ይዘንለትና “ግልፅ የሚያደርጋት ማብራሪያዋ በማለት (ቀጣዩን አንቀፅ ያስከተሉት): **«ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።» (26) «ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልግገዛም)።...»**

«...ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።...» “ላኢላሀ” ማለት ሲሆን

«...ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር...» ማለት ደሞ “ኢለሏህ” ማለት ነው።

ለሸሃዳህ (የምስክርነት ቃል) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»** (አሊ ዒምራን 18)

ትርጉሙም: “ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም።”

“ላ ኢላሀ”: ከአላህ ውጭ የሚመለከውን በሙሉ ታወግዛለች፤

“ኢለሏህ”: አምልኮን ለአላህ ብቻ በአምልኮ ተጋሪ በሌለው መልኩ ያፀድቃል፤ በንግስናውም ተጋሪ እንደሌለው ሁሉ።

ግልፅ የሚያደርጋት ማብራሪያዋ ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«{ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ፡ ፡»(26) «ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልግገዛም)። እርሱ በእርግጥ ይመራኛልና።» (27) በዝርዮቹም ውስጥ ይመለሱ ዘንድ (ባንድ አምላክ ማመንን) ቀሪ ቃል አደረጋት። (28)»**(ዙኽሩፍ 26-27)

እንዲሁም: «የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።» (አሊ-ዒምራን 64) **(1)**

የሆነ ሰው "የ 'ላኢላሀ ኢለላህ' ትርጉም 'ላ መዕቡደ ኢለላህ/ከአላህ ውጭ የሚመለክ የለም' ማለት ነው።" ቢልስ? እኛም እንለዋለን "ይህ አገላለፅ ስህተት ነው።" እንለዋለን። ምክንያቱም በዚህ አገላለፁ መሰረት ከአላህ ውጭ የሚመለከውን በሙሉ ትክክል እያደረገ ነውና። ነገር ግን "...በእውነት የሚመለክ..." በሚለው አገላለፅ ከአላህ ውጭ በሚመለኩት እንደካደ እና ከአላህም ውጭ **በእውነት** የሚመለክ እንደሌለ ግልፅ ያደርጋል።

"የ 'ላኢላሀ ኢለላህ' ትርጉም 'ከአላህ ውጭ በእውነት ጌታ የለም' ማለት ነው።" ቢልስ?

እኛም እንለዋለን "ይህ ንግግር ትክክል ነው፤ ነገር ግን የ 'ላኢላሀ ኢለላህ' ትርጉም አይደለም። ይህ ተውሒዱ ሩቡቢያ ነው፤ ይህ ደሞ ነብዩ ﷺ የተላኩባቸው ሙሽሪኮች የሚያፀድቁት ግን ደሞ እስልምና ውስጥ ያላስገባቸው አቋም ነው።"

(1) «የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ።...»
አንቀፁ በሃይማኖቶች መካከል ማስማማት የሚባለው ውድቅ እንደሆነ ያስይዘናል።

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ይህን አንቀፅ ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ለመሆናቸው ማስረጃ አድርጎ ጠቀሰ፤ በአንቀፁ ላይ አላህ መልእክተኝነታቸውን በቋንቋዊ ህጉ መሰረት ሶስት ማጠናከሪያ ሊባል በሚችል አገላለፅ ነው ያፀናላቸው።

(2) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና የ "ሙሓመደን ረሱሉሏህ" የምስክርነት ቃል ትርጉም አብራራ: ይህ የምስክርነት ቃል ትክክለኛ ይሆን ዘንድ በእያንዳንዱ ወንድም ሆነ ሴት ሙስሊም ተከታዮቹ ነጥቦች ግዴታ ናቸው:

መልእክተኛው ﷺ ባዘዙበት መታዘዝ፣ የተናገሩበት እውነት ብሎ መቀበል፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉት መራቅና እሳቸው በደነገጉት መልኩ እንጅ አላህ ላይመለክ የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና።

ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ለመሆናቸው ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«ከነሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ።።»** (አት-ተውባህ 128) **(1)**

"ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ነው" የሚለው የምስክርነት ቃል ትርጉም: ባዘዙት መታዘዝ፣ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉት መራቅ እና እሳቸው በደነገጉት መልኩ እንጅ አላህ ላይመለክ ማለት ነው። **(2)**

ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር "የሚመለኩ ሳይሆን የሚያመልኩ ባርያ እና የማያስተባብሏቸው መልእክተኛ ናቸው" ብሎ ማመን ነው ይህ ሲባል፡

- የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና ባዘዙት ሁሉ ልንታዘዛቸው፤ ምክንያቱም ከአላህ የሚያደርሱ ልኡክ ናቸው
- የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፤ እውነተኛና እውነት የሚባሉ ናቸው
- ያስጠነቀቁትንና የከለከሉትን መራቅ፤ ነብዩ ﷺ የከለከሉትን በአንድ በኩል አድርገህ አንተ በሌላኛው በኩል ልትሆን
- ጥራት ይገባውና አላህ ላይመለክ ነው ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ ቢሆን እንጅ፤ በዚህ ደሞ ለሙብተዲያች ረድ (አፀፋዊ ምላሽ) አለበት።

ለሶላትና ለዘካት እንዲሁም የተውሒድ ተፍሲር ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «**አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።።**» (አል-በይናህ 5) (1)

ለፆም ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «**እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡ ፡**»(አል-በቀራህ 183) (2)

ለሓጅ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «**...ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።።**» (አል-ዒምራን 97) **(3)**

(1) ሶላት ሁለተኛው ማአዘን:

ያም በተክቢር (አሏሁ አክበር) ተጀምሮ በተስሊም (አሰላሙ ዓለይኩም) የሚያልቅና አላህን (ለየት ባሉ) ንግግሮችና ተግባሮች ማምለክ ማለት ነው። የዲን መሰረት ነች፤ የተደነገገችውም ቀጥታ ከአላህ ለነብዩ ነው። ይህም የሆነው ነብዩ ﷺ ወደ ሰማይ አርገው በነሩበት ጊዜ ነው።

ዘካ ሶስተኛው ማአዘን:

በቋንቋ ደረጃ: መጨመርና መጥራራት ማለት ነው።

ሁለት አይነት ነች: የአካል ዘካ እና የገንዘብ ዘካ

(2) ፆም አራተኛው ማአዘን:

በቋንቋ ደረጃ: መታቀብ ማለት ሲሆን

በሸሪዓ ደረጃ: ፀሃይ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በመፆም ኒያ ፀሃይ እስከምትጠልቅበት ሰዓት ድረስ ከሚያስፈጥሩ ነገራቶች በመታቀብ ለአላህ መገዛት ማለት ነው። ፆም ሶስቱንም የሶብር አይነቶች አቅፎ የያዘ በመሆኑ በላጭ ከሚባሉ የአምልኮ አይነቶች የሚመደብ ነው፤ የፆሞኛን ምንዳ አላህ ወደራሱ አስጠግቶ መግለፁ ደሞ ጉዳዩን ከፍ ከሚያደርጉልን ነጥቦች መካከል ነው።

(3) ሓጅ አምስተኛው ማአዘን:

በቋንቋ ደረጃ: ማሰብ ማለት ሲሆን

በሸሪዓ ደረጃ: ደግሞ ከነብዩ ﷺ ፈለግ በመጣበት መልኩ የሓጅ ስርዓቶችን በመፈፀም ለአላህ መገዛት ማለት ነው።

ያም ከእድሜ ልክ አንዴ ግዜ ሓጅ ማድረግ (በሚችል) ሙስሊም ላይ ሁሉ ላይ ግዴታ ነው።

ሁለተኛዋ እርከን: ኢማን

በቋንቋ ደረጃ ፡ አምኖ መቀበል

በሸሪዓ ደረጃ: በሸሪዓ ደረጃ: በአንደበት የሚባል፣ በልብ እምነት ተደርጎ የሚያዝ፣ በአካልና በልብም የሚተገበር በታዛዥነት የሚጨምርና በአመፅ የሚቀንስ ነው።

እምነት እንደሸሪዓው አምስት ነገራቶችን ሊያሟላ ግድ ነው። ከነዚህ ነገራቶች አንዳች ነገር ከጎደለ አህሉ ሱና ወልጀማዓ ዘንድ ኢማን ከሚለው ጥቅል ፍች ይወጣል።

ለነኝህ ጥቅል ፍቹ ላይ ለተጠቀሱት አምስት ነገራቶች ማስረጃቸው ምንድን ነው? የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ብለዋል: "ከፍተኛው 'ላኢላሀ ኢለሏህ' የሚለው ቃል ሲሆን..." በሚለው ሓዲሥ መሰረት ንግግር ኢማን ውስጥ እንደሚካተት ይጠቁመናል።

"ዝቅተኛው ደሞ አስቸጋሪን ነገር ከመንገድ ማስወገድ ነው።" በሚለው መሰረት ደሞ ተግባርም ኢማን ውስጥ እንደሚካተት ይጠቁማል።

"ሓያእም..." የሚለው ደሞ የልብን ተግባር የሚገልፅ ነው።

ሁለተኛዋ እርከን: ኢማን

ሰባ ምናምን ደረጃ ያለው ሲሆን ከፍተኛው ***ላኢላሀ ኢለሏህ*** ዝቅተኛው ደግሞ ከመንገድ የሚያሰናክልን ነገር ማስወገድ ነው፤ ሓያእም የኢማን ቅርንጫፍ ነው።

ስድስት ማአዘኖች አሉት:

በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በኪታቦቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ልታምን እንዲሁም በቀደር በክፉውም በደጉም ልታምን ነው።

ለነዚህ ስድስት ማአዘኖች ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም። ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው...»** (አል-በቀራህ 177).

ለቀደር ማስረጃው ደግሞ ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው።»** (አል-ቀመር 49).

ከፍ ያለው አላህ (ስለ ሙናፊቆች) እንዲህ ይላል: **«ማንኛችሁ ነው ይህች (ምዕራፍ) እምነትን የጨመረችለት የሚል ሰው አልለ»** (አት-ተውባ 124) ይህ ደሞ ኢማን እንደሚጨምር ጥቆማ የሚሰጥ ሲሆን እንደሚጨምር ከፀና (በተቃራኒው) መቀነሱ የግድ ነው። ስለዲን መቀነስ በግልፅ ከነብዩ ﷺ ተከታዩ ሓዲሥ መጥቷል "**የዲንም የአዕምሮም ጉድለት ኑሮባት... አላየሁም።**" ስለዚህ ዲን ይቀንሳል።


ስድስቱ የኢማን ማአዘናት
በአላህ ማመን
በመላእክቶች ማመን
በኪታቦች ማመን
በመልእክተኞች ማመን
በመጨረሻው ቀን ማመን
በክፉም በደጉም ቀደር ማመን
የመጀመሪያው ማአዘን በአላህ ማመን አራት ነገራቶችን ግድ ያስብላል
ጥራት ይገባውና በአላህ ህልውና ማመን: በአራቱም መልኩ የተረጋገጠ ነው
በ(ተውሒደል ሩቡቢያህ)ጌትነት አሃዳዊነቱ ማመን
በ(ተውሒደል ኡሉሂያህ)አምላክነት አሃዳዊነቱ ማመን
በ(ተውሒደል አስማኢ ወሲፋት)ስምና ባህርያት አሃዳዊነቱ ማመን
በአዕምሮ ፍጥረት ያለ ፈጣሪ ሊገኝ መቻሉን አዕምሮ አይቀበለውም« ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?» (አል-ጡር 35)
በተጨባጩ በችግርና በመከራ ጊዜ እጅህን ወደላይ ከፍ አድርገህ “ያ ረብ! (ጌታየ ሆይ!)” ብትል ችግርህ በአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ፍቃድ ተቀርፎልህ ታገኘዋለህ።
በተፈጥሮአዊ ማንነት “ተወላጅ ሁሉ የሚወለደው በተፈጥሮአዊ ማንነቱ (በኢስላም ላይ) ሆኖ ነው፤ ወላጆቹ ናቸው አይሁድ ወይም ክርስትያን ወይም ደሞ እሳት አምላኪ የሚያደርጉት።” (ቡኻሪይና ሙስለ ምነ
በሸሪዓዊ እይታ ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና “በቁርአን ምንም አይነት አንቀፅ የለም ወደ አላህ አሃዳዊነት የሚጠቁም ቢሆን እንጅ። ”

ሁለተኛው ማአዘን በመላእክቶች ማመን

መላእክቶች: የማይታየው አለም ላይ ያሉ፤ አላህ ከብርሃን የፈጠራቸው፤ አላህን የማያምፁ ታዛዦች፤ መንፈስ (ህይወት) አላቸው «ቅዱሱ መንፈስ» (አል-ነሕል 87) አካልም «... መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፣ ባለ ሶስት ሶስትም፣ ባለ አራት አራትም ክንፎች የኾኑ መልክተኞች አድራጊ ለኾነው አላህ ይገባው። በፍጥረቱ ውስጥ የሚሻውን ይጨምራል።...» (ፋጢር 1) አዕምሮም ልቦናም አላቸው «ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጸም ጊዜ ጌታችሁ ምን አለ?» ይላሉ» (ሰባእ 23) በነሱው (ህልውና) እናምናለን፤ ከነሱ መካከል ስሞቻቸውን ባሳወቀንም ጅብሪል፣ ሚካኤልንና ኢስራፊልን ይመስል፤ ባህርያቸውንም «...አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም። የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።» (አት-ተሕሪም 6) በድርጊቶቻቸውም የዓርሽ ተሸካሚዎችን ይመስል፤ እነሱን በማስመልከት በጥቅሉም ይሁን በዝርዝር የመጣውን ሁሉ እናምናለን።

ሶስተኛው ማአዘን በመፃህፍቶች ማመን

አላህ በዘይቤያዊ አነጋገር ሳይሆን በግልፅ የተናገረበት መሆኑን እናምናለን፤ ከሱ የወረዱ እንጅ ፍጥረታት አለመሆናቸውን፤ ከመልዕክተኞቹ ፆ ሁሉ መፃህፍትን እንዳወረደላቸውም፤ በኪታቦቹም እናምናለን አላህ ስለ ኪታቦቹ በነገረን ስም፣ መረጃና ህግጋት እስካልተሻረ ድረስ በጥቅሉም በዝርዝርም እናምናለን። ቁርአንም ከሱ በፊት የወረዱትን ተውራት፣ ኢንጅል፣ ዘቡር፣ የኢብራሂምና የሙሳ (ዓለይሂማ ሰላም) ሱሑፍንም ሁሉ እንደሻረ እናምናለን።

አራተኛው ማአዘን በመልእክተኞች ማመን

ከጌትነት መገለጫ እንዳችም ነገር የሌላቸው የሰው ልጆች መሆናቸውን፤ አምላኪ ባርያዎች እንጅ የማይመለኩ መሆናቸውን፤ አላህ የላካቸውና መልእክቱን ያስተላለፈላቸው እንዲሁም በተአምራቶች ያጠናከራቸው ናቸው፤ እነሱም አደራቸውን ተወጥተው ህዝቦቻቸውንም መክረው ተልእኳቸውንም አድርሰዋል፤ በአላህም መንገድ እውነተኛውን ትግል ያደረጉ መሆናቸውን ማመናችን ግዴታ ነው፤ በነሱም (ህልውና) እናምናለን፡ አላህ እነሱን በማስመልከት ስለስሞቻቸውም፣ ሥለባህሪዎቻቸውም ጥቅል በሆነ መልኩም ይሁን በዝርዝርም የነገረንን ሁሉ እናምናለን። የነብያቶች መጀመርያ አደም፤ የመልእክተኞች መጀመርያ ኑሕና የነብያቶችም ይሁን የመልእክተኞች መደምደምያ ሙሐመድ ሶለሏሁ ዓለይሂሙ ሰላም መሆናቸውን እንዲሁም ቀደምት ሸሪዓዎች በሙሉ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ ይዘውት በመጡት እንደተሻረ እናምናለን። የቆራጥነት ባለቤት የሚባሉትም አላህ ቁርአኑ ላይ በሁለት ቦታዎች በሱረቱ ሹራ እና በሱረቱል አሕዛብ ጠቅሷቸዋል፤ እነሱም: ሙሐመድ ﷺ ፣ ኑሕ ዓለይሂ ሰላም፣ ኢብራሂም ዓለይሂ ሰላም፣ ሙሳ ዓለይሂ ሰላም፣ ዒሳ ዓለይሂ ሰላም ናቸው።

አምስተኛው ማአዘን በመጨረሻው ቀን ማመን

ነብዩ ﷺ ከሞት በኃላ ስላለው በተናገሩት ሁሉ ማመንን የሚያጠቃልል ነው። የቀብር ፈተና፣ በጥሩምባ መነፋቱ፣ ሰዎች ከቀብራቸው መቀስቀሳቸው፣ በሚዛን፣ በመዝገብ፣ በሲራጥ፣ በሓውድ (የነብዩ ወንዝ) ፣ በምልጃ (ሸፋዓ)፣ በጀነት፣ በጀሃነም፣ ከሞት በኃላ ጀነትም ውስጥ አማኞች ጌታቸውን ማየታቸው እና በሌሎችም የሩቅ ሚስጥሮች (እናምናለን)።

ስድስተኛው ማአዘን በበጎውም በመጥፎውም ቀደር ማመን

(ይህ ማአዘን አራት ነገራቶችን ሊያካትት ግድ ይለዋል)

እውቀት:
ጥራት ይገባውና አላህ ሁሉንም ነገር በጥቅሉም በዝርዝርም እንደሚያውቅ ማመን

መፃፉ:
አላህ ሁሉም ነገር እስከዕለተ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ክንውን ሁሉ እንደፃፈው ማመን

መሻት:
አላህ የሻው እንደሚሆን አላህ ያልሻው ደሞ እንደማይሆንና ባርያም የራሱ ነፃ ፍላጎት እንዳለው ነገር ግን ከአላህ መሻት ስር መሆኑን ማመን

መፍጠር:
የሰው ልጆችም ሌላውም ከድርጊቶቹ ጋ አላህ የፈጠረው መሆኑ፤ ማስረጃውም:
«...አላህ የሁሉም ፈጣሪ...» (አል-አንዓም 101)
«አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን።» (አስ-ሷፋት 96)

ማወቅም መፃፉ መፍለግና መፍጠሩ

እሱው ነው ክንውኑ ሂደት የፍጡሩ

በሚለው ስንኝ አራቱም እርከኖች ይገኛሉ።

ሶስተኛው ደረጃ ኢሕሳን ከፍተኛው የዲን እርከን ሲሆን፤ አንድ ማአዘን ያለውና ከስሩ ሁለት

የተጣደ አምልኮ (ሲባደቱል ሙሻሀዳህ)

(አምልኮውን ከማጣጣም ጋ) አላህ ዘንድ ላለው ወዶ፣ ከጅሎና ናፍቆ የሚደረግ አምልኮ ነው፤ የነብያቶችና የመልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም አምልኮ ሲሆን ሌሎችም ሊደርሱበት የሚችሉት ደረጃ ነው።

የቁጥጥር አምልኮ (ሲባደቱል ሙራቀባህ)

(የሚቆጣጠር እንዳለ አስቦ) በፍርሃትና በስጋት የሚደረግ አምልኮ ሲሆን የትኛውም ሙስሊም ከዚህ ደረጃ አይወጣም።

ሶስተኛው ደረጃ: ኢሕሳን አንድ ማአዘን ነው ያለው "**አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።**" ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{**አላህ ከእነዚያ ከሚፈሩትና ከእነዚያም እነሱ መልካም ሠሪዎች ከኾኑት ጋር ነውና።**}» (አል-ነሕል 128) እንዲሁም: «**አሸናፊ አዛኝ በኾነው (ጌታህ) ላይም ተጠጋ። ۝ በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ። ۝ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)። ۝ እነሆ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና። ۝**» (አሽ-ሹዐራእ 217-220) እንዲሁም: «**(ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርአን አታነብም፣ ማንኛውንም ሥራ (አንተም ሰዎቹም) አትሠሩም በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ።**» (ዩኑስ 61)

ከሐዲሥ ማስረጃውም: የተሰራጨው ከዑመር ረድየሏሁ ዓንሁ የተዘገበው የጅብሪል ሐዲሥ፡

ማብራሪያ: በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ባርያ ለአላህ ውዴታ ኖሮት ምንም ያህል ፍርሃት ሳይኖረው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በዚህ ደረጃ ላይ ላለ ባርያ ለአምልኮ ከፍተኛ ግፊቱ የሚመነጨው ለአላህ ካለው ውዴታ ነው፤ ነብዩ ﷺ ም "ታድያ አመስጋኝ ባርያ አልሆንምን!" ማለታቸውም እዚሁ የሚመደብ ነው።

«ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ ﷺ ጋ ሳለን ልብሱ በጣም ነጭ ፀጉሩ በጣም ጥቁር የሆነ ሰው ብቅ አለ። የመንገደኛ ምልክትም አይታይበትም ከኛ መካከልም የሚያውቀው ሰው የለም። ወደ ነብዩ ﷺ ተጠግቶ ጉልበቱን ከጉልበታቸው አስደግፎ ተቀመጠ። እጁንም ታፋው ላይ አደረገና "አንተ ሙሐመድ ሆይ! እስኪ ስለ ኢስላም ንገረኝ?" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም ﷺ **"ኢስላም `ማ በ'ላኢላህ ኢለሏህ ሙሐመደን ረሱሉሏህ' የምስክርነት ቃልህን ልትሰጥ፣ ሶላት (ስርአቱን አሟልተህ) ልትሰግድ፣ ዘካን ልታወጣ፣ ረመዷንን ልትፆም፣ መንገዱን ከቻልክ ደሞ ሓጅ ልታደርግ ነው።"** አሉት። "እውነት ብለሃል" አላቸው። "ይጠይቀውና 'ትክክል ነህ' ይላቸዋል። ተገረምን!"» ይላል። «"ስለኢማንስ ንገረኝ እስኪ!" አላቸው። እሳቸውም **"በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በኪታቦቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ልታምንና በቀደርም ክፉውም ሆነ ደጉን ልታምን ነው።"** አሉት። "እውነት ብለሃል!" አላቸው። "እስኪ ደሞ ስለ ኢሕሳን ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም **"አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።"** "ስለ ሰዓቲቱስ ንገረኝ እስኪ!" አላቸው። እሳቸውም **"ተጠያቂው ከጠያቂው በተሻለ የሚያውቀው ነገር የለም።"** አሉት። "ታድያ እስኪ ስለምልክቶቹ ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም **"ሴት ባርያ ጌታዋን(አለቃዋን) መውለዷ፣ ጫማና ልብስ የሌላቸው ሰዎች እረኞች በህንፃ ሲወዳደሩ ታያለህ"** አሉትና ሄደ። ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ ቆየን የአላህ መልዕክተኛም ﷺ **"ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?"** አሉ። እኔም "አሏህና መልዕክተኛው ﷺ ይበልጥ ያውቃሉ" አልኩኝ። እሳቸውም **"ጅብሪል ነው! የዲናችሁን ጉዳይ ሊያስተምራችሁ መጥቶ(ነው)።"** (ሙስሊም)

ይህ ሓዲሥ ለኢስላም፣ ለኢማንና ለኢሕሳን ማእዘናት ማስረጃ ነው። **"ተጠያቂው ከጠያቂው በተሻለ የሚያውቀው ነገር የለም።"** የሚለው ከአላህ ውጭ ሰዓቲቱ መች እንደምትቆም የሚያውቅ እንደሌለ አመላካች ነው።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ "አንዲት ባርያ ጌታዋን መውለዷ" ማለታቸው

ማለትም: ከ(ልጆች) ጨቋኝነት ብዛት (አንፃር)

ወይም: የባርነት ብዛት

ወይም: የነገራቶች መቀያየር

ወይም ደሞ፡ ንጉስ (አለቃዋ) ባርያን ያገባትና ልጅ ትወልድለታለች ከዛም ከአባቱ ሞት በኃላ ልጅየው ንጉስና የእናቱ አሳዳሪ ይሆናል።

"ጫማና ልብስ የሌላቸው ሰዎች ነባር ድሃ እረኞች በህንፃ ሲወዳደሩ ታያለህ"

"العالة" ማለትም ድሆች ማለት ነው።

ማለት ሁኔታዎች ተቀይረው ይህ ድህነትም ተቀይሮ ሃብትና መዝረክረክ ይሆናል።

ከጅብሪል (ዓለይሂ ሰላም) ሓዲሥ የምንረዳቸው ቁምነገሮች

(1) በአንድ ተማሪ ላይ ስድስት መብቶች አሉበት: የራሱ ሓቅ፣ የአስተማሪዎቹ መብት፣ የተማረበት ቦታ መብት፣ የባልደረቦቹ መብት፣ የመፃህፍቱ መብትና ለተማረው እውቀት ሓቅ ናቸው።

የራሱ ሓቅ: እውቀት አምልኮ በመሆኑ [ኢኽላስ እና ተከታይነት] ፤ የምር ሰለፎችን ተከታይ ሁን፤ በእውቀት የተመረከዘ ፍርሃት፣ አሏህ ያየኛል ባይነት፣ የመተናነስ ክንፍን ዝቅ ማድረግ ኩራትን ማስወገድ ይኑርህ።

መብቃቃት እና ዙህድን መላበስ: በሂልም ነፀብራቅ ማሸብረቅ፤ የተሟላ ስብእናን መላበስ፣ የወንድነት መገለጫዎችን መተግበር መንደላቀቅን መተውና ከዛዛታ መቀማመጦች መራቅ፣ ርህራሄን፣ የፅናትና የማረጋገጥ ስብእናን ተላበስ።

(እውቀትን) በማደንም በኩል ጥልቅ ሃሳብ እና ከፍተኛ ጉጉት፣ እውቀቱን ነጥሎ ማውጣት፣ ሃላፊነትን መጠባበቅ፣ መንቀሳቀስ፣ የተማርከውን በፅሁፍና በሽምደዳ ጠብቆ ማቆየት፣

ቅርንጫፋዊ እውነትን ከመሰረታዊው ለይቶ እያወጡ ግንዛቤን ማስፋት፤ በአላህ ላይ መመካት፤ የእውቀት አደራን መጠበቅና እውነተኛ መሆን ይኖርብሃል።

የሂልም ፈላጊ ጋሻው "አላውቅም" ማለቱ፤ መዋእለ ንዋዩ(ጊዜ)ን በአግባቡ መጠቀም፣ ራስን ሰብሰብ ማድረግ (በጠቅላላ እውቀት)፣ (ዓረብኛውን) አስተካክሎ ማንበብ፣ ፈር ማስያዝ፣ በሂደት ደሞ ረዣዥም ኪታቦችን መላመድ።

ተገቢ ጥያቄን ስርአት ባለው መልኩ መጠየቅ፣ ለተባለው ማዳመጥ መገንዘብና መስራት፣ ያለጭቅጭቅ መወያየት፣ እውቀትን መከለስ፣ በቁርአንና በሓዲሥ መጠመድ፣ የየትምህርቱ መሰረታዊ ጭብጥ ማጥናት።

(በተማርከው) መስራት: ከፍ ብሎ ለመታየት ፍላጎትን፣ ዝናንና የዱንያ ፍቅርን መሸሽ፤

ስለራስ (እንዳጎደሉ) በመጥፎ መጠርጠር፣ ስለሌሎች (ይሻላሉ በሚል) በበጎ ጥርጣሬ ላይ መሆን፤

የእውቀት ዘካን አትዘንጋ: እውነት ላይ ደፋር፣ በመልካም አዛዥ ከመጥፎ ከልካይ፣ ጥቅም እና ጉዳትን ማመዛዘን፣ እውቀትን እያሰራጩ ሌሎችን መጥቀምን ማሰብ፣ ያለህን ደረጃ ተጠቅመህ በሙስሊሞች መካከል ማስተካከልና እውነትን ማሰራጨት ነው።

ተከባብረህ መኖር፣ እውቀትን መጠበቅ፣ ለእውነት ብለህ ዱንያን እጣ እንጅ ለዱንያ ብለህ መስለህ አለመኖር፣ ብቁ ከመሆንህ በፊት አስተማሪነትንና ደረጃን ተው።

ለዓሊም ማንዳለጥና ለውለሞች የሃሳብ ልዩነት ያለህን አቋም አስተውል።

ወዳጅነትና ጠላትነት የምትመሰርትበት ቡድንተኝነትና ጎጠኝነት ሳይኖርብህ አወዛጋቢ ነጥቦችን አስወግድ፤

<u>ለሸይኹ ያለው ሓቅ (መብት):</u> ይህን ርእስ በማስመልከት ሁለት ጠርዘኞች እና አንድ መካከለኛ አቋም አለ፤ በምድር ላይ የተከሰተው የመጀመርያው ሽርክ ደጋግ ሰዎችን በማስመልከት ሰዎች ድንበር ማለፋቸው ነው። ደጋግ ሰዎችን በማስመልከት ድንበርም ሳይታለፍ ተገቢውንም ባለማስቀረት መካከለኛ አቋም ሊኖር ይገባል።

ለሚማርበት ቦታ ሓቅ(አለው)።

ለ**ቂርአት ጓደኞቹ** ያለው ሓቅ: ጥራት ይገባውና አላህ እንዲህ ይላል: {ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ…}(አሊ-ዒምራን 110) የአላህ መልዕክተኛም ﷺ “**እንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።**” ብለዋል።

ለኪታቡ ያለው ሓቅ: መፅሃፉን ተጠባብቆ ሊይዘው ይገባል፤ ምክንያቱም ጥራት ይገባውና አላህ እነኝህን ኪታቦች በመስጠቱ ፀጋውን ውሎልናልና ተጠባብቆ መያዙ የግድ ነው።

ለእውቀቱ ያለው ሓቅ: ሁልጊዜም ቢሆን አስረግጦ በመያዝና በክለሳ መጠባበቅ፣ በሱው መስራት፣ ምክንያቱም ያወቀ ሰው የመስራት ግዴታው አለበትና። ከዚህ በኃላ ወደዚህ እውቀት ጥሪ ያደርጋል፤ ምክንያቱም ፀጋ ነውና ይህንን ፀጋ ማመስገን ደሞ ግዴታ ነው።

(2) ከጥያቄ ስርአቶች መካከል የጎላ ጥቅምና ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ማስቀደም

(3) አንድ ተማሪ የራሱን ውበት መጠበቅ ይኖርበታል።

(4) ነብዩ ﷺ ከሞቱ በኃላ ግን “አላህና መልእክተኛው ይበልጡን ያውቃሉ” አይባልም።

ሶስተኛው መሰረታዊ መርሆ: ነብያችሁን ሙሓመድን ﷺ ማወቅ።

እሱም: **ሙሓመድ** ኢብኑ **ዓብዲላህ** ብኒ **ዓብዲል ሙጥሊብ** ብኒ **ሃሺም**፤ ሃሺም ከቁረይሽ ጎሳ ሲሆን ቁረይሽ ደሞ ከዓረብ፤ ዓረብም ደሞ ከኢስማዒል ኢብኒ ኢብራሂም አልኸሊል ዝርያ ነው። በሳቸውም በነብያችንም በላጭ የሆነው ሶለዋትና ሰላም ይስፈንባቸውና ዕድሜያቸው ስሳ ሶስት አመት ነበሩ። ከዚህም አርባውን ከነብይነታቸው በፊት ሃያ ሶስቱን የአላህ መልእክተኛና ነብይ ሆነው።

"ኢቅራእ" ሲወርድ ነብይ ሆነው "አል-ሙዘሚል" ሲወርድ ረሱልነትን አገኙ።

አገራቸው "መካ" ሲሆን ሂጅራ አድርገው ወደ "መዲና" የተሰደቱት።

ይህች አንቀፅ ስለነብዩ ﷺ ታሪክ አጠር ባለ መልኩ ትገልፃለች፤ ስማቸውን ዘራቸውንና ዕድሜያቸውን እንዲሁም ጥቂት ስለዳዕዋቸው ትዳስሳለች።

ስለ ነብዩ ﷺ አንዳንድ ነገራቶችን ማወቅ ግድ ይለናል፤ ከነዚህም፡

ስምና ዘራቸውን:
ስምና የዘር ግንዳቸውን: ሙሓመድ ኢብኑ ዓብዲላህ ብኒ ዓብዲል ሙጥሊብ ብኒ ሃሺም፤ ሃሺም ከቁረይሽ ጎሳ ሲሆን ቁረይሽ ደሞ ከዓረብ፤ ዓረብም ደሞ ከኢስማዒል ኢብኒ ኢብራሂም አልኸሊል ዝርያ ነው። በሳቸውም ሶለላሁ ዓለይህም ወሰለም

ዕድሜያቸውን:
ዕድሜያቸው ስሳ ሶስት አመት ነበሩ። ከዚህም አርባውን ከነብይነታቸው በፊት ሃያ ሶስቱን የአላህ መልእክተኛና ነብይ ሆነው።

የመልእክተኝነት ቆይታቸው ወደ ሁለት ይከፈላል

የመካ ቆይታ: ለአስራ ሶስት አመታት የዘለቀች

የመዲና ቆይታ: ለአስር አመታት የዘለቀች

እሳቸው ነብይ (ብቻ) ናቸው? ወይስ ረሱልም?

ነብይም ረሱልም ናቸው። ነብይ የሆኑት "ኢቅራእ" ሲወርድ ሲሆን መልእክተኝነትን ያገኙት ደሞ በሱረቱ ል ሙደሢር ነው።

ከታሪካቸው ﷺ ቅንጭብ (በጨረፍታ)

በመካ ቆይታቸው የዳዕዋው ይዘት በተውሒድ ዙርያና ከሽርክ ርቆ አምልኮን ለአላህ ብቻ ጥርት ማድረግ ላይ ነበር። በዚህ ዳዕዋ ለአስራ ሶስት አመታት ቀጠሉ።

ከዚያም ወደመዲና ሂጅራ ማድረግን ታዘዙ። ዳዕዋው ግን ሌሎቹ የአምልኮ፣ የመስተጋብርና ሌላው የህይወት ዘርፍ ህግጋቶች ከመውረዳቸው አንፃር አሁንም በተውሒድ ላይ ነው የቀጠለው።

ይሁን እንጅ የነብዩን ﷺ የዳዕዋ ታሪክ ለተመለከተ ሰው የነብዩ ﷺ ወደ ተውሒድ ዳዕዋ ማድረግ እስከህልፈተ ህይወታቸው ድረስ እንደቀጠለ ነው። በዚህ ላይ ደሞ ሠዎችን ተውሒድን ከመማር ችላ በሚያስብሉና "ተውሒድን ለመማር የሆነ ያክል ደቂቃ በቂው ነው" ብለው በሚሞግቱ ሰዎች ላይ ግልፅና ጉልህ የሆነ አፀፋዊ ምላሽ (ረድ) አለበት።

አላህ ከሽርክ እንዲያስጠነቅቁና ወደ ተውሒድ ጥሪ እንዲያደርጉ ላካቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:

«{አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ۝ ተነሳ አስጠንቅቅም።۝ ጌታህንም አክብር۝ ልብስህንም አጥራ።۝ ጣዖትንም ራቅ።۝ ማብዛትንም የምትፈልግ ኾነህ፤ (በረከትን) አትለግስለለ።۝ለጌታህም (ትዕዛዝ) ታገሥ።(7)» (አል-ሙደሢር 1-7)

(ተነሳ አስጠንቅቅም።) ማለትም ከሽርክ ሊያስጠነቅቅና ወደ ተውሒድ ሊጣራ ማለት ነው። **(ጌታህንም አክብር።)** በተውሒድ አልቀው። **(ልብስህንም አጥራ።)** ስራህን ከሽርክ አፅዳው

(ጣዖትንም ራቅ።) ጣኦትን መራቁ ማለትም መተውና ከሽርኩም ከሽርክ ሰዎችም መጥራራት ማለት ነው። በዚህ መልኩ ወደ ተውሒድ ጥሪ እያደረጉ ለአስር አመታት ቆዩ። ከአስር አመት በኃላ ወደ ሰማይ አረጉ አምስት ሶላቶችም ተደነገጉ፤ ሶስት አመታትን መካ ላይ እንደሰገዱ ወደ መዲና ሂጅራ እንዲያደርጉ ታዘዙ።

"ወደ ሰማይ አረጉ" ከሚለው ንግግር (ጋ በተያያዘ) ተከታዮቹን ቁምነገሮች እናገኛለን

(1) ነብዩ ﷺ ስለሩቅ ሚስጥር በተናገሩበት አምነናል፣ እውነት ብለን ተቀብለናል እጃችንን ሰጥተናል እንላለን

(2) የአምስቱ ሶላቶች አሳሳቢነት፤ ምክንያቱም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ የደነገጋቸው ሰማይ ላይ ነውና።

ሂጅራ ማለት ከሽርክ ሃገር ወደ ተውሒድ ሃገር መሰደት ማለት ነው። ከሽርክ አገር ወደ ተውሒድ ሃገር ሂጅራ ማድረግ በዚህ ኡማ ላይ ግዴታ ነው። እስከሰዓቲቱ መቆም ድረስም ቀጣይ ነች።

ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «እነዚያ (ለእምንት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ» አሏቸው። «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ። «የአላህ ምድር ትሰደዱበት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን» አሉዋቸው። እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት። በመመለሻነትም ከፋች!(97) ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃኖችም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይምመሩ ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም) (98) እነዚያም አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል። አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው።(99)» (አን-ኒሳእ 97-99).

እንዲሁም «እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ)። እኔንም ብቻ ተገዙኝ።» (አል-ዓንከቡት 29:56) አልበቹዉይ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል: የዚች አንቀፅ መውረድ ምክንያት በመካ የነበሩ ሂጅራ ያልወጡ ሰዎች ነው። አላህም በኢማን ስያሜ ጠራቸው።

ለሂጅራ ከሓዲሥ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቃል ነው: **“ሂጅራ አትቋረጥም ተውባ እስክትቋረጥ ድረስ፤ ተውባም አትቋረጥም ፀሃይ በመግቢያዋ እስክትወጣ ድረስ።”** (አቡ ዳውድ)

ሂጅራ ወደ ሶስት ይከፈላል:

- አላህ እንድንተዎ ግዴታ ያደረገውን ሁሉ ሂጅራ ማድረግ (መተው)፤ ስራም ይሁን ሰሪ ወይም ጊዜም ይሁን ቦታ።
- ከመካ ወደ መዲና የሚደረግ ሂጅራ፤ ይህ በመካ መከፈት የተቋረጠ ነው።
- ከኩፍር ሃገር ወደ ኢስላም አገር መሰደት ፤ ፍርዱ ግዴታ ነው።

- ስራ: ጥራት ይገባውና አላህ የከለከለው ሁሉ፤ ከምንም በላይ ሽርክ። ሰሪ: ካፊርና ሙናፊቆች እንዲሁም ሌሎችም። ጊዜ: ካፊሮች በአል አድርገው የሚይዟቸው ጊዜያት። ቦታ: ካፊሮች በአል አድርገው የሚይዙባቸው ቦታዎች።

ተውባ የሚቋረጠው ከሁለት በአንዱ ነው:

(1) ፀሃይ በመግቢያዋ በመውጣቷ

(2) ወይም ሞት አፋፍ ላይ ሲኮን: {ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ኀጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚልና ለነዚያም እነርሱ ከሓዲዎች ኾነው ለሚሞቱ አይደለችም። እነዚያ ለእነሱ አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል።}

የነብዩ ﷺ “ከ(መካ) መከፈት በኃላ ሂጅራ የለም።” ማለት ከመካ ወደ መዲና ለማለት ነው። እዚህጋ ከነብዩ ﷺ የሆነ ጥቆማ የሚሰጠን ነገር አለ: “መካ” ተመልሳ የኩፍር አገር እንደማትሆን ነው ።

መዲና ላይ በተረጋጉ ጊዜ በተቀሩት የዲነል ኢስላም ድንጋጌዎች ታዘዙ፤ እንደ ዘካ **(1)** ፣ ፆም፣ ሓጅ፣ ጅሀድ፣ አዛን፣ በመልካም ማዘዝ ከመጥፎ መከልከል፣ እና በሌሎችም የእስልምና ድንጋጌዎች ታዘዙ።

በዚህ መልኩ አስር አመት አሳለፉ፤ ከዛ በኃላ ህይወታቸው አለፈ የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና። **(2)** ዲናቸው ቀሪ ሲሆን፤ ይሀውና ዲናቸው። አንዳች ኸይር ነገር የለም ህዝባቸውን ያዘዙ ቢሆን እንጅ፤ ክፉ ነገርም የለም ከሷው ያስጠነቀቁ ቢሆን እንጅ። እሳቸው የጠቆሙት መልካም ነገር "ተውሒድ" እና አጠቃላይ አላህ የሚወደውና የሚያስደስተው ሁሉ። እሳቸው ያስጠነቀቁበት ክፉ ነገር ሽርክ እና አጠቃላይ አላህ የሚጠላውና የሚቃወመው ሁሉ። **(3)**

(1) ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚንን አላህ ይዘንላቸውና የሚከተለውን ብለዋል "ዘካ መጀመርያ በመካ ነበር የተደነገገችው፤ ነገር ግን የኒሷቡ (የዘካ ግዴታ ማውጫ ዝቅተኛ ገደብ) መጠንም ሆነ የግዴታው ለከት አልተቀመጠለትም ነበር። መዲና ከገቡ በኃላ ግን ኒሷቡም ተቀመጠለት ግዴታውም ተገደበለት።"

(2) ነብዩ ﷺ ከሂጅራ በኃላ በአስረኛው አመት ሙተው በዓኢሻ (ረድየሏሁ ዓንሃ) ቤት ተቀበሩ።

(3) ምንም አይነት በጎ ነገር የለም ኡማውን ያመላከተ ቢሆን እንጅ፤ መጥፎ ነገርም የለም ከሱ ያስጠነቀቀ ቢሆን እንጅ። አደራውን መወጣታቸው፣ ተልዕኳቸውን ማድረሳቸው፣ ለኡማውን ተገቢውን ምክር ማስተላለፋቸው፣ በአላህም መንገድ ላይ ተገቢውን ትግል ማድረጋቸው፣ ጠፊ ካልሆን በማይሳሳትበት በነጣ ማስረጃ ላይ ትተውን (መሄዳቸው) መመስከር ግድ ነው።

ከባባዶቹ ክልከላዎች

ትልቁ ሽርክ:	**ትንሹ ሽርክ**:	**ከባባድ ወንጀሎች**:	**ትናንሽ ወንጀሎች**:
ከ(እስልምና) መንገድ ያስወጣል	ከ(እስልምና) መንገድ አያስወጣም	ለየት ባለ መልኩ መቀጣጫ የመጣበት ሁሉ	ለየት ባለ መልኩ መቀጣጫ ያልመጣበት ክልከላ ሁሉ

አላህ ለሰው ልጆች በመላ ላካቸው፤ በሁለቱ ከባባዶች የሰው ልጆችና አጋንንቶች ሁሉ ላይም መታዘዙን ግዴታ አደረገ።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ።} (አል-አዕራፍ 158) (1)

አላህም ዲኑን በሱ አሟላ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።...}(አል-ማኢዳህ 3)(3)

ለመሞታቸው ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {አንተ ሟች ነህ፤ እነርሱም ሟቾች ናቸው።(30) ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ።(31)} (አዝ-ዙመር 30-31)

(1) ነብዩ ﷺ ወደሰው ልጆች በመላ ተላኩ። በዚህም ከሱ በፊት የነበሩት ህግጋት በሙሉ ተሻሩ። አይሁድም ይሁን ክርስትያን በነብዩ ﷺ ጊዜ ወይም ባለንበት ጊዜ (የእስልምና) ጥሪ ደርሷቸው ወደ ዲኑ ካልገቡ ካፊሮች ናቸው። የአላህ ሰላም ይስፈንባቸውና ሙሳና ዒሳ በነበሩበት አቋም ላይ እንኳ ቢሆኑ፤

(1) ማስረጃውም: {የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣} (አሊ-ዒምራን 64)

(2) እንዲሁም ተከታዩ ቃል: {ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና... ተዋጉዋቸው።} (ተውባ 29)

(3) የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቃል "ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታየ እምላለሁ፤ አንድም አይሁዳዊ ወይም ክርስትያን ስለኔ አይሰማም ከዚያም በኔ ሳያምን አይቀርም የእሳት ሰው ቢሆን እንጅ።"

2. ይህች አንቀፅ በካፊሮች ላይ "ረድ" አለባት።

አምስተኛ: መደምደምያ

(1) ሰዎች ሁሉ ያለጥርጥር ሞትን ቀማሽ ናቸው። ለታላቁ ቀን ለትንሳኤ ቀንም ተቀስቃሾች ናቸው። የዚያኔ ይተሳሰባሉ ሁሉም እንደየስራቸው ይመነዳሉም።

(2) ከሞት በኃላ በመቀስቀስና (አላህ ፊት) በመተሳሰብ ያስተባበለ ክዷል ምክንያቱ ከኢማን ማእዘናት አንዱን አውግዟልና።

(3) ኑሕ ዓለይሂ ሰላም የመጀመርያውም መልእክተኛ ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ቃል ነው: **{እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን።...}** (አን-ኒሳእ 163)

የነብያቶች መጀመርያ ደሞ አደም ነው። ማስረጃውም «ነብዩ ﷺ ስለ አደም ነብይነት ተጠይቀው **"አዎ አላህ ያናገረው ነብይ ነው አሉ።"** »

የነብያቶችም የመልዕክተኞችም መጨረሻ ደሞ ሙሓመድ ﷺ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ቃል ነው: {ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው።...} (አል-አሕዛብ **40)**

ከነብዩ ﷺ በኃላ ነብይነትን ወይም መልዕክተኝነትን የሞገተ ውሸታምና ካፊር ነው። ሙግቱን የተቀበለውም እንደሱው ከሃዲ ነው።

የሰው ልጆች ከሞቱ በኃላ ይቀሰቀሳሉ፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው። **{ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ። በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን። ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን።}**(ጣሀ 55)
እንዲሁም **{አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ። (17) ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል። ማውጣትንም ያወጣችኋል።}** (18)(ኑሕ 17-18)
ከመቀስቀስ በኃላ በስራቸው የሚተሳሰቡ እና የሚመነዱ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በሰማያት ያለውና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያን ያጠፉትን በሠሩት ሊቀጣ እነዚያን ያሳመሩትንም በመልካሚቱ (ገነት) ሊመነዳ (የጠመመውንና የቀናውን ያውቃል)።}**(አን-ነጅም 31) (1)
ሞቶ በመቀስቀስ ያስተባበለ (በእስልምና)ክዷል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{እነዚያ የካዱትን በፍጹም የማይቀሰሱ መኾናቸውን አሰቡ። «አይደለም በጌታዬ እምላለሁ። በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ። ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ። ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው።»} በላቸው።}** (አት-ተጋቡን 7) (2)
አላህ መልእክተኞችን በሙሉ አብሳሪ እና አስጠንቃቂ አድርጎ ነው የላካቸው፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{...አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)}** (አል-ኒሳእ 165)
የመጀመርያቸው ኑሕ ዓለይሂ ሰላም ሲሆን የመጨረሻቸው ሙሓመድ ﷺ ነው። የነብያት መደምደምያም እሱው ነው።
የመጀመርያቸው ኑሕ ዓለይሂ ሰላም ለመሆኑ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን።...}** (አን-ኒሳእ 163) (3)

በባርያዎች ሁሉ በጣኦት መካድንና በአላህ ማመንን ግዴታ አድርጎባቸዋል። ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል: “ጧጉት” ማለት አንድ ባርያ በአምልኮትም ይሁን በመከተል አልያም በመታዘዝ በኩል ወሰኑን ያለፈበት ማለት ነው።

ለሁሉም ህዝብ ከኑሕ ጀምሮ እስከ ሙሓመድ ድረስ አንዱን አላህን ብቻ በማምለክ የሚያዘዛቸውና ጧጉትን ከማምለክ የሚከለክላቸው መልዕክተኛ ተልኳል።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።...}** (አል-ነሕል 36)

ጧጉቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። በአላህ የተረገመው ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው...ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ።...}** (አል-በቀራህ 256)

ይህ ነው የ ላኢላህ ኢለሏህ ትርጉም። በሓዲሥም **“የጉዳዮች ራስ ኢስላም ነው፤ ምሰሶው ሶላት ነው፤ ሻኛው ደሞ በአላህ መንገድ መታገል ነው።”**

አላህ መልእክተኞችንና ነብያቶችን አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርጎ ላካቸው። ሁላቸውም ደሞ ወደ ተውሒድ በሚደረግ ጥሪና ጧጁትና ሽርክን በየአይነቱ በመዋጋት በኩል አንድ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ... መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።...}**(አል-ነሕል 36) በእያንዳንዱ ህዝብ ማለት ነው። **{...أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ}** **{«አላህን ተገዙ፤... በማለት}** ማለትም የአላህን አሃዳዊነት አፅኑ። **{وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ...}**[النحل: ٣٦] **{...ጣዖትንም ራቁ»}** ማለትም ጣኦታትን በአንድ በኩል አድርጋችሁ እናነተ በሌላኛው በኩል ሁኑ። ይህ በማስጠንቀቅና ከነሱ በማስራቅ በኩል ዲካ የደረሰ እና ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች የመጥራራት ፅኑነት ነፀብራቅ ነው።

አላህ በመላ ባርያዎቹ ላይ በጧጉት መካድን እና በአላህ ማመንን ግዴታ አድርጓል። በአላህ ከማመን በፊት በጧጉት መካድ የግድ ነው። **«...በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው...»** (አልበቀራ 256)

ጧጉት: ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን የተላፈበት ማለት ነው። በማምለክ ሊሆን ይችላል (ድንጋይና ዛፍን ይመስል) ፣ በተከታይነት ሊሆን ይችላል (ክፉ ምሁራኖች መከተልን ይመስል) ፣ ወይም በመታዘዝም ሊሆን ይችላል (ከአላህ ትእዛዝ የሚያስወጣን ትእዛዝ መታዘዝን) ይመስል።

ጧጉቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። በአላህ የተረገመው ኢብሊስ [ሸይኹ በመንገር መልክ እየረገሙት ነው] ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።

አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ መፍረድ ሲባል

ትልቁ ኩፍር

“የሰው ልጅ ህግ እንደአላህ ህግ ነው” ወይም “ከዛ በላይ ነው” ብሎ የሚያምን ከሆነ

ትንሹ ኩፍር

“አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ መፍረድ ውዳቂ ነው” ብሎ እያመነ ነገር ግን በስሜቱ ተታሎ፣ ወይ በስልጣን ፍቅር፣ ወይም ከዚህ ውጭ በሆኑ (መሰል) ምክንያቶች ከሆነ ነው።

ኢማም ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንላቸውና ጅሃድን ወደ አራት ይከፍሉታል

ነፍስያን መታገል:

በማወቅ፣ በመተግበር፣ ዳዕዋ (ጥሪ) በማድረግና በመታገስ የሚሆን ነው።

ሸይጧንን መታገል:

ውዥንብሮችን (ሽርክና ቢድዓ) እና ስሜታዊነትን (ትላልቁንም ትናንሹንም) በመተው።

ካፊሮችንና ሙናፊቆችን መታገል:

በልብ፣ በአንደበት፣ በገንዘብና በነፍስ የሚሆን ነው።

የበደል፣ የቢድዓና የዉግዝ ነገራቶች ባላባቶችን መታገል

በልብ፣ በአንደበት፣ በገንዘብና በነፍስ የሚሆን ነው።

መደምደምያ

አስተዋይ ሁሉ ይህንን ታላቅ ፅሁፍ እያንዳንዱ ሰው ቀብሩ ላይ ለሚያስፈልገው ከያዘው ትላልቅ መሰረቶች አንፃር ሊያገናዝበውና እጅግ በጣም ልዩ ትኩረት ሊቸረው ግዴታ ነው።

ይህን (ይመስላል)፤ የአላህ ሶላዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን

ማጠቃለያ በሰንጠረዥ

ሶስቱ መሰረቶች (በአጭሩ የቀብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሶስቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?	አራቱ ቁምነገሮችና ማስረጃቸው (ሱረቱል ዓስር)	እውቀት	ያም አላህን ማወቅ፣ ነብዩን ﷺ ማወቅና ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ ነው። (ሶስቱን መሰረቶች)
		በሱው መስራት	“እውቀት ተግባርን ጥሪ ያደርግለታል፤ ምላሽ ከሰጠው (ይቀጥላል) አለበለዚያ ግን ይተወዋል።” እውቀት ኖሮት በእውቀቱ ያልሰራ ከጣኦት አምላኪ በፊት አለለት ኪሳራ
		ወደሱ ጥሪ ማድረግ	የዳዕዋ ቅድመ መስፈርቶች: የአላህን ፊት ብቻ መፈለግ፡ ሸሪዓዊ እውቀት መኖር፡ ዳዕዋ የሚደረግለትን ሰው ሁኔታ ማወቅ፡ ጥበብ መላበስ፡ እና ትእግስት።
			አስቀድሞ ዳዕዋ የሚደረግበት ጉዳይ ተውሒድ ነው፡ የነብያቶችና የመልዕክተኞች ፈለግም ዪህው ነው፡ ትልቁ የዳዕዋ እርከን ወደ ተውሒድ መጣራትና ሽርክን ማውገዝ ነው።
		ለሚያጋጥም ጫና መታገስ	አላህን በመታዘዝ ላይ መታገስ፡ (ሶላትን ይመስል)፡ አላህን ከማመፅ (ወለድን ይመስል)፡ እንዲሁም በአላህ ቀደር ላይ (ድህነትን ይመስል)።
			በ እውቀት ላይ መታገስ፡ ከዚያም በመልካም ስራ፡ ከዚያም በዳዕዋ ላይ
	ሶስቱ ነጥቦች	የጌትነት አሃዳዊነቱ (በጌትነቱ ብቸኛ የተደረገ የማድ በአምላክነቱም ብቸኛ ሊደረግ ይገባዋል) እና በስምና ባህሪያት አሃዳዊነቱ	
		የአምልኮ አሃዳዊነቱ(ኢኽላስ)፡ አላህ በአምልኩው ማንም እንዲጋራው አይፈልግም፡ ቅርብ መላኢካም ይሁን የተላከ ነብይ	
		ከሽርክ እና ክሽርክ ሰዎች መጥራራት; በልቦና (ካፊሮችን መጥላት)፡ በአንደበት (እኔ ከምትገዙት ሁሉ ንፁህ ነኝ)፡ እንዲሁም በተግባር (በበአላቶቻቸውና በስነስርአቶቻቸው ባለመሳተፍና እነሱን ባለመመሰሰል)	

ሶስቱ መሰረቶች (በአጭሩ የቀብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሶስቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?	ተውሒድን የመማር አስፈላጊነት	(ሓኒፊያህ): ከሽርክ ያዘነበለችና በኢኽላስና በተውሒድ ላይ የተገነባች መንገድ
		ተውሒድ በቋንቋ ደረጃ: ስርወ ቃሉ ወሐደ፡ ዩወሒዱ ተውሒደን ከሚለው የመጣ ሲሆን ብቸኛ አደረገ እንደማለት ነው **እንደሸሪዓ**: አላህን በሚነጠልባቸው ነገሮች በጌትነቱ በአምላክነቱ እና በስምና ባህሪያቱ ቢቸኛ ማድረግ ማለት ነው። ሶስት አይነት ነው፡
		1. **ተውሒዱ ሩቡቢያ**: አላህን በድርጊቶቹ መነጠል፡ እንደመፍጠርና ንግስና እንዲሁም ማስተናበርን ይመስል። 2. **ተውሒዱል ኡሉሂያህ**: አላህን በአምልኮ መንጠል 3. **ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት**: አላህን ራሱን በኪታቡ ወይም በመልዕክተኛው ﷺ አንደበት በገለፀበትና በሰየመበት መልኩ ብቸኝነቱን ማፅደቅ ማለት ነው። ይህም ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅና ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ያላንዳች ማዛባትና ውድቅ ሳያደርጉ እንዲሁም ያላንዳች ሁኔታ መግለፅ ውስጥ መግባትና ያለማመሳሰል ነው።
		ሽርክ ማለት ከአላህ ጋ ሌላን አካል መጣራት ማለት ሲሆን ምድር ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች ከባዱ ነው።
	ሶስቱ መሰረቶች	ጥራት ይገባውና አላህን ማወቅ፡ ሲባል ጌታህ ማን ነው? ጌታህን በምን አወቅከው? ጌታ ተመላኪው ነው። የአምልኮ አይነቶች፡ ከአምልኮ አይነቶች አንዳች ነገርን ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው? ከማስረጃ ጋ
		ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ፡ ሲባል የኢስላም ፍች፡ የዲን እርከኖች፡ የኢስላም ማእዘናት፡ የምስክርነት ቃል(የሸሃዳ) ፍች፡ የኢማን ማእዘኖች እና ቅርንጫፎቹ፡ ኢሕሳን፡ የዲን እርከኖች ማስረጃቸው እንዲሁም የመጨረሻው ቀን ምልክቶች
		መልዕክተኛውን ﷺ ማወቅ: ሲባል የዘር ግንዳቸውን፣ የተወለዱበትን ማወቅ፣ ዕድሜያቸውን፣ ነብይና መልዕክተኝነታቸውን፣ አገራቸውን፣ የመላካቸው ጥበብ፣ ለተውሒድ ዳዕዋ ያሳለፉትን ጊዜ፣ ኢስራእ እና ሜዕራጅ፣ ሶላት መቸ የት ተደነገገች? ሂጅራ ማድረግ ፍርዱና ጊዜው፣ ሌላው ዲንጋጌ መቸ ግዴታ ሆነ? የዳዕዋ ቆይታቸው፣ ህልፈታቸው፣ ይዘውት የመጡት ዲን፣ በጥቅሉ ለሁለቱም ከባባዶች(ሰውና አጋንንት) መላካቸው፣ የዲኑ ሙሉነትና የፀጋ መሟላት ማወቅ ነው።

ማጠቃለያ	ከሞት በኋላ መቀስቀስና ስራን መተሳሰብ፡ ሞቶ በመቀሰቀስ የሚያስተባብል ከሃዲ መሆኑ፡ የመልዕክተኞች ሃላፊነትና ዳዕዋቸው፡ የመልዕክተኞች መጀመሪያና መደምደሚያ፡ ሁለቱ የተውሒድ ማእዘናትበጢጉት መካድና በአላህ ማመን፡ የጢጊት ፍች፡ የጢጊት ራስ የሚባሉት፡ በጢጊት የመካድ ሁኔታው፡ የላኢላሃ ኢለሏህ ትርጉም፡ ኢስላም የዲኑ የበላይ መሆኑ፡ የዲን ምሰሶ ሶላት፡ የዲኑ ሻኛ ጅሃድ ላይ መሆኑ።			
የመፋለም አይነቶች	ነፍስያን መታገል	ሱረቱል ዓስር ላይ በተጠቀሰው መልኩ መታገል (ማወቅ፣ (ባወቁት) መስራት፣ ወደሱው መጥራት፣ መታገስ)		
	ሸይጧንን መታገል	ስሜት	ከባባድ ወንጀሎች (ልዩ መቀጣጫ የመጣባቸው ሁሉ)	
			ትናንሽ ወንጀሎች (ልዩ መቀጣጫ ያልመጣበት ዉጉዝ ነገር ሁሉ)	
		ውዥንብሮች	ትልቁ ሽርክ (ከእስልምና ያስወጣል) እና ትንሹ ሽርክ	
			ቢዳዓዎች(መጤዎች)	
	ካፊሮችን እና ሙናፊቆችን መታገል	በልቦና፣ በአንደበት፣ በአካልና በገንዘብ የሚሆን ነው		
	የበደል፡ የቢዳዓ እና የተወገዙ ነገራቶች ባላባቶችን መታገል	በእጅ፣ በአንደበትና በልቦና የሚሆን ነው		
ጢጉት	ጢቹት: ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን የተላፈበት ማለት ነው። በማምለክ ሊሆን ይችላል (ድንጋይና ዛፍን ይመስል)፣ በተከታይነት ሊሆን ይችላል (ክፉ ምሁራኖች መከተልን ይመስል)፣ ወይም በመታዘዝም ሊሆን ይችላል (ከአላህ ትእዛዝ የሚያስወጣን ትእዛዝ መታዘዝን ይመስል)።			
ሰነቱ መሰረቶቹ (በአጭሩ የቁብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሰነቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?				

ጢቹቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። የአላህ እርግማን ይስፈንበትና [ከመንገር አንፃር እየረገሙት ነው]ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።

አላሁ አዕለም የአላህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን

የሶስቱ መሰረቶችና ማስረጃቸው ፈተና

በቅንፉ ወስጥ ካሉት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

(1) የኡሱሉ ሠላሣ / ሶስቱ መሰረቶች ኪታብ ፀሃፊ ስም (ሙሓመደ ቢን ሱለይማን አትተሚሚይ~ሙሓመድ ቢን ዓብዱልወሃብ~የተጠቀሱት ሁሉ)።

(2) ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ አገላለፅ የቀብር ጥያቄዎች ማለት ነው? (እውነት – ሃሰት).

(3) ሽይኹ ብኡሱሉ ሠላሣ ውስጥ ለሚቀራው ሰው ዱዓ ያደረጉለት (በሁለት ቦታ – በሶስት ቦታ).

(4) የሽይኹ ኪታቦች የሚለዩት (በቀላልነታቸው – ጥቅል በሆነ መልኩ ካስቀመጡ በኋላ ዝርዝር ዉስጥ የሚገቡ በመሆናቸው - ማስረጃቸው ከቁርአን እና ከሓዲሥ በመሆኑ – ለተማሪ በሚያደርጉት ዱዓ – ወቅታዊ ውዝንብሮች ላይ በሚሰጡት ረድ-በትንታኔዎቹ ብዛት – አንገብጋቢ ጥያቄዎችን እያነሱ በሚሰጡት ምላሽ – አላህ በለገሳት ተቀባይነት – ሁሉም).

(5) "አል ኡሱሉ ሠላሣ" ሶስቱ መሰረቶች የሚለውን ኪታብ ወደ 5 ና 6 ምዕራፍ ከፋፍለን ማየት እንችላለን። (እውነት – ሃሰት)

(6) ተውሒድን መማር (ግለሰባዊ ግዴታ/ፈርዱ ዓይን – ማህበራዊ ግዴታ/ፈርዱ ኪፋያ)።

(7) የአራቱ ቁምነገሮች ማስረጃ (ሱረቱል ዓስር – ሱረቱል ኢኽላስ).

(8) አውቆ የማይሰራበት ተመሳሳይነቱ (ከክርስቲያኖች ጋ – ከአይሆዶች ጋ – ሁሉም መልስ ነው).

(9) ትእግስት ወደ (ሁለት – ሶስት) ይከፈላል

(10) ሱረቱል ዓስርን በማስመልከት የኢማም ሻፊዒይ ንግግር መልዕክት: ("ሑጃ" ለማቆም/ ለማስረጃነት በቂ ነች– ከሌሎቹ ሱራዎች ታብቃቃለች)።

(11) ከተውሒድ ክፍሎች አንዱን ብቻ የያዘ ተውሒድን ይዟል ሊባል አይችልም (እውነት – ሃሰት)

(12) ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት የሚሆነው በ (ልቦና፣ በአንደበትና በተግባር – ከስራውና ከሰሪው በመጥራራት – ሁሉም መልስ ነው)

(13) "እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው" በአንቀፁ መሰረት "መስጊዶች" በማለት የተፈለገበት (የተገነቡ መስጅዶች – የሱጁድ አካላት – ሱጁድ የሚደረግባቸው ቦታዎች - ሁሉም)

(14) የሰለፎች አካሄድ የሆነው: (ማስረጃን ካስደገፉ በኋላ ማመን – ካመኑ በኋላ ማስረጃን መፈለግ)

(15) ከሙስሊም ዑለሞች ሆኖ የጠመመ ተመሳሳይነቱ ከ (አይሁዶች ⁄ – ክርስቲያኖች ⁄).

(16) ከሙስሊም ዓቢዶች መካከል ሆኖ የጠመመ ተመሳሳይነቱ (ከአይሁዶች ⁄ – ከክርስቲያኖች ⁄)

(17) ሶስቱ ቁምነገሮች የተባሉት ሶስቱን መሰረቶች ነው (እውነት – ሃሰት).

(18) የዱዓ አይነቶች (የአምልኮ ዱዓና የልመና ዱዓ ፤ የቀጥታ ዱዓ እና ዱዓ በተዘዋዋሪ)

(19) የልመና ዱዓ አይነቶች (ሁለት – አራት)

(20) ሰዎች ሰበብን በማስመልከት አይነታቸው (ሁለት ፅንፈኞችና አንድ ሚዛናዊ – ትልቁ ሸርክ፣ ትንሹ ሸርክና የሚፈቀድ)

(21) ፍጡራንን በጭንቅ ድረሱልኝ ማለት የሚቻለው (በልቁ ያለገደብ – በሚችሉት - ከአራቱ ቅድመ ሁኔታዎች አንፃር የሚችል ከሆነ)

(22) የ “ላኢላሃ ኢለሏህ” ትርጉም (አላህ ከተለምዶ መውጣት የሚችል መሆኑ – ከአላህ ውጭ የሚመለክ የለም - ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም – ሁሉም መልስ ነው)

(23) በሃይማኖቶች ማስማማት ማለት (ይፈቀዳል – ከባድ ወንጀል – ክህደት)

(24) ስለ አላህ ህልውና ማስረጃዎች በጥቅሉ (ብዙ ናቸው – አራት ናቸው)

(25) መላኢኮች ልቦና አላቸውን? (አዎ – አይ)

(26) በኢማንና በተውሒድ መካከል ያለው ቁርኝት: ኢማን ጥቅል ሲሆን ተውሒድ የሱ ክፋይ ነው (እውነት – ሃሰት)

(27) የኢማን ማእዘናት (5, 6, 8)

(28) ሙሽሪኮች የሆነ ያክል አላህን ያመልካሉ (እውነት – ሃሰት)

(29) ከአላህ ዉጭ ሳይወድ የተመለከ(ጧጉት – ጧጉት አይደለም)

(30) በማስተናበርና ዝናብ በመልቀቅ አላህን መነጠል ተውሒዱል… (ኡሉሂያ/አምልኪዊ – ሩቡቢያ/የጌትነት – አስማኢ ወሲፋት/ስምና ባህሪያት).

(31) የተውሒድን መሰረት ከሚንዱ መካከል (ትልቁ ሸርክ - ትንሹ ሸርክ – ቢድዓ)

(32) የግዴታዎች ሁሉ ግዴታ ለወላጆች መልካም መዋል ነው። (እውነት – ሃሰት)

(33) ከሓራም ነገራቶች ሁሉ የከፋው ዝሙትና አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል ነው (እውነት – ሃሰት)

(34) ሚዕራጅ ማለት ነበዩ ሶለሏሁ ዓለይሂ ውሰለም ከመካ ወደ በይተል መቅዲስ ያደረጉት ጉዞ ነው (እውነት – ሃሰት)

(35) ነብዩ ﷺ የተላኩት (ውደ ህዝባቸው ብቻ – ወደ ሰው ልጆችና አጋንንቶች)

(36) ነብዩ ﷺ (ሙተዋል – ነብያቶች አይሞቱም)

(37) ሞቶ በመቀስቀስ ያስተባበለ ሰው ክህደቱ (ትልቁን ክህደት – ትንሹን ክህደት)

(38) የነብያቶች ዲን (አንድ ነው – ለእያንዳንዱ ነብይ ዲን አለው)

(39) ሂጅራ(ስደት ማድረግ) (ከመካ መከፈት በኋላ ተቋርጧል – እስከመጨረሻው ቀን ድረስ ይቀጥላል)

(40) ሂጅራ ማለት (ከኩፍር አገር ወደተውሒድ አገር መሰደት ነው – አላህ ሓራም ያደረገውን መተው ነው)

(41) ዲነል ኢስላም ተሟልቷል ከደጋጎች ህልም በሚመጣ ካልሆነ በቀር (እውነት – ሃሰት)

(42) አምልኮን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠት ሽርክነቱ (ትልቁ – ትንሹ)

(43) በድርጊቱ ላይ ፍርድ መስጠትና በድርጊቱ ፈፃሚ ላይ ፍርድ መስጠት ልዩነት የለውም (እውነት –ሃሰት)

(44) የነብያቶች መጀመሪያ (ኑሕ ዓለይሂ ሰላም– አደም ዓለይሂ ሰላም)

(45) ነብያችን ﷺ (ነብይ ናቸው - መልዕክተኛ ናቸው)

በ ‘ሀ’ ረድፍ ላሉት በ’ለ’ ረድፍ ካሉት የሚዛመዳቸውን ፈልግ

ረድፍ ‘ሀ’	መልስ	ተራ ቁጥር	ረድፍ ’ለ’
ተውሒድ በቋንቋ ደረጃ		1	የኢማም አሕመድ “ካፊርን ባየሁ ጊዜ የአላህን ጠላት ላለማየት ብየ አይኖቸን እጨፍናለሁ።”
ተውሒድ በሸሪዓ ደረጃ		2	ከሞት በኋላ በሚሆነው ሁሉ ማምንን ያካትታል
ተውሒዱል ኡሉሂያ (የአምልኮ አሃዳዊነቱ)		3	በአንደበት የሚባል ቃል፣ በልብ አምኖ በልብም በአካልም መስራት፣ በታዛዥነት ይጨምራል በማመፅ ይቀንሳል
ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ)		4	ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን
ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (የስምና ባህሪያቱ አሃዳዊነት)		5	ለአላህም ከአላህ ዉጭ ላለ አካልም
ሓኒፊያ		6	ግዴታ የሆነ፣ የሚፈቀድና የተከለከለ
በቁርአን ላይ የመጀመሪያው ትእዛዝና ጥሪ		7	ሸሪዓዊና ተጨባጩ
ብጤ		8	የቀብር ጥያቄዎች
ኸሸየህ		9	ማወቅ፣ መተግበር፣ መጣራትና መታገስ
ተወኩል		10	የአላህን ፊት ብቻ መፈለግና ሱናን መግጠሙ
አምልኮ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ መሟላት ያለባቸው ሁለቱ ቅድመ መስፈርቶች		11	ሰበቦችን እያደረሱ በአላህ ላይ ተማምኖ እሱ ላይ እውነተኛ መደገፍ ማለት ነው
የአራቱ ቁምነገሮች በአጭሩ		12	የሚፈራውን አካል ታላቅነትና ልዕለ ሃያልነት በማስመልከት እውቀት ላይ ተመርኩዞ መፍራት

ሶስቱ ነጥቦች በአጭሩ		13	አምሳያ፣ እኩያ፣ ምሳሌ
ሶስቱ መሰረቶች በአጭሩ		14	ሱረቱል በቀራህ
የሰበብ አይነቶች		15	ከሽርክ ያዘነበለችና በኢኽላስና በተውሒድ ላይ የተገነባች መንገድ
የስለት አይነቶች		16	አላህን ራሱን በኪታቡ ወይም በመልዕክተኛው ﷺ አንደበት በገለፀበትና በሰየመበት መልኩ ብቸኝነቱን ማፅደቅ ማለት ነው። ይህም ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅና ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ያላንዳች ማዛባትና ውድቅ ማድረግ እንዲሁም ያላንዳች ሁኔታ መግለፅ ውስጥ መግባትና ያለማመሳሰል ነው።
የእርድ አይነቶች		17	አላህን በአምልኮ መነጠል
የኸውፍ አይነቶች		18	አላህን በመፍጠር፣ በንግስናውና በአስተናባሪነቱ መነጠል
ኢስላም		19	አላህን በሚነጠልበት ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው
የዲን እርከኖች		20	ስርወ ቃሉ ‘ወሐደ’ የሚል ሲሆን መነጠል ማለት ነው
ኢማን		21	ፀሃይ በመግቢያዋ መውጣቷና ሞት አፋፍ ላይ መሆን
በመጨረሻው ቀን ማመን የሚያካተው		22	ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን ያለፈበት ማለት ነው። በማምለክ ወይም በተከታይነት አልያም በመታዘዝ ሊሆን ይችላል
ከሽርክ ሰዎች መጥራራት ፅኑነት አንፃር		23	ተውሒዱ ሩቡቢያ እና ተውሂዱል አስማኢ ወሲፋት፣ ተውሒዱል ኡሉሂያ እንዲሁም ከሽርክና ክሽርክ ሰዎች መጥራራት
ተውባ የሚቋረጥበት ገዜ		24	ራስን ለአላህ በተውሒድ ማስገዛት፣ በታዛዥነት ለሱ መጎትተ ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት
ጂጉት		25	ቅርፅ ኖሮት ከአላህ ውጭ የተመለከ

አራቱ መርሆዎች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው፤ እናመሰግነዋለን፣ እገዛውን እንጠይቀዋለን፣ መሃርታውን እንለምነዋለን፣ ከነፍሳችን ክፋትና ከክፉ ስራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራውን የሚያጠም የለውም፤ ያጠመመውንም የሚመራ የለውም፤ ከአላህ ውጭ (በእውነት) የሚመለክ እንደሌለ ብቸኛና ተጋሪ የሌለው መሆኑንና ሙሓመድም ﷺ ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በመቀጠል፡

የትንታኔው መግቢያ

የዚህ ፅሁፍ ደራሲ

ሸይኹል ኢስላም፤ የተውሒድ ጥሪ የተሃድሶ መሪ(ሙጀዲድ)፤ ኢማም ሙሓመድ ቢን ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ፤ በቅፅል ስማቸው አቡ-ል-ሑሰይን (ይባላሉ)።

በዑየይና መንደር በ1115 ዓ. ሒ. ተወልደው በ1206 ዓ. ሒ. ሞቱ።

«አራቱ መርሆዎች» ከተከታታይ የተማሪዎች ትምህርት ሁለተኛዋ ነች፤ ይህ ፅሁፍ ትኩረት የተቸረበት በርከት ያሉ ምክንያቶች አሉት፡ ከነሱም፡

- ዑለሞች እንድንማረው በመምከራቸው
- በደጋግ ቀደምት አበው (ሰለፍ) ዑለሞች ከመመራት አንፃር
- በወቅታዊ ሙሽሪኮች ውዥንብር ላይ መልስ ስላለበት
- የከሸፉ-ሽ-ሹቡሃት አጭር ጭብጥ ከመሆኑ አንፃር
- ከሸፉ-ሽ-ሹቡሃትን ከማስተማራችን በፊት ተማሪው ላይ ውዥንብር እንዳይቀርበት በዚህ እንጀምራለን



የአራቱ መርሆዎች ማውጫ
ይህ ፅሁፍ ወደ ሶስት ይከፈላል፤ እነሱም:

- (1) መግቢያ (የስኬት ርእስ)
- (2) ተውሒድን የመማር አንገብጋቢነት
- (3) መርሆዎቹ



መጀመርያ: መግቢያ (የስኬት ርእሶች)

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው (1) ቸሩ አላህን የታላቁ ዓርሽ ጌታን በዱንያም በአኼራም ይወዳጅህ ዘንድ (2) የትም ብትሆን የተባረክ ያደርግህ ዘንድ እለምነዋለሁ። (3)

(1) ሸይኹ ፅሁፉ በቢስሚላህ የጀመሩበት ምክንያት

{1} በአላህ መፅሃፍና በነብያቶች (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር

{2} ከሱ በፊት ፅሁፎቻቸውን በቢስሚላህ መጀመር ልምዳቸው በነበሩ ቀደምትና ዑለሞች ከመከተል አንፃር

{3} በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ "አላህን የሚፈራ ሙእሚን (ሁሉ) የአላህ ወዳጅ (ወልይ) ነው።" ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {﴿أَلَا إِنَّ أَولِيَاءَ اللَّهِ لَا خَوفٌ عَلَيهِم وَلَا هُم يَحزَنونَ۝الَّذينَ آمَنوا وَكانوا يَتَّقونَ﴾[يونس: ٦٢-٦٣]} {ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም።(62) (እነሱም) እነዚያ ያመኑትና ይፈሩት የነበሩ ናቸው።}(ዩኑስ 62-63)

በረካ: መፋፋትና መጨመር ማለት ነው

ተበሩክ: መፋፋትንና መጨመርን መፈለግ

ሙባረክ: የትም ሆኖ በዛው(በበረካው) የሚጠቀም

ተበሩክ ለሁለት ይከፈላል

የተደነገገ ተበሩክ:

- ተጨባጭ: እውቀትና ዱዓን የመሰሉ፤ አንድ ሰው በእውቀቱ በረካ ሊገኝ ይችላል፣ ወደ መልካም ነገር በሚያደርገው ጥሪ ሊሆን ይችላል። የዚህኔ በረካ ይሆናል። ምክንያቱም ብዙ መልካም ነገርን አግኝተንበታልና። እንደሸይኹል ኢስላም ኪታብና መሰል አላህ በረካንና ኸይርን በኪታቦቻቸው ላይ ያሰፈነባቸው እንዲሁም ኡማው የተጠቀመባቸው ዑለሞች።
- ሸሪዓዊ: በመስጅደል ሓራም ወይም በመስጅደ ነበውይ መስገድን ይመስል

የተከለከለ ተበሩክ: በተጨባጭም ይሁን በሸሪዓው ያልፀና ሲሆን ከትንሹ ሽርክ አይነቶች የሚመደብ ነው።

...ሲሰጡ ከሚያመሰግኑ ያደርግህ ዘንድ... (1)

(1) ፀጋም ፈተና ነው፤ በርካታ ማስረጃ ያለው ሲሆን ከነዚህም: {﴿...وَنَبلوكُم بِالشَّرِّ وَالخَيرِ فِتنَةً وَإِلَينا تُرجَعونَ﴾[الأنبياء: ٣٥]} {...ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን። ወደኛም ትመለሳላችሁ።}(አል-አንቢያእ 35) {﴿...فَلَمّا رَءاهُ مُستَقِرًّا عِندَهُ قالَ هذا مِن فَضلِ رَبّي لِيَبلُوَني أَأَشكُرُ أَم أَكفُرُ وَمَن شَكَرَ فَإِنَّما يَشكُرُ لِنَفسِهِ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ رَبّي غَنِيٌّ كَريمٌ﴾[النمل: ٤٠]} {...እርሱ ዘንድ ረግቶ ባየውም ጊዜ «ይህ ከጌታዬ ችሮታ ነው። የማመሰግን ወይም የምክድ መኾኔንሊሞክረኝ (ቸረልኝ)። ያመሰገነም ሰው የሚያመሰግነው ለራሱ ነው። የካደም ሰው ጌታዬ ከእርሱ ተብቃቂ ቸር ነው» አለ።}(አል-ነምል 40) {﴿فَأَمَّا الإِنسانُ إِذا مَا ابتَلاهُ رَبُّهُ فَأَكرَمَهُ وَنَعَّمَهُ فَيَقولُ رَبّي أَكرَمَنِ﴾[الفجر: ١٥]} {ሰውማ ጌታው በሞከረው ጊዜ፣ ባከበረውና ባጣቀመውም (ጊዜ) «ጌታዬ አከበረኝ (አበለጠኝ)» ይላል።}(አል-ፈጅር 15)

በሓዲሥም: «ከበኒ እስራኢሎች የሆኑ ሶስት ሰዎችን አላህ ሊፈትናቸው...»
ፀጋ ከተውሒደል ሩቡቢያና ከተውሒደል ኡሉሂያ ጋ የተቆራኘ ሲሆን ሹክርም ደሞ ሁለት አይነት ነው:
ከፀጋ በፊት ከአላህ ጋ ተሳሰር

- ይህ አይነቱ ከባርያ ፀጋን የሚለግሰው አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን ቁርጥ ያለ እምነት ይጠይቃል። ልቦናው ከአላህ ውጭ ባለ አካል አይንጠለጠልም፤ ኸይርንም ከሱ ቢሆን እንጅ አይከጅልም።

ባለቤቱ እሱ በመሆኑ ጀነት የምትፈለገው ከሱ እንደሆነው ሁሉ ሲሳይም ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ እንጅ ሊፈለግ አይገባውም።
{{وَتَوَكَّل عَلَى الحَيِّ الَّذي لا يَموتُ...﴾ [الفرقان: ٥٨]} {በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ።...} (አል-ፉርቃን 58)
{﴿...إِنَّ الَّذينَ تَعبُدونَ مِن دونِ اللَّهِ لا يَملِكونَ لَكُم رِزقًا فَابتَغوا عِندَ اللَّهِ الرِّزقَ...﴾ [العنكبوت: ١٧]}
{...እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዙዋቸው ለእናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም። ...} (አል-ዓንከቡት 17) ማለትም ሲሳይ ከሌላ ሳይሆን ከሱ (ፈልጉ) {﴿...وَاعبُدوهُ
﴿...وَاشكُروا لَهُ إِلَيهِ تُرجَعونَ﴾ [العنكبوت: ١٧]} {...ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ዘንድ ብቻ ፈልጉ፡ ፡...} (አል-ዓንከቡት 17)
ፀጋው ከተከሰተ በኃላ ሹክር (ማድረግ) ይህም:

- በልቦና: ሲሳይ ለጋሹ ባለውለታ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን እውነተኛ በሆነ እምነትና ሙሉ በሆነ መማረክ ነው። በአንድ ባርያ ላይ ያለው ፀጋ ሁሉ ከአሏሁ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን አምኖ መቀበል።
- በአንደበት: የአላህን ፀጋ በማመስገንና ስለፀጋው በማውራት፣ በማወደስ ነው። አላህ በቁርአኑ የሚከተለውን ስላለ: {﴿وَأَمّا بِنِعمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّث﴾ [الضحى: ١١]} {በጌታህም ጸጋ አውራ፤ (ማለጻት)።} (አል-ዱሓ 11)
- በአካል: ፀጋውን አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በሚያስደስተው ላይ ማዋል። ወደሱ ከመቅረብ አንፃር ታዛዥነትን አስታኮ እና ትእዛዙን በመከተል አመጉን ርቆ ማለት ነው።

... ሲፈተን ታጋሽ... (ነ)

ትእግስት በመላ ህዝብ መሰረት ግዴታ ስለሆነ ነው።
ሰዎች ዱንያ ላይ መከራ ሲያጋጥማቸው (ከሚያስተናግዱበት አንፃር) ለአራት ይከፈላሉ፤ እነሱም
ብስጩ
ታጋሽ
ደስተኛ
አመስጋኝ

(1) ብስጭት: ሓራም ነው፤ ከትላልቅ ወንጀሎች አንዱ ነው። እንዲሁም
በልቦና
በአንደበትና
በአካል የሚገለፅ ነው።
በልቦና መበሳጨት: ኢብኑል ቀይም አልጀውዝያህ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ[መልእክቱ]: "...አንዳንድ ጊዜ ሰው በአንደበቱ የማይለው ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እሱ ዘንድ ያለችው ነፍሱ ግን ጌታውን በማስመልከት ያለውን መጥፎ ጥርጣሬ ታጋልጥበታለች። በውስጡ 'ጌታየ በድሎኛል!' 'ጌታየ ከልክሎኝ ነው!' 'ጌታየ ነው ያቀበኝ!' ይብዛም ይነስም ሌላም ሌላም ይላል።" ነፍስህን ፈትሻት ከዚህ ነፃ ነህ? ከሷ ከዳንክ በርግጥም ከከባድ ተርፈሃል።
በአንደበት መበሳጨት: ይህ በጩሀት፣ በሙሾ፣ 'ወይኔ' ወይም 'ወዮው!' በማለት፣ በመራገም፣ በመሳደብ የሚገለፅ ነው።
መበሳጨት በአካል: ደረትን በመደለቅ፣ አንገትያ (ልብስን) በመቅደድ፤ ፀጉርን በመንጨት የሚገለፅ ነው።
(2) ትእግስት: ፍርዱ በመላ ህዝብ ስምምነት መሰረት ግዴታ ነው። በልቦና፣ በአንደበቱና በአካሉ ትእግስትን መላበስ ግዴታው ነው። ኢማም አሕመድ እንዲህ ይላሉ "ትእግስት በቁርአን ወደ ዘጠና ጊዜ አካባቢ መጥቷል፤ የኢማን ግማሽ ነው። ኢማን ሲባል ሁለት ነውና: ግማሹ ትእግስት ግማሹ ደሞ ምስጋና ነው።" (መዳሪጁ ሳሊኪን ኢብኑል ቀይም)
(3) ደስተኝነት: ኢስላማዊ ፍርዱ "ሙስተሓብ" (የተወደደ) ሲሆን ከትእግስት ከፍ ያለ ደረጃ አለው።
(4) አመስጋኝነት: ኢስላማዊ ፍርዱ "ሙስተሓብ" ሲሆን በላጩና የተሟላው ደረጃ ነው።

ሁለተኛ: አራቱ መርሆዎች
አላህ እሱን ለመታዘዝ ይግጠምህና እወቅ! ሓኒፍ (ወደ እውነት የተዘነበለች) የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ "አላህን በብቸኝነት ጥርት አድርገህ ማምለክ ነው።" አላህ የሰው ልጆችን በሙሉ ያዘዘውም በዚሁ ነው። ለሷም ነው የፈጠራቸው: ልክ ከፍ ያለው አላህ በተከታዩ አንቀፅ እንዳለው: {﴿وَما خَلَقتُ الجِنَّ وَالإِنسَ إِلّا لِيَعبُدونِ﴾ [ሱረቱ አዝ-ዛሪያት: 56]} {ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።}(ዛርያት 56)(1)

አላህ የፈጠረህ እሱን ልታመልከው መሆኑን ከተረዳህ አምልኮ ከተውሒድ ጋ ካልሆነ አምልኮ እንደማይባልም እወቅ። ልክ ሶላት ከጡሀራ ውጭ ሶላት ልትባል እንደማትችለው ሁሉ። አምልኮ (ዒባዳ) ላይ ሽርክ ከገባበት ይበላሻል ነጂሳ እንዳረፈበት ጡሀራ ማለት ነው። አምልኮ ላይ ሽርክ ከታከለበት እንደሚያበላሻት፣ ስራን እንደሚያጠፋና ባለቤቱንም እሳት ላይ ዘውታሪ እንደሚያደርገው ካወቅክ ይበልጥ የሚያሳስብህ ጉዳይ ጉዳዩን ማወቅ መሆኑን ተረዳህ ማለት ነው። ምናልባት አላህ ከዚህ ሽርክ ከሚባለው ሰንሰለት ቢያተርፍህ፤ ያን በማስመልከት አላህ ተከታዩ አንቀፅ ያስተላለፈበትን: {﴿إِنَّ اللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِ وَيَغْفِرُ ما دونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشاءُ...﴾[النساء: ٤٨] አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። ...}(አል-ኒሳእ 48)

ይህም አላህ በቁርአን የጠቀሳቸውን አራት መርሆዎችን በመረዳት ነው።

የመጀመርያው መርህ: እነዚያ የአላህ መልዕክተኛ የተፋለሟቸው ከሀዲያን አላህ ፈጣሪና አስተናባሪ መሆኑን የሚያፀኑ ሆነው ሳለ ወደ ኢስላም አላስገባቸውም። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {﴿قُل مَن يَرزُقُكُم مِنَ السَّماءِ وَالأَرضِ أَمَّن يَملِكُ السَّمعَ وَالأَبصارَ وَمَن يُخرِجُ الحَيَّ مِنَ المَيِّتِ وَيُخرِجُ المَيِّتَ مِنَ الحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ الأَمرَ فَسَيَقولونَ اللَّهُ فَقُل أَفَلا تَتَّقونَ﴾[يونس: ٣١]} {«ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው» በላቸው። «በእርግጥም አላህ ነው» ይሉሃል። «ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ) አትፈሩትምን» በላቸው።} (የኑስ 31) (2)

(1) አላህ ይዘንለትና ሸይኹ ለምን ተውሒድ እንደምንማር እያብራሩ ነው።

(2) እነዚያ ነብዩ ከመሃላቸው የተላኩባቸው ህዝቦች በተውሒዱ ሩቡቢያ ያፀኑ ነበር፤ ይህ ከመሆኑም ጋ ግን የአላህ መልእክተኛ ﷺ ተፋለሟቸው። በነሱና በረሱል ﷺ መካከል የነበረው አለመግባባት ነጥብ ተውሒዱል ኡሉሂያን በማስመልከት ነበር። ከዒባዳ አንዳችንም ቢሆን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሰጠ መሸሪክ ከሃዲ ነው።

ሁለተኛው መርሆ: እነሱ የሚሉት "ወደነሱ የተቅጣጨንበትና እነሱን የለመንበት ምክንያት መቅረብንና ሸፈዓን ብቻ ፈልገን ነው።"

መቅረብን ፍላጎታቸው እንደሚያደርጉ ማስረጃው: {﴿...وَالَّذينَ اتَّخَذوا مِن دونِهِ أَولِياءَ ما نَعبُدُهُم إِلّا لِيُقَرِّبونا إِلَى اللَّهِ زُلفىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحكُمُ بَينَهُم في ما هُم فيهِ يَختَلِفونَ إِنَّ اللَّهَ لا يَهدي مَن هُوَ كاذِبٌ كَفّارٌ﴾[الزمر: ٣]} {...እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም።}(አልዙመር 3)(1)

ሸፋዐ (ምልጃ) ሁለት አይነት ነው: የፀና ሸፋዓ እና የተወገዘ ሸፋዓ ናቸው። (2)

(1) የሽርክና የክህደት ሰዎች ውድቅ የሆኑ አማልክቶቻቸውን አይጣሩ፤ ወደነሱ አልተቅጣጩ (ወደ አላህ) መቀራረብንና ምልጃን ፈልገው ቢሆን እንጅ። በዚህም ነብዩ ﷺ ዘንድ ካፊሮች ሊሆኑና ሊፋለሟቸው ተገባቸው።
(2) ሸፋዓ: በ(ዓረብኛ)ቋንቋ ደረጃ ነጠላን ጥንድ ማድረግ ማለት ሲሆን እንደሸሪዓው ለሌሎች ጥቅም ለማምጣት ወይም ክፋት ለመመከት አማካኝ መሆን ማለት ነው።

የምልጃ (ሸፋዓ) አይነቶች

የተወገዘ:
ቁርአን ያወገዛት አይነት ሸፋዓህ። ከአላህ ውጭ በማይችለው ጉዳይ ከሌላ አካል መፈለግ ነው። ኢስላማዊ ፍርዱ: ትልቁ ሽርክ

ፍጡራኖች በሚችሉት: አራት መስፈርቶች ከተሟሉ ይቻላል
- ያለ (ቅርብ)
- በሕይወት ያለ
- የሚችል
- ሰበብ (ተደርጎ ሊያዝ) ይገባል

የፀናች: ይህች ከአላህ የምተፈለገዋ ነች። እንደቅድመ መስፈርትም
- ለሸፋዓው አላህ ሊፈቅድ ይገባል
- ሸፋዓ አድራጊውን አላህ ሊወድለት(እውቅና ሊሰጠው)
- ሸፋዓ ለሚደረግለትም (ሊወድለት) ይገባል።

{በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች (ሊማለዱለት) ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ ቢኾን እንጅ ምልጃቸው ምንም አትጠቅምም።} (ነጅም 26)

አጠቃላይ መልእክተኞች፣ ነብያቶች፣ መላኢኮች፣ የተውሒድ ሰዎች እንዲሁም ህፃናቶች የሚያደርጉት ምልጃ
- የተውሒድ ሰዎች ደረጃ ከፍ እንዲል የሚደረግ ሸፋዓህ
- ከተውሒድ ሰዎች ሆኖ [ስራው] እሳት ያስፈረደበት እሳት እንዳይገባ
- እሳት የገባ የተውሒድ ሰው ከእሳት እንዲወጣ

ማንም ሳይጋራቸው ነብዩ ﷺ ብቻ የሚያደርጉት
- ትልቁ ሸፋዓህ
- ለአጎታቸው ቅጣቱ እንደቀንስለት ያደረጉት ምልጃ
- የጀነት በሮች እንዲከፈቱ የሚያደርጉት ምልጃ

ውግዝ የሆነችዋ ሸፋዓህ: አላህ እንጅ ሌላ በማይችለው ጉዳይ ከሌላ መፈለግ፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሽያጭ (መበዛት)፣ ወዳጅነትም፣ ምልጃም የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ። ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው።} (አልበቀራህ 254)
የፀናችዋ ሸፋዓህ: ከአላህ የምትፈለገዋ ስትሆን ሸፋዓህ አድራጊውን በሚያደርገው ሸፋዓህ የሚከበር ነው። ሸፋዓ የሚደረግለትም ደግሞ ከአላህ ፍቃድ በኃላ እና አላህ ተግባሩንም ንግግሩንም ለወደደለት ነው የሚሆነው። ልክ ከፍ ያለው አላህ በቁርአን እንዳለው: {...ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው} (በቀራህ 255)

ሶስተኛው መሰረታዊ መርህ: (1) ነብዩ ﷺ የወጡት በሚባዳቸው የተለያዩ በሆኑ ሰዎች ነው። ከነሱ መካከል መላእክቶችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ነብያቶችንና ደጋግ ሰዎችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ዛፎችንና ድንጋዮችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ፀሃይና ጨረቃ የሚያመከክ አለ፤ ነብዩ ﷺ ግን ልዩነር ሳይፈጥሩ ሁሉንም ነው የተፋለሚቸው።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {وَقاتِلوهُم حَتّىٰ لا تَكونَ فِتنَةٌ وَيَكونَ الدّينُ كُلُّهُ لِلَّهِ...﴾[الأنفال: ٣٩] {ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው።...}(አል-አንፋል 39)

ለፀሃይና ጨረቃ(መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {وَمِن آياتِهِ اللَّيلُ وَالنَّهارُ وَالشَّمسُ وَالقَمَرُ لا تَسجُدوا لِلشَّمسِ وَلا لِلقَمَرِ وَاسجُدوا لِلَّهِ الَّذي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُم إِيّاهُ تَعبُدونَ﴾[فصلت: ٣٧] {ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው። ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡ ፡ ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ። እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)።}(ፉሲለት 40)

ለመላእክቶች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {وَلا يَأمُرَكُم أَن تَتَّخِذُوا المَلائِكَةَ وَالنَّبِيّينَ أَربابًا...﴾[آل عمران: ٨٠] {መላእክትንና ነቢያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)።...}(አሊ-ዒምራን 80)

(1) ይህች መርሆ ሽርክ የሚሆነው ግኡዝ ጣኦትን በማምለክ ብቻ ነው በሚሉት ላይ "ረድ" ለማድረግ ግልፅና ጉልህ ማስረጃ ነች። ከድሮውም ሽሪዓዊ ማስረጃዎች የመጡት በተለይ ግኡዝ ጣኦታትን ሌሎቹንም ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ውዳቂዎችን አንድ ጉድጓድ ላይ ጨምሮ በማውገዝ ነው። የአላህ መልእክተኛ ﷺ በመካከል ልዩነት ሳይፈጥሩ ሁሉንም እንደጪጉት ቆጥረው አንድንም ሳያስቀሩ አምልኮ ሁሉ ለአላህ እንዲሆን ነው የተፋለሚቸው።

ለነብያቶች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {وَإِذ قالَ اللَّهُ يا عيسَى ابنَ مَريَمَ أَأَنتَ قُلتَ لِلنّاسِ اتَّخِذوني وَأُمِّيَ إِلـٰهَينِ مِن دونِ اللَّهِ قالَ سُبحانَكَ ما يَكونُ لي أَن أَقولَ ما لَيسَ لي بِحَقٍّ إِن كُنتُ قُلتُهُ فَقَد عَلِمتَهُ تَعلَمُ ما في نَفسي وَلا أَعلَمُ ما في نَفسِكَ إِنَّكَ أَنتَ عَلّامُ الغُيوبِ﴾[المائدة: ١١٦] {አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፦ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል።} (አል-ማኢዳህ 116)

ለደጋጎች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ። እዝነቱንም ይከጅላሉ። ቅጣቱንም ይፈራሉ።...} (አል-ኢስራእ 57) ለዛፍና ድንጋይ (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን?(19) ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?)} (አል-ነጅም 19-20)

በአቢ ዋቂዲን አለይሂይ ረድየሏሁ ዓንሁ ሓዲሥ እንዲህ የሚል ይገኛል “ለእስልምና (የእምነት) ቃል እንግዶች ሳለን ከነብዩ ﷺ ጋ ወደ ሑነይን ዘመቻ ወጣን። ለሙሽሪኮችም ደሞ እሷው ጋ የሚቀማመጡባትና ትጥቃቸውን የሚያንጠለጥሉባት የሆነች ‘ዛቱ አንዋጥ (የመንጠልጠል ባለቤት)’ የሚሏት የቁርቁራ ዛፍ አለቻቸው። በጉዟችን ሳለን የቁርቁራ ዛፍ በተመለከትን ጊዜ ‘የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! ለነሱ እንዳላቸው ለኛም የመንጠልጠል ባለቤት አድርጉልን’ አልናቸው።...” (ሓዲሡ ሱነን ቲርሚዚይ አብዋቡል ፊተን ሓዲሥ ቁጥር 2180 ላይ ዘግበውታል)

አራተኛው መርሆ: የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርክ ከቀደምቶች ሽርክ የበረታ ነው። ምክንያቱም ቀደምቶቹ ሽርክ የሚፈፅሙት በተድላ ጊዜ እንጅ በጭንቅ ጊዜ አላህን ጥርት አድርገው ነው የሚገዙት። የወቅቱ ሙሽሪኮች ግን ሽርካቸው ዘወትር በተድላም በጭንቅም ጊዜ ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል። ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ።}(አል-ዐንከቡት 65) (1)

አሏህ ይበልጡን ያውቃል፤ የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይስፈን።

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና በዚሁ መርሆ የወቅቱ ሙሽሪኮች አቋም አደገኝነት ልክ ግልፅ ማድረጉ ነው። ሽርካቸው ከቀደምቶች ሽርክ የከፋ ነውና። ምክንያቱን የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርካቸው በጭንቅም በተድላም ጊዜ ነው። የድሮ ሙሽሪኮች ሽርክ ግን ሲመቻቸው ነውንጅ የሚያጋሩት በጭንቅ ጊዜ በአላህ ብቸኛ ተመላኪነት ያምናሉ።
እነዚያ ነብዩ ﷺ በመካከላቸው የተላኩባቸው ሰዎች ሽርካቸው ያነሰ ከመሆኑም ጋ አላህ ዘንድ ካፊር ከሆኑ እንዴት ነው ታድያ ሽርካቸው ዘወትር በተድላም በጭንቅም የሆኑ ሰዎች?! የነሱ ካፊር መሆን በቀዳሚነት ይሆናል ማለት ነው።

✓ ባለቤቱ እሱ በመሆኑ ጀነት የምትፈለገው ከሱ እንደሆነው ሁሉ ሲሳይም ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ እንጅ ሊፈለግ አይገባውምና ከሱ ጋ መተሳሰሩ የግድ ነው	ከተውሒዱል ሩቡቢያህ ጋ በተያያዘ	ፀጋን ማመስገን
✓ በልቦናው ያመሰግናል፡ እሱ ዘንድ ያለው ፀጋ ሁሉ ከአላህ እንጅ ከሌላ እንዳልሆነ በማመንና በማረጋገጥ	ከተውሒዱል ኡሉሂያህ ጋ በተያያዘ	
✓ በአንደበቱ ያመሰግናል፡ {«ይህ ከጌታዬ ችሮታ ነው። የማመሰግን ወይም የምክድ መኾኔን ሊሞክረኝ (ቸረልኝ)።}(ነምል 40)		
✓ በአካሉ ያመሰግናል፡ ፀጋን ሁሉ ከምንነቱ አንፃር ሰጪ ዘንድ በሚያስመሰግን ቦታ ላይ ፀጋን ማዋል፤ የገንዘብ ፀጋ ሹክር አሏህን በመታዘዝ ላይ ማፍሰሱ ሲሆን የእውቀት ሹክር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጠየቀ መስጠት ነው።		
✓ ብስጩ፡ ፍርዱ ከትላልቅ ወንጀል የሚመደብ ሲሆን ወደ ትንሹ ሸርክ የሚደርስበትም ሁኔታ አለ። ብስጭቱ በልቦና፣ በአንደበትም በአካልም ሊሆን የሚችል ነገር ነው።	መካሪ ላይ ሲሆኑ ሰዎች ያላቸው ሁኔታ	ፀጋን አመስጋኝ {ለመፈተንም በዝቶም በሰጠም እንሞክራችኋለን። ወደኛም ትመለሳላችሁ።}(አል አንቢያእ 35)
✓ ታጋሽ፡ የትእግስት ፍርዱ በኡመተል ኢስላም ሙሉ ስምምነት መሰረት ግዴታ ነው። ትእግስትም በልቦና፣ በአንደበትና በአካል የሚሆን ነው። ትእግስት መቅመሱ እንደስሙ መራራ ቢሆንም ፍሬው ግን ከማር የጣፈጠ ነው።		ሲሰጥ አመስጋኝ
✓ ወዶ የሚቀበል፡ ፍርዱ የተወደደ ነው። ለአላህ ካለው ዑዴታ አንፃር ያጋጠመው ነገር ሁሉ ከአሏህ መሆኑንና አሏህ በባሪያው ላይ የሚወስነው ሁሉ መልካም መሆኑንም ያውቃል።		የሰኬት ርእሶች
✓ አመስጋኝ፡ እጅግ በጣም ትልቁ ደረጃ ነው። ይበልጥ የተወደደና ከአመስጋኝ ባሪያዎች የሚሆንበትም ነው።		መግቢያ፤ የሰኬት ርእሶችን ይዘለሉ
		አራቱ መርሆዎች ፤ የ " ከሸፉ ሹሁፉ " (ውሸጉብሮችን ማጋለጥ) ኪታብ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ማለት ነች

ወንጀል በሰራም ጊዜ መሃርታን ይጠይቃል

❖ አል-ሓኒፊያ፡ የኢብራሂም መንገድ፤ አሏህ የፈጠረህ እሱን ልታመልከው ነው። አምልኮ ደሞ ከተውሒድ ጋ ሆኖ ካልሆነ በቀር አምልኮ አይባልም። አምልኮ ላይ ሽርክ ከታከለበት ያበላሻታል ስራዋንም ዉድቅ ያደርጋታል፤ የድርጊቱ ባለቤትም ዘላለም እሳት ዉስጥ ከሚሆኑት ይመደባል። ስለዚህ አንተ ዘንድ ያለው ትልቁ ሃሳብ እሱኑ ማወቅ ነው።

ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማረው? እና የሽርክ አደገኝነት

1. አንደኛ መርሆ፡ እነዚያ የአሏህ መልእክተኛ የተላኩባቸው ሙሽሪኮች በተውሒዱል ሩቡቢያህ ቢያፀድቁም በተውሒዱል ኡሉሂያህ አያፀድቁም ነበር፤ ይህ ታዲያ ውደ ኢስላም አላስገባቸውም።
2. ሁለተኛው መርሆ፡ ካፊሮች ጣኣታትን ሲያመልኩ ምክንያታቸው መቀራረብንና ምልጃን መፈለጋቸው ነው።
3. ሶስተኛው መርሆ፡ የአሏህ መልእክትኛ የተላኩባቸው ሰዎች በሚያመልኩት የተለያዩ ቢሆኑም በመካከላቸው ልዩነት ሳይፈጥሩ ነው የተፋለሟቸው።
4. አራተኛ መርሆ፡ የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርክ ከድሮዎቹ የባሰ ነው።

አራቱ መርሆዎች:

የአራቱ መርሆዎች ፈተና

ስም.....
ከኪታቡ ተውሒድ የሸመደድከው መጠን.....
አራቱን መርሆዎች ሸምድደሃቸዋልን.....

ድርጊቱ	ከቁርአን ወይም ከሓዲሥ ማስረጃው
ፀጋ ፈተና ለመሆኑ	
ካፊሮች በሩቡቢያ እንደሚያፀድቁ	
መቀራረብን እንደሚፈልጉ	
የተወገዘችዋ ምልጃ	
ለፀሃይና ጨረቃ (መመለክ) ማስረጃው	
ለመላእክቶች (መመለክ) ማስረጃው	
ለነቢያቶች (መመለክ) ማስረጃው	
ለሷሊሆች (መመለክ) ማስረጃው	
ለድንጋይና ዛፎች (መመለክ) ማስረጃው	
ሙሽሪኮች በጭንቅ ጊዜ በኢኽላስ እንደሚያጠሩነ በተድላ ጊዜ እንደሚያጋሩ	
ስለ ሽርክ(ክፋት) ማስረጃው	

ስለ ተከታዮቹ (ነጥቦች) የምታውቀውን ፃፍ

ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማማረው?	ነ. 2. 3. 4.
1. 6	7 8 9 10
ለምንድን ነው አራቱን መርሆዎች የምንማማረው?	1 2
አራቱ መርሆዎች ወደ ስንት ይከፈላሉ	1 2 3
መርሆዎቹ የምን ኪታብ(ይዘት) ጥቅል ናቸው?	
ለምንድን ነው ኪታብ ከሸፉ ሹቡሃትን የማንማረው?	
የስኬት ርእሶች	1 2 3
አል-ሓኒፊያ ማለት	
መርሆዎቹን የመማር ፍሬ	
የአሏህ ወዳጆች የሚባሉት	ሸይኹል ኢስላም እንዲህ ብለዋል፡
ለዛም ማስረጃው	
ፀጋን ማመስገን በምን ይሆናል? ከምሳሌው ጋ	1
2	
3	
የአንድ ባርያ ትስስሩ እንዴት ነው የሚሆነው?	
በመከራ ጊዜ የሰዎች ሁኔታ ከኢስላማዊ ፍርዱ ጋ	1. ፍርዱ የሚገለፅበት በ..... እና..... በ..... 2. ፍርዱ የሚገለፅበት በ..... እና..... በ.....
3.	4.
ሸፋዓህ(ምልጃ) በቋንቋ ደረጃ	ሸፋዓህ (ምልጃ) ከሸሪዓ አንፃር
ሸፋዓህ ወደ ስንት ይከፈላል?	1 2
የፀናችዋ ሸፋዓህ ቅድመ መስፈርቶች	1 2 3
አይነቶቿ 1	ከፍሎቿ፡..... ..... እና .....
2	ከፍሎቿ፡..... .....እና .....
አንደኛ መርሆ	
ሁለተኛው መርሆ	
ሶስተኛ መርሆ	

አራተኛ መርሆ	
ስራን ሽርክ ከታከለበት	ማስረጃው፡

ማውጫ ሰንጠረዥ

1	መግቢያ	3 - 5
2	አራቱ ቁምነገሮች	6 - 10
3	ሶስቱ ነጥቦች	11 - 14
4	ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት	15
5	ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች	16 - 42
6	መደምደሚያ	43 - 45
7	ማጠቃለያ በሰንጠረዥ	46 - 49
8	ፈተና	50 - 54
9	አራቱ መርሆዎች	55-66
10	የፈተና ጥያቄዎች	67-69
11	ማውጫ ሰንጠረዥ	70

የ «ኢስላምን አፍራሾች» ማብራሪያ

የዳዕዋው ኢማም ሸይኹል ኢስላም
ሙሓመድ ቢን ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ
አላህ ይዘንለት ፤ በሰፊው ጀነትም ያስገባውና

ማብራሪያው በክቡር ሸይኽ
ዶ/ር ሀይሠም ቢን ጀሚል ሰርሓን
በክቡሩ መስጅደ-ል-ነበውይ የትምህርት ተቋም ነባር አስተማሪ
የታእሲለል ዒልምይ ዌብሳይት ሹም
http://attasseel-alelmi.com

ለሱም፣ ለወላጆቹም እንዲሁም ይህ ኪታብ እንዲወጣ እገዛ ላደረጉ ሁሉ

አላህ መሃርታውን ይለግስ

የመጀመሪያ እትም

መብቱ ብህግ የተጠበቀ ነው።

ከሸይኹ ማረጋገጥ በኋላ በነፃ ለማደል መተርጎም ወይም ማተም
ለፈለገ ካልሆነ በቀር

በዚህ ያግኙን:

islamtorrent@gmail.com

ኢስላምን አፍራሾች

ሸይኹል ኢስላም ሙሓመድ ቢን ዓብዱል ወህ-ሃብ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል፡

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

እስልምናን አፍራሾች አስር መሆናቸውን እወቅ

የመጀመርያው: በአምልኮ ከአላህ ጋር ተጋሪ ማድረግ: ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል።...} (አን-ኒሳእ 48) እንዲህም ይላል {...እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።} (አል-ማኢዳህ 72) ለሌላ አካል ማረድም እዚሁ የሚካተት ነው። ለአጋንንት ወይም ለቀብር እንደማረድ ማለት ነው።

ሁለተኛ: በሱ እና በአላህ መካከል የሚማፀናቸው፣ ሸፋዓ/ምልጃ የሚለምናቸው፣ የሚመካባቸው አማካኝ ያደረገ የካደ ለመሆኑ ኢጅማዕ (ሙሉ ስምምነት) አለበት።

ሶስተኛ: የአጋሪዎችን ካፊርነት ያላፀና፣ ወይም ካፊር ለመሆናቸው ከተጠራጠረ ወይም ደሞ መንገዳቸውን ትክክል ነው ያለ ካፊር ሆኗል።

አራተኛ: የየትኛውም አካል መመርያ ከነብዩ ﷺ መመርያ ይልቅ የተሟላ ነው ብሎ ያመነ፣ ወይም የሌላ አካል ህግጋት ከሳቸው ህግጋት የተሻለ ነው ብሎ ያመነ - ሰው ሰራሽ ህግን ከሳቸው ህግ እንደሚያስበልጡት አይነቱ - ካፊር ነው።

አምስተኛ: ነብዩ ﷺ ይዘውት ከመጡት (መመርያ) አንዳች ነገርን የጠላ ቢሰራበት እንኳ ካፊር ነው።

ስድስተኛ: ከነብዩ ﷺ ሃይማኖት በአንዳች ነገር ወይም በአላህ ምንዳ ወይም ደሞ በቅጣቱ የተሳለቀ ክዷል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...«በአላህና በአንቀጾቹ፣ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን» በላቸው። (65) አታመካኙ፤ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ።...} (አት-ተውባህ 65-66)

ሰባተኛ: ድግምት -መስተፋቅርና መስተፃርርም እዚሁ የሚመደቡ ናቸው። - ወይ የሰራው አልያም የወደደ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።} (አል በቀራህ 102)

ስምንተኛ: አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝና መርዳት። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱው ነው። አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም።} (አል ማኢዳህ 51)

ዘጠነኛ: ልክ ኸዲር ከሙሳ ﷺ ሸሪዓ እንደወጣው ሁሉ ለአንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሐመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን ካፊር ነው።

አስር: ላይማረው ላይሰራበት ከአላህ ዲን ጀርባውን የሰጠ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንከለኞቹ ተበቃዮች ነን።} (ሰጅዳህ 22)

በነዚህ አፍራሾች መካከል የቀልዱም ይሁን የምሩ አልያም ፈርቶም ልዩነት የለውም። ተገዶ ካልሆነ በቀር። ሁሉም አደገኛ ሊባል የሚችልና ብዙ ጊዜ የሚከሰትም ጭምር ነው። ሙስሊም ሊጠነቀቀውና በራሱ ላይ ሊሰጋ ይገባዋል። ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን። የአላህ ሶለዋት ከፍጥረቱ ምርጡ በሆኑት፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ይስፈን።

ማብራሪያ

የሸይኹ መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው እስልምናን አፍራሾች አስር መሆናቸውን እወቅ

የኢስላም ሙሁራኖች ለምንድን ነው ኪታቦቻቸውን በቢስሚላህ የሚጀምሩት?

- በአላህ መፅሃፍና በነብያት (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር
- {ጣጣ እያለበት አላህን በማወደስ ያልተጀመረ ጉዳይ ሁሉ የተቆረጠ ነው} የሚለው ሓዲሥ ዶኢፍ ቢሆንም ትርጉም ከመስጠት አንፃር
- ቀደምቶችን ከመከተል አንፃር
- በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

በቁርአንና በሓዲሥ ቁጥር ከተጠቀሰ፡

- ከተጠቀሰው ቁጥር በቁርአንና በሓዲሥ ሌላ ተጨማሪ ብዛት ካላገኘን የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም ይይዛል። ማለትም: አይጨመርበትም። ለምሳሌ በጅብሪል ዓለይሂ ሰላም ሓዲሥ የተጠቀሰው የኢስላምና የኢማን ማእዘናት
- በቁርአንና በሓዲሥ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ ካገኘን ግን የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም አልባ ይሆናል። ማለትም: በቁርአንና በሓዲሥ በመጣው ልክ ይጨመርበታል። ለምሳሌ: "አምስት ነገራቶች ከተፈጥሮ ናቸው።..." እንዲሁም "ሰባት አውዳሚዎችን ተጠንቀቁ..." መሰል የነቢዩ ﷺ ንግግሮች።

አንዳንድ ጊዜ ለምንድን ነው ቁጥር የሚወሳውና ትርጉምም ላይኖረው?

ይህ ከነብዩ ﷺ ጥሩ የማስተማር ችሎታ ነው። ምክንያቱም እንዲህ የሚያደርጉት አድማጮቹ በዚሁ መድረክ ላይ የሚባለውን ከጊዝያቶች በኋላ ቶሎ ይመጣላቸው ዘንድ አስተካክለው እንዲይዙት ስለፈለጉ ነው። “ሶስት የምምልባቸው ነገራቶች አሉ። የምነግራችሁ ነገርም አለኝ ሸምድዱት፤ ‘ምፅዋት የአንድን ባርያ ገንዘብ አይቀንስበትም...’”

ለምንድን ነው (ኢስላምን) ስለሚያፈርሱት ነገራቶች የምንማረው?

እንድንጠነቀቀውና እንዳያንዳልጠን የጎላ ጥቅም አለው። ኧረ እንደውም እጅግ በጣም ጠቃሚ ከሚባሉት ነው። ልክ ዒዱአችን እንዳይፈርስ ዒዱእ የሚፈርሱ ነገራቶችን እንደምንማረው፤ ሶላታችን ውድቅ እንዳይሆን ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶችን እንደምንማረው ነው። ሑዘይፋ ኢብኑል የማን ረድየላሁ ዓንሁ እንዲህ ይላል፡ “ሰዎች የአላህ መልዕክተኛን ﷺ ስለመልካም ነገር ይጠይቁ ነበር፤ እኔ ግን ስለመጥፎ ነገር ነበር የምጠይቃቸው፤ እንዳያገኘኝ ስጋት።”

ኢስላምን የሚያፈርሱ ነገራቶች ምን ምን ናቸው?

እነኝህ እስልምናውን ሊያፈርሱና ከኢስላም አውጥተው ወደ ትልቁ ኩፍር የሚያስገቡ ነገራቶች ናቸው። ኢስላም {ለ አላህ ራስን በተውሒድ ማስገዛት፤ በታዛዥነት ለሱ መጎተት፤ ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት}

ትርጉም፡
አንድን ሙስሊም ከኢስላም ወደ ትልቁ ኩፍር የሚያስወጡ ነገራቶች ማለት ነው። አላህ ሊጠብቀንና ነፃ ሊያድርገን ዘንድ እንለምነዋለን።

ለምንድን ነው ዑለሞች አንዳንዴ አፍራሾች አንዳንዴም አበላሾች ሌላ ጊዜ ደሞ ዒድቅ የሚያደርጉ እያሉ የሚገልፁት?
ይህም ተማሪ እንዳይሰላች አገላለፁን ከማስፋት አንፃር ነው እንጅ ትርጉሙ አንድ ነው። የዒዱእ/የኢስላም አፍራሾች፣ ሶላትን ዒድቅ የሚያደርጉ፣ ፆምን የሚያበላሹ እንደሚባለው።

እነዚህን አፍራሾች በዑለሞች መካከል ሙሉ ስምምነት አለባቸውን?
አዎ

በቁጥርስ የተገደቡ ናቸውን?
አይ በቁጥር የተገደቡ አይደሉም
ለምን ታድያ አስር ናቸው አለ?
አደገኞቹን ማለቱ ነው በቃል እንዲሸመደዱ።

ጥቅል በሆነ መልኩስ በቁጥር መገደብ ይቻላልን?

(የሚያከፍር) ጥርጣሬ፡ የነቢዩ ﷺ ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑ ክርስቲያንና አይሁዶች ካፊር ለመሆናቸው መጠራጠር

(የሚያከፍር) እምነት፡ ከአላህ ውጭ ባለ አካል ጥቅም ይመጣል የሚል እምነትን ይመስል

(የሚያከፍር) ድርጊት፡ ድግምትን ይመስል

(የሚያከፍር) ንግግር፡ አላህን ወይም መልዕክተኛውን ﷺ መስደብ ይመስል

አስሩን አፍራሾች ነብዩ ﷺ አውስተዋቸዋልን? ማስረጃውስ?

አዎ እነኝህን አፍራሾች በሙሉ ነብዩ ﷺ አውስተዋቸዋል። ኧረ እንደውም (ኢስላምን) አፍራሽ ሁሉ ከቁራንና ሓዲሥ ማስረጃ አለው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {እንደዚሁም (እውነቱ እንዲገለጽና) የወንጀለኞችም መንገድ ትብራራ ዘንድ አንቀጾችን እንገልጻለን።} (አል አንዓም 55)

አንድ አፍራሽ ነገርን ላደረገ ያየ ወይም ያወቀ ሁሉ የኩፍር ፍርድ ይሰጥበታልን?

አይ በግላዊነት ለይቶ ካፊር ለማለትማ በእውቀታቸው ሰሪዎች ወደሆኑ የሸሪዓ ዳኛ ዑለሞች መመለስ ግድ ነው። የአላህ መልዕክታኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ፡ "የትኛውም ሰው ለወንድሙ 'አንተ ካፊር' ያለ አንዳቸው ላይ ታርፋለች።"

አፍራሾችን በማስመልከት የፃፈ ማን አለ?

በፊቅህ ዙርያ የፃፈ ሁሉ "የሙርተድን ብይን" ሲያሰፍር አፍራሾችን ጠቅሷል። ራሱን በቻለ መልኩ አንድ ኪታብ አድርጎ ለመፃፉ ግን (ሸይኹ) የመጀመርያ ነው።

አፍራሾችን በማስመልከት በድርጊቱ እና በፈፃሚው መካከል ልዩነት ይደረጋልን?

አዎ እንዴታ። ምክንያቱም ኩፍር ላይ የወደቀ ሁሉ ኩፍር የሚያርፍበት አይደለምና። ግለሰብን በኩፍር ለመፈረጅ ማስረጃን ማቆምና ውዥንብር መነሳቱ የግድ ነው። አላህ ይዘንለትና የሸይኹ አላማም ግለሰቦችን ማክፈር አይደለም። ይልቅ አላማው አፍራሾችን ማስጠንቀቅ ነው። ይህም ደሞ ኡማው ጋ መመካከር ነው።

አፍራሾችን በማስመልከት የተማረ ሰው ምን ማድረግ ይኖርበታል?

አንድ ሙስሊም ሊጠነቀቅበትና በራሱም ላይ ስጋት ሊያድርበት ሊያስጠነቅቅም ይገባዋል። በግለሰቦች ላይ ፍርድ መስጠቱ ላይ ግን ወደ ታላላቅ ዑለሞችና ወደ የሸሪዓው ዳኞች መመለስ ይገባል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡

{ከጎሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእመናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልዕክተኛ በእርግጥ መጥላችሁ። ቢያፈገፍጉም አላህ በቂዬ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። በእርሱ ላይ ተጠጋሁ እርሱም የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው በላቸው።} (ተውባ 128)

የመጀመርያው አፍራሽ

በአምልከ ለአላህ ተጋሪ ማድረግ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ { አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።} (ኒሳእ 48) እንዲሁም { እነዚያ «አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ። አልመሲህም አለ፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።» እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ።} (አልማኢዳህ 72) ከአላህ ዉጭ ላለ አካል እርድ ማቅረብም ከዚሁ ይመደባል። ለጅን እንደሚያርዱት ማለት ነው።

የሽርክ አይነቶች

ትልቁ

(ሽይኹም የፈለጉት ይህ አይነቱን ነው)

ተጨባጩ፡ ከአላህ ውጭ ላለ አካል በአስተናባሪነት በኩል ድብቅ ችሎታ እንዳለው ወይም ደሞ ጥቅምን ማምጣትና ክፋትን መመከት እጁ ላይ እንዳለ ማመን።

- ከመንገዱ(ከኢስላም) ያስወጣል
- ስራን በሙሉ ያበላሻል
- ደምና ንብረቱን ለባለስልጣኑ ሓላል ያደረግበታል
- ጀሃነም ዉስጥ ለዘላለም ዘውታሪ ያደርገዋል
- (ከመለያዎቹ) በሸሪዓ “ትልቁ” በሚል ከተጠራ
- ትልቅነቱን በሚጠቁም ቋንቋዊ አገላለፅ ከመጣ

ትንሹ

ተጨባጩ፡ አላህ ሰበብ ያላደረገውን ሰበብ ማድረግ እንዲሁም ወደ ትልቁ ሽርክ የሚያዳርስ ሁሉ።

- ከመንገዱ(ከኢስላም) አያስወጣም
- ስራን በሙሉ አያበላሽም
- ደምና ንብረቱን ሓላል አያደርግበትም
- ጀሃነም ዉስጥ ለዘላለም ዘውታሪ አያደርግም
- (ከመለያዎቹ) በሸሪዓ “ትንሹ” በሚል ከተጠራ
- በሸሪዓ ሽርክ ቢባልም ትልቅነቱን በሚጠቁም አገላለፅ ካልሆነ

ትልቁ ሽርክ መሃርታ ይደረግበታልን?

እዛው ባለበት ለሞተ መሃርታ የለውም። ምክንያቱም አላህ እንዲህ ስላለ፡ { አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም።} (ኒሳእ 48) ከሱ ተውባ ካደረገ ግን ይማርለታል። አላህ እንዲህ ስላለ { በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና።} (ዙመር 53) ይህም ፀሃይ በመግቢያዋ እስካለውጣች ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ{"ሂጅራ አትቋረጥም ተውባ እስክትቋረጥ ድረስ፤ ተውባም አትቋረጥም ፀሃይ በመግቢያዋ እስክትወጣ ድረስ።"} ወይም ሞት አፋፍ ላይ እስካልሆነ፤ ማለትም ጣዕረ ሞት ላይ እስካልሆነ። አላህ እንዲህ ይላል {ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ኃጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚል... አይደለችም።...} (ኒሳእ 18)

የተከለከሉ ነገራቶች አይነት

ትልቁ ሽርክ

ከባዱ ነው።

ትንሹ ሽርክ

ከትልቁ ሽርክ ያነሰ ከትልቁ ወንጀል በላይ

ከባባድ ወንጀሎች

ፈፃሚውን በማስመልከት እርግማን፣ (ከራሕመት) መባረር (ከሱ) መጥራራትን ከካፊሮች/ከሙሽሪኮች ነው በሚልና መሰል ልዩ መቀጣጫ የመጣበት፤ ወይም ከሙእሚኖች አይደለም የተባለበት አልያም ከአስቀያሚ እንስሳት የተመሳሰለበት

ትናንሽ

ሸሪዓ ልዩ መቀጣጫ ሳያስከትል የከለከለው ሁሉ

(ኢስላማዊ) ፍርዱ

ተውባ ማድረግ ግዴታ ነው። ነብዩ ﷺ (ሙሽ አውራጅ ተውባ ካላደረገች...) በሌላ ሓዲሥ (ከባባዶቹ ከተራቁ...) ስላሉ

ደረጃዋ

ይለያያል፤ ነብዩ "የከባዶች ሁሉ ከባድ (ወንጀል)..." እንዳሉት

የሰሪው ፍርድ፡

ኢማኑ ያልተሟላ አማኝ ወይም በኢማኑ አማኝ በወንጀሉ አመፀኛ ነው። ባለው ኢማን ልክ ይወደዳል ባለው ወንጀል ልክ ይጠላል።ወንጀሉን በሚፈፅምበት ጊዜ አይቀማመጡትም

ብዛቱ

በቁጥር ባይገደበም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መርህ ይገደባል


የእርድ አይነቶች
የተፈቀደ
ለስጋ፣ እንግዳን ለማክበር፣ ለንግድ ብሎ ማረድ
ከአላህ ውጭ ላለ አካል በውዴታ እና በማላቅ
(ሽይኹም የፈለገው ይህን ነው)
ትልቁ ሽርክ ነው። ለጅን ለቀብር ባለቤቶች ማረድ ብሎ እንደማረድ አይነቱ
ለአላህ
የተደንገገውም እሱው ነው፤ ሃድይ፣ ኡዱሒያና ሶደቃን ይመስል።

ሁለተኛው አፍራሽ

በሱ እና በአላህ መካከል የሚማፀናቸው፣ ሸፋዓ (ምልጃ) የሚለምናቸው፣ የሚመካባቸው አማካኝ ያደረገ የካደ ለመሆኑ ኢጅማዕ (ሙሉ ስምምነት) አለበት።

የሸፋዓ (ምልጃ) አይነቶች

ከአላህ ውጭ ሌላ በማይችለው

የተወገዘችው

ሸይኹ የፈለጉትም ይህን ነው ይህች ቁርአን ያወገዛትና አላህ እንጅ በማይችለው ጉዳይ ከአላህ ውጭ የምትፈለገዋ ነች፤ ከትልቁ ሽርክ ትመደባለች።

የፀደቀችው

አላህ ለራሱ ያፀደቃትና ከሱ እንጅ የማትፈለገዋ ናት፤ ተከታዮቹ መስፈርቶቿ ናቸው

(1) ለሸፈዓው አላህ መፍቀዱ

(2) ሸፋዓ ለሚያደርገው የአላህ ዉዴታ መኖሩ

(3) ሸፈዓ ለሚደረግለት የአላህ ዉዴታ መኖሩ

ፍጡራን በሚችሉት

አራት መስፈርቶች ከተሟሉ ይፈቀዳል

(1) ያለ/ቅርብ መሆን

(2) ህያው መሆን

(3) የሚችል

(4) ሰበብ ተደርጎ ሊያዝ ይገባል

አጠቃላይ የመልዕክተኞች፣ የነብያቶች፣ የመላዕክቶችና የጨቅላ ህፃናት ምልጃ

(1) የተውሒድ ሰዎች ደረጃ ከፍ እንዲል የሚደረግ ምልጃ

(2) ለእሳት የተገባን የተውሒድ ሰው እንዳይገባት

(3) እሳት የገባን የተውሒድ ሰው ከሷ እንዲወጣ

ለነብዩ ﷺ ብቻ የሆነ

(1) ታላቁ ሸፋዓ

(2) የነብዩ ﷺ ለ አቡጣሊብ የቅጣት መቀነስ ምልጃ

(3) የጀነት በሮች እንዲከፈቱ የሚያደርጉት ምልጃ

አንድ ሰው ለወንድሙ "ዱዓ አድርግልኝ" ማለቱ ትክክል ነውን?

በዚሁ ፍላጎቱ የሆነ ያክል መተናነስ ካለበት ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ አይነት ነው። የተፈለገው ከሀያው፣ ቅርብና ከሚችል ሰው ሆኖ ሰበብ ተደርጎ የሚያዝ ከሆነ ግን የሚቻል ቢሆንም መተው ይሻላል።

ተወኩል

የተደነገገውን ሰበብ እያደረሱ እውነተኛ የሆነ በአላህ ላይ ተማምኖ መደገፍ ነው።

የተፈቀደው

መተናነስ ሳይታከልበት ነገራቶችን ሊያከናውን በሚችልበት ነገር ላይ መደገፍ፤ አንዳች ነገርን ለመግዛት ተወካይ ማድረግን ይመስል

ትንሹ ሽርክ

ከሙሉ መተናነስ ጋ ሀያው በሆነ አካል ላይ መደገፍ፤ ሀያው የሆነን አካል ከሰበብ በላይ አድርጎ ለሲሳይ መደገፍን ይመስል

ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ ከሰጠው ትልቁ ሽርክ ነው

ሸይኹም የፈለጉት ይህን ነው

የአምልኮና የመተናነስ ተወኩል። በእጁ ላይ የመጥቀምና መጉዳት ችሎታ አለ በሚል እምነት በተመኩበት ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ። መተናነስን አይነት ነገር ያዘለና ሙታኖች ላይ መደገፍን አይነቱ።

"በእገሌ ላይ እደገፋለሁ/እመካለሁ" ወይም "በአላህ ላይ እመካለሁ ከዚያም በእገሌ" ማለት ይፈቀዳልን? ትክክለኛውስ የትኛው ነው?

"በእገሌ እመካለሁ" ማለትህም ሆነ "በአላህ እመካለሁ ከዚያም በእገሌ" ማለትህ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ይህ ከአላህ ውጭ ላለ አካል የማይገባ የልቦና ስራ ነው። ይልቅ "እገሌን ወክያለሁ" ማለትም ነገራቶችን ትቸለታለሁ በል። ነብዩም ﷺ አንዳንድ ባልደረቦቻቸውን ለጥቅልም ሆነ ለልዩ ጉዳዮቻቸው ወክለዋቸዋል።

ሶስተኛ አፍራሽ

የአጋሪዎችን ካፊርነት ያላፀና፣ ወይም ካፊር ለመሆናቸው ከተጠራጠረ ወይም ደሞ መንገዳቸውን ትክክል ነው ያለ ካፊር ሆኗል።

አጋሪዎች በኢስላም ያላቸው ፍርድ

የነብዩ ﷺ ጥሪ ደርሶት አምኖ ያልተቀበለ ሁሉ ትልቁን ክህደት የፈፀመ ከሃዲ ነው። አላህ እንዲህ ስላለ፡ {ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።} (አሊ ዒምራን 85)

አህሉል ኪታብ(ክርስቲያንና አይሁዶች) አጋሪዎች ላይ ይመደባሉን?

አዎ በሳቸው ያላመኑት አህሉል ኪታቦች ከነሱ ይመደባሉ። አላህ እንዲህ ስላለ፡ {ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው፡ ፡} (ተውባ 29) ነብዩም ﷺ እንዲህ ስላሉ "ከዚህ ኡማ አንድም አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያን ስለኔ አይሰማም ከዚያም በተላኩበት ሳያምን አይሞትም ክእሳት ጓዶች ቢሆን እንጅ"

ይህ ማለት ቃል የገባንላቸውን አንወጣላቸውም ማለት ነውን?

ቃል የተግባባነውን የአላህን ዒዴታ እንድናገኝ ቃላችንን ልንፈፅምለት የግድ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {(እነዚህ) በቃል ኪዳናቸው ለእናንተ ቀጥ እስካሉላችሁ ድረስ ለነርሱም ቀጥ በሉላቸው።} (ተውባ 7) ሰዎች ከአጋሪዎች ጋ ባላቸው መስተጋብር ሶስት አይነት ናቸው፡

በበአላቶቻቸው፣ ብዝግጅቶቻቸውና በስነስርዓቶቻቸው የሚሳተፉ ፅንፎች

በግድያ፣ በዝርፊያ፣ በተንኮልና በመምታት ድንበር የሚያልፍ ፅንፍ

አህሉሱና ወልጀማዓህ ያሉበት ሚዛናዊ አቋም በበአላቶቻቸውም ሆነ በስነስርአቶቻቸው አለመሳተፍ፤ የተወጡትን ቃል እንፈፅምላቸዋለን፤ ድንበር አንተላለፍባቸውም፤ በግብይት እንጋራቸዋለን፤ ወደተውሒድም ጥሪ እናደርግላቸዋለን።

አራተኛው አፍራሽ

አራተኛ: የየትኛውም አካል መመርያ ከነብዩ ﷺ መመርያ ይልቅ የተሟላ ነው ብሎ ያመነ፣ ወይም የሌላ አካል ህግጋት ከሳቸው ህግጋት የተሻለ ነው ብሎ ያመነ - ሰው ሰራሽ ህግን ከሳቸው ህግ እንደሚያስበልጡት አይነቱ - ካፊር ነው።

በሰው ሰራሽ ህግ የመፍረድ አይነቶች

የአላህ ህግ አጥብቀው ሊይዙት የሚገባ ለሰውም ለአገሩም ሁሉ የሚበጀው እሱ ነው ብሎ እያመነ የሰው ሰራሽ ህግን በነፍስያው፣ ለስልጣን ፍለጋና መሰል ምክንያት ካስቀደመ ይህ ከባድ ያልሆነው ክህደት ነው። ትንሹ ክህደትና አመፅም ነው። በዚህ ፍርድ ሳቢያ የሙስሊምን ሓቅ ከጣሰበት ተጨማሪ በዳይነት እንዲሁም ከመንገዱ የሚያስወጣውን ትልቁን ክህደት ይሰጋበታልም።

የአላህ ህግ አይበጅም ብሎ ሰው ሰራሽ ህግን ከአላህ ህግ ሊያስበልጥ ነው። ይህ እምነት ካለው ከኢስላም የሚያስወጣውን ትልቁን ክህደት ፈፅሟል ካፊር ሆኗል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {...ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።} (ተውባ 31)

አምስተኛው አፍራሽ

ነብዩ ﷺ ይዘውት ከመጡት (መመርያ) አንዳች ነገርን የጠላ ቢሰራበት እንኳ ካፊር ነው።

ለዚህ አፍራሽ ማስረጃው

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {ይህ እነርሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው። ስለዚህ ሥራዎቻቸውን አበላሸባቸው።} (ሙሐመድ 9) እንዲሁም {በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።} (ኒሳእ 65) እንዲህም ይላል {አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለኢስላም ይከፍትለታል። ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል። እንደዚሁ አላህ በእነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል።} (አልአንዓም125)

ለአላህ ብሎ መውደድና መጥላት

ለአላህ ብሎ መውደድና መጥላት ከግዴታዎች ብሎም ከታማኝ የኢማን ዘለበቶች ነው።

ለአላህ ብሎ መውደዱ ግዴታ የሆነው ምንድን ነው?

- አላህ የሚወደውን ስራ በሙሉ፤ ያም እንደተውሒድ ያለውን ሸሪዓ ይዞት የመጣው ሁሉ ማለት ነው
- በሱ የሚሰሩትን እንደነቢያቶች፣ መልዕክተኞች፣ መላዕክቶች፣ ሱሓቦችና ሁሉንም የተውሒድ ጓዶችን
- ለይለቱል ቀድርንና የለሊቱን የመጨረሻ አንድ ሶስተኛ የመሰሉ አላህ የሚወዳቸውን ጊዜዎችን
- መካንና የነቢዩ መዲናን የመሰሉ አላህ የሚወዳቸው ቦታዎችን

ለአላህ ብሎ መጥላቱ ግዴታ የሚሆነው ምንድን ነው?

- አላህ የሚጠላውንና የማይፈልገውን ስራ፤ ያም እንድሸርክ ያለውን ሸሪዓ የከለከለው ሁሉ
- እንደሙሽሪኮች ፣ ሙናፊቅና ሸያጢን አይነት ሰሪዎችን
- ፀሃይ እንደሚመለክበት አይነቱ አላህ የሚጠላቸው ጊዜይቶችን
- ሸርክ እንደሚፈፀምባቸው ያሉ አላህ የሚጠላቸውን ቦታዎችን

ሴት ልጅ (የሚስት) ብዛትን ብትጠላ ትከፍራለችን?

ተጨባጭ ላይ ያለው ሸሪዓዊ ፍርዱን አትጠላም፤ ነገር ግን (ለራሷ) ባሏ በሷ ላይ ደርቦ ማግባቱን አትፈልግም፤ ይህ ደሞ የማትወቀስበት ጉዳይ ነው።

ስድስተኛ አፍራሽ

ከነብዩ ﷺ ሃይማኖት በአንዳች ነገር ወይም በአላህ ምንዳ ወይም ደሞ በቅጣቱ የተሳለቀ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...«በአላህና በአንቀጾቹ፣ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን» በላቸው።(65) አታመካኙ፤ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ።...}(አት-ተውባህ 65-66)

ተሳላቂ

ትርጉሙና (ኢስላማዊ) ፍርዱ

መሳለቅ ማለት ማፌዝ ማለት ነው። ተሳላቂ ሰው ፍርዱ ወይም ተሳዳቢ እውነትን የተወ ክህደትን የካደ ካፊር ነው። ያም ከመንገዱ የሚያወጣ ክህደት ነው። ባለቤቱም ጀሃነም ዉስጥ ዘውታሪ ነው።

ስድብ የሰማ ደሞ ሊያወግዝ አልያም ከአካባቢው ሊርቅ ይገባዋል፤ ሳያወግዝ ተመልካች ወይም ተራኪ አይነቱም ያው ነው። አላህ እንዲህ ስላለ {በእናንተም ላይ በመጽሐፉ ውስጥ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷም ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ድረስ ከእነሱ ጋር አትቀመጡ። ማለትን በእርግጥ አወረደ። እናንተ ያንጊዜ ብጤያቸው ናችሁና። አላህ መናፍቃንን እና ከሓዲዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና።} (ኒሳእ 140)

ተውባው ተቀባይነት የሚያገኘው በተከታዮቹ መስፈርቶች ነው፡

- አላህን ተገቢ በሆነ መልኩ ሊያወድስ
- እየተሳለቀ ከተናገረው ራሱን ሊያጠራ
- እንድናምነው የፀፀቱ ምልክት ሊያሳላ
- የአላህ መልዕክተኛን ﷺ የሰደበ ግን ተውባው ትክክለኛ ከሆነ አላህ ይቀበለዋል፤ ለድርጊቱ ግን (የሙስሊሞች) ባለስልጣን ይገለዋል

ንግግሩ የኩፍር መልዕክት ካለውስ ካፊር ይባላልን?

ግልፅ ይደረግለትና ተውባ ካደረገ እንተወዋለን፤ አለበለዚያ ግን ጉዳዩ ወደ ዳኞችና ወደ ታላላቅ ዑለሞች ይመለሳል።

ሰባተኛ አፍራሽ

ድግምት - መስተፋቅርና መስተፃርርም እዚሁ የሚመደቡ ናቸው። - ወይ የሰራው አልያም የወደደ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።} (አል በቀራህ 102)

ድግምት

የደጋሚ ምልክቶች

- ከመንገዱ(ከኢስላም) ያስወጣል
- ሸሪዓዊ ሩቃ የሚፈቀድባቸውን መስፈርቶች መጣስ ። እየቋጠሩ መትፋት
- የተቆራረጡ ፊደላቶችን መፃፍ፤ በማይገባ ቋንቋ ማነብነብ ። መስተፋቅርና መስተፃርር
- ከዋክብትን መመልከት፣ መዳፍንና ስኒን ማንበብ
- ህመምተኛን ሓራምን እንዲያደርግ፤ ወይም ሶላት እንዲተው አልያም በእርድ ጊዜ ቢስሚላህ ማለትን እንዲተው ማዘዝ
- የእናት ስም መጠየቅ
- የሩቅ ሚስጥር አውቃለሁ ብሎ መሞገት

(ኢስላማዊ) ፍርዱ

ድግምት ትልቁ ኩፍር ነው፡ አላህ እንዲህ ስላለ {...«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።...} (አልበቀራ 102)

ደጋሚ ዘንድ መሄድ (ኢስላማዊ) ፍርዱ

መምጣት ሲባል እዚህ ላይ የተፈለገው መቀማመጡ፤ ወይም ሰው አልያም መልዕክት መላኩ ነው። እንዲሁም “ስነከዋክብት”፣ መዳፍና ስኒ ንባብ የሚተላለፍባቸውን ቲቪ፣ ዌብሳይት፣ መፅሄቶችን መመልከትም እንደዚሁ ነው። ወደ ጠንቋይ የሄደ በሓዲሥ እንደመጣው የአርባ ቀን ሶላቱ ተቀባይነት አያገኝም፤ በሚናገረው እውነት ብሎ ከተቀበለ ግን ነቢዩ እንዲህ ብለዋል {ወደ ጠንቋይ ሂዶ እውነት ብሎ የተቀበለው በሙሐመድ ላይ በውረደው ክዷል።} ለማውገዝ ብቁ ሆኖ የሄደ ሲቀር።

ድግምትን ማክሸፍ

ይህ ማለት በተደገመበት ሰው ላይ ድግምቱን ማክሸፍ ሲሆን ሁለት አይነት ነው

የተከለከለ

ከድግምት የሆነ ያክል ካለበት፤ ይህን በማስመልከት ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል {ከሸይጧን ስራ ናት}

የተደነገገ

ሸሪዓዊ በሆነ ሩቃ፣ በተፈቀደ መድሃኒትና በዱዓ የሚደረገው ነው።

ድግምትን በድግምት መሻር ይቻላል ለሚሉ ሰዎት ምላሽ

1. ድግምትን በድግምት መሻር ቁርአንና ሓዲሥን እንዲሁም ቀደምት ሰለፎች የነበሩበትን የሚቃረን ነው።
2. በቁርአንና ከነቢያዊ ሱና በተገኙ ዱዓዎች የሚገኘው ፈውስን ማሳነስን ይዟል።
3. ድግምትንና ደጋሚዎችን ማጠናከርና እነሱን ብዙሃኑ ማህበረሰብ ዘንድ ማመቻቸትን አካቷል።
4. እርግጠኛ ከሆነው ቁርአናዊ እንዲሁም መሰረት ባላቸው ዱዓዎች ከመተካከም ይልቅ ግምታዊ ወደሆነው ድግምታዊ መተካከም መዘንበልን ይዟል።
5. ከተደገመ ሰው ድግምትን በማክሸፍ ሂደት ላይ ድግምት ሻሪውም የሚሻርለትም ሸይጧን ድግምቱን እንዲፈታ በሚወደው መልኩ መቀራረብ ግድ ያስብላል
6. ከነብዩ ﷺ እንደመጣው አንድ የተደገመበት ሰው ትዕግስት ካደረገ ጀነት አለለት
7. ድግምትን በድግምት መሻር ለተደገመበት ሰው በድግምት ላይ ድግምትን ነው የሚጨምርበት
8. ነብዩም ﷺ ተደግመዋል፤ በሸሪዓዊ ሩቃ እንጅ በድግምት አልሻሩትም

ስምንተኛ አፍራሽ

አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝና መርዳት። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱው ነው። አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም።}(አል ማኢዳህ 51)

አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝ

አንድ ሙስሊም ግድ የሚሆንበት ከአጋሪዎችና ከሃይማኖታቸው መጥራራትና በዚህም መካድ፤ የተውሒድ ሰዎችን መወዳጀትና ሃይማኖታቸውን መውደድ ነው። ኩፍርን የወደደ ወይም የተደሰተበት ወይም በዛ ላይ የተባበረና ሙሽሪኮችን ያገዘ ከመንገዱ የሚያስወጣውን አይነት ክህደት ፈፅሟል።

እኛ ዘንድ በተጨባጩ አጋሪዎችን ማገዝ ሁለት አይነት ነው፡

ከመንገዱ የሚያወጣ ኩፍር ያልሆነ

አጋሪዎችን ወዶ ሙስሊሞችን ጠልቶ ሳይሆን ለዱንያዊ ጥቅም ተብሎ

ክህደትና መቀልበስ

እነሱን ወዶ፣ ሙስሊሞችን ጠልቶ በሙስሊሞች ላይ የበላይ እንዲሆኑ ፈልጎ አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ መርዳት

ዘጠነኛ አፍራሽ

ልክ ኸዲር ከሙሳ ሸሪዓ ዓለይሂ ሶላቱ ወሰላም እንደወጣው ሁሉ ለአንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሐመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን ካፊር ነው።

አንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሐመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን

በዑለሞች ሙሉ ስምምነት መሰረት ከመንገዱ የሚያወጣውን አይነት ትልቁን ክህደት የፈፀመ ካፊር ነው። የሚመለስ ከሆነ ተብራርቶለት ተውቦ እንዲያደርግ ይጠየቃል አለበለዚያ ይገደላል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ።} (አል አዕራፍ 158) የአላህ መልዕክተኛም ﷺ እንዲህ ይላሉ "ሙሳ ወንድሜ በህይወት ቢሆን ኖሮ እኔን ከመከተል ውጭ አማራጭ አይኖረውም ነበር።"

የነቢዩ ጥሪ የደረሳቸው አህሉል ኪታቦችም እዚሁ ይካተታሉ፤ እንዳሳለፍነው አጋሪዎች ናቸውና። ኸዲርስ ከሙሳ መንገድ ወጥቷል እንዴ? እኛ የኸዲር ከሙሳ መንገድ መውጣት የፀና አይደለም። ቢፀድቅ እንኳ ምናልባት ከሙሳ ህዝብ ስላልሆነ ይሆናል። ነብይ ሲላክ ወደ ህዝቦቹ ብቻ ነው የነበረው፤ ነብያችን ﷺ የተላኩት ግን አጠቃላይ ወደ ሰው ልጆች ነውና አንድም ሰው ከመመሪያቸው ሊወጣ አይገባውም።

አስረኛ አፍራሽ

ላይማር ላይሰራበት ከአላህ ዲን ጀርባውን የሰጠ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።}(ሰጅዳህ 22)

ለአላህ ዲን ጀርባን መስጠት

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ፡ "አላህ መልካም የሻለትን ሰው ዲኑን ያስገነዝበዋል"። አላህ መልካም ያልሻለት ደሞ ዲኑን ከመማር ይዘናጋል ጀርባውን ይሰጣል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ { በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።} (ሰጅዳህ 22) የጀሃነም ሰዎችም ደሞ -አላህ ይጠብቀንና- ተንኮለኞቹ ናቸው።

ጀርባ መስጠት ኢስላማዊ ፍርዱ

ጀርባ መስጠቱ በማዳመጥም ሆነ በልቦናው እውነትም ዒሸትም ሳይል ወዳጅ ጠላትነት ሳይፈጥር ይዘው ለመጡትም ቀና እንኳ የማይል ከሆነ ከመንገዱ የሚያስወጣው ትልቁን ክህደት የፈፀመ ከሃዲ ነው።

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {ለእነርሱም፡- «አላህ ወደ አወረደው (ቁርአን)ና ወደ መልክተኛው ኑ» በተባሉ ጊዜ መናፍቃን ከአንተ መሸሸን ሲሸሹ ታያቸዋለህ።} (ኒሳእ 61) እንዲህም ይላል፡ {ከጌታውም ማስታወሻ የሚያፈገፍግ ሰው አስቸጋሪን ቅጣት ያገባዋል።} (ጅን 17)

የሸይኹ መደምደሚያ

በነዚህ አፍራሾች መካከል የቀልዱም ይሁን የምሩ አልያም ፈርቶም ልዩነት የለውም፤ ተገዶ ካልሆነ በቀር። ሁሉም አደገኛ ሊባል የሚችልና ብዙ ጊዜ የሚከሰትም ጭምር ነው። ሙስሊም ሊጠነቀቀውና በራሱ ላይ ሊሰጋ ይገባዋል። ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን። የአላህ ሶለዋት ከፍጥረቱ ምርጥ በሆኑት፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ይስፈን።

በነዚህ አፍራሾች መካከል ልዩነት የለም፡

ፈሪ

በአንዳች ነገር ሳይገደድ ዋሽቶ በገንዘቡ ወይም በደረጃው ለተቃጣ ችግር ስጋት እንዳደረገው የሚያመካኝ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {ከሰዎችም በአላህ አመንን የሚል ሰው አልለ። በአላህም (በማመኑ) በተሰቃየ ጊዜ የሰዎችን ማሰቃየት እንደ አላህ ቅጣት ያደርጋል። ከጌታህም እርዳታ ቢመጣ እኛ በእርግጥ ከእናንተ ጋር ነበርን ይላሉ። አላህ በዓለማት ሕዝብ ልቦች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ አይደለምን?} (አል ዓንከቡት 10)

ያመረረ

ያ ማለት አፍራሽን ፈልጎ አድርጎ በቂ ምክንያት የሌለው ነው

እየቀለደ ለሆነ፡

ያ ማለት አንድ አፍራሽ ነገርን ያደርግና ቀልድ እንደሆነ የሚሞግት ነው

መገደድ

ከአፍራሾች መካከል አንዱንም ተገዶ ያደረገ ካፊር አይሆንም። በመገደዱ ዑዝር የሚያሰጡት የመገደድ መስፈርቶችም ተከታዮቹ ናቸው፡

1. ፈሪ አልያም አስመሳይ ስለሆነ ሳይሆን በእውነት የተገደደ ሊሆን ይገባል
2. ድንበር ላያልፍ፤ ለምሳሌ በመስደቡ የሚከፍርበትን አንድ ሰው እንዲሰድብ ቢገደድ ተላልፎ ከአንድ በላይ መስደቡ ኩፍር ይሆንበታል፤ ምክንያቱም ተገዶ የነበረው አንድ ብቻ ነበርና ነው።
3. በቻለው ልክ ሊቃረነው፤ ኩፍርን እንዳይፈጥ
4. ልቦናው በኢማን የረጋ ሊሆን፤ ማለትም በአንደበቱ የሚለው ልቦናው በኢማን የረጋ ከመሆኑም ጋ ሊሆን
5. የተገደደበት ወደሌሎች የሚተላለፍ ብክለትና የሰዎች መጥመም ላይኖረው

አስፈላጊ ማስታወሻዎች

አንደኛ፡ ሸይኹ በዚህ ኪታብ ሰዎችን ማክፈር ፍላጎቱ አይደለም፤ ይልቅ ሰዎች እንዲያውቁ፣ ከሱም እንዲርቁና እንዲጠነቀቁ ነው። ከተጠነቀቋት ኢማናቸውም ትክክል ይሆናል ከአሳማሚው ቅጣትም ይድናሉ። ልክ ሌሎችንም ከሷ ሊያስጠነቅቁ እንደሚገባቸው ሁሉ። እሷም ልትታወቅና ሊጠነቀቋት ተገቢ የሆነች ከባድ አደጋ ነች።

ሁለተኛ፡ የሙስሊም ከሽርክ መጠንቀቅ ሸሪዓዊ እውቀትን በማወቅ ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ይላሉ "አላህ መልካም የሻለትን ሰው ዲኑን ያስገነዝበዋል" ዲንን መገንዘብ ከትላልቅና አሳሳቢ ግዴታዎች ነው። የሰው ልጅ በዚሁ ራሱን ከሽርክ፣ ከቢድዓና ከአመፅ ያቅብበታል። ሁሌም ጌታውን በማስመልከት እውቀቱ በጨመረ ቁጥር በድርጊቱም በሁኔታውም ሁሉ (አላህ) በሱ ላይ ላለው ተቆጣጣሪነት (ተገዥ መሆን) ይጨምራል። የሰው ልጅ በእውቀት ከፍ ባለ ቁጥር ኢኽላሱም ይጨምራል ኢማኑም ይሟላል። አንዳንድ የእውቀት ባለቤቶች እንዲህ ይላሉ "እውቀትን ለሌላ ብለን ፈለግን ለአላህ ካልሆነ ብሎ እምቢተኛ ሆነ እንጅ!"።

ሶስተኛ፡ ግለሰብን ከነዚህ አፍራሾች መካከል በአንዱ አርፎ ማስረጃ እንደቆመለትና የመክፈሩን ፍርድ ከመስጠት የሚከለክለው ነገር አለመኖሩ ካልተረጋገጠ በቀር ካፊር ሊባል አይችልም። የኩፍር ፍርድ መስጠት ያለበትም በሙስሊሞች ጉዳይ የተሾመ ወይም ደሞ እንደ ቃዲ(ዳኛ) አይነቱ የሱ ተተኪ መሆን ይኖርበታል። ብዙሃኑ ማህበረሰብ `ማ በእንደዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ ለመዘፈቅ ሊደፍር አይገባውም።

አራተኛ፡ ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ኪታቡን እንዲህ ብሎ በዱዓ ደመደመ፤ "ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን።" ይህም ለተማሪው ካለው ቅን አሳቢነትና ርህራሄ አንፃር ነው። በሌሎቹ ኪታቦቹም ላይ ልምዱ ነው። አላህ መሃርታውን ይለግሰው፤ ምንዳውንም ያብዛለትና።

ራስክን ፈትን

ለተከታዮቹ ጥያቄዎች በተሰጠው ቦታ ላይ መልሱን አስቀምጥ

1. ዑለሞች ለምንድን ነው በቢስሚላህ የሚጀምሩት?

   (1).....

   (`2).....

   (3).....

   (4).....

2. የኢስላም አፍራሾች ማለት ምን ማለት ነው?

   .....

   .....

3. ለምንድን ነው ዑለሞች አንዳንዴ አፍራሾች አንዳንዴም አበላሾች ሌላ ጊዜ ደሞ ኢስላሙን ዉድቅ የሚያደርጉ የሚሉት?

   .....

   .....

4. እነዚህ አፍራሾች በዑለሞች መካከል ሙሉ ስምምነት አለባቸውን?

   .....

   .....

5. እነዚህ አፍራሾች በቁጥር የተገደቡ ናቸውን?

-የተገደቡ ናቸው -የተገደቡ አይደሉም -በቁጥር ሳይሆን በጥቅሉ የተገደቡ ናቸው

6. ሸይኹ ለምንድን ነው አስር ናቸው ያለው?

.....

.....

7. በቁርአንና በሓዲሥ ቁጥር ከተወሳ ትርጉም ይሰጠዋልን? ማለትም አይጨመርበትም?

.....

.....

8. ለምንድን ነው አንዳንድ ጊዜ ቁጥር ተጠቅሶ ትርጉም የማይኖረው?

.....

.....

9. የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም የሚኖረውን ቦታ ምሳሌ ጥቀስ?

.....

.....

10. ቁጥር ተጠቅሶ ትርጉም የማይኖረውን ቦታ ምሳሌ ጥቀስ?

.....

.....

11. ሸይኹ ከአስር በላይ አፍራሽ እንዳለ ያስባልን?

.....

.....

12. የትኛው ንግግሩ ነው ይህን የሚያሲዘን?

.....

.....

13. አፍራሾችን መገደብ ይቻላልን?

.....

.....

14. አፍራሾችን እንዴት መገደብ ይቻላል?

(1).....

(2).....

(3).....

(4).....

15. ለምንድን ነው ስለ አፍራሾች የምንማረው?

.....

.....

16. ከሸይኹ ውጭ ስለ አፍራሾች የፃፈ አለን?

.....

.....

17. አፍራሾችን በማስመልከት በስራውና በሰሪው መካከል ልዩነት አለን?

.....

.....

18. ከምን አኳያ ይለያያሉ?

.....

.....

19. ሸይኹ አፍራሾችን በመጥቀስ የፈለገበት ግለሰቦችን ማክፈር ነውን?

.....

.....

20. ስለ አፍራሾች የተማረ ሰው ምን ይጠበቅበታል?

.....

.....

21. ሸይኹ ይበልጥ የፈለገው የትኛውን አይነት ሽርክ ነው?

.....

.....

22. በትልቁና በትንሹ ሽርክ መካከል ልዩነቱን እንዴት እንወቅ?

.....

.....

.....

.....

.....

.....

23. ትልቁን ሽርክ የፈፀመ ሙሽሪክ ሽርኩ ተቅባይነት ያገኛልን? ተቀባይነት የማያገኝውስ መች ነው?

.....

.....

24. የትኛው ነው የከፋው ትንሹ ሽርክ ወይስ ከባድ ወንጀል?

.....

.....

25. ለወንጀል ከባድ መሆን ሚዛኑ ምንድን ነው?

.....

.....

26. ከባባድ ወንጀሎች በቁጥር የተገደቡ ናቸውን?

.....

.....

27. ከባድ ወንጀል የሰራ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው? እንወደዋለን ወይስ እንጠላዋለን?

.....

.....

.....

.....

28. ከባድ ወንጀልን የሰራ ሰው ይቀጣመጡታልን?

.....

.....

29. ከባባድ ወንጀሎች ይበላለጣሉን? ማስረጃውስ ምንድን ነው?

.....

.....

30. ከባባድ ወንጀሎች በመልካም ስራ ይሰረዛሉን? ወይስ ተውባ ግዴታ ነው?

.....

.....

31. የተከለከሉ ነገራቶች ስንት አይነት ናቸው?

.....

.....

32. የትልቁ ሽርክ አይነቶችን ጥቀስ

(1).....

(2).....

(3).....

(4).....

33. የእርድ አይነቶችን ጥቀስ

(1).....

(2).....

(3).....

34. እርድ ከትልቁ ሽርክ የሚሆነው መች ነው?

.....

.....

35. የሸፋዓ (ምልጃ) አይነቶችን ጥቀስ

(1).....

(2).....

(3).....

36. ተወኩል (መደገፍ) ምንድን ነው?

.....

.....

37. ተወኩል ለስንት ይከፈላል?

(1).....

(2).....

(3).....

38. "በእገሌ ላይ ተደገፍኩ/ተመካሁ" ወይም "በአላህ ከዚያም በእገሌ..." ማለት ትክክል ነውን?

- ትክክል ነው - ትክክል አይደለም

39. ምንስ ነው ማለት ያለበት?

.....

.....

40. አጋሪዎች (ሙሽሪኮች) ከሃዲ ለመሆናቸው ማስረጃው ምንድን ነው? አህሉል ኪታብስ ከነሱ ይመደባሉን?

.....

.....

41. ይህ ማለት ቃላችንን አንፈፅምላቸውም ማለት ነውን?

.....

.....

42. ቃል ከመገባባት አንፃር ሰዎች ስንት አይነት ናቸው?

(1).....

(2).....

(3).....

43. በሰው ሰራሽ ህግ መፍረድ ስንት አይነት ነው?

.....

.....

44. ለአላህ ብሎ መውደድ ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

45. ለአላህ ብለን የምንወደው ማንን ነው? ለአላህ ብለን የምንጠላውስ ማንን ነው?

.....

.....

46. ተሳላቂ ከየትኛው የኩፍር አይነት ነው?

.....

.....

47. ለተሳላቂ (ዳኞች ዘንድ) ተውባ አለውን? መስፈርቶችስ?

(1).....

(2).....

(3).....

48. ነብዩን ﷺ መስደብ ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

49. (የሚያከፍር) ስድብን የሚያዳምጥ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

50. ደጋሚ ካፊር ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?

.....

.....

51. የደጋሚ ምልክቱ ምንድን ነው?

.....

.....

52. ጠንቋይ ዘንድ መሄድ ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

53. እነሱ ዘንድ የሚኬደው እንዴት ነው?

.....

.....

54. ድግምትን በድግምት የማክሸፍ አይነቶችን ጥቀስ?

(1).....

(2).....

55. ድግምትን በድግምት ማክሸፍ ይቻላል ለሚል እንዴት እንመልስለት?

(1).....

(2).....

(3).....

(4).....

(5).....

(6).....

(7).....

(8).....

56. አጋሪዎችን(ሙሽሪከችን) ማገዝ ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

57. ከነብዩ መሓመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ለማንም ቢሆን ይፈቀዳልን?

.....

.....

58. ኸድር ከሙሳ(መመሪያ) ወጥቷልን?

.....

.....

59. (ከዲነል ኢስላም)ጀርባ መስጠት ፍርዱ ምንድን ነው?

.....

.....

60. በሸይኹ ንግግር መሰረት ፈሪ ሲል ምን ማለቱ ነው? የተገደደውን ማለቱ ነውን?

.....

.....

61. የመገደድ መስፈርቶችን ጥቀስ

(1).....

(2).....

(3).....

(4).....

(5).....

62. ከምን አንፃር ነው በዱዓ የደመደሙት?

.....

.....

63. አንድ ሙስሊም እንዴት ነው በራሱ ላይ ሽርክ የሚሰጋው?

.....

.....